# የማርቆስ ወንጌል መግቢያ

## መግቢያ

### ጸሐፊው

ከወንጌሉ ውስጥ ምንም ዐይነት ማስረጃ ማግኘት ባይቻልም፣ ይህን ወንጌል የጻፈው ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ መሆኑን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ትቀበላለች:: ከሚሰጡት ማስረጃዎች ሁሉ ዋነኛ የሚባለው ፓፒያስ (140 ዓ.ም. ገደማ) ከተባለ የቤተ ክርስቲያን አባት የተገኘው ነው፤ ይህም ማስረጃ:-

(1) ማርቆስ ለሐዋርያው ጴጥሮስ የቅርብ ሰው ስለ ነበረ፣ ጌታ የተናገረውንና ያደረገውን ሁሉ ከእርሱ አግኝቶአል፤

(2) ማርቆስ ስለ ጌታ የጻፈው፣ የታሪኩን ቅደም ተከተል የጠበቀ መረጃ አግኝቶ ሳይሆን፣ ጴጥሮስ ለጥንት ቤተ ክርስቲያን እንደ አስፈላጊነቱ ይሰብክ የነበረውን መሠረት አድርጎ ነው፤

(3) ማርቆስ ይህን የወንጌል መልእክት በጥንቃቄ ጠብቆ ዘግቦአል:: እንግዲህ በዚህ አመለካከት መሠረት፣ የማርቆስ ወንጌል የጴጥሮስ ስብከት እንደ ሆነና፣ ይህንኑ ስብከት ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ አቀነባብሮና መልክ አስይዞ አቅርቦአል ወደሚል መደምደሚያ ላይ ያደርሳል (የሐሥ 10፥37 ማብ ይመ)::

### ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ በአዲስ ኪዳን

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ከጴጥሮስ ጋር ቀረቤታ እንዳለው የሚነገርለት ማርቆስ፣ በአዲስ ኪዳን ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ እንደ ሆነ በእርግጠኝነት ይታመናል:: ስሙ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ ኪዳን የተጠቀሰው ከእናቱ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ነው:: እናቱ በኢየሩሳሌም ቤት እንደ ነበራትና ቤቷንም አ ማኞች ለጸሎት ይጠቀሙበት እንደ ነበር (ሐሥ 12፥12):: እንዲሁም ጳውሎስና በርናባስ ከኢየሩሳሌም ወደ አንፆኪያ ሲመለሱ፣ ማርቆስ ከእነርሱ ጋር ነበር (ሐሥ 12፥25):: በመቀጠል ስለ ማርቆስ የተገለ ጸው፣ ጳውሎስና በርናባስ የመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉዞ ባደረጉ ጊዜ እነርሱን ለመርዳት አብሮአቸው ተጉዞ ነበር:: ጳውሎስና በርናባስ ወደ ጵንፍልያ ሲሄዱ ግን ተለይቶአቸው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ (ሐሥ 13፥13):: በዚህ ሁኔታው ጳውሎስ በጣም አዘነ፤ ማርቆስ አብሮአቸው በሁለተኛው ጉዞአቸው ለመሄድ በፈለገ ጊዜ ግን ጳውሎስ ተቃወመው:: ከዚህ የተነሣ ጳውሎስና በርናባስ በሐሳብ ተለያዩ፤ በርናባስ የአክስቱ ልጅ የሆነውን ማርቆስን (ቈላ 4፥10) ይዞት ወደ ቆጵሮስ ሄደ:: ከዚህ ውጭ በሐ ዋርያት ሥራ ውስጥ ስለ ማርቆስ የተጠቀሰ ምንም ነገር አይገኝም:: ነገር ግን ጳውሎስ ለቈላስያስ ሰዎች በጻፈው መልእክት ውስጥ የማርቆስን ሰላምታና "ወደ እናንተ ሲመጣ ተቀበሉት" የሚል ጽፎ እናገኛለን (ቈላ 4፥10):: በፊልሞና 24 ላይ የጳውሎስ የሥራ አጋር እንደ ሆነ የተገለጠ ሲሆን፣ ጳውሎስ በሕይወት ዘመኑ መጨረሻ አካባቢ ማርቆስን ለአገልግሎቱ በጣም እንደ ፈለገው በ2ጢሞ 4፥11 ላይ ተገልጾአል::

### ወንጌሉ የተጻፈበት ጊዜ

ማቴዎስና ሉቃስ ወንጌላትን የጻፉት የማርቆስ ወንጌልን ተመርኩዘው ነው የሚሉ ሰዎች፣ የማ ርቆስ ወንጌል የተጻፈው በ50ዎቹ ወይም በ60ዎቹ ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ነው ብለው ያምናሉ:: ሌሎች ደግሞ የወንጌሉን ርእስ ጉዳይና የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች የማርቆስን ስም ጠቅሰው የጻፉትን ከግምት በማስገባት መጽሐፉ የተጻፈው ኢየሩሳሌም በ70 ዓ.ም. ከመውደሟ ጥቂት ጊዜያት ቀደም ብሎ እንደ ሆነ ይናገራሉ::

### ወንጌሉ የተጻፈበት ቦታ

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን እንደምታምነው ከሆነ፣ የማርቆስ ወንጌል የተጻፈው፣ "በኢጣሊያ አገር" ወይም በሮም ከተማ ነበር (ኢሬኔዎስና የእስክንድርያው ቀሌምንጦስ):: እነዚህ ጸሐፊዎች የማርቆስን ወንጌል ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ያገናኛሉ:: ከላይ የተሰጠው ሐሳብ ከዚህ በታች በሚገኙ ማስረጃዎች ይደገፋል:-

(1) ጴጥሮስ በሕይወት ዘመኑ ፍጻሜ አካባቢ ሮም እንደ ነበረና በሰማዕትነት የሞተው እዚያ እንደ ሆነ ይገመታል፤

(2) ጴጥሮስ ሮም በነበረበት በዚህ ጊዜ ማርቆስም እዚያው እንደ ነበረና ከጴጥሮስ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንደ ነበረው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማስረጃ መኖሩ ነው (2ጢሞ 4፥11፤ 1ጴጥ 5፥13 ይመ፤ በእነዚህ ክፍሎች "ባቢሎን" የሚለው ስም፣ የሮም የምሥጢር መጠሪያ ሊሆን ይችላል)::

### ተደራስያን

አንዳንድ ማስረጃዎች እንደሚያመለክቱት ይህ ወንጌል የተጻፈው ሮም ላለችው ቤተ ክርስቲያን ወይም ቢያንስ ከአሕዛብ ወገን ለነበሩ አንባብያን ነው:: ማርቆስ ስለ አይሁድ ልማዶች አብራርቶአል

(7፥2-4፤15፥42)፤ የአራማይክን ቃላት ተርጕሞአል (3፥17፤ 5፥41፤ 7፥11:34፤ 15፥22)፤ ደግሞም ስለ ስደትና ስለ ሰማዕትነት ለመጥቀስ ልዩ ፍላጐት ያለው ይመስላል (8፥34-38፤ 13፥9-13)፤ ምክንያቱም ሮማውያን አማኞች ሊያውቁት የሚገባቸው ጉዳይ ስለ ነበረ ነው። ይህ ወንጌል በሮማውያን ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱና በፍጥነት መሠራጨቱ፣ ቀድሞውኑ የተጻፈው ለእነርሱ መሆኑን ያስረዳል።

**ዐላማው**

የማርቆስ ወንጌል ከሮም ጋር ግንኙነት እንዳለው ከጥንት ጀምሮ ስለሚታመን፣ ምናልባት የተጻፈበት ምክንያት የሮም ቤተ ክርስቲያን ከ64-67 ዓ.ም. ገደማ ከገጠማት ከፍተኛ ስደት የተነሣ ሊሆን ይችላል። በ64 ዓ.ም ኔሮ ሮምን በእሳት አውድሞ በክርስቲያኖች ላይ ያላከከበትና ከፍተኛ ስደት ያስከተለው ሁኔታ፣ ይህ ወንጌል እንዲጻፍ ያደረገ ዐቢይ ምክንያት ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ በሮማውያን አማኞች ዘንድ ሰማዕታት አልነበሩም ማለት አይቻልም። ማርቆስ የጌታችንን ሕይወት በምሳሌነት ለአንባቢዎቹ ማቅረቡ፣ እነርሱም መከራ ለመቀበል የተዘጋጁ እንዲሆኑ ለማደፋፈር ሳይሆን አይቀርም። በዚህ ወንጌል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለ መከራና ስለ ደቀ መዝሙርነት ተጠቅሶ ይገኛል (1፥12-13፤ 3፥22:30፤ 8፥34-38፤ 10፥30:33-34:45፤ 13፥8:11-13 ይመ)።

**አጽንዖት የተሰጠባቸው አርእስት ጕዳዮች**

(1) ***መስቀል፤*** ማርቆስ ከሰው አንጻር (12፥12፤ 14፥1-2፤ 15፥10)፣ እንዲሁም ከእግዚአብሔር አንጻር (8፥31፤ 9፥31፤ 10፥33) የመስቀልን አስፈላጊነት በአጽንዖት አመልክቶአል።

(2) ***ደቀ መዝሙርነት፤*** ኢየሱስ ሊቀበል ያለውን መከራና ሥቃይ አስቀድሞ በሚናገሩ ክፍሎች ጋር ደቀ መዝሙርነትን አያይዞ አቅርቦአል (8፥34-9፥1፤ 9፥35-10፥31፤ 10፥42-45)።

(3) ***የኢየሱስ ትምህርቶች፤*** ከሌሎቹ ወንጌል ጸሓፍያን ጋር ሲነጻጸር፣ ማርቆስ ጌታ ኢየሱስ ያስተማራቸውን ትምህርቶች የጠቀሰው በጥቂቱ ቢሆንም፣ ስለ ኢየሱስ መምህርነት በአጽንዖት ጽፎአል። ኢየሱስን በተመለከተ፣ "መምህር"፣ "አስተማረ"፣ "ትምህርት" እና "ረቢ" የሚሉትን ቃላት በማርቆስ ወንጌል ውስጥ 39 ጊዜ ይገኛሉ።

(4) ***"የመሲሕነቱ ምስጢርነት"፤*** ደቀ መዛሙርቱን ወይም ታምር የተሠራለትን ማንኛውም ሰው፣ ስለ ማንነቱ ወይም ስላደረገው ነገር እንዳይናገሩ ኢየሱስ አጥብቆ ይከለክል ነበር (1፥34:44፤ 3፥12፤ 5፥43፤ 7፥36-37፤ 8፥26:30፤ 9፥9)።

(5) ***የእግዚአብሔር ልጅ፤*** ኢየሱስ ሰው መሆኑን ማርቆስ በአጽንዖት ቢገልጽም (3፥5፤ 6፥6:31:34፤ 7፥34፤ 8፥12:33፤ 10፥14፤ 11፥12 ይመ)፣ መለኮት መሆኑንም መግለጽ አልዘነጋም (1፥1:11፤ 3፥11፤ 5፥7፤ 9፥7፤ 12፥1-11፤ 13፥32፤ 15፥39 ይመ)።

**ልዩ ባሕርያቱ**

የማርቆስ ወንጌል ቀላልና እጥር ምጥን ያለ፣ በቃላትም ያላሸበረቀ ነው፤ ይሁን እንጂ የኢየሱስን አገልግሎት ሲያቀርብ ትኵረት ያደረገው ከተናገረውን ይልቅ ያደረገው ሥራ በማቅረብ ላይ ነው። ማርቆስ ከአንዱ የኢየሱስ ሕይወትና አገግሎት ገለጻ ወደ ሌላው ፈጥኖ ይሸጋገራል። ከአንዱ ትረካ ወደ ሌላው የሚሸጋገረው "ወዲያው" በሚል ተውሳከ ግስ ነው (የ1፥2 ማብ ይመ)። መጽሐፉ በአጠቃላይ፣ "የ...ወንጌል መጀመሪያ" (1፥1) በሚል ባሕርይው ተለይቶ ይታወቃል። የክርስቶስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤውም፣ "መጀመሪያ" የሚለውን ክፍል ሲያጠቃልል፣ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው የሐዋርያት ስብከት ደግሞ የዚሁ ክፍል ቀጥያ ነው።

**አስተዋፅኦ**

1. የኢየሱስ አገልግሎት መጀመሪያ (1፥1-13)
   - ሀ. መንገድ ጠራጊው (1፥1-8)
   - ለ. መጠመቁ (1፥9-11)
   - ሐ. መፈተኑ (1፥12-13)
2. የኢየሱስ አገልግሎት በገሊላ (1፥14-6፥29)
   - ሀ. በገሊላ የመጀመሪያ አገልግሎቱ (1፥14-3፥12)
     - (1) የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት መጠራት (1፥14-20)
     - (2) በቅፍርናሆም የተደረጉ ታምራት (1፥21-34)
     - (3) በገሊላ ውስጥ መመላለሱ (1፥35-45)
     - (4) በቅፍርናሆም የነበረው አገልግሎቱ (2፥1-22)
     - (5) ስለ ሰንበት የተነሣው ክርክር (2፥23-3፥12)
   - ለ. በገሊላ የኋለኛው ጊዜ አገልግሎቱ (3፥13-6፥29)
     - (1) የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መመረጥ (3፥13-19)
     - (2) በቅፍርናሆም ማስተማሩ (3፥20-35)
     - (3) ስለ መንግሥተ ሰማያት የተነገሩ ምሳሌዎች (4፥1-34)

(4) ወደ ገሊላ ባሕር ማዶ የተደረገ ጉዞ (4፥35-5፥20)
(5) በገሊላ የተደረጉ ሌሎች ታምራት (5፥21-43)
(6) ኢየሱስ በተወለደበት ከተማ የነበረ አለማመን (6፥1-6)
(7) ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ጥንድ ጥንድ ሆነው ገሊላ ውስጥ ያደረጉት ጉዞ (6፥7-13)
(8) ንጉሥ ሄሮድስ ስለ ኢየሱስ አገልግሎት የነበረው አመለካከት (6፥14-29)

3. ኢየሱስ ከገሊላ ስለ መውጣቱ (6፥30-9፥32)
   ሀ. ወደ ገሊላ ባሕር ምሥራቅ ዳርቻ (6፥30-52)
   ለ. ወደ ገሊላ ባሕር ምዕራብ ዳርቻ (6፥53-7፥23)
   ሐ. ወደ ፊንቄ (7፥24-30)
   መ. ወደ ዐሥር ከተማ አካባቢ (7፥31-8፥10)
   ሠ. ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ አካባቢ (8፥11-9፥32)
4. የኢየሱስ የመጨረሻ አገልግሎቱ በገሊላ (9፥33-50)
5. የኢየሱስ አገግሎት በይሁዳና በፓርያ (ም 10)
   ሀ. ስለ ባልና ሚስት ፍቺ የተሰጠ ትምህርት (10፥1-12)
   ለ. ስለ ሕፃናት የተሰጠ ትምህርት (10፥13-16)
   ሐ ወጣቱ ሐብታም ሰው (10፥17-31)
   መ. ስለ ኢየሱስ ሞት አስቀድሞ መነገሩ (10፥32-34)
   ሠ. የሁለቱ ወንድማማቾች ልመና (10፥35-45)
   ረ. የበርጤሜዎስ ዐይን በራ (10፥46-52)
6. የኢየሱስ ሕማማቱ (ም 11-15)
   ሀ. በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ (11፥1-11)
   ለ. ቤተ መቅደስን ማንጻቱ (11፥12-19)
   ሐ. ከአይሁድ መሪዎች ጋር የመጨረሻው ክርክር (11፥20-12፥44)
   መ. በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ስለ ዘመን ፍጻሜ የተሰጠ ትምህርት (ም 13)
   ሠ. ኢየሱስ ሽቱ ስለ መቀባቱ (14፥1-11)
   ረ. የኢየሱስ መያዝ፣ ፍርድ ፊት መቅረብና ሞት (14፥12-15፥47)
7. የኢየሱስ ትንሣኤ (ም 16)

## የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት

1፥2-8 ተጓ ምብ ማቴ 3፥1-11፤ ሉቃ 3፥2-16

1 የእግዚአብሔር ልጅ[ሀ]፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ።

[2]በነቢዩ በኢሳይያስ፣ እንዲህ ተብሎ ተጽፎ አል፤ "እነሆ መንገድህን የሚያዘጋጅ መልእ ክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ፤ [3]'የጌታን መንገድ አዘጋጁ፤ ጥርጊያውንም አስተካክሉ እያለ በበረሓ የሚጮኽ ድምፅ'።

[4]ስለዚህ መጥምቁ ዮሐንስ በበረሓ እያጠ መቀና ለኀጢአት ስርየት የንስሓ ጥምቀት እየሰበከ መጣ። [5]የይሁዳ አገር በሞላ፣ የኢ የሩሳሌም ሰዎች በጠቅላላ ወደ እርሱ በመ ሄድ ኀጢአታቸውን እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠመቁ። [6]ዮሐንስ የግመል ጠጕር ይለብስ፣ በወገቡ ጠፍር ይታጠቅ፣ አንበጣና የበረሓ ማር ይበላ ነበር። [7]ስብከ ቱም፣ "እኔ ጐንበስ ብዬ የጫማውን ማሰሪያ መፍታት ከማይገባኝ፣ ከእኔ የሚበልጥ ከእኔ በኋላ ይመጣል፤ [8]እኔ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል" የሚል ነበር።

## የኢየሱስ መጠመቅና መፈተን

1፥9-11 ተጓ ምብ - ማቴ3፥13-17፤ ሉቃ3፥21-22
1፥12፡13 ተጓ ምብ - ማቴ 4፥1-11፤ ሉቃ 4፥1-13

[9]በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የገሊላ ከተማ ከሆነችው ከናዝሬት መጥቶ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ። [10]ከውሃው በሚወጣበትም ጊዜ፣ ሰማያት ተከፍተው፣ መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ሲወርድ አየ፤ [11]"የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፤ በአንተ ደስ ይለኛል" የሚል ድምፅ ከሰማይ ተሰማ።

[12]ወዲያውም መንፈስ ቅዱስ ወደ በረሓ መራው፤ [13]በሰይጣንም እየተፈተነ አርባ ቀን በበረሓ ቈየ። ከአራዊትም ጋር ነበር፤ መላእ ክትም አገለገሉት።

## የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት መመረጥ

1፥16-20 ተጓ ምብ - ማቴ 4፥18-22፤ ሉቃ 5፥2-11፤ዮሐ1፥35-42

[14]ዮሐንስ እስር ቤት ከገባ በኋላ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ወንጌል እየሰበከ ወደ ገሊላ

1፥1 ማቴ 4፥3
1፥2 ሚል3፥1፤ ማቴ11፥10፤ ሉቃ7፥27
1፥3 ኢሳ40፥3፤ ዮሐ1፥23
1፥4 ቍ8፤ ማቴ3፥1፤ሉቃ1፥77፤ ዮሐ1፥26፡33፤ ሐሥ1፥5፡22፤11፥16፤ 13፥24፤18፥25፤ 19፥3፡4
1፥6 ዘሌ11፥22፤ 2ነገ1፥8
1፥7 ሐሥ13፥25
1፥8 ኢሳ44፥3፤ ኢል2፥23፤ዮሐ1፥33፤ ሐሥ1፥5፤2፥4፤ 11፥16፤19፥4-6
1፥9 ማቴ2፥23፤ 3፥1
1፥10 ዮሐ1፥32
1፥11 ማቴ3፥17
1፥13 ዘፀ24፥18፤ 1ነገ19፥8፤ ማቴ4፥10፤ዕብ4፥15
1፥14 ማቴ3፥1፤ 4፥12፡23

[ሀ]1 አንዳንድ ቅጆች *የእግዚአብሔር ልጅ* የሚለው ሐረግ የላቸውም።

1፥1 *ኢየሱስ፤* የስሙ ትርጕም፣ "ጌታ ያድናል" ማለት ነው። *ክርስቶስ፤* በዕብራይስጥ "መሲሕ" ሲባል፣ ትርጕሙም የተቀባ ማለት ነው። *ወንጌል፤* "ኡዋንጌሌዎን" ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን፣ ትርጕሙም፣ "የምሥራች" ማለት ነው፤ የምሥራቹ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ የሰጠን ድነት ነው። *መጀመሪያ፤* በመግቢያው ሥር፣ 'ልዩ ባሕርያቱ' የሚለውን ይመ (ዮሐ 1፥1 ይመ)።

1፥2-3 *በነቢዩ በኢሳይያስ፤* ማርቆስ ጥቅሱ የተገኘው ከነቢዩ ከኢሳይያስ እንደ ሆነ ይጥቀስ እንጂ፣ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ስንኞች የተወሰዱት ከሚል 3፥1 ነው፤ ሦስተኛው ስንኝ ግን ከኢሳ 40፥3 የተወሰደ ነው (የማቴ 27፥9 ማብ ይመ)። የኢየሱስን አገልግሎት ለማስተዋል ከብሉይ ኪዳን መጀመር ያስፈልጋል። ኢሳይያስ ስለ እግዚ አብሔር የሚናገረው ስለ ልጁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆኖ ይገኛል (ቍ 1)። የተጠቀሰው ክፍል ስለ መልእክተኛው፣ ስለ ምድረ በዳና ስለ ጌታ ይናገራል፤ እያንዳንዳቸውም ከቍ 4-8 ባለው ክፍል በሚገባ ተገልጸዋል።

1፥4 *በበረሓ፤* ከሙት ባሕር በስተ ምዕራብ የሚገኝ ቦታ ሲሆን፣ ከዋሪዎቹ መካከል፣ "የሙት ባሕር ጥቅልል መጻሕፍት" የተባሉትን ጽሑፎች የጻፉና ያቈዩ ይገኛሉ። *ኢየጠመቀ፤* ሰዎች ኀጢአታቸውን እየተናዘዙ ወደ እርሱ ሲመጡ መጥምቁ ዮሐንስ ያጠምቃቸው ስለ ነበር፣ "መጥምቁ" ወይም፣ "አጥማቂው" በመባል ይታወቃል። *የንስሓ፤* ቍርጥ ውሳኔ አድርጎ ከኀጢአት ወደ ጽድቅ ሕይወት መመለስን ያመለክታል። የዮሐንስ ለንስሐ ትኵረት ማስጠት፣ የነቢያትን ትምህርት የሚያስገነዝብ ነው (ለምሳሌ ሆሴ 3፥4-5)። እግዚአብሔር ምን ጊዜም በንስሐ ከኀጢአት ለሚመለሰው ይቅርታ ያደርግለታል። *ጥምቀት፤* ዮሐ ንስ ይሰብክ የነበረው የንስሐን ጥምቀት ነበር፤ ይኸውም ከንስሐ በኋላ ወይም ከንስሓ በፊት የሚደረግ መጠመቅ ማለት ነው። ጥምቀት ዮሐ ንስ ይሰብካቸው ለነበሩ ሰዎች እንግዳ ነገር አልነበረም፤ አሕዛብ ወደ ይሁዲነት ሲገቡ ጥምቀት እንደሚያስፈልግ ያውቁ ነበር፤ ይሁን እንጂ የአብርሃም ዘር የሆኑት አይሁድ፣ ንስሐ ገብተው መጠመቅ እንደ ሚያስፈልጋቸው አልሰሙም ነበር። *ዮሐንስ . . . መጣ፤* ማርቆስም፣ እንደ ዮሐንስ ስለ ጌታ ልደት ሳይጠቅስ ትረካውን በመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ይጀምራል። "ዮሐንስ" የስሙ ትርጕም፣ "እግዚአብሔር ባለ ብዙ ጸጋ ነው" ማለት ነው።

1፥5 *በሞላ . . . በጠቅላላ፤* ከዮሐንስ ትምህርት የተነሣ የተፈጠረውን የሰዎችን ከፍተኛ ፍላጎት ለማሳየት፣ በማጋነን የተነገረ አገላለጽ ነው። የእስራኤል ሕዝብ ለብዙ መቶ ዓመታት ነቢይ አልነበረውም። *ዮርዳኖስ ወንዝ፤* በመካከለኛው ምሥራቅ ከሚገኙት ታላላቅ ወንዞች መካከል ዋነኛው ሲሆን፣ ከበረዶአማው አርሞንዔም ተራራ ተነሥቶ ወደ ሙት ባሕር ይፈሳል። ለኢየሩሳሌም ቅርብ የሆነው የወንዙ ዳርቻ የሚገኘው ሠላሳ ሁለት ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ነው።

1፥6 *የግመል ጠጕር . . . ጠፍር፤* ኤልያስና ሌሎቹም የቀድሞ ነቢያት እንደዚሁ ይለብሱ ነበር (2ነገ 1፥8፤ ከዘካ 13፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። *አንበጣና የበረሓ ማር፤* የማቴ 3፥4 ማብ ይመ።

1፥7-8 *ስብከቱ፤* ማርቆስ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የተረከው በመጠኑ ሲሆን (ከማቴ 3፥7-12፤ ሉቃ 3፥7-17 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ትኵረቱ "ከዮሐንስ በሚበልጠው" በኢየሱስ መምጣት ላይ ነው።

1፥8 *በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል፤* የማቴ 3፥11 ማብ ይመ።

1፥9 *በዚህ ጊዜ፤* ኢየሱስ ይፋ አገልግሎቱን የጀመረው በሠ ላሳ ዓመቱ ገደማ (ሉቃ 3፥23)፣ በ27 ዓ.ም ሳይሆን አይቀርም፤ አገልግሎቱንም ከመጀመሩ በፊት በናዝሬት ከተማ ይኖር እንደ ነበር ይታወቃል። *ናዝሬት፤* የማቴ 2፥23 ማብ ይመ። *በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ፤* ስለ ኢየሱስ መጠመቅ አስፈላጊነት ማቴ 3፥15 እና ማብ ይመ።

*1፥10-11፤* በዚህ ክፍል የሥላሴ ሦስቱም አካላት በግልጽ ሲሳተፉ ይታያል፤ (1) አብ ተናገረ፤ (2) ወልድ ተጠመቀ (3) መንፈስ ቅዱስ በወልድ ላይ በርግብ አምሳል ወረደ።

1፥10 *መንፈስ ቅዱስ . . . በእርሱ ላይ ሲወርድ፤* ኢየ ሱስን ለአገልግሎት ማዘጋጀቱን ያመለክታል፤ ይህም፣ ጌታ በናዝ ሬት በሚገኘው ምኵራብ፣ 'የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው' ካለው ጋር ይገናዘባል (ሉቃ 4፥18)። *እንደ ርግብ፤* የመንፈስ ቅዱስ ባሕርይ፣ እንደ ርግብ እርጋታ የተሞላበት ንጹሕና ፍጹም ገር መሆኑን የሚያመለክት አገላለጽ ነው (ማቴ 10፥16 ይመ)።

*1፥11፤* መዝ 2፥7 እና ኢሳ 42፥1 *በሰያፍ* የሚጠቀሱም ነው። *ልጄ አንተ ነህ፤* ማርቆስ በቍ 1 ላይ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ይገልጻል፤ እዚህ ላይ ደግሞ እግዚአብሔር አብ ራሱ፣ ኢየሱስ ልጁ መሆኑን በግልጽ ይናገራል። *ድምፅ፤* አንዳንድ ጊዜ እግዚ አብሔር በቀጥታ ከሰማይ ይናገራል (9፥7፤ ዮሐ 12፥28-29 ይመ)።

1፥12 *ወዲያውም፤* ይህ ቃል የማርቆስ የአጻጻፍ ስልት ልዩ ባሕርይ ነው፤ በወንጌሉም ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ይገኛል (ለምሳሌ ቍ 18፡20፡23፡28-29፡42-43 ይመ)።

1፥13 *ሰይጣን፤* የዘፍ 3፥1፤ ዘካ 3፥1፤ ራእ 2፥9-10፤ 12፥9-10 ማብ ይመ። *እየተፈተነ፤* በማቴ 4፥1-11 ላይ ያለውን ማብ ይመ። *አርባ፤* የማቴ 4፥2 ማብ ይመ። *አራዊት፤* ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን፣ አንበሳና የመሳሰሉት አራዊት በ ፓሌስቲና ምድር በብዛት ይኖሩ ነበር፤ ከዚሁ ጋር አያይዞ በምድረ በዳ እነዚህ አራዊት መኖራቸውን የጻፈው ማርቆስ ብቻ ነው። *መላእክትም አገለገሉት፤* የእስራኤልን ሕዝብ በምድረ በዳ እንዳገለገሉት ማለት ነው (ዘፀ 23፥20፡23፤32፥34 ይመ)።

1፥14 *ዮሐንስ እስር ቤት ከገባ በኋላ፤* ማቴ 4፥12 እና የሉቃ 3፥20 ማብ ይመ። *የእግዚአብሔርን ወንጌል፤* ከእግዚአብሔርና ስለ እግዚአብሔር የሆነው የምሥራች ቃል ማለት ነው።

ሄዶ፣ 15“ጊዜው ደርሶአል፤ የእግዚአብሔር መንግ
ሥት ቀርባለች፤ ንስሓ ግቡ፤ በወንጌልም
እመኑ!” እያለ ይሰብክ ነበር።
16ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲያልፍ፣
ስምዖንና ወንድሙ እንድርያስ ዓሣ አጥማጆች
ስለ ነበሩ፣ መረብ ወደ ባሕር ሲጥሉ አያቸው።
17ኢየሱስም፣ “ተከተሉኝ፤ ሰው አጥማጆች
አደርጋችኋለሁ” አላቸው። 18እነርሱም ወዲያ
ውኑ መረባቸውን ትተው ተከተሉት።
19ትንሽ እልፍ እንዳለ፣ የዘብዴዎስ ልጅ
ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ በጀልባ ሆነው
መረባቸውን ሲያበጃጁ አያቸውና፣ 20ወዲ
ያውኑ ጠራቸው። እነርሱም አባታቸውን ከቅ
ጥር ሠራተኞቹ ጋር በጀልባው ላይ ትተው
ተከትለውት ሄዱ።

## ኢየሱስ ርኩስ መንፈስ አስወጣ

1፥21-28 ተጓ ምብ - ሉቃ4፥31-37

21ከዚያም ወደ ቅፍርናሆም ሄዱ፤ ኢየሱስም
ወዲያው በሰንበት ቀን ወደ ምኵራብ ገብቶ
ማስተማር ጀመረ። 22እንደ ጸሐፍት ሳይሆን፣
እንደ ባለ ሥልጣን በማስተማሩ ሕዝቡ በትም
ህርቱ ተገረሙ። 23በዚያን ጊዜ በምኵራ
ባቸው ውስጥ የነበረ ርኩስ^a መንፈስ ያደረበት
አንድ ሰው እንዲህ በማለት ጮኸ፤ 24“የናዝ
ሬቱ ኢየሱስ ሆይ፤ ከኛ ምን ትሻለህ? ልታጠፋን
መጣህን? እኔ ማን እንደ ሆንህ ዐውቃለሁ፤
አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ!”
25ኢየሱስም፣ “ጸጥ በል፤ ከእርሱም ውጣ!”

1፥15 ዮሐ3፥15፤ ሮሜ5፥6፤ ሐሥ20፥21፤ገላ4፥4፤ ኤፌ1፥10
1፥18 ማቴ4፥19
1፥21 ቍ39፤ ማቴ4፥23፤ማር10፥1
1፥22 ማቴ7፥28፡29
1፥24 መዝ16፥10፤ ኢሳ41፥14፡16፡20፤ ማቴ2፥23፤8፥29፤ ሉቃ1፥35፤24፥19፤ ዮሐ1፥45፡46፤6፥69፤ ሐሥ3፥14፤4፥10፤ 24፥5፤1ዮሐ2፥20
1፥25 ቍ34
1፥26 ማር9፥20
1፥27 ማር10፥24፡32
1፥28 ማቴ9፥26
1፥29 ቍ21፡23
1፥31 ሉቃ7፥14
1፥32 ማቴ4፥24
1፥34 ማቴ4፥23፤ ማር3፥12፤ ሐሥ16፥17፡18

ብሎ ገሠጸው። 26ርኩሱም መንፈስ ሰውየውን
በኀይል ካንፈራገጠው በኋላ እየጮኸ ወጣ።
27ሕዝቡ በሙሉ በመገረም፣ “ይህ ነገር ምን
ድን ነው? ሥልጣን ያለው አዲስ ትምህርት
መሆኑ ነው! ርኩሳን መናፍስትን እንኳ ያዛል፤
እነርሱም ይታዘዙለታል!” እያሉ እርስ በርስ
ተጠያየቁ። 28ወዲያውም ዝናው በገሊላ ዙሪያ
ባሉ ስፍራዎች ሁሉ ተዳረሰ።

## ኢየሱስ ብዙዎችን ፈወሰ

1፥29-31 ተጓ ምብ - ማቴ 8፥14-15፤ ሉቃ4፥38፡39
1፥32-34 ተጓ ምብ - ማቴ 8፥16፡17፤ ሉቃ4፥40፡41

29ወዲያው ከምኵራብ እንደ ወጡ፣ ከያዕ
ቆብና ከዮሐንስ ጋር ወደ ስምዖንና ወደ
እንድርያስ ቤት ገቡ። 30የስምዖን አማት
በትኵሳት በሽታ ታማ ተኝታ ነበር፤ ስለ እርሷም
ነገሩት፤ 31ስለዚህም እርሱ ወደ ተኛችበት
በመሄድ እጇን ይዞ አስነሣት፤ ትኵሳቱም
ተዋት፤ ተነሥታም ታገለግላቸው ጀመር።
32ጀንበር ከጠለቀች በኋላ፣ ምሽት ላይ
የአካባቢው ሰዎች ሕመምተኞችንና በአጋን
ንት የተያዙትን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ።
33የከተማዋ ሕዝብ በሙሉ በቤቱ ደጅ ላይ
ተሰብስቦ ነበር። 34እርሱም በተለያየ በሽታ
የታመሙትን ብዙዎችን ፈወሰ፤ ብዙ አጋን
ንትም አወጣ፤ ነገር ግን አጋንንቱ የኢየሱስን
ማንነት ያውቁ ስለ ነበር እንዲናገሩ አልፈቀ
ደላቸውም።

^a23 ወይም *ክፉ* ፤ እንዲሁም ቍ26 እና 27 ይመ

1፥15 *የእግዚአብሔር መንግሥት፤* የማቴ3፥2 ማብ ይመ።
*ቀርባለች፤* የንጉሡ የክርስቶስ ወደ ዓለም መምጣት፣ መንግሥቱ
ወደ ሕዝቡ እንዲቀርብ ያደርጋል።
1፥16 *ገሊላ ባሕር፤* ከባሕር ወለል በታች 700 ጫማ
ያህል ዝቅ ብሎ የሚገኝ ውብ ባሕር ሲሆን፣ ርዝመቱ 22.5
ኪ.ሜ.፣ ስፋቱም 10 ኪ. ሜ. ያህል ነው። ደግሞም የጌንሳሬጥ
ባሕር (ሉቃ 5፥1)፣ ወይም የጥብርያዶስ ባሕር (ዮሐ 6፥1፤
21፥1) በመባል ይታወቃል። በብሉይ ኪዳን ዘመንም የኪኔሬት
ባሕር በመባል ይታወቃል (ለምሳሌ ዘኍ 34፡11)። *ስምዖን፤* ኢየ
ሱስ ለዚህ ደቀ መዝሙር ጴጥሮስ የሚል ስም ሰጥቶታል (3፥16፤
ማቴ 16፥18፤ ዮሐ 1፥42)። *መረብ፤* የማቴ 4፥18 ማብ ይመ።
1፥17 *ተከተሉኝ፤* የደቀ መዝሙርነት ጥሪ ቀልጭ ያለና
ፍጹም ራስን መስጠት የሚጠይቅ ነው። ኢየሱስ ስምዖንና እንድ
ርያስን ሲያገኝ ይህ የመጀመሪያ ጊዜው አልነበረም (ዮሐ 1፥35-
42 ይመ)። *ሰው አጥማጆች፤* ወንጌላውያን ማለት ነው (ሉቃ
5፥10 ይመ)።
1፥21 *ቅፍርናሆም፤* የማቴ 4፥13 ማብ ይመ። *ምኵራብ፤*
በዚያን ዘመን ለነበሩ አይሁድ ዋነኛ የአምልኮ ተቋም ነበር።
ይህም በምርኮ ዘመን የተመሠረተ ሲሆን፣ አይሁድ ቅዱሳት
መጻሕፍትን የሚያጠኑብትና እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት
ቦታና ሁኔታ የሚያመቻች ነበር። በአንድ ከተማ ቢያንስ ዐሥር
ባለ ትዳር አይሁዳውያን ወንዶች ከተገኙ፣ ምኵራብ ማቋቋም
ይቻል ነበር። *ማስተማር ጀመረ፤* ጳውሎስ ከጊዜ በኋላ እንዳ
ደረገው ሁሉ (ሐሥ 13፥15፤ 14፥1፤ 17፥2፤ 18፥4 ይመ)፣ አንድ
እንግዳ መምህር፣ በምኵራብ መሪዎች ጋባዥነት እንዲያስተምር
የሚፈቅደውን ልማድ ጌታም ተጠቅሞበት ያስተምር ነበር።
1፥22 *ጸሐፍት፤* የማቴ 2፥4 ማብ ይመ። *ተገረሙ፤* የኢ
የሱስ ትምህርትና ተግባር በሕዝቡ ዘንድ ያስከተለውን አድናቆት
ማርቆስ ደጋግሞ ይጠቅሳል (2፥12፤ 5፥20፡ 42፤ 6፥2፡51፤ 7፥37፤
10፥26፤11፥18 ይመ፤ እንዲሁም 15፥15 ይመ)። አድናቆትን
ያመጣው ሌላ ሳይሆን፣ የኢየሱስ ባሕርይ የሆነው መለኮታዊ
ሥልጣኑ ነበር። ጸሐፍት ያደርጉት እንደ ነበረው፣ ሰብአዊ
ሊቃውንትን በመጥቀስ አላስተማረም፤ ሥልጣኑ በቀጥታ ከአባቱ
ከአብ ነበርና።
1፥23 *በምኵራባቸው ውስጥ የነበረ ... አንድ ሰው ጮኸ፤*
እንደ እውነቱ ከሆነ የጮኸው ሰውየው ሳይሆን ጋኔኑ ነበር።
*ርኩስ መንፈስ ያደረበት፤* ጋኔን በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠ
ሩትን ሰዎች ማሠቃየትና ማጥፋት ዕቅዱ ነበር፤ ይሁን እንጂ ኢየ
ሱስ ኀያል ጠላቱ እንደ ሆነና የሰይጣንን ኀይላት ለማጥፋት
ሥልጣን እንዳለው ጋኔኑ ተረድቶአል።
1፥24 *የእግዚአብሔር ቅዱስ፤* ይህ ስያሜ በአቻነት በሉቃ
4፥34 ላይ ከተገለጸው ሌላ፣ በዮሐ 6፥69 ላይ ብቻ ይገኛል፤
የሚያመለክተውም ከመሲሕነቱ ይልቅ የክርስቶስ የባሕርይ ገንዘቡ
መለኮት መሆኑን ነው (ሉቃ 1፥35 ይመ)። ምናልባት አጋንንቱ
ስሙን የጠሩት፣ የአንድን ሰው ስም በትክክል በመጥራት ያን
ሰው መቈጣጠር ይቻላል የሚለውን ዐጕል እምነት ተከትለው ሊሆን
ይችላል። ሰውየው የተያዘው በአንድ ርኩስ መንፈስ ብቻ ሳይ
ሆን፣ በርኩሳን መናፍስት ነበር (5፥9 ይመ)፤ የተናገረው ግን
አንዱ ብቻ ነበር።
1፥25 *ጸጥ በል፤* በግሪኩ፣ “ተለጐም” ማለት ነው። የኢ
የሱስ ታላቅ ሥልጣን፣ አጋንንት ያደሩበትን ሰው ጩኸት ዝም
አሰኝቶአል።
1፥27 *ሥልጣን ያለው፤* ኢየሱስ በሥልጣን በማስተማሩ
(ቍ22)፣ ደግሞም እዚህ ላይ ታምር በማድረጉ ሕዝቡ ተደነቁ።
1፥29 *ወደ ስምዖንና ወደ እንድርያስ ቤት፤* ኢየሱስና ደቀ
መዛሙርቱ ወደዚያ የሄዱት፣ ምግብ ለመመገብ ሳይሆን አይቀ
ርም፤ ምክንያቱም ዋናው የሰንበት ምግብ የሚቀርበው ወዲያው
ከምኵራብ አገልግሎት በኋላ ነበር።
1፥30 *የስምዖን አማት፤* በ1ቆሮ 9፥5 ላይ ጴጥሮስ ባለ
ትዳር እንደ ነበር ተጠቅሶአል።
1፥32 *ጀንበር ከጠለቀች በኋላ ... አመጡ፤* አንድ ነገር
ከመሸከማቸው በፊት ፀሓይ ጠልቃ ሰንበት እስኪያልፍ መጠበቅ
ነበረባቸው (ኤር 17፥21-22 ይመ)።
1፥34 *የኢየሱስን ማንነት ያውቁ ስለ ነበር፤* ሉቃስ፣
‘ክርስቶስ መሆኑን ያወቁ ስለነበር” ይላል (ሉቃ 4፥41)። ኢየሱስ
እርሱ ክርስቶስ መሆኑን በግልጽ ከማወጅ ይልቅ፣ ማንነቱን
በቃሉና በተግባሩ ለመግለጽ ፈለገ፤ አጋንንትም ይህን ዕቅዱን
እንዲያስናክሉበት አልፈቀደም።

## ኢየሱስ በገለልተኛ ስፍራ ጸለየ
1፥35-38 ተጓ ምብ - ሉቃ 4፥42:43

35ማለዳም ገና ጎሕ ሳይቀድ፣ ኢየሱስ ተነሥቶ
ከቤት ወጣ፤ ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራም
ሄዶ ይጸልይ ጀመር:: 36ስምዖንና ባልደረቦቹም
ተከትለው ይፈልጉት ጀመር፤ 37ባገኙትም ጊዜ፣
"ሰዉ ሁሉ ይፈልግሃል" አሉት::
38እርሱም፣ 'ከዚህ ተነሥተን በአቅራቢያ
ወዳሉት መንደሮች እንሂድ፤ እዚያም ልሰብክ፤
የመጣሁት ለዚሁ ነውና" አላቸው:: 39ስለዚህ
ወደ ምኵራባቸው እየገባ በመስበክና አጋንን
ትን በማስወጣት በመላዋ ገሊላ ይዘዋወር
ጀመር::

## ኢየሱስ ለምጻሙን ሰው አነጻ
1፥40- 44 ተጓ ምብ - ማቴ 8፥2-4፤ ሉቃ5፥12-14

40አንድ ለምጻምᐩ ወደ እርሱ ቀርቦ ከፊቱ
በመንበርከክ፣ "ብትፈቅድ እኮ ልታነጻኝ ትች
ላለህ" በማለት ለመነው::
41ኢየሱስም ለሰውየው በመራራት እጁን
ዘርግቶ ዳሰሰውና፣ "እፈቅዳለሁ፣ ንጻ" አለው::
42እርሱም ወዲያው ከለምጹ ነጻ፤ ከበሽታውም
ተፈወሰ::
43ኢየሱስም ሰውየውን አጥብቆ በማስጠንቀቅ
እንዲህ ሲል አሰናበተው፤ 44"ለማንም አንድ
ነገር እንኳ እንዳትናገር ተጠንቀቅ፤ ነገር
ግን ምስክር እንዲሆናቸው ሄደህ ራስህን ለካህን
አሳይ፤ ስለ መንጻትህም ሙሴ ያዘዘውን
መሥዋዕት አቅርብ" አለው:: 45ሰውየው ግን
በሄደበት ሁሉ ነገሩን በሰፊው አወራ፣
ወሬውንም አሠራጨ:: በዚህ ምክንያት ኢየሱስ
ወደ ማንኛውም ከተማ በግልጽ መግባት
አልተቻለውም፤ ከዚህም የተነሣ ከከተማ
ውጭ በሚገኙ ሰዋራ ቦታዎች መኖር ጀመረ፤
ሰዎች ግን ከየአቅጣጫው እርሱ ወዳለበት
መምጣት አላቋረጡም::

## ኢየሱስ ሽባ ፈወሰ
2፥3-12 ተጓ ምብ - ማቴ9፥2-8፤ ሉቃ5፥18-26

2 ኢየሱስ ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ቅፍር
ናሆም እንደ ተመለሰ፣ ወደ ቤት መግ
ባቱን ሕዝቡ ሰማ:: 2ስለዚህ ከበሩ ውጭ
እንኳ ሳይቀር ስፍራ እስኪታጣ ድረስ ብዙ ሕዝብ
ተሰበሰበ፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል
ሰበከላቸው:: 3ጥቂት ሰዎችም አንድ ሽባ
በአራት ሰዎች አሸክመው ወደ እርሱ አመጡ::
4ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ኢየሱስ ወዳለበት
መቅረብ ስላልቻሉ፣ የቤቱን ጣራ እርሱ
ባለበት በኩል ነድለው ቀዳዳ በማበጀት
ሽባው የተኛበትን ዐልጋ በዚያ አወረዱ::
5ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን፣
"አንተ ልጅ፣ ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል!" አለው::
6በዚያ ተቀምጠው የነበሩ አንዳንድ ጸሐፍት
ስለዚህ ነገር በልባቸው እያሰላሰሉ፣ 7"ይህ
ሰው እንዴት እንዲህ ይላል? በአምላክ ላይ
የስድብ ቃል እየተናገረ እኮ ነው! ከአንዱ ከእግዚ
አብሔር በስተቀር ማን ኀጢአትን ሊያስተስርይ
ይችላል?" ብለው አሰቡ::
8ኢየሱስም ወዲያው በልባቸው የሚያስ
ቡትን በመንፈሱ ተረድቶ፣ "እንዴት እንዲህ
ታስባላችሁ? 9ሽባውን፣ 'ኀጢአትህ ተሰርዮ
ልሃል' ከማለትና፣ 'ተነሥተህ ዐልጋህን ተሸክመህ
ሂድ' ከማለት የቱ ይቀላል? 10ነገር ግን የሰው
ልጅ በምድር ላይ ኀጢአትን ለማስተስረይ
ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ በማለት

1፥35 ሉቃ3፥21
1፥38 ኢሳ60፥1
1፥39 ማቴ4፥23:24
1፥40 ማር10፥17
1፥44 ዘሌ13፥49፤ 14፥1-32፤ማቴ8፥4
1፥45 ማር2፥13፤ ሉቃ5፥15:16:17፤ ዮሐ6፥2
2፥2 ቍ13፤ ማር1፥45
2፥3 ማቴ4፥24
2፥5 ሉቃ7፥48
2፥7 ኢሳ43፥25
2፥10 ማቴ8፥20

ᐩ40 ለምጽ የሚለው ቃል በግሪኩ አገላለጽ የተለያዩ የቆዳ በሽታዎችን ያመለክታል

1፥36 *ባልደረቦቹ፤* እንድርያስ፣ ያዕቆብ፣ ዮሐንስ፣ ምናልባትም ፊልጶስና ናትናኤል ሳይሆኑ አይቀሩም (ከዮሐ 1፥43-45 ጋር ያነጻጽሩ)::

1፥39 *በመላዋ ገሊላ፤* ወደ ገሊላ ካደረጋቸው ከሦስቱ ጕዞዎች፣ ይህኛው የመጀመሪያው ጕዞ ይመስላል (ሁለተኛው በሉቃ 8፥1ላይ፣ ሦስተኛው በማር 6፥6 እና በማቴ 11፥1 ላይ ይገኛል)::

1፥40 *ለምጻም* አማራጭ ትርጕሙን ይመ (ዘሌ 13-14 ይመ)::

1፥41 *ዳሰሰውና፤* እንደዚህ ያለውን ሰው መንካት በሙሴ ሕግ መሠረት ያረክሳል (ዘሌ 13 በተለይ ቍ 45-46 ይመ፤ እን ዲሁም ከዘሌ 5፥2 ጋር ያነጻጽሩ):: ጌታ ለሰውየው ያደረገለት አዘኔታ ከሃይማኖታዊ ሥርዐት ልቆ ተገኝቷል::

1፥44 *ለማንም አንድ ነገር እንኳ እንዳትናገር፤* የማቴ 8፥4፤ 16፥20 ማብ ይመ:: *ምስክር እንዲሆናቸው፤* መሥዋዕት ማቅረቡ የፈውሱን እውነተኛነት ከማረጋገጡ ሌላ፣ ኢየሱስ የሙሴን ሕግ እንዳከበረ ያሳያል:: አይሁድ ለምጽን የሚያነጻ እግዚአብሔር ብቻ ነው ብለው ስለሚያምኑ (2ነገ 5፥1-14ይመ)፣ የለምጻሙ መፈወስ ኢየሱስ መለኮታዊ ኀይል እንዳለው ያመለክታል:: *ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፤* የሉቃ 5፥14 ማብ ይመ::

1፥45 *ወደ ማንኛውም ከተማ በግልጽ መግባት አልተቻለውም፤* ኢየሱስ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሕዝቡ ዘንድ እየታወቀ በመሄዱና (1፥28፤ 3፥7-8፤ ሉቃ 7፥17 ይመ) የአይሁድ አለቆችም ከቀን ወደ ቀን ተቃውሞአቸውን እያባባሱ በመምጣታቸው (2፥6-7:16:23-24፤ 3፥2:6:22 ይመ) ከገሊላ ወጣ ብሎ በአካባቢው ወዳሉ ወደ ሌሎች ቦታዎች መሄድ ግድ ሆነበት::

2፥1 *ቤት፤* ኢየሱስ በቅፍርናሆም በነበረ ጊዜ፣ ማረፊያው የጴጥሮስ ቤት ሳይሆን አልቀረም (1፥21:29 ይመ)::

2፥2 *ብዙ ሕዝብ ተሰበሰበ፤* ቀደም ሲል ኢየሱስን በአድናቆት የተቀበሉት ሰዎች (1፥32-33:37)፣ ተመልሶም ሲመጣ በጋለ ስሜት ተቀብለውታል::

2፥3 *ሽባ፤* ይህ ሰው መራመድ የማይችል ነበር ከማለት በቀር፣ ስለ በሽታው በግልጽ የተነገረ ነገር የለም:: አራቱ ሰዎች ኢየሱስን በዚያኑ ዕለት ለማግኘት ያደረጉት ከፍተኛ ጥረት፣ በሽተኛው አሥጊ ደረጃ ላይ እንደ ነበረ ያመለክታል::

2፥4 *የቤቱን ጣራ ... ነድለው፤* በፓሌስቲና የሚገኝ ቤት ጣራው ጠፍጣፋ ስለ ሆነ፣ በውጭ በኩል በደረጃ ይወጣል፤ ጣራ ውም በዕንጨት ተዋቅሮ በላዩ ላይ የተነባበረ ሸክላ ይደራረባል፤ በድንጋይም ተገጥሞ በስፍራው ይያዛል::

2፥5 *ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ፤* የሽባውንና እርሱን ይዘውት የሄዱትን የአራቱን ሰዎች ብርቱ ጥረት፣ ኢየሱስ ከእምነት እንደ ሆነ ተመለከተላቸው:: *አንተ ልጅ፤ ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል፤* ኢየሱስ ለሰውየው ከሁሉ በላይ የሚያስፈልገውን የኀጢአት ይቅርታ በቅድሚያ ሰጠው::

2፥7 *በአምላክ ላይ የስድብ ቃል እየተናገረ እኮ ነው! ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ማን ኀጢአትን ሊያስተሰርይ ይችላል?* በአይሁድ ትምህርተ መለኮት መሠረት መሲሑ እንኳ የኀጢአትን ስርየት ማስገኘት አይችልም ነበር፤ ኢየሱስ ኀጢአትን ይቅር ማለቱ የመለኮት ባሕርይ አለኝ እንደ ማለት በመሆኑ፣ አምላክን እንደ መሳደብ ተቈጥሮበታል (የ14፥64 ማብ ይመ)::

2፥9 *የቱ ይቀላል?* ኢየሱስ ኀጢአትን ይቅር ማለትም ሆነ መፈወስ ሁለቱም ቀላል እንዳልሆኑ ለመግለጽ የተናገረው ይሆናል፤ ሁለቱም በሰው ዐቅም ሊከናወኑ የሚችሉ አይደሉም፤ ለእግዚ አብሔር ግን ሁለቱም ቀላል ናቸው::

2፥10 *ነገር ግን . . . እንድታውቁ፤* ይህ ለጸሓፍት የተነገረ ሳይሆን አይቀርም፤ "ሽባውን" የሚለው ቃል ቀድሞ ከሚናገራ ቸው ሰዎች ዘወር ብሎ ለሌላ ሰው መናገሩን ያመለክታል:: "የሰው ልጅ" ስለሚለው ስያሜ የ 8፥31 ማብ ይመ:: ከታምራት አስፈላጊነት አንዱ የኢየሱስን መለኮትነት ማሳየት ነው:: የታምራዊ ምልክቶችን ጥቅም በዮሐንስ ወንጌል (2፥11፤ 20፥30- 31) የተጠ ቀሰውን ይመ::

ሽባውን፣ [11]"ተነሥተህ ዐልጋህን ተሸክመህ
ወደ ቤትህ ሂድ" አለው:: [12]እርሱም ተነሥቶ
ሁሉም እያዩት ዐልጋውን ተሸክሞ ሄደ፤
በስፍራው የነበሩትም ሁሉ በሁኔታው በመደ
ነቅ፣ "የዚህ ዐይነት ነገር ፈጽሞ አይተን አናው
ቅም!" በማለት ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረቡ::

## የሌዊ መጠራት

2፥14-17 ተጓ ምብ - ማቴ 9፥9-13፤ሉቃ5፥27-32

[13]ኢየሱስም ዳግም ወደ ባሕሩ ዳርቻ ወጣ፤
ሕዝቡም በብዛት ወደ እርሱ መጡ፤ እርሱም
አስተማራቸው:: [14]በዚያም ሲያልፍ የእልፍ
ዮስን ልጅ ሌዊን በቀረጥ መቀበያው ስፍራ
ተቀምጦ አየውና፣ "ተከተለኝ" አለው፤ እር
ሱም ተነሥቶ ተከተለው::

[15]በማቴዎስ ቤት በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፣
ብዙ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ኀጢአተኞች ተከትለ
ውት ስለ ነበር፣ ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ይመገቡ ነበር:: [16]ከፈሪሳውያን ወገን
የነበሩ ጸሐፍት ከኀጢአተኞችና ከቀረጥ ሰብሳቢ
ዎች ጋር ሲበላ ባዩት ጊዜ፣ ደቀ መዛሙርቱን
"ከቀረጥ ሰብሳቢዎችና ከኀጢአተኞች ጋር
ለምን ይበላል?" ሲሉ ጠየቋቸው::

[17]ኢየሱስም የሚናገሩትን ሰምቶ፣ "ሐኪም
የሚያስፈልጋቸው ሕመምተኞች እንጂ ጤነ
ኞች አይደሉም፤ እኔ ኀጢአተኞችን እንጂ
ጻድቃንን ወደ ንስሓ ልጠራ አልመጣሁም"
አላቸው::

2፥12 ማቴ9፥8፡33
2፥13 ማር1፥45፤ሉቃ5፥15፤ዮሐ6፥2
2፥14 ማቴ4፥19
2፥16 ሐሥ23፥91 ማቴ9፥11
2፥17 ሉቃ19፥10፤ 1ጢሞ1፥15

## ስለ ጾም የቀረበ ጥያቄ

2፥18-22 ተጓ ምብ - ማቴ9፥14-17፤
ሉቃ 5፥33-38

[18]የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና ፈሪሳውያን
ይጾሙ ነበር፤ አንዳንድ ሰዎችም መጥተው ኢየ
ሱስን፣ "የዮሐንስና የፈሪሳውያን ደቀ መዛ
ሙርት ሲጾሙ፣ የአንተ ደቀ መዛሙርት
የማይጾሙት ለምንድን ነው?" አሉት::

[19]ኢየሱስም፣ እንዲህ አላቸው፤ "ሙሽራው
ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎቹ ሊጾሙ ይች
ላሉን? ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሊጾሙ
አይችሉም፤ [20]ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት
ወቅት ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ግን ይጾማሉ::

[21]"በአሮጌ ልብስ ላይ አዲስ ጨርቅ የሚጥፍ
ማንም የለም፤ ይህ ቢደረግ ግን፣ አዲሱ ጨርቅ
አሮጌውን ይቦጭቀዋል፤ ቀዳዳውም የባሰ ይሰ
ፋል:: [22]እንዲሁም አዲስ የወይን ጠጅ በአሮጌ
አቊማዳ የሚያስቀምጥ የለም፤ ይህ ከተደረገማ
የወይን ጠጁ አቊማዳውን ያፈነዳዋል፤ የወይን
ጠጁም አቊማዳውም ይበላሻሉ:: ስለዚህ አዲስ
የወይን ጠጅ መቀመጥ ያለበት በአዲስ አቊ
ማዳ ነው::"

## ኢየሱስ የሰንበት ጌታ ነው

2፥23-28 ተጓ ምብ - ማቴ12፥1-8፤ ሉቃ6፥1-5
3፥1-6 ተጓ ምብ - ማቴ12፥9-14፤ ሉቃ 6፥6-11

[23]በሰንበት ቀን ኢየሱስ በእርሻ መካከል
ሲያልፍ፣ አብረውት በመንዝ ላይ የነበሩት
ደቀ መዛሙርቱ እሸት ይቀጥፉ ጀመር::
[24]ፈሪሳውያንም፣ "እነሆ፤ በሰንበት ቀን ለምን
የተከለከለ ነገር ያደርጋሉ?" ሲሉ ጠየቁት::

2፥18 ማቴ6፥16-18፤ሐሥ13፥2
2፥20 ሉቃ17፥22
2፥23 ዘዳ23፥25
2፥24 ማቴ12፥2

2፥12 *በሁኔታው በመደነቅ፤* የ 1፥22 ማብ ይመ::

2፥14 *የእልፍዮስን ልጅ ሌዊን፤* ማቴዎስን ነው (ማቴ 9፥9፤ 10፥3 ይመ):: መጠሪያ ስሙ ሌዊ ሆኖ፣ "ማቴዎስ" ("የእግዚአብሔር ስጦታ") የሐዋርያነት ስሙ ሳይሆን አይቀርም:: *በቀረጥ መቀበያው ስፍራ፤* ሌዊ፣ በገሊላው ገዥ በሄሮድስ አንቲጳስ ዘመን ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር (የሉቃ 3፥12 ማብ ይመ):: ኢየሱስ ሌዊን ያገኘበት የቀረጥ መሰብሰቢያ ቦታ፣ ከደማስቆ ተነሥቶ፣ ቅፍርና ሆምን ይዞ ወደ ሜድትራኒያን ባሕርና ወደ ግብፅ በሚወስደው ዓለም አቀፍ መንገድ ላይ ነበር (ኢሳ 9፥1 ላይ ይህ መንገድ "የባሕር መንገድ" ተብሎአል):: *እርሱም ተነሥቶ ተከተለው፤* የሉቃ 5፥28 ማብ ይመ::

2፥15 *ኀጢአተኞች፤* የሙሴን ሕግ መሠረት አድርገው ጸሐፍት የሰጡትን ትምህርት ያልተቀበሉትንና እጅግ ክፉ የሆኑትን ሰዎች የሚያመለክት ሲሆን፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎችን፣ አመንዝራዎችን፣ ቀማኞችንና የመሳሰሉትን የሚገልጽ ነበር:: *ይመገቡ ነበር፤* ከአንድ ማዕድ ተካፍሎ መብላት ወዳጅነትን የሚያመለክት ነበር::

2፥16 *ከፈሪሳውያን ወገን የነበሩ ጸሐፍት፤* ጸሐፍት ሁሉ ፈሪሳውያን ነበሩ ማለት አይደለም፤ ፈሪሳውያን የተባሉት፣ ከሶርያውያን የጭቈና አገዛዝ ነጻ ለመውጣት በተደረገው ጦርነት (166-142 ዓ.ቅ.ክ.) ከመቃብያን ጋር ግንባር የፈጠሩ ሐሲዲም በተባሉ ሃይማኖት አጥባቂ ወገኖች እግር የተተኩ ናቸው:: "ፈሪሳውያን" ተብለው መጠራት የጀመሩትም በዮሐንስ ሕርቃኑስ ዘመነ መንግሥት (135-105 ዓ.ቅ.ክ.) ነበር:: አንዳንዶቹ እውነተኛ የሃይማኖት ቅናት ያላቸው ሰዎች ቢሆኑም፣ ከጌታ ጋር ሲከራከሩ ከነበሩት ብዙዎቹ ግን ግብዞች፣ ምቀኞች፣ ግትሮችና ወግ አጥባቂዎች ነበሩ:: በፈሪሳውያን አመለካከት የእግዚአብሔር ጸጋ የሚገኘው ሕጉን አክብረው ለተገኙ ሰዎች ብቻ ነበር፤ የማቴ 3፥7፤ ሉቃ 5፥17 ማብ ይመ:: *ከቀረጥ ሰብሳቢዎች፤* በአይሁድ ኅብረተ ሰብ ዘንድ፣ ከእነርሱ ወገን የሆኑ ቀረጥ ሰብሳቢዎች የተናቁ ዜጎች ናቸው፤ ምስክሮች ወይም ዳኞች መሆንም አይችሉም ነበር፤ ከምኵራብም ይገለላሉ፤ ቤተ ሰቦቻቸውም እንኳ በአይሁድ ዘንድ የተናቁ ነበሩ፤ የማቴ 5፥46 ማብ ይመ::

2፥17 *ኀጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ... ልጠራ አልመጣሁም፤* ራሱን እንደ ጻድቅ የሚቈጥር ሰው ድነት እንደ ሚያስፈልገው አያውቅም፤ ኀጢአተኝነቱን የተረዳ ግን የድነትን አስፈላጊነት ያውቃል::

2፥18 *የዮሐንስ ... ደቀ መዛሙርት፤* የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ይጾሙ የነበረው፣ መጥምቁ ዮሐንስ በእስር ቤት ስለ ነበረ (1፥14 ይመ) ሊሆን ይችላል፤ ወይም ዮሐንስ መዳን ተቃርቦአል እያለ ሲሰብክ ስለ ነበር፣ ይህ ፈጥኖ እንዲደርስ እንደ ንስሓ ቈጥረው የመጾም ልማድ ኖሮአቸው ሊሆን ይችላል:: *የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት፤* በመሠረቱ ፈሪሳውያን አስተማሪዎች አልነበሩም፤ ይሁን እንጂ ከእነዚሁ ውስጥ ጸሐፍት የሆኑት ደቀ መዛሙርት ነበሯቸው:: በሌላ በኩል ደግሞ፣ ሐረጉ በፈሪሳውያን ትምህርት የተጠመዱትን ሰዎች በጥቅሉ ሊያመለክት ይችላል:: *ሲጾሙ፤* በሙሴ ሕግ ጾም የታዘዘው በማስተሰሪያ ቀን ብቻ ነው (ዘሌ16፥29:31፤ 23፥27-32፤ ዘኍ29፥7):: ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ግን፣ አይሁድ በዓመት ውስጥ አራት ተጨማሪ ጾም ይጾሙ ነበር (ዘካ 7፥5፤ 8፥19):: ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፣ ፈሪሳውያን በሳምንት ሁለት ቀን ይጾሙ ነበር (ሉቃ 18፥12 ይመ)::

2፥19 *ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎቹ ሊጾሙ ይችላሉን?* ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ከሙሽራ ሚዜዎች ጋር አነጻጸረ:: የአይሁድ የሰርግ ድግስ የተለይ የመደሰቻ ጊዜ ነበር፤ የግብዣውም ጊዜ እስከ ሳምንት ይዘልቅ ነበር:: ጾም ከኀዘንና ከተመስጦ ጋር የተያያዘ በመሆኑ፣ ፈንጠዝያ በሚደረግበት የሰርግ ሰሞን ጾም የሚታሰብ ነገር አይደለም::

2፥20 *ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወቅት፤* ሙሽራው ኢየሱስ ነው፤ ከደቀ መዛሙርቱም በሞት ይወሰዳል፤ በዚያን ጊዜ መጾም ተገቢ ይሆናል::

2፥22 *በአዲስ አቊማዳ፤* የማቴ 9፥17 ማብ ይመ::

2፥23 *እሸት ይቀጥፉ፤* በዘዳ 23፥25 መሠረት እሸት መቅጠፍ ስለ ተፈቀደ፣ የደቀ መዛሙርቱ ድርጊት በራሱ ስሕተት አልነበረበትም::

2፥24 *በሰንበት ቀን ... የተከለከለ፤* "ሚሽናህ" በተባለው የአይሁዳ ትውፊት መጽሐፍ ውስጥ በዕለተ ሰንበት አዝመራን መሰብሰብ (ደቀ መዛሙርቱ ያደረጉት እንኳ ሳይቀር) የተከለከለ

[25]እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "ዳዊት በተራበና
የምግብ ፍላጎት በጸናበት ጊዜ አብረውት
ከነበሩት ሰዎች ጋር ያደረገውን አላነበባች
ሁምን? [26]በሊቀ ካህናቱ በአብያታር ዘመን
ወደ እግዚአብሔር ቤት ገብቶ፣ ካህናት ብቻ
እንዲበሉት የተፈቀደውን የተቀደሰ ኅብስት
ራሱ በልቶ አብረውት ለነበሩትም ሰዎች
ሰጣቸው።"

[27]ደግሞም እንዲህ አላቸው፤ "ሰንበት ለሰው
ተፈጠረ እንጂ፣ ሰው ለሰንበት አልተፈጠረም፤
[28]ስለዚህ የሰው ልጅ የሰንበት ጌታዋ ነው።"

3 በሌላ ጊዜ ወደ ምኵራብ ገባ፤ በዚያም
እጁ የሰለለች ሰው ነበር። [2]በምክንያት
ሊከሱት የሚፈልጉ ሰዎችም በሰንበት ቀን
ይፈውሰው እንደ ሆነ ለማየት ይጠባበቁ
ነበር። [3]እርሱም እጁ የደረቀችውን ሰው፣
"በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ተነሥተህ ቁም"
አለው።

[4]ኢየሱስም፣ "በሰንበት ቀን የተፈቀደው
መልካም ማድረግ ነው ወይስ ክፉ? ሕይወት
ማዳን ነውን ወይስ ማጥፋት?" አላቸው። እነ
ርሱ ግን ዝም አሉ።

[5]በልባቸው ደንዳናነት አዝኖ በዙሪያው የቆ
ሙትን በቍጣ ተመለከታቸውና ሰውየውን፣
"እጅህን ዘርጋ!" አለው፤ ሰውየውም እጁን
ዘረጋ፤ እጁም ፍጹም ደኅና ሆነችለት።

[6]ፈሪሳውያንም እንዴት ሊያጠፉት እንደ
ሚችሉ ከሄሮድስ ወገን ከሆኑት ጋር መመ
ካከር ጀመሩ።

## ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ተከተሉ

3፥7-12 ተጓ ምብ – ማቴ 12፥15:16፤ ሉቃ6፥17-19

[7]ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ባሕሩ
ሄደ፤ ከገሊላ የመጣ እጅግ ብዙ ሕዝብም
ተከተለው፤ [8]የሚሠራውን ነገር የሰሙ ሰዎችም
ከይሁዳ፣ ከኢየሩሳሌም፣ ከኤዶምያስ፣ በዮር
ዳኖስ ማዶ ካለው አገር እንዲሁም ከጢሮስና
ከሲዶና አካባቢ ወደ እርሱ መጡ። [9]የተሰ
በሰበውም ሕዝብ እንዳያጨናንቀው አነስተኛ
የሆነ ጀልባ እንዲያዘጋጁለት ደቀ መዛሙርቱን
አዘዛቸው። [10]ብዙዎችን ፈውሶ ስለ ነበር፣ በሕ
መም የሚሠቃዩ ሁሉ ሊዳስሱት ይሽቀዳ
ደሙ ነበር። [11]ርኩሳን መናፍስትም ባዩት
ቍጥር ከፊቱ እየወደቁ፣ "አንተ የእግዚአብሔር
ልጅ ነህ!" በማለት ይጮኹ ነበር። [12]እርሱ
ግን ማንነቱን እንዳይገልጹ አጥብቆ ይገሥጻቸው
ነበር።

## የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መሾም

3፥16-19 ተጓ ምብ ማቴ 10፥2-4፤ ሉቃ6፥14-16፤ሐሥ1፥13

[13]ኢየሱስ ወደ ተራራ ወጥቶ የሚፈልጋ
ቸውን ወደ እርሱ እንዲመጡ ጠራቸው፤

ʷ11 ወይም ክፉ፤ እንዲሁም ቍ 30 ይመ

2፥26 ዘሌ24፥5-9፤ 1ሳሙ21፥1-6፤ 2ሳሙ8፥17፤1ዜና24፥6
2፥27 ዘፀ23፥12፤ ዘዳ5፥14፤ቈላ2፥16
2፥28 ማቴ8፥20
3፥1 ማቴ4፥23፤ ሉቃ1፥21
3፥2 ማቴ12፥10፤ ሉቃ14፥1
3፥6 ማቴ12፥14፤ 22፥16፤ማር12፥13
3፥7 ማቴ4፥25
3፥8 ማቴ11፥21
3፥10 ማቴ4፥23፤ 9፥20
3፥11 ማቴ1፥23፡ 24፤4፥3
3፥12 ማቴ8፥4፤ ማር1፥24:25:34፤ ሐሥ16፥17:18
3፥13 ማቴ5፥1

ነበር፤ ዘፀ 34፥21 ይመ።

2፥25 *ዳዊት . . . ያደረገውን፤* 1ሳሙ 21፥1-6 ይመ። ከብሉይ ኪዳን በተጠቀሰው ሁኔታና ደቀ መዛሙርቱ ሕግን ተላልፈዋል ተብለው በተከሰሱበት በዚህ ድርጊት መካከል ተመሳሳይ ሁኔታ ይታያል፤ ይኸውም በሁለቱም ሁኔታ ቅዱሳን የተባሉ ሰዎች የተከለከለውን ነገር መፈጸማቸው ነው፤ ይሁን እንጂ በሰንበት ዕለት በጎ ማድረግና በሞት አፋፍ የሚገኘውን ሕይ ወት ማዳን፣ "የተፈቀደ" ተግባር በመሆኑ፣ ዳዊትና የጌታ ደቀ መዛሙርት የፈጸሙት ከሕጉ መንፈስ ውጪ አልነበረም (ኢሳ 58፥6-7፤ ሉቃ 6፥6-11፤ 13፥10-17፤ 14፥1-6 ይመ)።

2፥26 *በሊቀ ካህናቱ በአብያተር ዘመን፤* በ1ሳሙ 21፥1 በተገለጸው መሠረት፣ የአብያተር አባት አቢሜሌክ በዚያን ጊዜ ሊቀ ካህናት ነበር (የ2ሳሙ 8፥17 ማብ ይመ)። *የተቀደሰ ኅብስት፤* የማቴ 12፥4 ማብ ይመ።

2፥27 *ሰንበት ለሰው ተፈጠረ እንጂ፣ ሰው ለሰንበት አልተ ፈጠረም፤* የአይሁድ ትውፊት፣ ሰንበትን በመጠበቅ ሕግ ላይ እጅግ ብዙ ደንቦችን ስላከለበት፣ ከዐቅም በላይ ሸክም ሆኖ ነበር። ዕለተ ሰንበት አንድ ሰው ሥጋውን፣ አእምሮውንና መንፈሱን የሚያድስበት ቀን መሆኑን በመግለጽ፣ ኢየሱስ የተደራ ረተውን የሰው ሥርዐት ወደ ኋላ ጥሎ፣ እግዚአብሔር ሰንበትን ለሰዎች ያዘጋጀበትን ዐላማ በአጽንዖት አስረዳ (ዘፀ20፥8-11 ይመ)።

*2፥28፤* የሉቃ 6፥5 ማብ ይመ።

*3፥1-6፤* ኢየሱስ የሰንበት ጌታ መሆኑ የተገለጠበት ክፍል ነው (2፥28 ይመ)።

3፥2 *ሊከሱት፤* ኢየሱስ በአንድ ስፍራ ከተገኘ፣ ስብከቱን፣ ተግባሩንና ማንነቱን በተመለከተ አንድ አቋም መያዝ የግድ ይሆናል። በ2፥6-7 ላይ ቀደም ሲል የተከሠተው ጥላቻ እየተስፋፋ መጥቶአል (የቍ 6 ማብ ይመ)። *ሰዎችም፤ ፈሪሳውያንን ነው* (ቍ6 ይመ፤ ከሉቃ 6፥7 ጋር ያነጻጽሩ)። *በሰንበት ቀን ይፈውሰው እንደ ሆነ ለማየት፤ ፈሪሳውያን፣* ኢየሱስ ታምራት የማድረግ ኀይል እንደ ነበረው ማመናቸውን ያሳያል። በዚህ ጊዜ የነበረው ጥያቄ፣ "ሊያድነው ይችላልን?" ሳይሆን፣ "በዚህ ቀን ሊያድነው ይደፍራልን?" የሚል ነበር። አንድ ሰው ሕይወቱ በሞት አፋፍ ላይ የሚገኝ ከሆነ፣ በሰንበት ቀን ርዳታ እንዲደረግለት የአይሁድ ሕግ ያዛል፤ ኢየሱስ ያዳነው ሰው ግን እንደሚታወቀው፣ እዚህ ደረጃ ላይ አልደረሰም፤ የ2፥25፤ ሉቃ 13፥14 ማብ ይመ።

3፥4 *መልካም ማድረግ ነው ወይስ ክፉ? ሕይወት ማዳን ነውን ወይስ ማጥፋት?* "ኢየሱስ፣ ፈውሶ ሕይወትን ከማቈየትና ሳይፈውሱ ቀርቶ ሕይወት ሲጠፉ ከማየት የቱ እንደሚሻል" ጠየቀ። ይህ ጥያቄ ምስጢር ያዘለ ነው፤ ኢየሱስ ሰውየውን ለማዳን ሲጥር፣ ፈሪሳውያን ግን ጌታን ለመግደል ያሤሩ ነበርና። ስለዚህ እዚህ ላይ ሰንበትን ማን እንደ ሻራት ግልጽ ነው። *እነርሱ ግን ዝም አሉ፤* 12፥34 ይመ።

3፥6 *ፈሪሳውያንም እንዴት ሊያጠፉት እንደሚችሉ . . . መመካከር ጀመሩ፤* ኢየሱስን ለማጥፋት የተመካከሩት፣ በዚህ ክፍል በተጠቀሰው ምክንያት ብቻ ሳይሆን፣ ቀደም ሲል ባደረ ጋቸው ድርጊቶችም ጭምር ነገር ይዘውበት ነው (2፥6-7:16-17:24 ይመ) ፈሪሳውያንና ከሄሮድስ ወገን የሆኑት ኢየሱስን ለማጥፋት በሕማማቱ ሰሞን ማክሰኞ ዕለት እንደ ገና ሲማከሩ ይታያሉ (12፥13)። *ከሄሮድስ ወገን ከሆኑት፤* የሄሮድስ ሥርወ መንግ ሥት መሠረት የሆነውን የሮምን መንግሥት ይደግፉ ነበር። የሄሮድስ ወገኖች የተባሉት ኢየሱስን በመቃወም ከፈሪሳውያን ጋር የተባበሩበት ምክንያት፣ ኢየሱስ በፖለቲካ ረገድ ሕዝቡን የሚቀሰቅስ ስለ መሰላቸው ነበር፤ የማቴ 22፥15-17 ማብ ይመ።

*3፥8፤* እዚህ ላይ የኢየሱስ ዝና በሕዝቡ ዘንድ በፍጥነት እየተስፋፋ መምጣቱን እንረዳለን። የተጠቀሰው የቦታዎች ዝርዝር የሚያመለክተው፣ ሕዝቦቹ እየጐረፉ የመጡት ከቅፍርናሆምና ከአካባቢዋ ብቻ ሳይሆን፣ ከእስራኤልና ከአጎራባች አገሮች ጭምር መሆኑን ነው። ማርቆስ ከኤዶምያስ በስተቀር በተጠቀሱት ስፍራዎች ሁሉ ኢየሱስ አገልግሎት ማከናወኑን ይገልጻል (ስለ ገሊላ 1፥14፤ በዮርዳኖስ ማዶ ስላለው አገር 5፥1 እና 10፥1፤ ስለ ጢሮስና ሲዶና 7፥24:31፤ ስለ ይሁዳ 10፥1 ስለ ኢየሩ ሳሌም 11፥11 ይመ)። *ኤዶምያስ፤* "ኤዶም" ለሚለው የዕብራ ይስጥ ቃል የግሪኩ አቻ ነው። እዚህ ላይ ግን የሚያመለክተው የቀድሞዋን የኤዶም ግዛት ሳይሆን፣ ከይሁዳ በስተ ደቡብ የሚገኘውን የፓሌስቲናን ምዕራባዊ ክፍል ነው።

3፥11 *ርኩሳን መናፍስት፤* የ1፥23 ማብ ይመ። *አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!* ርኩሳን መናፍስቱ የኢየሱስን ማንነት ዐው ቀዋል፤ ሆኖም አላመኑበትም (የ1፥24 ማብ ይመ)።

3፥12 *ማንነቱን እንዳይገልጹ፤* የኢየሱስ ማንነት የሚገለ ጽበት ጊዜ ገና አልደረሰም ነበር (1፥34 እና ማብ፤ እንዲሁም የማቴ 8፥4፤ 16፥20 ማብ ይመ)፤ ደግሞም የኢየሱስ ማንነት መገለጽ ያለበት በአጋንንት አማካይነት መሆን የለበትም።

እነርሱም ወደ እርሱ መጡ። 14ከእርሱ ጋር
እንዲሆኑ፣ ለስብከትም ይልካቸው ዘንድ ዐሥራ
ሁለቱን ሾማቸው፤ ሐዋርያትም ብሎ ጠራ
ቸው[ሠ]፤ 15አጋንንትን እንዲያስወጡም ሥልጣን
ሰጣቸው። 16የሾማቸውም ዐሥራ ሁለቱ እነዚህ
ናቸው፤ ጴጥሮስ ብሎ የጠራው ስምዖን፣
17ቦአኔርጌስ ይኸውም፣ 'የነጐድጓድ ልጆች'
ብሎ የጠራቸው የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና
ወንድሙ ዮሐንስ፤ 18እንድርያስ፣ ፊልጶስ፣
በርቶሎሜዎስ፣ ማቴዎስ፣ ቶማስ፣ የእልፍዮስ
ልጅ ያዕቆብ፣ ታዴዎስ፣ ተቀናቃኙ ስምዖን፣
19እንዲሁም አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ
ይሁዳ።

## ኢየሱስና ብዔል ዜቡል

3፥23-27 ተጓ ምብ - ማቴ12፥25-29፤
ሉቃ11፥17-22

20ከዚያም ኢየሱስ ወደ አንድ ቤት ገባ፤
እርሱና ደቀ መዛሙርቱ ምግብ መብላት
እንኳ እስኪሳናቸው ድረስ ሕዝቡ እንደ ገና
በብዛት ተሰበሰበ። 21ሁኔታውን የሰሙ ዘመ
ዶቹም፣ "አእምሮውን ስቶአል" በማለት ይዘ
ውት ለመሄድ ወዳለበት መጡ።

22ከኢየሩሳሌም የመጡ ጸሐፍትም፣ "ብዔል
ዜቡል[ረ] አድሮበታል፤ አጋንንትን የሚያወጣው
በአጋንንት አለቃ ነው" አሉ።

23እርሱም ጠራቸውና በምሳሌ እንዲህ አላቸው፤
"ሰይጣን ሰይጣንን እንዴት ሊያስወጣ ይችላል?
24እርስ በርሱ የሚከፋፈል መንግሥት ሊጸና
አይችልም፤ 25ቤትም እርስ በርሱ ከተለያየ
ሊቆም አይችልም። 26እንደዚሁም ሰይጣን እርስ
በርሱ የሚፃረርና የሚከፋፈል ከሆነ ሊቆም
አይችልም፤ ያበቃለታል። 27ከዚህም የተነሣ
አንድ ሰው አስቀድሞ ኀይለኛውን ሰው ሳያስር
ወደ ኀይለኛው ሰው ቤት ሊገባና ንብረቱን
ሊዘርፍ አይችልም፤ ቤቱን መዝረፍ የሚቻ
ለው ኀይለኛውን ሰው ሲያስር ብቻ ነው።
28እውነት እላችኋለሁ፤ የሰው ልጆች ኀጢአ
ትና የሚሳደቡት ስድብ ሁሉ ይሰረይላቸዋል፤

3፥14 ማር6፥30
3፥15 ማቴ10፥1
3፥16 ዮሐ1፥24
3፥20 ቍ7፤
ማር6፥31
3፥21 ዮሐ10፥20፤
ሐሥ26፥24
3፥22
ማቴ9፥34፤10፥25፤1
1፥18፤12፥24፤15፥1፤
ዮሐ7፥20፤8፥48፡52፤
10፥20
3፥23 ማር4፥2፡10
3፥27 ኢሳ49፥24፡25
3፥29 ማቴ12፥31፡
32፤ሉቃ12፥10
3፥31 ቍ21
4፥1 ማር2፥13፤3፥7
4፥2 ቍ11፤
ማር3፥23
4፥3 ቍ26

29ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ
ቃል የሚናገር ሁሉ የዘላለም ኀጢአት ዕዳ
ይሆንበታል እንጂ ለዘላለም አይሰረይለትም።
30ይህንንም ያለው፣ "ርኩስ መንፈስ አለ
በት" ስላሉት ነበር።

## የኢየሱስ እናትና ወንድሞቹ

3፥31-35 ተጓ ምብ - ማቴ12፥46-50፤
ሉቃ8፥19-21

31ከዚህ በኋላ እናቱና ወንድሞቹ መጡ፤
በውጭ ቆመውም ሰው ልከውበት አስጠሩት።
32በዙሪያው የተቀመጡ ብዙ ሰዎችም፣ "እነሆ፤
እናትህና ወንድሞችህ ውጭ ይፈልጉሃል"
አሉት።

33እርሱም መልሶ፣ "እናቴ ማን ናት
ወንድሞቼስ እነማን ናቸው?" አላቸው።

34በዙሪያው ወደ ተቀመጡትም በመመ
ልከት፣ እንዲህ አለ፤ "እናቴና ወንድሞቼ
እነዚህ ናቸው" 35የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያ
ደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ፣ እኅቴ፣ እናቴም
ነውና።"

## የዘሪው ምሳሌ

4፥1-12 ተጓ ምብ - ማቴ13፥1-15፤ ሉቃ8፥4-10
4፥13-20 ተጓ ምብ - ማቴ13፥18-23፤
ሉቃ8፥ 11-15

4በሌላ ጊዜ ደግሞ በባሕሩ አጠገብ ያስተ
ምር ጀመር። እርሱ ባለበት አካባቢ እጅግ
ብዙ ሕዝብ ስለ ተሰበሰበ፣ በባሕሩ ላይ ወዳ
ለች ጀልባ ገብቶ ተቀመጠ፤ ሕዝቡም ሁሉ
በባሕሩ ዳርቻ ባለው ስፍራ ላይ ተሰብስቦ
ነበር። 2እርሱም ብዙ ነገሮችን በምሳሌ አስ
ተማራቸው፤ እንዲህም አላቸው፤ 3"ስሙ፤
አንድ ዘሪ ዘር ሊዘራ ወጣ። 4ዘሩን በሚዘራበ
ትም ጊዜ አንዳንዱ መንገድ ላይ ወደቀ፤
ወፎችም መጥተው ለቀሙት በሉት። 5ሌላው
በቂ ዐፈር በሌለበት በጭንጫ ቦታ ላይ ወደቀ፤
ዐፈሩ ጥልቀት ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፤

ሠ14 አንዳንድ ቅጆች *ሐዋርያትም ብሎ ጠራቸው* የሚለው ሐረግ የላቸውም
ረ22 ግሪኩ *ብዔዜቡል* ወይም *ብዔልዜቡል* ይላል

3፥14 *ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ፤* የዐሥራ ሁለቱ ሥልጠና፣ ልዩ ልዩ ትምህርትንና የአገልግሎት ልምምድን ያካተተ ብቻ ሳይሆን፣ ከኢየሱስ ጋር ዘወትር መገኘትንና የጠበቀ ኅብረት ማድረግም ነበር። *ሐዋርያትም ብሎ ጠራቸው፤* የ6፥30 ማብ ይመ።

*3፥16-19፤* የሉቃ 6፥14-16 ማብ ይመ።

3፥17 *የነጐድጓድ ልጆች፤* ባሕሪያቸውን ለማመልከት ሳይሆን አይቀርም (የ10፥37፤ የሉቃ 9፥54-55 ማብ ይመ)።

3፥18 *ታዴዎስ፤* "የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ" ማለት ይሆናል (ሉቃ 6፥16፤ ሐሥ 1፥13 ይመ)። *ተቀናቃኙ፤* የማቴ 10፥4 ማብ ይመ።

3፥19 *የአስቆሮቱ፤* ምናልባት የስሙ ትርጕም፣ "የቄርዮት ሰው" (የቄርዮት ሄዝሮን ከተማ) ማለት ሊሆን ይችላል (ኢሱ 15፥25 ይመ)። ይህ የቄርዮት ሄዝሮን ከተማ ከሔብሮን ከተማ ዐሥራ ዘጠኝ ኪ.ሜ. ያህል በስተ ደቡብ ርቆ ይገኝ ነበር።

3፥20 *አንድ ቤት፤* የጴጥሮስና የእንድርያስ ቤት ሳይሆን አይቀርም (1፥29፤ 2፥1 ይመ)።

3፥21 *ዘመዶቹም . . . ይዘውት ለመሄድ ወዳለበት መጡ፤* ከናዝሬት ወደ ቅፍርናሆም መምጣታቸውም ጥርጥር የለውም፤ ርቀቱም 48 ኪ.ሜ. ገደማ ይሆናል (ቍ 31 ይመ)።

3፥22 *ብዔል ዜቡል፤* የማቴ 10፥25 ማብ ይመ።

3፥23 *በምሳሌ፤* እዚህ ላይ የቃሉ አገባብ በማነጻጸር ስሜት ነው (የ4፥2 ማብ ይመ)።

3፥27 *ኀይለኛው ሰው ቤት ሊገባና ንብረቱን ሊዘርፍ፤* ኢየሱስ ሰዎችን ከሰይጣን እስራት ነጻ በሚያወጣበት ጊዜ፣ ሰይጣንን አስሮ ቤት ንብረቱን መዝረፉ ነው።

3፥28 *እውነት እላችኋለሁ፤* ኢየሱስ የሚናገረውን እውነት ለማጽናት የሚጠቀምበት ማረጋገጫ ነው (8፥12፤ 9፥1፡41፤ 10፥15፡29፤ 11፥23፤ 12፥43፤ 13፥30፤ 14፥9፡18፡25፡30 ይመ)።

3፥29 *በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ ... ለዘላለም አይሰረይለትም፤* ኢየሱስ ይህን ኀጢአት በቍ 30 ላይ ገልጾአል (ከቍ 22 ጋር ያነጻጽሩ)። ጸሐፍት ኢየሱስ ያደረገውን የማዳን ታምር፣ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይሆን ከሰይጣን ነው አሉ (የማቴ 12፥31 ማብ ይመ)።

3፥31 *እናቱና ወንድሞቹ፤* የሉቃ 8፥19 ማብ ይመ።

3፥35 *የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፤* የእግዚ አብሔር መንፈሳዊ ቤተ ሰብ አባል መሆን፣ የአንድ ምድራዊ ቤተሰብ አባል ከመሆን ይበልጣል፤ አንድ ክርስቲያን የእግዚ አብሔር ቤተ ሰብ አባልነቱን የሚያረጋግጠው ጌታን ሲታዘዝ ነው (የ10፥30 ማብ ይመ)።


4፥1 *ተቀመጠ፤* ተቀምጦ ማስተማር የአይሁድ መምህራን ልማድ ነበር (ማቴ 5፥1፤ ሉቃ 5፥3፤ ዮሐ 8፥2 ይመ)።

4፥2 *በምሳሌ፤* መንፈሳዊ ወይም ሥነ ምግባራዊ እውነታን ለመግለጽ እጥር ምጥን ባለ ዘይቤ፣ በማነጻጸር (የ3፥23 ማብ ይመ)፣ በማመሳሰል ወይም በአበው ተረት መልክ የሚቀርብ በተራ አኗኗር ላይ የተመሠረተ ትረካ ነው። በመሠረቱ አንድን ዋና ሐሳብ ይገልጻል እንጂ፣ በምሳሌው ውስጥ የተካተተ ነገር ሁሉ ትርጕም ይኖረዋል ማለት አይደለም፤ የማቴ 13፥3፤ የሉቃ 8፥4 ማብ ይመ።

*4፥3-8፤* በዚያን ዘመን ዘር የሚዘራው በእጅ ስለ ነበር፣ አንዳንዱ ቅንጣት ባልተፈለገ ቦታ መውደቁ አይቀርም (የሉቃ

# ኢየሩሳሌም

## በኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ዘመን




*ቦታዎቹ የሚታወቁ ቢሆንም የሕንጻዎቹ አሠራር ግን አይታወቅም:: ሥዕሉ የቀረበው ከሮማውያን ሕንጻ አሠራር በመነሣት ነው::

**ቦታዎቹና የሕንጻዎቹ አሠራር አይታወቅም፤ ሆኖም በታሪክ ተጽፈው ስለሚገኙ ለገለጻ እንዲያመች የቀረቡ ናቸው::

***ጥንታዊ ገጽታዎች ስሉ ወይም አቀማመጣቸው በማስረጃ የተደገፈ ነው:: ስማቸው ካልተጻፈ በስተቀር በዚህ ስዕል ላይ የሚታዩት ሕንጻዎችና መንገዶች በሰዓሊው ምናብ የቀረቡ ናቸው:: የቅጥሮቹ ከፍታ ከቤተ መቅደሱ በስተቀር በአጠቃላይ አይታወቅም::

በምሥራቅ፣ በደቡብና በምዕራብ በኩል ያሉ ሸለቆዎች የከተማውን መስፋፋት በሰሜን በኩል ብቻ እንዲሆን አድርገዋል::

6ፀሓይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፤ ሥር ስላል
ነበረውም ደረቀ:: 7ሌላው ዘር ደግሞ በእሾኽ
መካከል ወደቀ፤ እሾኹም አድጎ የዘሩን ተክል
ስላነቀው ፍሬ አላፈራም:: 8ሌላው ዘር ደግሞ
በመልካም መሬት ላይ ስለ ወደቀ በቅሎ
አደገ፤ ፍሬም ሰጠ፤ አንዱ ሠላሣ፣ አንዱ ሥልሳ፣
ሌላውም መቶ ፍሬ አፈራ::" 9ቀጥሎም ኢየ
ሱስ፣ "የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ" አለ::

10ብቻውን በሆነ ጊዜ፣ ዐሥራ ሁለቱና አብ
ረውት የነበሩት ሌሎች ስለ ምሳሌዎቹ ጠየ
ቁት:: 11እርሱም፣ "ለእናንተ የእግዚአብሔር
መንግሥት ምስጢር ተሰጥቶአችኋል፤ በውጭ
ላሉት ግን ነገር ሁሉ በምሳሌ ይነገራቸዋል፤
12ይኸውም፣ "ማየቱን እንዲያዩ እንዳያስተ
ውሉትም፣ መስማቱን እንዲሰሙ ልብ እንዳ
ይሉትም፣ እንዳይመለሱና ኀጢአታቸው እንዳይ
ሰረይላቸው ነው" አላቸው::

13ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ "ይህን
ምሳሌ አልተረዳችሁትምን? ታዲያ ሌሎቹን
ምሳሌዎች ሁሉ እንዴት ልትረዱ ትችላላ
ችሁ? 14ዘሪው ቃሉን ይዘራል:: 15አንዳንድ ሰዎች
በመንገድ ላይ የወደቀውን ዘር ይመስላሉ፤
ቃሉን በሚሰሙበት ጊዜ ሰይጣን ወዲያውኑ
መጥቶ በውስጣቸው የተዘራውን ቃል ይወ
ስደዋል:: 16እንዲሁም ሌሎች በጭንጫ ቦታ
ላይ የተዘራውን ዘር ይመስላሉ፤ ቃሉን በሚሰ
ሙበት ጊዜ በደስታ ይቀበሉታል፤ 17ነገር ግን
ሥር የሌላቸው ስለ ሆኑ የሚቈዩት ለጥቂት
ጊዜ ብቻ ነው፤ በቃሉ ምክንያት መከራ
ወይም ስደት በመጣ ጊዜ ወዲያውኑ ይሰና
ከላሉ:: 18ሌሎቹ ደግሞ በእሾኽ መካከል የተዘ
ራውን ዘር ይመስላሉ፤ ቃሉን መስማት ይሰ
ማሉ፤ 19ነገር ግን የዚህ ዓለም ውጣ ውረድ፣
የሀብት አጓጊነት እንዲሁም የሌሎች ነገሮች
ምኞት ቃሉን አንቀው በመያዝ ፍሬ እንዳያፈራ
ያደርጉታል:: 20ሌሎቹ በመልካም መሬት ላይ
የተዘራውን ዘር ይመስላሉ፤ እነዚህም ቃሉን
ሰምተው የሚቀበሉና ሠላሳ፣ ሥልሳ፣ መቶም
ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው"

4፥8 ዮሐ15፥5፤
ቈላ1፥6
4፥9 ቍ23፤
ማቴ11፥15
4፥11 ማቴ3፥2፤
1ቆሮ5፥12፡13፤
ቈላ4፥5፤1ተሰ4፥12፤
1ጢሞ3፥7
4፥12 ኢሳ6፥9:10፤
ማቴ13፥13-15
4፥14 ማር16፥9፤
ሉቃ1፥2፤ሐሥ4፥31፤
8፥4፤16፥6፤17፥11፤
ፊል1፥14
4፥15 ማቴ4፥10
4፥19 ማቴ19፥23፤
1ጢሞ6፥9:10:17፤
1ዮሐ2፥15-17
4፥21 ማቴ5፥15
4፥22 ኤር16፥17፤
ማቴ10፥26፤ሉቃ8፥1
7፤12፥2
4፥23 ቍ9፤
ማቴ11፥15
4፥24 ማቴ7፥2
4፥25 ማቴ25፥29
4፥26 ማቴ13፥24
4፥29 ራእ14፥15
4፥30 ማቴ13፥24
4፥33 ዮሐ16፥12
4፥34 ዮሐ16፥12

### የመቅረዙ መብራት ምሳሌ

21እንዲህም አላቸው፤ "መብራት አምጥታ
ችሁ ከዕንቅብ ወይም ከዐልጋ ሥር ታስቀ
ምጣላችሁን? የምታስቀምጡት በመቅረዙ ላይ
አይደለምን? 22ስለዚህ ተደብቆ የማይገለጥ፣
ተሸሽጎ ወደ ብርሃን የማይወጣ የለም፤ 23ሰሚ
ጆሮ ያለው ይስማ::"

24በመቀጠልም፣ "ስለምትሰሙት ነገር ጥንቃቄ
አድርጉ፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈር
ላችኋል፤ እንዲያውም ከዚያ የበለጠ ይጨመር
ላችኋል:: 25ላለው ይጨመርለታል፤ ከሌለው
ላይ ግን፣ ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል"
አላቸው::

### የአዳጊው ዘር ምሳሌ

26ከዚያም፣ እንዲህ አለ፤ "የእግዚአብሔር
መንግሥት ይህን ትመስላለች፤ አንድ ሰው
መሬት ላይ ዘር ይዘራል:: 27ሰውየው ሌሊት
ይተኛል፤ ቀን ይነሣል ነገር ግን እርሱ ሳያውቅ
ያ ዘር በቅሎ ያድጋል፤ 28ምድርም ራስዋ
በመጀመሪያ ቡቃያውን፣ ቀጥሎ ዛላውን፣
ከዚያም በዛላው ላይ የጐመራ ፍሬ ታስገኛለች፤
29ፍሬው እንደ በሰለም መከር በመድረሱ፣
ሰውየው ወዲያው ማጭዱን አንሥቶ አጨዳ
ይጀምራል::"

### የሰናፍጭ ቅንጣት ምሳሌ

4፥30-32፤ ተጓ ምብ - ማቴ 13፥31፡32፤ ሉቃ 13፥18:19

30ደግሞም እንዲህ አለ፤ "የእግዚአብሔርን መን
ግሥት ከምን ጋር እናነጻጽራታለን? በምንስ
ምሳሌ እንገልጻታለን? 31በምድር ላይ ከሚ
ዘራው ዘር ሁሉ እጅግ ያነሰችውን የሰናፍጭ
ቅንጣት ትመስላለች፤ 32ተዘርታ ካደገች በኋላ
ግን፣ በአትክልቱ ቦታ ከሚገኙት ዕፀዋት
ሁሉ ትበልጣለች፤ የሰማይ ወፎችም በትላልቅ
ቅርንጫፎቿ ጥላ ሥር ያርፋሉ::"

33ኢየሱስም ሰዎች መረዳት በሚችሉበት
መጠን፣ እነዚህን በመሳሰሉ ብዙ ምሳሌዎች
ነገራቸው:: 34ምንም ነገር ያለ ምሳሌ አይነ

8፥5 ማብ ይመ)::

4፥8 *መቶ ... አፈራ፤* መቶ እጥፍ የሚደርስ ምርት ማግኘት የተለመደ አልነበረም (ዘፍ 26፥12 ይመ):: መከር ለእግዚአብሔር መንግሥት መጠቃለል የተለመደ ምሳሌ ነበር (ኢል 3፥13፤ ራእ 14፥14-20 ይመ)::

4፥11 *የእግዚአብሔር መንግሥት ምስጢር፤* በአዲስ ኪዳን፣ "ምሥጢር" ሲባል እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገለጸው ነገር ማለት ነው፤ ምስጢሩም (ከዚህ ቀደም ያልታወቀው) የተገለጠው ለሁሉ ሲሆን፣ የሚያስተውሉት ግን እምነት ያላቸው ብቻ ናቸው:: በዚህ ክፍል መሠረት ምስጢሩ በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት የእግዚአብሔር መንግሥት መቅረብ ሊሆን ይችላል::

4፥12 *ይኸውም፤* ኢየሱስ በምሳሌ በማስተማሩ አገልግሎቱ ከኢሳይያስ አገልግሎት ጋር ይመሳሰላል፤ የኢሳይያስ አገልግሎት የተወሰኑ ተከታዮች ቢያስገኝም (ኢሳ 8፥16)፣ እግዚአብሔር ለሰጠው ማስጠንቀቂያና ላደረገው ጥሪ እንቢተኞች የሆኑት ምን ያህል አንገተ ደንዳኖች እንደ ሆኑ ያጋልጣል::

4፥14 *ቃሉን፤* ኢየሱስ ይሰብክ ለነበረው የእግዚአብሔር ቃል ባለን አቀባበል ላይ እንድናተኵር ያደርጋል፤ ቃሉ እያሌ መሰናክሎች ቢደቀኑበትም፣ ውሎ አድሮ የእግዚአብሔርን ዐላማ ይፈጽማል::

4፥17 *መከራ ወይም ስደት፤* 8፥34-38፤ 10፥30፤ 13፥9-13 ይመ::

4፥19 *የሀብት አጓጊነት፤* ብልጽግና ዐጕል የሆነ በራስ የመመካትን፣ የመደላደልንና የመመቻቸትን ስሜት ያሳድራል (10፥17-25፤ ዘዳ 8፥17-18፤ 32፥15፤ መክ 2፥4-11፤ ያዕ 5፥1-6 ይመ)::

4፥21 *መብራት አምጥታችሁ፤* መብራት ብርሃን እንዲሰጥ እንጂ፣ እንዳይደበቅ ከፍ ተደርጎ እንደሚቀመጥ ሁሉ፣ የዓለም ብርሃን የሆነው ኢየሱስም (ዮሐ 8፥12) መገለጥ አለበት:: *መብራት፤* የማቴ 5፥15 ማብ ይመ::

4፥25 *ላለው ይጨመርለታል፤* አሁን እውነትን ዐውቀን ከተመላለስንበት፣ ወደፊት ይበልጥ እንቀበላለን፤ እንደ ዐቅማችን የተቀበልነውን እውነት ሥራ ላይ ባናውለው ግን፣ ከዚያ የምናተርፈው አንዳች አይኖርም::

*4፥26-29፤* ይህን ምሳሌ የጻፈው ማርቆስ ብቻ ነው:: የዘሪው ምሳሌ ዘሩ እንዲበቅልና መከሩም ፍሬያማ እንዲሆን የዐፈሩ ለምነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ ያሳያል፤ እዚህ ላይ ግን ትኵረት የተሰጠው ዘሩ ራሱ ያለው ምስጢራዊ ኀይል ላይ ነው:: የወንጌሉ ቃል የራሱ የሆነው ኀይል አለው::

4፥29 *መከር በመድረሱ . . . ማጭዱን አንሥቶ አጨዳ ይጀምራል፤* በኢል 3፥13 ላይ ለእግዚአብሔር መንግሥት መጠቃለል ምሳሌ ሆኖ የቀረበውን መከር በሲያፍ የሚመለከት ይመስላል::

*4፥30-34፤* የዚህ ምሳሌ ዋና ሐሳብ የእግዚአብሔር መንግሥት ከጅምሩ ሲታይ ከቍጥር የማይገባ መምሰሉ ነው፤ ለሕዝብ የተገለጠውም ዓለም በናቀውና በጠላው በኢየሱስና ዐይን በማይሞሉ በዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ነው:: ይሁን እንጂ የዚህ መንግሥት ታላቅነትና ኀይል ለዓለም የሚገለጥበት ቀን ይመጣል::

ግራቸውም ነበር። እርሱና ደቀ መዛሙርቱ
ብቻ በሚሆኑበት ጊዜ ግን ሁሉንም ነገር
በዝርዝር ያስረዳቸው ነበር።

## ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ

4፥35-41 ተጓ ምብ - ማቴ8፥18፡23-27፤ ሉቃ8፥22-25

[35]ያን ቀን በመሸ ጊዜ፣ "ወደ ማዶ እንሻገር"
አላቸው። [36]እነርሱ ሕዝቡን ትተው በጀልባዋ
ውስጥ እንዳለ በዚያው ይዘውት ሄዱ፤ ሌሎች
ጀልባዎችም አብረውት ነበሩ። [37]በዚህ ጊዜ
ኀይለኛ ዐውሎ ነፋስ ተነሣ፤ ማዕበሉም ውሃ
እስኪሞላት ድረስ ጀልባዋን ያናውጣት
ነበር። [38]ኢየሱስ ግን ትራስ ተንተርሶ ከጀ
ልባዋ በስተ ኋላ በኩል ተኝቶ ነበር። እነርሱም
ቀስቅሰውት፣ "መምህር ሆይ፤ ስናልቅ አይገ
ድህምን?" አሉት።
[39]እርሱም ተነሥቶ ነፋሱን ገሠጸው፤ ባሕሩ
ንም፣ "ጸጥ፣ ረጭ በል!" አለው። ነፋሱም
ጸጥ፣ ርጭ አለ፤ ፍጹምም ጸጥታ ሆነ።
[40]ደቀ መዛሙርቱንም፣ "ስለ ምን እንዲህ
ፈራችሁ? እስከዚህ እምነት የላችሁምን?" አላ
ቸው።
[41]እነርሱም በፍርሀት ተውጠው እርስ በር
ሳቸው፣ "ነፋሱም ሞገዱም የሚታዘዙለት
ይህ ማን ነው?" ተባባሉ።

## አጋንንት ያደረበት ሰው መፈወሱ

5፥1-17 ተጓ ምብ - ማቴ8፥28-34፤ ሉቃ8፥26-37
5፥18-20 ተጓ ምብ - ሉቃ 8፥38፡39

**5** ባሕሩን ተሻግረው ጌርሴኖን[ሀ] ወደ ተባለ
አገር መጡ። [2]ኢየሱስ ከጀልባ እንደ
ወረደ፣ ርኩስ[ለ] መንፈስ ያደረበት ሰው
ከመቃብር ቦታ ወጥቶ ሊገናኘው ወደ እርሱ
መጣ። [3]ይህ ሰው በመቃብር ቦታ ውስጥ
የሚኖርና ማንም በሰንሰለት እንኳ ሊያስ
ረው የማይችል ነበር። [4]ብዙ ጊዜ በእግር
ብረትና በሰንሰለት ይታሰር ነበር፤ ነገር ግን
የእጅ ሰንሰለቱን ይበጥስ፣ የእግር ብረቱንም
ይሰብር ነበር። ማንም ይዞ ሊያቈየው የሚችል
አልነበረም።
[5]በመቃብሮቹና በተራራዎቹ መካከል ቀንና
ሌሊት እየተዘዋወረ በመጮኽ ሰውነቱን
በድንጋይ ይቈራርጥ ነበር።
[6]ይህም ሰው ኢየሱስን ከሩቅ ባየው ጊዜ
ወደ እርሱ ሮጦ ከፊቱ ተንበርክኮ ሰገደለት፤
[7]በታላቅ ድምፅ ጮኾም፣ "አንተ የልዑል
እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፤ ከእኔ ምን
አለህ? እንዳታሠቃየኝ በእግዚአብሔር ይገኛሁ!"
አለው። [8]ይህንንም ያለው ኢየሱስ፣ "አንተ
ርኩስ መንፈስ ከዚህ ሰው ውጣ!" ብሎት
ስለ ነበር ነው።
[9]ከዚያም ኢየሱስ፣ "ስምህ ማን ነው" ብሎ
ጠየቀው። "ብዙ ነንና ስሜ ሌጌዎን ነው"
አለው። [10]ከአገር እንዳያስወጣቸውም አጥብቆ
ለመነው።
[11]በአቅራቢያውም በሚገኝ ኰረብታ ላይ
ትልቅ የዐሣማ መንጋ ተሰማርቶ ነበር።
[12]ርኩሳን መናፍስቱም ኢየሱስን፣ "ወደ ዐሣማ

[ሀ]1 አንዳንድ ቅጆች *ጌራሴኖን*፣ ሌሎች ደግሞ *ጌርጌሴኖን* ይላሉ።
[ለ]2 ወይም *ክፉ*፤ እንዲሁም ቍ 8እና 13 ይመ።

4፥36 ቍ1፤ ማር3፥9፤5፥2፡21፤ 6፥32፡45
4፥40 ማቴ14፥31፤ ማር16፥14
5፥2 ማር1፥23፤4፥1
5፥7 ማቴ4፥3፤ 8፥29፤ሉቃ1፥32፤6፥3 5፤ሐሥ16፥17፤ ዕብ7፥1
5፥9 ቍ15

*4፥31፤* የማቴ 13፥31-32 ማብ ይመ።

4፥34 *ምንም ነገር ያለ ምሳሌ አይነግራቸውም ነበር፤* ኢየሱስ ምሳሌዎችን የተጠቀመባቸው እውነትን ገልጠ ለማሳየት፣ የማሰብ ችሎታቸውን ለማነሣሣትና መንፈሳዊ ግንዛቤን ለማነቃቃት ነበር። በዚህ ጊዜ ሰዎቹ የወንጌልን እውነት በጥልቀት ለመረዳት ልባቸው አልተዘጋጀም ነበር። ኢየሱስ ለብቻ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በሚሆንበት ጊዜ፣ ዝርዝር ሁኔታውን ይበልጥ ገልጦ ያስተምራቸው ነበር፤ ያም ሆኖ፣ ደቀ መዛሙርቱ ብዙ ጊዜ ትምህርቱ እንዲብራራላቸው ይፈልጉ ነበር።

*4፥35-41፤* በዚህ በሠለጠነ ዘመን ብዙ ሰው ታምራትን ማመን ቢያቅተውም፣ ኢየሱስ የቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን፣ የፍጥረት ሁሉ ጌታ እንደ ሆነ አዲስ ኪዳን በግልጽ ይመሰክራል።

4፥35 *ወደ ማዶ፤* ኢየሱስ የገሊላን አካባቢ ትቶ ወደ ጌርሴኖን አገር ሄደ (5፥1)።

4፥37 *ኀይለኛ ዐውሎ ነፋስ ተነሣ፤* በተራሮች ተከበበ በሰርጓዳ ስፍራ የሚገኘው የገሊላ ባሕር፣ ለድንገተኛ ብርቱ ማዕበል የተጋለጠ ነው፤ ከሚድትራኒያን ባሕር ተነሥቶ በተራራዎች መካከል ባለው መተላለፊያ እየነፈሰ የሚመጣው ቀዝቃዛ አየር፣ በባሕሩ ላይ ካለው ሞቃትና ከባድ አየር ጋር በሚጋጭበት ጊዜ ዐውሎ ነፋስ ይፈጠራል።

4፥38 *ትራስ ተንተርሶ ... ተኝቶ ነበር፤* ጌታ ኢየሱስ ደክሞት የጀልባው ኀላፊ በሚቀመጥበት ትራስ ተንተርሶ እንደ ተኛ በዐይነ ኅሊናችን ስንመለከት፣ የማርቆስ ወንጌል ዋነኛ ባሕርይ የጌታን ፍጹም ሰው መሆን መግለጽ እንደ ሆነ እናስተውላለን።

4፥41 *ይህ ማን ነው?* ኢየሱስ እዚህ ላይ ካደረገው ታምር አኳያ ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ፣ 'እርሱ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነው' ከማለት ሌላ ምን አለ! የእግዚአብሔር ሀልዎትና ኀይል በግልጽ ታይቶአል (መዝ 65፥7፤ 107፥25-30፤ ምሳ 30፥4 ይመ)። ማርቆስ ለዚህ ጥያቄ የሚሆነውን መልስ ያመለከተው ገና በወንጌሉ መግቢያ ላይ ነው (1፥1)። ኢየሱስ፣ ደቀ መዛሙርቱ እርሱ አምላክ መሆኑን እንዲያምኑና እንዲቀበሉ ለማድረግ እንዲህ ያለውን ታምር ያሳያቸው ነበር።

5፥1 *ባሕሩን ተሻግረው፤* የዐሣማ መንጋ በዚያ አካባቢ በብዛት በመኖሩ፣ ከባሕሩ በስተ ምሥራቅ የሚኖሩት በአብዛኛው አሕዛብ እንደ ነበሩ አያጠራጥርም፤ በአይሁድ ዘንድ ዐሣማ ርኩስ ስለ ሆነ አይበሉም ነበርና። *ጌርሴኖን ወደ ተባለ አገር፤* ከገሊላ ባሕር በስተ ደቡብ ምሥራቅ 56 ኪ.ሜ. ያህል ላይ የነበረች ጌራሳ ስትሆን፣ ወሰኗ ከባሕሩ በስተ ምሥራቅ እስካለው ጠረፍ ሳይደርስ አይቀርም፤ በአሁኑ ዘመን፣ "ኬርሳ" የተባለች መንደር ስሟን ወርሳ ትገኛለች። በደቡብ በኩል 1.5 ኪ.ሜ ያህል ላይ፣ ከጠረፉ፣ 37 ሜትር ያህል ራቅ ብሎ ዘቅዘቅ ያለ ተዳፋት አለ፤ ከዚሁ ቦታ 3 ኪ.ሜ ያህል ራቅ ብሎም የመቃብር ዋሻዎች ይገኛሉ፤ እነዚህ ዋሻዎች ቀደም ብሎ ለመኖሪያነት ያገለገሉ ይመስላሉ።

5፥3 *በመቃብር ቦታ ውስጥ የሚኖርና፤* ይህ ዋሻ ለሙታን እንደ መቃብር፣ ለሕያዋን ደግሞ እንደ መኖሪያ ማገልገሉ እንግዳ ነገር አልነበረም፤ እጅግ የደኸዩ ሰዎች በዚህ ዐይነት ዋሻ ይኖሩ ነበር።

5፥4 *ብዙ ጊዜ ... በሰንሰለት ይታሰር ነበር፤* የአካባቢው ነዋሪዎች በአንድ በኩል ለራሳቸው ድኅነት እንዳይሆን ሲሉ ቢያስሩትም፣ እንዲህ ታስሮ መጣሉ ግን የባሰ እንዲዋረድ አድርጎታል።

5፥5 *በመጮኽ ሰውነቱን በድንጋይ ይቈራርጥ ነበር፤* የትረካው እያንዳንዱ ቃል የሰውየውን አሳዛኝ ሁኔታ ከመግለጹም በላይ፣ ርኩስ መንፈስ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን ሰው ማጐሳቈልና እንዳልነበረ ማድረግ ዐላማው መሆኑን ያሳያል።

5፥7 *የልዑል እግዚአብሔር ልጅ፤* የ1፥24 ማብ ይመ። *ከእኔ ምን አለህ?* "እኔና አንተን ምን የሚያገናኘን ነገር አለ?" እንደ ማለት ነው። ይህን መሰል አገላለጽ በብሉይ ኪዳን የሚገኝ ሲሆን (ለምሳሌ 2ሳሙ 16፥10፤ 19፥22)፣ "በእኔ አትድረስብኝ" እንደ ማለት ነው። እዚህ ክፍል ላይ ጋኔኑ የሚናገረውም በሰውየው አንደበት ተጠቅሞ ነበር። *እንዳታሠቃየኝ በእግዚአብሔር ይገኛሁ፤* ልመናውን በእግዚአብሔር ስም ማቅረቡ ምጸት ያለበት ቢሆንም፣ ጋኔኑ ቅጣት እንደሚደርስበት ስላወቀ የመጨረሻውን የመማጸኛ ቃል ተጠቅሟል።

5፥9 *ብዙ ነንና ስሜ ሌጌዎን ነው፤* አንድ የሮም ሌጌዎን (ክፍለ ሰራዊት) 6000 ወታደሮች አሉት። እዚህ ላይ ቃሉ የሚያመለክተው ሰውየው በአጋንንት መያዙን ሲሆን፣ ምናልባትም የእግዚአብሔር ኀይል ያለበትን ኢየሱስን በመቃወም የተሰለፈውን የኀይላት ብዛት የሚያሳይ ሳይሆን አይቀርም።

5፥10 *ከአገር እንዳያስወጣቸውም፤* አጋንንቱ ወደ ዘላለማዊ ቅጣት፣ ይኸውም "ወደ ጥልቁ" እንዳይወርዱ በጣም ፈርተው

ዎቹ ስደደን፤ እንድንገባባቸውም ፍቀድልን”
ብለው ለመኑት::
[13]እርሱም ፈቀደላቸው:: ርኩሳን መናፍስቱም
ወጥተው በዐሣማዎቹ ገቡባቸው፤ ሁለት ሺህ
ያህል ዐሣማዎችም በገደሉ አፋፍ በመንደርደር
ቍልቍል ወርደው በባሕር ውስጥ ሰጠሙ::
[14]እረኞቹ ሸሽተው ሄዱ፤ ወሬውን በከተ
ማና በገጠር አዳረሱት፤ ሕዝቡም የሆነውን
ለማየት ካለበት ወጣ:: [15]ወደ ኢየሱስም
በመጡ ጊዜ፣ የአጋንንት ሰራዊት አድረው
በት የነበረው ሰው፣ ልብስ ለብሶና አእምሮው
ተመልሶለት በዚያ ተቀምጦ አዩት፤ ፈሩም::
[16]ይህን ያዩ ሰዎችም አጋንንት ስላደረበት
ሰው የተደረገውንና ስለ ዐሣማዎቹም ለሕዝቡ
አወሩ:: [17]ከዚያም ሕዝቡ አገራቸውን ለቆ
እንዲሄድላቸው ኢየሱስን ይለምኑት ጀመር::
[18]ኢየሱስ ወደ ጀልባዪቱ በሚገባበት ጊዜ፣
አጋንንት አድሮበት የነበረው ሰው አብሮት
ለመሄድ ለመነው:: [19]ኢየሱስ አልፈቀደለትም፤
ነገር ግን፣ “ወደ ቤትህ ሂድ፣ ለዘመዶችህም
ጌታ ምን ያህል ታላቅ ነገር እንዳደረገልህና
ያሳየህን ምሕረት ንገራቸው” አለው:: [20]ሰው
የውም ሄደ፤ ኢየሱስ ያደረገለትን ነገር ሁሉ
ዐሥር ከተማ* በተባለው አገር ያወራ ጀመር፤

5፥15 ቊ9:16:18፤ ማቴ4፥24
5፥19 ማቴ8፥4
5፥20 ማቴ4፥25፤ ማር7፥31
5፥21 ማቴ9፥1፤ ማር4፥1
5፥22 ቊ35:36:38፤ሉቃ13፥14፤ ሐሥ13፥15፤18፥18:17
5፥23 ማቴ19፥13፤ ማር6፥5፤7፥32፤8፥23፤16፥18፤ሉቃ4፥40፤13፥13፤ሐሥ6፥6
5፥25 ዘሌ15፥25-30
5፥28 ማቴ9፥20
5፥29 ቊ34

የሰሙትም ሁሉ ተደነቁ::

## የሞተችው ልጅና የታመመችው ሴት

5፥22-43 ተጓ ምብ - ማቴ9፥18-26፤ ሉቃ8፥41-56

[21]ኢየሱስ እንደ ገና በጀልባ ወደ ማዶ በተ
ሻገረ ጊዜ፣ ብዙ ሕዝብ በዙሪያው ተሰባ
ሰበ፤ በባሕሩ ዳርቻም እንዳለ፣ [22]ከምኵራብ
አለቆች አንዱ ኢያኢሮስ የተባለው ወደዚያ
መጥቶ ስለ ነበር፣ ኢየሱስን ባየው ጊዜ በእ
ግሩ ላይ ወድቆ፣ [23]“ትንሿ ልጄ በሞት አፋፍ
ላይ ናትና ድና በሕይወት እንድትኖር መጥተህ
እጅህን ጫንባት” በማለት አጥብቆ ለመነው::
[24]ኢየሱስም አብሮት ሄደ::
ብዙ ሕዝብም ዙሪያውን እያጨናነቀው ተከ
ተለው:: [25]ዐሥራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈ
ሳት የኖረችም ሴት በዚያ ነበረች፤ [26]በብዙ ባለ
መድኀኒቶች ዘንድ በመንከራተት ያላትን ሁሉ
ብትጨርስም፣ ሕመሙ ባሰባት እንጂ አልተሻ
ላትም ነበር:: [27]ስለ ኢየሱስም በሰማች ጊዜ፣
ከበስተ ኋላው በሰዎች መካከል መጥታ ልብ
ሱን ነካች፤ [28]ምክንያቱም፣ “እንደ ምንም ብዬ
ልብሱን ብቻ እንኳ ብነካ እፈወሳለሁ” የሚል
እምነት ነበራት:: [29]የሚፈሰው ደሟ ወዲያውኑ
ቆመ፤ ከሥቃይዋ መገላገሏም በሰውነቷ ታወ

*20 *ዐሥር ከተማ* የሚባለውን አካባቢ ግሪኩ ዴካፖሊስ ይለዋል::

ነበር (ሉቃ 8፥31)::

5፥13 *እርሱም ፈቀደላቸው፤* የማቴ 8፥32 ማብ ይመ::

5፥16 *ስለ ዐሣማዎቹም ... አወሩ፤* ጋኔን አድሮበት የነበረው ሰው ሁኔታው መለወጡ የሚያስደንቅ ከመሆኑም በላይ፣ ዐሣማዎቹ ባሕር ውስጥ ገብተው መሞታቸው አሳሳቢ ጉዳይ ነበር፤ ምክንያቱም ለባለ ዐሣማዎቹ ትልቅ የሀብት ኪሳራ ነበር::

5፥17 *አገራቸውን ለቆ እንዲሄድላቸው ... ይለምኑት ጀመር፤* ልመናቸው በአንድ በኩል የባሰ ጥፋት እንዳያመጣባቸው ሊሆን ይችላል፤ በሌላም በኩል ሊያስተውሉትና ሊመረምሩት የማይችሉት ብርቱ ኀይል በመካከላቸው በመከሠቱ ሊሆን ይችላል::

5፥19 *ጌታ ምን ያህል ታላቅ ነገር እንዳደረገልህ ... ንገራቸው፤* ከለምጽ ፈውሶት የተደረገለትን በጎነት ለማንም እንዳይናገር ከተነገረው ሰው ጋር ሲነጻጸር፣ ትእዛዙ ጉላ ያለ ልዩነት አለው (1፥44፤ 1፥34፤ 3፥12፤ ይመ፤ እንዲሁም የማቴ 8፥4 ማብ ይመ)፤ ለዚህኛው የተለየ ትእዛዝ የተሰጠው፣ በአሕዛብ ምድር ስለ ኢየሱስ መሲሕነት በሰፊት ቢወራም አደጋ ሊያስከትል ባለመ ቻሉ ይሆናል::

5፥20 *ዐሥር ከተማ፤* የማቴ 4፥25 ማብ ይመ::


5፥21 *ወደ ማዶ፤* ኢየሱስ የባሕሩ ምዕራብ አካባቢ፣ ወደ ሆነው ወደ ቅፍርናሆም ሳይመለስ አልቀረም::

5፥22 *ከምኵራብ አለቆች፤* የምኵራብ አለቃ ተራ ምእመን ሲሆን፣ ተግባሩም ሕንፃውንና የአምልኮውን ሥርዐት የመቈጣጠር አስተዳደራዊ ኀላፊነት ነበር:: በሁሉም ቦታ ባይሆንም (ሐሥ 13፥15 ይመ)፣ ብዙ ምኵራቦች አንድ አንድ አለቃ ብቻ ነበራቸው:: አንዳንድ ጊዜ ማዕረጉ ለክብር ብቻ ይሰጥና አለቆቹ ምንም ዐይነት የአስተዳደር ኀላፊነት አይኖራቸውም::

5፥25 *ዐሥራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈሳት፤* የሴትየዋ ችግር ምን እንደ ሆነ በትክክል አልታወቀም፤ እርሷን የነካ ሰው ሁሉ በሥርዐቱ መሠረት እንደ ርኩስ ስለሚቈጠር (ዘሌ 15፥25-33)፣ ሰዎች ያገሏት ነበር፤ ከዚህም የተነሣ ኑሮዋ አስከፊ መሆኑ አያጠራጥርም::

5፥26 *በብዙ ባለ መድኀኒቶች ዘንድ በመንከራተት፤* “ታልሙድ” የተባለው የአይሁድ መጽሐፍ፣ ለዚህ ዐይነቱ ሕመም ፈውስ ያስገኛል የሚለውን የመድኃኒትና የሕክምና ዝርዝር ይዟል::

5፥28 *ልብሱን ብቻ እንኳ ብነካ፤* የሴትየዋ ልብስ መዳሰስ እምነትዋን የሚያጠናክር ነገር ቢሆንም፣ ፈውሱ የእምነቷ ውጤት



ቃት::
[30]ወዲያውኑ ኢየሱስ፣ ኀይል ከእርሱ እንደ ወጣ
ዐውቆ፤ ወደ ሕዝቡ ዘወር በማለት፣ "ልብሴን
የነካው ማን ነው?" አለ::
[31]ደቀ መዛሙርቱም፣ "ሕዝቡ ተጨናንቆ
ሲጋፋህ እያየህ፣ 'ማን ነው የነካኝ?' እንዴት
ትላለህ? አሉት::
[32]ኢየሱስ ግን ይህንን ያደረገው ማን እንደ
ሆነ ለማየት ዙሪያውን ተመለከተ:: [33]ሴትዮ
ዋም ምን እንደ ተደረገላት ባወቀች ጊዜ እየፈ
ራችና እየተንቀጠቀጠች መጥታ በፊቱ ተደፋች፤
እውነቱንም ሁሉ ነገረችው:: [34]እርሱም፣ "ልጄ
ሆይ፤ እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ፤
ከሥቃይሽም ዕረፊ" አላት::
[35]ኢየሱስም በመነጋገር ላይ እያለ፣ ሰዎች
ከምኵራቡ አለቃ ከኢያኢሮስ ቤት መጥ
ተው፣ "ልጅህ ሞታለች፤ ከእንግዲህ መምህሩን
ለምን ታደክመዋለህ?" አሉት::
[36]ኢየሱስ ግን ሰዎቹ የተናገሩትን ችላ በማ
ለት የምኵራቡን አለቃ፣ "እመን ብቻ እንጂ
አትፍራ!" አለው::
[37]ከጴጥሮስና ከያዕቆብ እንዲሁም ከያዕ
ቆብ ወንድም ከዮሐንስ በቀር ማንም እንዲ
ከተለው አልፈቀደም:: [38]ወደ ምኵራቡ አለቃ
ቤት እንደ ደረሱ፣ ኢየሱስ ግርግሩንና ሰዎ
ቹም ዋይ ዋይ እያሉ አምርረው ሲያለቅሱ
ተመለከተ:: [39]ወደ ቤትም ገብቶ፣ "ይህ
ሁሉ ግርግርና ልቅሶ ምንድን ነው? ብላቴ
ናዪቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም" አላ
ቸው:: [40]ሰዎቹ ግን ሣቁበት::
ሰዎቹን ሁሉ ከቤት ካስወጣ በኋላ፣ የብላ
ቴናዪቱን አባትና እናት እንዲሁም አብረ
ውት የመጡትን ደቀ መዛሙርት አስከትሎ
ብላቴናዪቱ ወዳለችበት ገባ:: [41]ከዚያም የብላ
ቴናዪቱን እጅ ይዞ፣ "ጣሊታ ቁሚ!" አላት፤
ትርጕሙም፣ "አንቺ ልጅ ተነሺ" ማለት
ነው:: [42]ብላቴናዪቱም ወዲያውኑ ተነሥታ
ቆመች፤ ወዲያ ወዲህም ሄደች:: ዕድሜዋም
ዐሥራ ሁለት ዓመት ነበር:: ሰዎቹም በሁኔ
ታው እጅግ ተደነቁ:: [43]እርሱም ይህን ነገር
ማንም እንዳያውቅ አጥብቆ አስጠነቀቃቸው፤
የሚበላ ነገር እንዲሰጧትም ነገራቸው::

5፥30 ሉቃ5፥17፤ 6፥19
5፥34 ማቴ9፥22፤ ሐሥ15፥33
5፥35 ቍ22
5፥37 ማቴ4፥21
5፥38 ቍ22
5፥39 ማቴ9፥24
5፥41 ማር1፥31፤ ሉቃ7፥14
5፥43 ማቴ8፥4
6፥1 ማቴ2፥23
6፥2 ማቴ4፥23፤ 7፥28፤ማር1፥21
6፥3 ማቴ11፥6፤ 12፥46፤ዮሐ6፥61
6፥4 ሉቃ4፥24፤ ዮሐ4፥44
6፥5 ማር5፥23
6፥6 ማቴ9፥35፤ ማር1፥39፤ ሉቃ13፥22
6፥7 ዘዳ17፥6፤ ማቴ10፥1፤ ማር3፥13፤ሉቃ10፥1
6፥11 ማቴ10፥14

## ነቢይ በአገሩ አይከበርም

6፥1-6 ተጓ ምብ - ማቴ13፥54-58

**6** ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ ወደ
ገዛ አገሩ ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም ተከ
ተሉት:: [2]ሰንበትም በደረሰ ጊዜ፣ በምኵራብ
ያስተምር ጀመር፤ የሰሙትም ብዙ ሰዎች፣
ተደነቁ::
እነርሱም እንዲህ አሉ፤ "ይህ ሰው እነዚ
ህን ነገሮች ከየት አገኛቸው? ይህ የተሰጠው
ጥበብ ምንድን ነው? ደግሞም እነዚህ ታምራት
እንዴት በእጁ ይደረጋሉ! [3]ይህ ዐናጢው አይደ
ለምን? የማርያም ልጅ፣ የያዕቆብና የዮሴፍ[a]፣
የይሁዳና የስምዖን ወንድም አይደለምን? እኅቶ
ቹስ እዚሁ እኛው ዘንድ አይደሉምን?" ከዚ
ህም የተነሣ ተሰናከሉበት::
[4]ኢየሱስም፣ "ነቢይ የማይከበረው በገዛ አገሩ፣
በዘመዶቹ መካከልና በቤተ ሰቡ ዘንድ ብቻ
ነው" አላቸው:: [5]እዚያም በጥቂት ሕመምተኞች
ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወሱ በስተቀር ምንም
ታምራት ሊሠራ አልቻለም፤ [6]ባለማመናቸውም
ተደነቀ::

## ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ላከ

6፥7-11ተጓ ምብ - ማቴ 10፥1፡9-14፤ ሉቃ9፥1፡3-5

ከዚያም ኢየሱስ በየመንደሩ እየተዘዋወረ ያስ
ተምር ነበር:: [7]ዐሥራ ሁለቱን ወደ እርሱ
ጠርቶ፣ ሁለት ሁለቱን ላካቸው፤ በርኩሳን[+]
መናፍስትም ላይ ሥልጣን ሰጣቸው::

[a]3 ግሪኩ ዮሴስ ይላል
[+]7 ወይም ክፉ

ነው (ቍ34 ይመ፤ ከሐሥ 19፥12 ጋር ያነጻጽሩ)::

5፥30 *ኀይል ከእርሱ እንደ ወጣ፤* አንዳንድ የዘመኑ፣ "የእምነት ትምህርት" አራማጆች እንደሚሉት ፈውስ ለማግኘት ከራስ በሚወጣ፣ "እምቅ ኀይል" መመካት ሳይሆን፣ የሚያድነን ከእግዚአብሔር ዘንድ (ከእኛ ውጭ) የሚወጣ ኀይል መሆኑን እንረዳለን::

5፥32 *ይህንን ያደረገው ማን እንደ ሆነ ለማየት ዙሪያውን ተመለከተ፤* ኢየሱስ የሴትየዋን እምነት በሰው ፊት ሳያደንቅና ፈውሷ ለዘለቄታ መሆኑን ሳያረጋግጥላት ተመልሳ ሕዝቡ መካከል እንድትገባ አልፈለገም::

5፥34 *አድኖሻል፤* "አድኖሻል" የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ፣ "ድነትን አግኝተሻል" ማለት ነው፤ እዚህ ላይ የሥጋ ፈውስን ("ከሥቃይሽ ዕረፊ") እና መንፈሳዊ ድነትን ("በሰላም ሂጅ") ያጠቃልላል:: በማርቆስ ወንጌል ብዙውን ጊዜ ሁለቱ ተጣምረው ይታያሉ (2፥1-12፤ 3፥1-6 ይመ)::

5፥37 *ከጴጥሮስና ከያዕቆብ … ከዮሐንስ፤* እነዚህ ሦስት ደቀ መዛሙርት ከኢየሱስ ጋር የተለየ ቅርበት ነበራቸው (የሐሥ 3፥1 ማብ ይመ)

5፥38 *ሰዎቹም ዋይ ዋይ እያሉ አምርረው ሲያለቅሱ፤* ሰው ሲሞት አስለቃሽ ቀጥሮ ወደ ለቅሶ ቤት ማምጣት የተለመደ ነበር፤ በዚህ ጊዜ ግን አስለቃሾችን ለማግኘት በቂ ጊዜ ነበረ ማለት ያስቸግራል::

5፥39 *ተኝታለች እንጂ አልሞተችም፤* የሉቃ 8፥52 ማብ ይመ::

5፥41 *ጣሊታ ቁሚ!* እዚህ ላይ የጥንቱን አራማይክ ቋንቋ የተጠቀመ የወንጌል ጸሐፊ ማርቆስ ብቻ ነው፤ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት ይህ ቋንቋ፣ ቀድሞ ፓሌስቲና ኋላም በክርስቲያኖች፣ "ቅድስት ምድር" በመባል በሚታወቀው ምድር ከነበሩት ቋንቋዎች አንዱ ነበር:: ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም ለተራ ንግግር ይጠቀሙበት የነበረው ቋንቋ ይህ ሳይሆን አይቀርም፤ በተጨማሪም በዕብራይስጥና በግሪክ ቋንቋም ሳይነጋገሩ አይቀርም::

5፥43 *ማንም እንዳያውቅ፤* በገሊላ አካባቢ የተፈወሱ ሰዎች ስለ ታምሩ ለማንም እንዳይናገሩ ኢየሱስ ብዙ ጊዜ አስጠንቅቆአቸዋል፤ አለበለዚያ ጌታ ዝናው እየገነነ በሄደ ቍጥር፣ የሃይማኖት መሪዎች ተቃውሞ እየከረረ መጥቶ፣ አገልግሎቱ መንገድ ላይ እስከ መቀጨት በደረሰ ነበር (1፥44፤ 5፥19፤ 7፥36፤ 8፥26 ይመ)::

6፥1 *ወደ ገዛ አገሩ፤* ማርቆስ ለይቶ ናዝሬት ባይልም፣ ናዝሬት መሆኑ ግልጽ ነው (የ1፥9 ማብ ይመ)::

6፥2 *በምኵራብ … ያስተምር ጀመር፤* የ1፥21 ማብ ይመ:: *ተገረሙ፤* የ1፥22 ማብ ይመ::

6፥3 *ዐናጢው፤* ማቴዎስ፣ ኢየሱስ "የዐናጢው ልጅ" እንደ ተባለ ይናገራል (ማቴ 13፥55)፤ ኢየሱስ 'ዐናጢው' የተባለው በማርቆስ ወንጌል ብቻ ነው:: ጥያቄው የተሰነዘረው ክብሩን ለመንካትና ለማጥላላት ነው፤ "እንደ እኛው ለፍቶ አዳሪ ተራ ሰው አይደለምን" ብሎ እንደ መጠየቅ ነው:: *የያዕቆብና የዮሴፍ፣ የይሁዳና የስምዖን ወንድም፤* የሉቃ 8፥19 ማብ ይመ:: *ተሰናከሉበት፤* ከእነርሱ ልዩ የሚያደርገውን ምክንያት ማግኘት አልቻሉም፤ ይልቁንም በተለየ ሁኔታ በእግዚአብሔር የተቀባ መሆኑ አልተዋጠላቸውም::

6፥5 *እዚያም … ምንም ታምራት ሊሠራ አልቻለም፤* ኢየሱስ በናዝሬት ከተማ ታምራት ለመሥራት ኀይል አልነበረውም ማለት ሳይሆን፣ እምነት በሌለበት ቦታ ታምራት መሥራት አልፈለገም ማለት ነው (ቍ6)::

6፥6 *ተደነቀ፤* የሉቃ 7፥9 ማብ ይመ::

6፥7 *ሁለት ሁለቱን፤* ጥንድ ጥንድ አድርጎ መላኩ፣ ከአንድ

8ይህንንም ትእዛዝ ሰጣቸው፤ “ለመንገ
ዳችሁ ከበትር በስተቀር፣ እንጀራ ወይም
ከረጢት ወይም ደግሞ ገንዘብ በመቀነታ
ችሁ አትያዙ፤ 9ጫማ አድርጉ፤ ነገር ግን
ሁለት እጀ ጠባብ አትልበሱ፤ 10ወደ አንድ
ቤት በምትገቡበት ጊዜ ከዚያች ከተማ እስ
ክትወጡ ድረስ እዚያው ቈዩ፤ 11የትኛውም
ቦታ የማይቀበላችሁ ወይም የማይሰማችሁ
ከሆነ፣ ከዚያ ስፍራ ስትወጡ ምስክር እንዲ
ሆንባቸው ከእግራችሁ ሥር ያለውን ትቢያ
በዚያ አራግፉ።”

12እነርሱም ከዚያ ወጥተው፤ ሰዎች ንስሓ
እንዲገቡም ሕዝቡን ሰበኩ፤ 13ብዙ አጋንንት
አስ ወጡ፤ ብዙ ሕመምተኞችንም ዘይት
እየቀቡ ፈወሱ።

### የመጥምቁ ዮሐንስ መሰየፍ

6፥14-29 ተጓ ምብ - ማቴ14፥1-12
6፥14-16 ተጓ ምብ - ሉቃ9፥7-9

14የኢየሱስ ስም እየታወቀ በመምጣቱ፣
ንጉሥ ሄሮድስ ይህንኑ ሰማ። አንዳንዶችም፣
“የዚህ ዐይነት ታምር በእርሱ የሚሠራው
መጥምቁ ዮሐንስ ከሙታን ቢነሣ ነው” ይሉ
ነበር*። 15ሌሎቹም፣ “ኤልያስ ነው” አሉ።

አንዳንዶች ደግሞ፣ ‘ከቀደምት ነቢያት እንደ
አንዱ ነቢይ ነው” ይሉ ነበር።

16ሄሮድስ ነገሩን ሲሰማ ግን፣ “እኔ ራሱን
ያስቈረጥሁት ዮሐንስ ከሙታን ተነሥቶአል
አለ።

17ሄሮድስ ራሱ የወንድሙን የፊልጶስን
ሚስት ሄሮድያዳን በማግባቱ ምክንያት፣ ተይዞ
እንዲታሰር ትእዛዝ በመስጠት ዮሐንስን ወህኒ
ቤት አስገብቶት ነበር 18ዮሐንስ ሄሮድስን፣
“የወንድምህን ሚስት ታገባት ዘንድ ሕግ
ይከለክልሃል” ይለው ነበርና። 19ሄሮድያዳም
በዚህ ቂም ይዛበት ልታስገድለው ፈለገች፤
ነገር ግን አልሆነላትም። 20ምክንያቱም ዮሐ

6፥12 ሉቃ9፥6
6፥13 ያዕ5፥14
6፥14 ማቴ3፥1
6፥15 ሚል4፥5፤ ማቴ16፥14፤21፥11፤ ማር8፥28
6፥17 ማቴ4፥12፤ 11፥2፤ሉቃ3፥19፡20
6፥18 ዘሌ18፥16፤20፥21
6፥20 ማቴ11፥9
6፥21 አስ1፥3፤ 2፥18፤ሉቃ3፥1
6፥23 አስ5፥3፡61 7፥2
6፥30 ማቴ10፥2፤ ሉቃ9፥10፤17፥5፤ 22፥14፤24፥10፤ ሐሥ1፥2፡26
6፥31 ማር3፥20

ንስ ጻድቅና ቅዱስ ሰው መሆኑን ሄሮድስ በ
ማወቁ ይፈራውና ይጠብቀው ነበር። ዮሐንስ
የሚናገረውን ሲሰማ ሄሮድስ ቢታወክም†
በደስታ ያደምጠው ነበር።

21በመጨረሻም አመቺ ቀን መጣ። ሄሮድስ
በተወለደበት ዕለት ለከፍተኛ ሹማምቱ፣
ለጦር አዛዦቹና በገሊላ ለታወቁ ታላላቅ
ሰዎች ግብዣ አደረገ። 22የሄሮድያዳም ልጅ
ገብታ በዘፈነች ጊዜ ሄሮድስንና ተጋባዦ
ቹን ደስ አሰኘቻቸው። ንጉሡም ብላቴናዪ
ቱን፣ “የምትፈልጊውን ሁሉ ጠይቂኝ እሰጥ
ሻለሁ” አላት። 23ደግሞም “እስከ መንግሥቴ
እኩሌታ ድረስ እንኳ ቢሆን፣ የምትጠይቂኝን
ሁሉ እሰጥሻለሁ” ሲል በመሐላ ቃል ገባላት።

24እርሷም ወጥታ እናቷን፣ “ምን ልለምነው?”
አለቻት።

እናቷም፣ “የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ” አለ
ቻት።

25ብላቴናዪቱም ወዲያው ፈጥና ወደ ንጉሡ
በመመለስ፣ “የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ አሁን
በሳሕን እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ” አለችው።

26ንጉሡ በነገሩ እጅግ አዘነ፤ በተጋበዙት
እንግዶች ፊት የመሐላ ቃሉን ለማጠፍ አልፈ
ለገም። 27ስለዚህ አንዱን ወታደር በፍጥነት
ልኮ፣ የዮሐንስን ራስ ቈርጦ እንዲያመጣ
አዘዘው፤ እርሱም ሄዶ በወህኒ ቤቱ ውስጥ
ራሱን ቈረጠ፤ 28በሳሕን አምጥቶ ለብላቴናዪቱ
ሰጣት፤ ብላቴናዪቱም ለእናትዋ ሰጠች።
29የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትም ይህን እንደ
ሰሙ መጡ፤ሬሳውንም ወስደው ቀበሩት።

### ኢየሱስ አምስት ሺህ ሰዎች መገበ

6፥32-44 ተጓ ምብ - ማቴ 14፥13-21፤ ሉቃ9፥10-17፤ ዮሐ6፥5-13
6፥32-44 ተጓ ምብ - ማር8፥2-9

30ሐዋርያትም በኢየሱስ ዙሪያ ተሰብስበው

*14 አንዳንድ ቅጆች ይል ነበር ይላሉ
†20 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ብዙ ነገር ያደርግ ነበር ይላሉ

ሰው ይልቅ ሁለት ምስክሮች በማድረግ ተቀባይነታቸውን ለማጠ
ናከር ሊሆን ይችላል (ከዘዳ 17፥6 ጋር ያነጻጽሩ)፤ በተጨማሪም
በዚህ የሥልጠና ወቅት እርስ በርስ እንዲደጋገፉ ሊሆን ይችላል።

6፥8 *እንጀራ ወይም ከረጢት ወይም ደግሞ ገንዘብ በመቀነታችሁ፤* ለሚያስፈልጋቸው ማንኛውም ነገር፣ የሚመሰክሩላቸው ሰዎች በሚያደርጉላቸው መስተንግዶ ላይ ሙሉ በሙሉ መደገፍ ይኖርባቸዋል ማለት ነው (ቍ 10 ይመ)።

6፥9 *ሁለት እጀ ጠባብ፤* የሌሊቱን ብርድ ለመከላከል ትርፍ እጀ ጠባብ መያዝ ያስፈልግ ነበር፤ ሆኖም ለሚያስፈልጋቸው የሌሊት ማረፊያ ሁሉ በእግዚአብሔር መታመን እንዳለባቸው ከዚህ መረዳት ይቻላል።

6፥11 *ከእግራችሁ ... ትቢያ ... አራግፉ፤* የማቴ 10፥14 ማብ ይመ።

6፥12-13 *ሰበኩ ... ብዙ አጋንንት አስወጡ፤* ይህ ተልእኮ ደቀ መዛሙርት ለመጀመሪያ ጊዜ ራሳቸውን ችለው በኢየሱስ ስም ያደረጉት አዲስ የአገልግሎት ምዕራፍ ነው (3፥14-15 ይመ)፤ ያስተማሩትም ትምህርት እርሱ ካስተማረው ጋር አንድ ዐይነት ነው (1፥15)።

6፥12 *ንስሓ እንዲገቡም፤* የ1፥4 ማብ ይመ።

6፥13 *ብዙ ሕመምተኞችንም ዘይት እየቀቡ፤* በጥንቱ ዓለም የወይራ ዘይት መድኀኒትነት ታምኖበት በሰፊው ጥቅም ላይ ውሎአል (ኢሳ 1፥6፤ ሉቃ 10፥34፤ ያዕ5፥14 ይመ)።

6፥14 *ንጉሥ ሄሮድስ፤* የማቴ 14፥1 ማብ ይመ፤ ሄሮድስ የአራተኛው ክፍል ገዥ ስለ ነበረ፣ ማርቆስ እርሱን፣ “ንጉሥ” ማለቱ የሽሙጥ ይመስላል፤ በሌላም በኩል ሄሮድስ በተለምዶ ይጠራበት የነበረውን ማዕረግ ተጠቅሞ ሊሆን ይችላል።

6፥15 *ኤልያስ ነው፤* ሚል 4፥5 ይመ።

6፥16 *ዮሐንስ ከሙታን ተነሥቶአል፤* ሄሮድስ የኅሊና ክስ አስጨንቆት ደግሞም ራሱን ለዐጕል እምነት የሰጠ ሰው በመ ሆኑ፣ መጥምቁ ዮሐንስ ከሞት ተነሥቶ ሊያሳድደው የመጣ መስሎት ፈራ።

6፥17 *ፊልጶስ፤* የማቴ 14፥3 ማብ ይመ። *ሄሮድያዳ፤* የ ማቴ14፥3 ማብ ይመ። *ተይዞ እንዲታሰር ... ዮሐንስን ወህኒ ቤት አስገብቶት፤* 1፥14፤ ሉቃ 3፥19-20 ይመ። ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የተባለው አይሁዳዊ ታሪክ ጸሐፊ ዮሐንስ ከሙት ባሕር በስተ ምሥራቅ በነበረው በፖርያ የጦር ሰፈር ታስሮ እንደ ነበር ይናገራል።

6፥22 *የሄሮድያዳም ልጅ፤* የማቴ 14፥6 ማብ ይመ።

6፥23 *እስከ መንግሥቴ እኩሌታ ድረስ እንኳ ቢሆን፤* የልግስናን መጠን ለመግለጽ የገባ ምሳሌያዊ አነጋገር እንጂ፣ ቃል በቃል መወሰድ የለበትም (አስ 5፥3፡6 ይመ)። ሁኔታው ልግስናን ለማሳየት አመቺ ጊዜ ከመሆኑም በላይ፣ የተጋባዡን ሕዝብ አድናቆት የሚያስገኝ አጋጣሚም ነበር።

6፥30 *ሐዋርያትም፤* ይህ ቃል በማርቆስ ወንጌል የሚገኘው በዚህና በ3፥14 (አንዳንድ ቅጆች) ላይ ብቻ ነው። ሐዋርያት፣ ሥልጣን የተሰጣቸው የኢየሱስ እንደራሴዎች ወይም ወኪሎች ነበሩ (የዕብ 3፥1 ማብ ይመ)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ቃሉ በጥቅሉ ጥቅም ላይ ውሎ ይገኛል (የግሪኩ ቃል፣ “መልእክተኛ” ተብሎ የተተረጐመበትን ዮሐ 13፥16 ይመ)። በመሠረታዊ አገባቡ ግን፡- (1) ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት የሚያመለክት ሲሆን (3፥14)፣ የዚህ አገባቡ ጳውሎስንም ይጨምራል (ሮሜ 1፥1)። (2) ሰፋ ባለ አገባቡ ደግሞ በርናባስን (ሐሥ 14፥14)፣

የሠሩትንና ያስተማሩትን ሁሉ ነገሩት:: [31]ብዙ
ሰዎች ይመጡና ይሄዱ ስለ ነበር ምግብ እንኳ
ለመብላት ጊዜ ስላልነበራቸው፣ "እስቲ ብቻች
ሁን ከእኔ ጋር ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራ
እንሂድና ጥቂት ዕረፉ" አላቸው::
[32]ስለዚህ ብቻቸውን ወደ አንድ ገለልተኛ
ስፍራ በጀልባ ሄዱ:: [33]እነርሱም ሲሄዱ ብዙ
ሰዎች አይተው ዐወቋቸው፤ ከከተሞችም ሁሉ
በእግር እየሮጡ ቀድመዋቸው ደረሱ:: [34]ኢየሱስ
ከጀልባዋ በሚወርድበት ጊዜ ብዙ ሕዝብ
ተሰብስቦ አየ፤ እረኛ እንደሌላቸው በጎች
ስለ ነበሩም አዘነላቸው፤ ብዙ ነገርም ያስተም
ራቸው ጀመር::
[35]በዚህ ጊዜ ቀኑ እየመሸ በመሄዱ ደቀ መዛ
ሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው እንዲህ አሉት፤
"ይህ ቦታ ምድረ በዳ ነው፤ ቀኑም መሽቶአል፤
[36]በአካባቢው ሰው ወዳለበት መንደር ሄደው
የሚበላ ነገር ገዝተው እንዲመገቡ አሰናብ
ታቸው::"
[37]እርሱ ግን መልሶ፣ "የሚበሉትን እናንተው
ስጧቸው" አላቸው::
እነርሱም፣ "ሄደን በሁለት መቶ ዲናር እን
ጀራ ገዝተን የሚበሉትን እንስጣቸውን?"
አሉት::
[38]እርሱም፣ "ስንት እንጀራ አላችሁ? እስቲ
ሄዳችሁ እዩ" አላቸው::
አይተውም፣ "አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ"
አሉት::
[39]ከዚያም፣ ሕዝቡን በለመለመ ሣር ላይ
በቡድን በቡድን እንዲያስቀምጡ አዘዛቸው::
[40]ሕዝቡም መቶ መቶና አምሳ አምሳ ሆነው
በቡድን በቡድን ተቀመጡ:: [41]እርሱም አም
ስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ
ሰማይ በማየት ባረከ፤ እንጀራውንም ቈርሶ
እንዲያቀርቡላቸው ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፤
ሁለቱንም ዓሣ ለሁሉም አካፈለ:: [42]ሁሉም
በልተው ጠገቡ፤ [43]ደቀ መዛሙርቱም ከተበ
ላው እንጀራና ዓሣ፣ ዐሥራ ሁለት መሶብ
ሙሉ ፍርፋሪ አነሡ:: [44]እንጀራውንም የበ
ሉት አምስት ሺህ ወንዶች ነበሩ::

## ኢየሱስ በባሕር ላይ በእግሩ ሄደ

6፥45-51 ተጓ ምብ ማቴ14፥22-32፤ ዮሐ6፥15-21
6፥53-56 ተጓ ምብ - ማቴ14፥34-36

[45]ወዲያውም እርሱ ሕዝቡን እያሰናበተ
ሳለ፣ ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ ወደ ቤተ ሳይዳ
ቀድመውት እንዲሻገሩ አዘዛቸው፤ [46]ከዚ
ያም ትቶአቸው ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ::
[47]በመሸም ጊዜ ጀልባዋ ባሕሩ መካከል
ነበረች፤ እርሱም ብቻውን በምድር ላይ ነበር::
[48]ነፋስ በርትቶባቸው ስለ ነበር፣ ደቀ መዛሙርቱ
ከመቅዘፊያው ጋር ሲታገሉ አያቸው፤ በአ
ራተኛውም ክፍለ ሌሊት ገደማ፣ በባሕር
ላይ እየሄደ ወደ እነርሱ መጣ፤ በአጠ
ገባቸውም አልፎ ሊሄድ ነበር:: [49]ነገር ግን
በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ ምትሐት
መስሎአቸው ጮኹ፤ [50]ሁሉም እርሱን
ባዩት ጊዜ ደንግጠው ነበርና::
እርሱም ወዲያውኑ አነጋገራቸውና፣ "አይዞ
አችሁ! እኔ ነኝ፤ አትፍሩ!" አላቸው:: [51]እር
ሱም በጀልባዋ ላይ ወጥቶ አብሮአቸው ሆነ፤
ነፋሱም ተወ፤ እነርሱም እጅግ ተደነቁ፤
[52]የእንጀራውን ታምር አላስተዋሉም ነበርና፤

6፥32 ቍ45፤ ማር4፥36
6፥34 ማቴ9፥36
6፥37 2ነገ4፥42-44
6፥38 ማቴ15፥34፤ ማር8፥5
6፥41 ማቴ14፥19
6፥45 ቍ32፤ ማቴ11፥21
6፥46 ሉቃ3፥21
6፥49 ሉቃ24፥37
6፥50 ማቴ14፥27
6፥51 ቍ32፤ ማር4፥39
6፥52 ማር8፥17-21
6፥53 ዮሐ6፥24፡25

የጌታን ወንድም ያዕቆብን (ገላ 1፥19)፣ ምናልባትም አንዲራኒቆንንና ዩልያንን (ሮሜ 16፥7) ሊጨምር ይችላል:: *የሠሩትንና ያስተማሩትን ሁሉ ነገሩት፤* ይህን ያደረጉት ወክሎ ስለ ላካቸው ነበር:: በገሊላ ምድር ለሦስተኛ ጊዜ ከሄዱበት የስብከት ጕዞ ተመልሰው መምጣታቸው ነበር (የ1፥39 ማብ ይመ)::

6፥32 *ብቻቸውን ... በጀልባ ሄዱ፤* ዮሐንስ ወደ ገሊላ ባሕር ማዶ እንደ ተሻገሩ ይናገራል (ዮሐ 6፥1)፤ ሉቃስ ደግሞ ቦታውን በትክክል በማመልከት ወደ ቤተ ሳይዳ እንደ ሄዱ ይገልጻል (ሉቃ 9፥10)፤ በዚህም መሠረት አምስቱ ሺህ ሰዎች የተመገቡት በሰሜን ምሥራቅ በኩል በሚገኘው የባሕሩ ጠረፍ ላይ ነበር ማለት ነው (የ7፥24 ማብ ይመ)::

6፥33 *በእግር እየሮጡ ቀድመዋቸው ደረሱ፤* ምናልባት ከፊት ለፊት የሚነፍስ ኀይለኛ ነፋስ ጀልባዋን ስለ ገታት፣ ሰዎቹ በባሕሩ ዙሪያ በእግራቸው በመጓዝ ጀልባዋን ሊቀድሙ ችለዋል::

6፥37 *ሁለት መቶ ዲናር፤* ለአንድ ሠራተኛ በቀን የሚከፈለው አንድ ዲናር ነበር (ማቴ 20፥2 ይመ)፤ በዚህ መሠረት የስምንት ወር ክፍያ ሲሰላ ሁለት መቶ ዲናር ይሆናል ማለት ነው::

6፥39 *በለመለመ ሣር፤* በገሊላ ባሕር አካባቢ ለምለም ሣር የሚገኘው ክረምት መውጫው ላይ ወይም በበልግ ዝናብ መጀመሪያ ላይ ነው::

6፥40 *መቶ መቶና አምሳ አምሳ ሆነው በቡድን በቡድን፤* በሙሴ ዘመን በምድረ በዳ የነበረውን የድንኳን ተከላ ሥርዐት ያስታውሳል (ለምሳሌ ዘፀ 18፥21):: "በቡድን" ለሚለው የገባው የግሪኩ ቃል፣ የአትክልትን የችግኝ መደብን የሚያመለክት ሥዕላዊ አገላለጽ አለው (ቍ 39)::

6፥42 *ሁሉም በልተው ጠገቡ፤* ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ምግባቸውን ተካፍለው በሉ፤ ሕዝቡም ይህንኑ ተከትለው የያዙትን ምሳ ተካፍለው በሉ የሚለውና ይህን ታምር ለማጣጣል የሚቀርበው ሐሳብ ተቀባይነት የለውም:: ሥጋ የሆነው አምላክ፣ ይህን ታምር ማድረግ አይሳነውም:: እውነተኛው እረኛ ሲመጣ በጎቹ ተሰብስበው የሚሰማሩበት ምድረ በዳ የለመለመ መስክ እንደሚሆን እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቶአል (ሕዝ 34፥23-31)፤ እዚህም ላይ የሚታየው መሲሑ በምድረ በዳ ከተከታዮቹ ጋር በግብዣ ላይ ሆኖ ነው (ከኢሳ 25፥6-9 ጋር ያነጻጽሩ):: ኢየሱስ አንዳች ነገር እንዳይጐድልብን የሚያስፈልገንን የሚሰጠን እረኛችን ነው (ከመዝ 23፥1 ጋር ያነጻጽሩ)::

6፥43 *ከተበላው እንጀራና ዓሣ፣ ዐሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ ፍርፋሪ፤* አይሁድ እንጀራ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ብለው ስለሚያምኑ፣ ከማዕድ የወደቀ ፍርፋሪ ለቅመው ያነሡ ነበር፤ ከመሬት የተነሣውንም ፍርፋሪ ከዘወትር ልብሳቸው ጋር ይዘውት በሚዞሩት ሙዳይ ሰብስበው ይይዛሉ:: ደቀ መዛሙርትም እያንዳንዳቸው ሙዳያቸውን ሞልተው ተመለሱ (8፥8 ይመ፤ እንዲሁም የማቴ 15፥37 ማብ ይመ)::

6፥44 *አምስት ሺህ፤* ቅፍርናሆምና ቤተ ሳይዳ በዚያን ጊዜ እያንዳንዳቸው ከ 2000 -3000 የሚገመት ሕዝብ ስለ ነበራቸው፣ በመስኩ ላይ የተመገቡ ሕዝብ ብዛት 5000 መሆኑ የሚያስደንቅ ነው:: *ወንዶች፤* በአራቱም ወንጌላት የተገለጸው ወንዶች መሆና ቸው ነው፤ ማቴዎስ ግን፣ "ከሴቶችና ከሕፃናት ሌላ" በማለት ሁኔታውን ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል (ማቴ 14፥21)::

6፥45 *ቀድመውት እንዲሻገሩ፤* ሰዎቹ ኢየሱስን ይዘው በግድ ለማንገሥ እንዳሰቡ ዮሐንስ ጠቅሶአል (ዮሐ 6፥14-15)፤ ስለዚህ ኢየሱስ፣ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ባሕሩ ማዶ እንዲሄዱ ነግሮአቸው፣ እርሱ ግን ሊጸልይ ዘወር ብሎ ወደ ኰረብቶቹ ሄደ::

6፥48 *በአራተኛውም ክፍለ ሌሊት፤* ከሌሊቱ 9:00 - 12:00 ሰዓት ማለት ነው፤ 13፥35 ይመ፤ እንዲሁም የማቴ 14፥25 ማብ ይመ:: *በባሕር ላይ እየሄደ፤* ባሕሩን የሚገዛውና ከሁሉ በላይ የሆነውን ጌታ ግርማዊ ሀልዎትና ኀይል የሚያሳይ ልዩ ክሥተት ነው (መዝ 89፥9፤ ኢሳ 51፥10፡ 15፤ ኤር 31፥35 ይመ)::

6፥49 *ምትሐት፤* በአይሁድ ዘንድ በነበረው ዐጕል እምነት፣ መናፍስት በሌሊት ከታዩ ያልታሰበ መከራ በሰው ላይ ይደርሳል ይሉ ነበር:: የደቀ መዛሙርትም ፍርሃት ከውሃ የሚወጣ መንፈስ ስለ መሰላቸው ነው::

6፥52 *የእንጀራውን ታምር አላስተዋሉም፤* አምስት ሺህ ሕዝብ መመገቡን አስተውለው ቢሆን ኖሮ፣ ኢየሱስ በውሃ ላይ

ልባቸውም ደንድኖ ነበር።
53በተሻገሩም ጊዜ፣ ጌንሴሬጥ ደርሰው ወረዱ፤
ጀልባዋንም እዚያው አቆሙ። 54ወዲያው እንደ
ወረዱም፣ ሕዝቡ ኢየሱስን ዐወቁት፤ 55ወደ
አካባቢውም ሁሉ በመሮጥ ሕመምተኞችን
በዐልጋ ላይ እየተሸከሙ እርሱ ወደሚገኝበት
ስፍራ ሁሉ ያመጡ ነበር። 56በየደረሰበት መንደር
ወይም ከተማ ወይም ገጠር ሁሉ ሕመምተ
ኞችን በየአደባባዩ እያስቀመጡ የልብሱን
ጫፍ እንኳ ለመንካት ይለምኑት ነበር፤ የነ
ኩትም ሁሉ ይድኑ ነበር።

## ኢየሱስ የአይሁድን ውጫዊ ሥርዐት ተቃወመ

7፥1-23 ተጓ ምብ - ማቴ 15፥1-20

7 ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያንና ከኢየሩሳሌም
የመጡ አንዳንድ ጸሐፍት በዙሪያው ተሰ
በሰቡ፤ 2ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንዶቹ ባል
ነጻ ማለት ባልታጠበ እጅ እንጀራ ሲበሉ
አዩ፤ 3ፈሪሳውያንና አይሁድ ሁሉ የአባቶችን
ወግ ለመጠበቅ ሲሉ፣ በሥርዐቱ መሠረት
እጃቸውን በጥንቃቄ ሳይታጠቡ አይበሉም
ነበርና። 4ከገበያ ሲመለሱም ታጥበው ራሳ
ቸውን ካላነጹ በስተቀር አይበሉም ነበር።
እንዲሁም ዋንጫን፣ ማሰሮን፣ ሳሕንና ዐልጋን
እንደ ማጠብ ያሉትን ሌሎችን ወጎች ይጠብቁ
ነበር።
5ፈሪሳውያንንና ጸሐፍትም፣ "ደቀ መዛሙ
ርትህ እንደ አባቶች ወግ በመኖር ፈንታ ባል
ታጠበ እጃቸው ለምን እንጀራ ይበላሉ?"
ብለው ጠየቁት።
6እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ኢሳይያስ
ስለ እናንተ፣ ስለ ግብዞች በትክክል ተንብ
ዮአል፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤
'ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን
ከእኔ የራቀ ነው፤
7በከንቱ ያመልከኛል፤ ትምህርታቸውም ሰው
ሠራሽ ሥርዐት ብቻ ነው።'
8የእግዚአብሔርን ትእዛዛዝ ትታችሁ የሰዎ
ችን ወግና ሥርዐት ታጠብቃላችሁ።"
9ደግሞም፣ እንዲህ አላቸው፤ "የራሳችሁን
ወግ ለመጠበቅ[b] ስትሉ፣ የእግዚአብሔርን ትእ
ዛዝ የምትተውበት ዘዴ አላችሁ። 10ሙሴ፣
'አባትህንና እናትህን አክብር፤ አባቱን ወይም
እናቱን የሚሳደብ ፈጽሞ ይሙት ብሎ ነበ
ርና፤ 11እናንተ ግን አንድ ሰው አባቱን
ወይም እናቱን፣ 'ከእኔ ማግኘት የሚገባችሁን
ርዳታ ሁሉ ቍርባን ይኸውም መባ አድር
ጌአለሁ ቢላቸው፣ 12እናንተም ይህ ሰው ለአባቱም
ሆነ ለእናቱ ከዚህ በኋላ ምንም ነገር እንዲ
ያደርግ አትፈቅዱለትም። 13ስለዚህ ለትውልድ
በምታስተላልፉት ወግ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽ
ራላችሁ፤ ይህን የመሰለም ብዙ ነገር ታደር
ጋላችሁ!"።
14ደግሞም ኢየሱስ ሕዝቡን ወደ እርሱ ጠርቶ
እንዲህ አላቸው፤ "ስሙኝ፤ ሁላችሁም አስተ
ውሉ፤ 15ከውጭ ወደ ውስጥ ገብቶ ሰውን
የሚያረክሰው አንዳች ነገር የለም፤ ይልቁን
ሰውን የሚያረክሰው ከራሱ ወደ ውጭ የሚ
ወጣው ነገር ነው፤ ሰሚ ጆሮ ያለው ቢኖር
ይስማ[c]።
17ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ከገባ በኋላ ደቀ
መዛሙርቱ ስለ ምሳሌው ጠየቁት። 18እርሱም፣
"እናንተም ነገሩ አይገባችሁምን? ከውጭ ወደ
ሰው ገብቶ ሊያረክሰው የሚችል አንዳች
ነገር የለም፤ 19ወደ ልቡ ሳይሆን ወደ ሆዱ
ይገባል፤ ከዚያም ከሰውነቱ ይወጣልና።
ኢየሱስ ይህን በማለቱ ምግብ ሁሉ ንጹሕ

6፥56 ማቴ9፥20
7፥2 ሐሥ10፥14፡ 28፤11፥8፤ ሮሜ14፥14
7፥3 ቍ5:8: 9:13፤ሉቃ11፥38
7፥4 ማቴ23፥25፤ ሉቃ11፥39
7፥5 ቍ3፤ገላ1፥14፤ ቈላ2፥8
7፥7 ኢሳ29፥13
7፥8 ቍ3
7፥9 ቍ3
7፥10 ዘፀ20፥12፤ 21፥17፤ዘሌ.20፥9፤ ዘዳ5፥16
7፥11 ማቴ23፥16፡ 18
7፥13 ቍ3፤ ዕብ4፥12
7፥17 ማር9፥28
7፥19 ሐሥ10፥15፤ ሮሜ14፥1-21፤ ቈላ2፥16፤ 1ጢሞ4፥3-5
7፥22 ማቴ20፥15

[a]4 አንዳንድ የጥንት ቅጆች የማዕድ ዐልጋ ይላሉ
[b]9 አንዳንድ ቅጆች ለማቆም ይላሉ
[c]15 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ሰሚ ጆሮ ያለው ቢኖር፣ ይስማ የሚለው የላቸውም።

በመሄዱና ባሕሩን ጸጥ በማድረጉ ባልተገረሙ ነበር። *ልባቸው ደንድኖ ነበር፤* የኢየሱስ ተቃዋሚዎች ልባቸውን እንዳደነደኑ ሁሉ፣ ደቀ መዛሙርቱም ልባቸውን በማደንደን ከተቃዋሚዎቹ ጋር ተመሳሳይ ሆኑ (3፥5)፤ 8፥17-21 ይመ፤ እንዲሁም የዘፀ 4፥21 ማብ ይመ።

6፥53 *ጌንሴሬጥ፤* የማቴ 14፥34 ማብ ይመ።

6፥56 *የልብሱን ጫፍ እንኳ ለመንካት፤* የ5፥28 ማብ ይመ።

7፥1 *ፈሪሳውያንና ከኢየሩሳሌም የመጡ፤* ኢየሱስ በገሊላ ያደረገውን ለመሰለል ከኢየሩሳሌም የተላኩ (3፥22 ይመ) ሃይማኖታውያን መልእክተኞች ናቸው፤ የ2፥16፤ የማቴ 2፥4 ማብ ይመ።

7፥3 *የአባቶችን ወግ፤* በወቅቱ እጅግ አስፈላጊና በጥንቃቄ የሚጠበቅ ሥርዐት ነበር (ቍ 5 እና የማቴ 15፥2 ማብ ይመ)። *በሥርዐቱ መሠረት ... ሳይታጠቡ፤* የዮሐ2፥6 ማብ ይመ።

7፥4 *ከገበያ፤* አይሁድ ከአሕዛብ ወይም ሕጉን ባለመጠበቃቸው ከረከሱ ሌሎች አይሁድ ጋር ሊገናኙ የሚችሉበት ስፍራ ነበር፤ በዚህም ራሳቸው በሥርዐቱ መሠረት ይረክሳሉ ተብሎ ይታመን ነበር።

7፥6 *ኢሳይያስ ... ተንብዮአል፤* ኢሳይያስ በዘመኑ የነበሩትን የሃይማኖት መሪዎች በድፍረት ገሥጾአል (ኢሳ29፥13)፤ ኢየሱስም የአይሁድ መሪዎችን ወግ ለመግለጽ፣ "ሰው ሠራሽ ሥርዐት" በማለት ከነቢዩ መጽሐፍ ይጠቅሳል (ቍ 7)።

7፥8 *የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ... የሰዎችን ወግና ሥርዐት፤* ኢየሱስ ሁለቱን ነገሮች በግልጽ ያነጻጽራል፤ ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር ትእዛዛት ስለ ሆኑና የሕግ የበላይነትም ስላላቸው ግድ መከበር አለባቸው። የአባቶች ወግ (ቍ 3) ግን የእግዚአብሔር ቃል ስላልሆኑ፣ ሥልጣን የላቸውም፤ የመከበርም ግዴታ የለባቸውም።

*7፥10፤* እዚህ ላይ አምስተኛው ትእዛዝ በአዎንታዊና በአሉታዊ መልኩ ተጠቅሶአል።

7፥11 *ቍርባን፤* ቃሉ የዕብራይስጥ ሲሆን፣ ትርጕሙ "ስጦታ" ማለት ነው። አንድ ኀላፊነት የጐደለው አይሁዳዊ ልጅ፣ ለወላጆቹ መፈጸም የሚገባውን ግዴታ ተስያለሁ በማለት ለእግዚአብሔር ማለትም ለቤተ መቅደስ ሊሰጥ ይችላል። ይሁን እንጂ ገንዘቡ ለሃይማኖት ሥራ ውሎአል ማለት አይቻልም። ይህ ቍርባን፣ አንድ ልጅ በተጻፈው ሕግ መሠረት ለወላጆቹ ማድረግ የሚገባውን ግዴታ ለመሸሽ ሲል፣ የሚፈጽመው ውጫዊ ሥርዐት ብቻ ነው፤ አንድ ሰው ድንገት በችኰላ ቢሳል እንኳ ስለቱ የግድ መከፈል እንዳለበት ያስተምራሉ። ይኸውም የቃሉን መንፈስ ሳይሆን፣ የፊደሉን ትርጕም ብቻ ከመከተል የመጣ ነው። ማርቆስ ቍርባን ለሚለው የዕብራይስጥ ቃል ለእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ የሚል ትርጕም በመስጠቱ፣ የማርቆስ ወንጌል ተደራስያን ከአሕዛብ ወገን እንደ ሆኑ ያመለክታል፤ ምናልባትም ሮማውያን ይሆናሉ።

7፥13 *ስለዚህ ለትውልድ በምታስተላልፉት ወግ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ፤* ጸሓፍት ለቍርባን ስለት ድጋፍ ይሆናል ብለው የሚያቀርቡት በዘኍ 30፥1-2 የተጻፈውን ቃል ነው፤ ኢየሱስ ግን የአንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ለመሻር ሲባል ሌላ ጥቅስ መጥቀስ አግባብ እንዳልሆነ በግልጽ አስቀምጦአል። ዘኍ 30፥1-2 በመምህራኑ ዐይን ቃል በቃል ሲተረጐም ትክክል ይመስላል ይሁን እንጂ ትርጕሙ የሕጉን አጠቃላይ መንፈስ የሳተ ነው፤ እግዚአብሔር አንዱን ሕግ ለመሻር ሌላውን ታዘዙ አላለምና።

*7፥16፤* የቍ 15 ላይ አግራጭ ትርጕም ይመ፤ በብዙዎች የግሪክ ቅጆች ላይ ቢኖርም፣ በአብዛኛዎቹ የጥንት ቅጆች ግን አይገኝም። ከ4፥9 ወይም ከ4፥23 በማገናዘብ ጽሑፉን የገለበጠው ሰው የጨመረው ሳይሆን አይቀርም።

7፥19 *ኢየሱስ ይህን በማለቱ ምግብ ሁሉ ንጹሕ መሆኑን ገለጠ፤* ማርቆስ ይህን ሐሳብ ጣልቃ ማስገባቱ ኢየሱስ ባስተ

መሆኑን ገለጠ።
20ቀጥሎም፣ እንዲህ አለ፤ “ከሰው የሚወጣ
ያ ሰውን ያረክሰዋል፤ 21ከውስጥ፣ ከሰው ልብ
የሚወጡት ክፉ ሐሳብ፣ ምንዝር፣ ስርቆት፤
ሰው መግደል፣ ዝሙት፣ 22መስገብገብ፣ ክፋት፣
ማታለል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስም ማጥፋት፣
ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው። 23እነዚህ ክፉ ነገሮች
ሁሉ ከሰው ይወጣሉ ሰውንም ያረክሱታል።”

## ሲሮፊኒቃዊቷ ሴት

7፥24-30 ተጓ ምብ - ማቴ 15፥21-28

24ከዚያ ተነሥቶ ወደ ጢሮስ[ከ] አገር ሄደ፤
ወደ አንድ ቤት ገብቶ እዚያ መኖሩን ማንም
እንዳያውቅበት ፈለገ፤ ሆኖም እዚያ መኖሩ
ሊሸሸግ አልቻለም። 25ወዲያው ግን ትንሺቱ
ልጇ በርኩስ[ኸ] መንፈስ የተያዘችባት አንዲት
ሴት ስለ እርሱ ሰምታ መጣችና በእግሩ ላይ
ወደቀች። 26ሴትየዋም ግሪካዊት፣ በትውልዷም
ሲሮፊኒቃዊት ነበረች። እርሷም ኢየሱስ ርኩስ
መንፈሱን ከልጇ እንዲያስወጣላት ለመነችው።
27እርሱ ግን፣ “የልጆችን እንጀራ ወስዶ
ለውሾች መጣል ተገቢ ስላልሆነ፣ መጀመሪያ
ልጆቹ ጠግበው ይብሉ” አላት።
28እርሷም መልሳ፣ “አዎን፣ ጌታ ሆይ፤ ውሾችም
ከገበታ በታች ሆነው የልጆችን ትራፊ ይበላሉ’
አለችው።
29እርሱም፣ “ስለዚህ ይህን ስላልሽ ሂጂ፤ ጋኔኑ
ከልጅሽ ወጥቶአል” አላት።
30እርሷም ወደ ቤቷ ስትመለስ ልጇ ዐልጋ
ላይ ተኝታ፣ ጋኔኑም ለቆአት አገኘቻት።

## የደንቈሮውና የድዳው መፈወስ

7፥31-37 ተጓ ምብ - ማቴ 15፥29-31

31ከዚያም ኢየሱስ ከጢሮስ አገር ተነሥቶ፣
በሲዶና በኩል አድርጎ ዐሥር ከተማ[ወ] በተ
ባለው አገር በማለፍ ወደ ገሊላ ባሕር መጣ።
32በዚያም ሰዎች ደንቈሮና ዲዳ የሆነ አንድ
ሰው ወደ እርሱ አመጡ፤ እጁንም እንዲ
ጭንበት ለመኑት።
33ኢየሱስም ሰውየውን ከሕዝቡ ለይቶ
ከወሰደው በኋላ፣ ጣቶቹን በጆሮው አስገባ፤
ከዚያም እንትፍ ብሎ የሰውየውን ምላስ
ዳሰሰ። 34ወደ ሰማይም ተመልክቶ ቃተተና፣
“ኤፍታህ!” አለው፤ ይኸውም፣ “ተከፈት”
ማለት ነው። 35ወዲያውም ጆሮዎቹ ተከፈቱ፤
ምላሱም ተፈቶ አጥርቶ መናገር ጀመረ።
36ኢየሱስ ይህን ለማንም እንዳይናገሩ አዘ
ዛቸው፤ ሆኖም እርሱ እንዳይናገሩ ባዘዛቸው
መጠን፣ ነገሩን አስፍተው አወሩት። 37ሕዝ
ቡም ከመጠን በላይ በመደነቅ፣ “ያደረገው ሁሉ
ጥሩ ነው፤ ደንቈሮዎች እንዲሰሙ፣ ድዳዎች
እንዲናገሩ እንኳ አድርጎአል” አሉ።

## ኢየሱስ አራት ሺህ ሰዎች መገበ

8፥1-9 ተጓ ምብ - ማቴ 15፥32-39
8፥1-9 ማመ - ማር6፥32-44
8፥11-21 ተጓ ምብ - ማቴ 16፥1-12

8 በዚያን ጊዜ፣ እንደ ገና ብዙ ሕዝብ ተሰበ
ሰበ። የሚበሉት ምንም ምግብ ስላልነበ
ራቸው ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶ፣
እንዲህ አላቸው፤ 2ከእኔ ጋር ሦስት ቀን
ስለቈዩና የሚበሉትም ስለሌላቸው እነዚህ
ሰዎች ያሳዝኑኛል፤ 3እንዲህ እንደ ተራቡ ወደ
ቤታቸው ብሰዳቸው አንዳንዶቹ ከሩቅ የመጡ

7፥22 ማቴ20፥15
7፥24 ማቴ11፥21
7፥25 ማቴ4፥24
7፥31 ቍ24፤ ማቴ4፥18:25፤ 11፥21፤ማር5፥20
7፥32 ማቴ9፥32፤ ማር5፥23፤ ሉቃ11፥14
7፥33 ማር8፥23
7፥34 ማር6፥41፤8፥12፤ ዮሐ11፥41
7፥35 ኢሳ35፥5:6
7፥36 ማቴ8፥4

ከ24 አያሌ የጥንት ቅጆች ጢሮስና ሲዳና የሚለው አላቸው
ኸ25 ወይም ክፉ
ወ31 የግሪኩ ዴካፖሊስ ይለዋል

ማረው ትምህርት ውስጥ ዋናው ጒዳይ ምን እንደ ሆነ አንባቢዎቹ እንዲያስተውሉ ለመርዳት ነው (ሐሥ 10፥9-16 ይመ)።

7፥20 *ያረክሰዋል፤* ኢየሱስ ሰው የሚረክሰው በልብ ንጽሕና ጒድለት እንጂ፣ ውጫዊ ሕግጋትን በመተላለፍ እንዳልሆነ በመግለጽ፣ አይሁድ ስለ መርከስ ያላቸውን አመለካከት ገለባበጠ። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት የሚቋረጠው ባልታጠበ እጅ ወይም በምንበላው ምግብ ሳይሆን፣ በኀጢአት ነው (ቍ 21-23 ይመ)።

7፥24 *ጢሮስ፤* በሰሜን ምዕራብ በኩል ገሊላን በሚያዋስነው፣ በፊንቄ (በዛሬው ሊባኖስ) ውስጥ ይገኝ የነበረ ከተማ ነው። ኢየሱስ ከቅፍርናሆም ተነሥቶ ወደ ጢሮስ አካባቢ የደረሰው 48 ኪ.ሜ ያህል ተጒዞ ሳይሆን አይቀርም። *ማንም እንዳያውቅበት ፈለገ፤* አምስቱን ሺህ ሰዎች ከመገበ ጀምሮ (6፥30-44)፣ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ብዙውን ጊዜ ወደ ውስጥ ሳይገቡ በገሊላ ዙሪያ ይመላለሱ ነበር፤ ዐላማውም የገሊላ ሰዎች ግጭት ሳይፈጥሩበት ደቀ መዛሙርቱን ለብቻ ለማስተማር ዕድል ለማግኘት ነበር (9፥30-31)። ፈቀቅ ያለባቸውም ቦታዎችም፦ (1) የገሊላ ባሕር ሰሜን ምሥራቅ ዳርቻ (6፥30-53)፤ (2) *ፊንቄ* (7፥24-30)፤ (3) *ዐሥር ከተማ* (7፥31-8፥10) እንዲሁም (4) *ፊልጶስ ቂሣርያ* (8፥27-9፥32) ነበሩ።

7፥26 *ግሪካዊት፤* እዚህ ላይ፣ “አሕዛብ” ማለት ሊሆን ይችላል። *ሲሮፊኒቃዊት፤* በዚያን ዘመን ፊንቄ በአስተዳደር ረገድ የሶርያ ግዛት ነበረች። ማርቆስ ይህን አባባል የመረጠው ምናልባት ይህች ሴት በሰሜኗ አፍሪካ ከሚገኙት ከሊቢያ-ፊኒቃውያን ሰዎች የተለየች መሆኗን ለማመልከት ይሆናል።

7፥27 *የልጆችን እንጀራ ወስዶ ለውሾች መጣል፤* የማቴ 15፥26 ማብ ይመ።

7፥28 *አዎን፣ ጌታ ሆይ፤* በዚህ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ፣ “ጌታ” ተብሎ የተጠራው እዚህ ላይ ብቻ ነው።

7፥31 *ከጢሮስ አገር ተነሥቶ በሲዶና በኩል አድርጎ … ወደ ገሊላ ባሕር ሄደ፤* ኢየሱስ ከጢሮስ በሰሜን በኩል ወደ ሲዶና (40 ኪ.ሜ. ያህል) ከተጓዘ በኋላ፣ በደቡብ ምሥራቅ በኩል ወደሚገኘው ወደ ሄሮድስ ፊልጶስ ግዛት በመዝለቅ፣ ወደ ገሊላ ባሕር ምሥራቃዊ ክፍል የሄደ ይመስላል። አካሄዱም ዙሪያ ጥምጥም የሆነበት ምክንያት፣ ሄሮድስ አንቲጳስ ባለ ሥልጣን ወደ ሆነባትና (6፥17-29) ብዙዎች ኢየሱስን በግድ ሊያነግሡት ወደ ፈለጉበት (6፥14-15) ወደ ገሊላ አውራጃ ላለመግባት ፈልጎ ሊሆን ይችላል። ሄሮድስ ከኢየሱስ ዝና የተነሣ ሥጋት ካደረበት ውሎ አድሮአል (6፥14-16)። *ዐሥር ከተማ፤* የቍ 24፤ የማቴ 4፥25 ማብ ይመ።

7፥34 *ኤፍታህ!* ማርቆስ ለአሕዛብ ተደራስያኑ ትርጒሙን የሰጠው ቃሉ የአራማይክ ስለ ሆነ ነው።

7፥35 *ጆሮዎቹ ተከፈቱ … አጥርቶ መናገር ጀመረ፤* ኢየሱስ የፈጸመው እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመቤዠት በሚመጣበት ጊዜ ለማድረግ የገባውን የተስፋ ቃል ነው (ኢሳ 35፥5-6 ይመ)።

7፥36 *ለማንም እንዳይናገሩ፤* 1፥44 ይመ፤ እንዲሁም የ5፥19:43፤ ማቴ 8፥4፤ 16፥20 ማብ ይመ።

*8፥1-10፤* በዚህ ክፍልና በ6፥34-44 ባሉት ትረካዎች መካከል ተመሳሳይነት ቢኖርም፣ ሁለቱ በተለያየ ጊዜ የተከናወኑ ድርጊቶች ናቸው። ኢየሱስ ራሱ ሕዝቡን ሁለት ጊዜ እንደ መገበ መናገሩ በተለያየ ጊዜ የተፈጸመ ድርጊት መሆኑን ያስረዳል (ቍ 18-20 ይመ)። በዝርዝር ሁኔታው ውስጥ ያሉት ልዩነቶችም የተመሳሳይነታቸውን ያህል ቁልጭ ያለ ልዩነት ይታይባቸዋል።

8፥1 *እንደ ገና ብዙ ሕዝብ ተሰበሰበ፤* ይህ ድርጊት የተከናወነው፣ “ዐሥር ከተማ” እንደ መሆኑ መጠን (7፥31 ይመ)፣ የተሰበሰበው ሕዝብ ከአይሁድና ከአሕዛብ ወገን የተውጣጣ ሊሆን ይችላል።

8፥2 *እነዚህ ሰዎች ያሳዝኑኛል፤* ሰዎቹ እረኛ እንደሌላቸው በጎች በመሆናቸው ቀደም ሲል ኢየሱስ እንዳዘነላቸው ሁሉ (6፥34)፣ አሁንም ምግብ ሳይበሉ ብዙ ጊዜ በመቈየታቸው ሲያዝንላቸው ይታያል።

ስለ ሆኑ በመንገድ ላይ ዝለው ይወድቃሉ::”
[4]ደቀ መዛሙርቱም መልሰው፣ “በዚህ ምድረ
በዳ እነዚህን ለመመገብ የሚያስችል እንጀራ
ከወዴት ይገኛል?” አሉት::
[5]እርሱም፣ “ስንት እንጀራ አላችሁ?” ብሎ ጠየ
ቃቸው::
እነርሱም፣ “ሰባት” አሉት::
[6]እርሱም፣ መሬት ላይ እንዲቀመጡ ሕዝ
ቡን አዘዘ፤ ሰባቱን እንጀራ ይዞ ካመሰገነ
በኋላ ቈርሶ ለሰዎቹ እንዲያድሉ ለደቀ መዛ
ሙርቱ ሰጣቸው፤ እነርሱም ለሕዝቡ አደሉት::
[7]እንዲሁም ትንንሽ ዓሣዎች ነበሯቸው፤ እርሱም
ዓሣዎቹን ባርኮ እንዲያድሏቸው አዘዘ:: [8]ሕዝ
ቡም በልተው ጠገቡ፤ ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ
የተረፈውን ቍርስራሽ ሰባት መሶብ ሙሉ
አነሡ:: [9]በዚያም አራት ሺህ ያህል ሰዎች
ነበሩ፤ ካሰናበታቸውም በኋላ፣ [10]ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ዳልማኑታ ወደ ተባለ ስፍራ ሄደ::
[11]ፈሪሳውያንም ወጥተው ከኢየሱስ ጋር
ይከራከሩ ጀመር:: ሊፈትኑትም ፈልገው ከሰ
ማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁት::
[12]እርሱም በመንፈሱ እጅግ በመቃተት፣ “ይህ
ትውልድ ምልክት የሚፈልገው ለምንድን
ነው? እውነት እላችኋለሁ፤ ለዚህ ትውልድ
ምንም ምልክት አይሰጠውም!” አለ:: [13]ከዚ
ያም ትቶአቸው በጀልባ ወደ ማዶ ተሻገረ::

## የፈሪሳውያንና የሄሮድስ እርሾ

[14]ደቀ መዛሙርቱ እንጀራ መያዝ ስለ
ረሱ፣ ከአንድ እንጀራ በቀር በጀልባ ውስጥ
ምንም አልነበራቸውም:: [15]ኢየሱስም፣ “ተጠ
ንቀቁ፤ ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ እርሾ ተጠበቁ”
ብሎ አዘዛቸው::
[16]እነርሱም እርስ በርሳቸው፣ “እንዲህ የሚለን
እኮ እንጀራ ስለሌለን ነው” ተባባሉ::
[17]ኢየሱስም ሐሳባቸውን ዐውቆ፣ እንዲህ
አላቸው፤ “እንጀራ ስለሌለን ነው በማለት ምን
ያነጋግራችኋል? አሁንም አታስተውሉምን?
ልብስ አትሉምን? ወይስ ልባችሁ ደንድኖአል?
[18]ዐይን እያላችሁ አታዩምን? ጆሮ እያላችሁ
አትሰሙምን? አታስታውሱምን? [19]አምስቱን
እንጀራ ለአምስት ሺህ ሰው በቈረስሁ ጊዜ
ስንት መሶብ ሙሉ ትርፍራፊ አነሣችሁ?”
እነርሱም፣ “ዐሥራ ሁለት” አሉት::
[20]“ሰባቱንስ እንጀራ ለአራት ሺህ በቈረስሁ

8፥2 ማቴ9፥36
8፥7 ማቴ14፥19
8፥8 ቍ20
8፥11 ማቴ12፥38
8፥12 ማር7፥34
8፥15 ማቴ14፥1፤ ማር12፥13፤ሉቃ12፥1፤1ቆሮ5፥6-8
8፥17 ኢሳ6፥9:10፤ ማር6፥52
8፥19 ማቴ14፥20፤ ማር6፥41-44፤ ሉቃ9፥17፤ዮሐ6፥13

8፥4 *እነዚህን ለመመገብ የሚያስችል እንጀራ ከወዴት ይገኛል?* *የደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ እነርሱ ዐቅም የለሽ መሆና* ቸውንና ኢየሱስ ብቻ መመገብ እንደሚችል የሚያመለክት ነው፤

ደግሞም አምስት ሺውን ሕዝብ መመገቡን (6፥34-44) አልዘ ነጉም፤ ሆኖም ለሰዎች እንጀራን የማዘጋጀቱ ተግባር ለእርሱ መተዋቸው ይመስላል:: በሌላም በኩል ጥያቄያቸው ገና መንፈሳዊ ግንዛቤ እንደሚጐድላቸው ሳያመለክት አይቀርም::

8፥8 *ሰባት መሶብ ሙሉ፤* የማቴ 15፥37 ማብ ይመ::

8፥9 *አራት ሺህ . . . ሰዎች፤* የ6፥44 ማብ ይመ::

8፥10 *ዳልማኑታ፤* ከጌንሳሬጥ ሜዳ በስተ ደቡብ፣ “ዳል ማኑታ” የሚል ስም የሚነበብበት ዋሻ ተገኝቶአል፤ ኢየሱስ በዚህ ጊዜ የሄደው ወደዚህ ቦታ ሳይሆን አይቀርም:: ማቴዎስ ጌታ ኢየ ሱስ ወደ መጌዶል አቅራቢያ እንደ ሄደ ይናገራል (ማቴ 15፥39 እና ያንኑ ማብ ይመ):: ዳልማኑታና መጌዶል በገሊላ ባሕር ምዕራብ ዳርቻ የነበሩ ሲሆን፣ ሁለቱም የአንድ ቦታ ስሞች ወይም አጠገብ ላጠገብ የነበሩ ሁለት የተለያዩ ቦታዎች ሊሆኑ ይችላሉ::


8፥11 *ፈሪሳውያንም፤* የ2፥16 ማብ ይመ:: *ከሰማይ ምልክት፤* ፈሪሳውያን፣ ጌታ ካደረጋቸው ታምራት ይልቅ መለኮታዊ ሥልጣኑን የሚገልጹ ተጨማሪ ምልክቶችን ፈለጉ፤ ኢየሱስ ግን ጥያቄያ ቸው ከማያምን ልብ የፈለቀ መሆኑን በማወቁ አልተቀበላቸውም::

8፥13 *ወደ ማዶ፤* ወደ ገሊላ ባሕር ምሥራቃዊ ዳርቻ ማለት ነው::

8፥15 *ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ እርሾ፤* በአዲስ ኪዳን፣ ‘እርሾ’ ሲባል የክፋትና የሙስና ምሳሌ ነው (ማቴ 16፥6:11፤ ሉቃ 12፥1፤ 1ቆሮ 5፥6-8፤ ገላ 5፥9፤ የማቴ 13፥33 ግን ከእነዚህ የተለየ ይመስላል፤ ያንኑ ማብ ይመ):: ምሳሌው ትንሿ እርሾ ትልቁን ሊጥ ልታቦካ እንደምትችል የሚያሳይ ነው፤ በዚህ ዐውድ አገባቡ የፈሪሳውያንንና የሄሮድስ አንቲጳስን መሠሪ ዐላማ ያሳያል (ሉቃ 23፥8 ይመ)፤ እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ መለኮታዊ ሥልጣኑን ታምር በመሥራት እንዲያረጋግጥላቸው ጠይቀዋል (የቍ 11 ማብ ይመ)::

*8፥18-20፤* ይህ ክፍል ኢየሱስ ሰዎችን በተለያየ ቦታ ሁለት ጊዜ እንደ መገበ ያመለክታል (በቍ 1-10 ላይ የተሰጠ ውን ማብ ይመ)::

## የጢሮስና ሲዶና አገር




አረማዊና ከፊል አረማዊ ወደ ሆኑት አካባቢዎች ባደረገው ልዩና አጭር ጕዞ፣ ኢየሱስ የጢሮስንና ሲዶናን አውራጃዎች እንዲሁም በኋላ ዴካፖሊስን የሚ ተዳደሩትን ዐሥር ከተሞች በመባል የሚታወቁትን ጎበኘ:: ኢየሱስ የተጠራው «ለጠፉት የእስራኤል በጎች» ቢሆንም በገሊላ የነበረው ውጥረት ወደዚህ ቦታ ሊያመጣው ችሏል:: በዚህ ቦታ እንኳ በስፋት ስለታወቀ በዚያ መኖሩን ለመሰወር አልተቻለም:: በንግድ እንቅስቃሴአቸው የታወቁት የጢሮስና ሲዶና ከተሞች ከኤልዛቤል ዘመን አንሥቶ የበኣሉ ባሕልና ሃይማኖት ምንጭ ሆነው ቆይተዋል:: ከተሞቹ በግሪክ ባሕል ተጽእኖ ሥር የነበሩ ሲሆን ይህም በዘመኑ ሥነ ሕንጻ ተገልጿል:: ሁለቱም ከተሞች እያንዳንዳቸው ታሪካዊ የከነዓናውያን ማዕከላት ሲሆኑ በውስጣቸውም የጥንት ነገሥታት መቃብሮችና የሔራክለስ፣ የአስታርትና የሌሎች አማልክት አብያተ ጣዖታት ይገኙባቸዋል::

ጊዜ ስንት መሶብ ሙሉ ትርፍራፊ አነሣችሁ?"
አላቸው::
እነርሱም፣ "ሰባት" አሉት::
21እርሱም፣ "እስከ አሁን አላስተዋላችሁም
ማለት ነውን" አላቸው::

## በቤተ ሳይዳ የተፈወሰው ዐይነ ስውር

22ከዚያም ወደ ቤተ ሳይዳ መጡ፤ ጥቂት
ሰዎችም አንድ ዐይነ ስውር ወደ ኢየሱስ
አምጥተው እንዲዳስሰው ለመኑት:: 23እርሱም
የዐይነ ስውሩን እጅ ይዞ ከሰፈር ውጭ
አወጣው፤ በዐይኖቹም ላይ እንትፍ ብሎበት፣
እጁንም በላዩ ጭኖ፣ "ምን የሚታይህ ነገር
አለ?" ሲል ጠየቀው::
24እርሱም ቀና ብሎ አይቶ፣ "ሰዎች እንደ
ዛፍ ሲንቀሳቀሱ አያለሁ" አለ::
25ኢየሱስም እንደ ገና እጆቹን በሰውየው
ዐይኖች ላይ ጫነ፤ በዚህ ጊዜ ዐይኖቹ በሩ፤
ብርሃኑም ተመለሰለት፤ ሁሉንም ነገር አጥርቶ
ማየት ቻለ:: 26ከዚያም፣ "ወደ መንደሩ አትግባ!
በመንደሩም ለማንም አትናገር°" ብሎ ወደ
ቤቱ ሰደደው::

## ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ የነበረው ግንዛቤ

8፥27-29 ተን ምብ - ማቴ 16፥13-16፤ ሉቃ9፥18-20

27ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ፊሊጶስ
ቂሣርያ መንደሮች ሄደ፤ በመንገድ ላይ ሳሉም
ደቀ መዛሙርቱን፣ "ሰዎች እኔን ማን ይሉ
ኛል?" ብሎ ጠየቃቸው::

8፥20 ቍ6-9፤ ማቴ15፥37
8፥21 ማር6፥52
8፥22 ማቴ11፥21፤ ማር10፥46፤ዮሐ9፥1
8፥23 ማር5፥23፤ 7፥33
8፥28 ማቴ3፥1፤ ሚል4፥5
8፥29 ዮሐ6፥69፤ 11፥27
8፥30 ማቴ8፥4፤ 16፥20፤17፥9፤ ማር9፥9፤ሉቃ9፥21
8፥31 ማቴ8፥20፤ 16፥21፤ማቴ27፥1፡ 2፤ሐሥ2፥23፤3፥13
8፥32 ዮሐ18፥20
8፥33 ማቴ4፥10
8፥34 ማቴ10፥38፤ ሉቃ14፥27

28እነርሱም፣ "መጥምቁ ዮሐንስ የሚሉህ
አሉ፤ ሌሎች ኤልያስ ነው ይሉሃል፤ ሌሎች
ደግሞ ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ" ብለው
ነገሩት::
29ቀጥሎም፣ "እናንተሳ ማን ትሉኛላችሁ?"
ሲል ጠየቃቸው::
ጴጥሮስም፤ "አንተ ክርስቶስ" ነህ" አለው::
30ኢየሱስም ስለ እርሱ ለማንም እንዳይ
ናገሩ አስጠነቀቃቸው::

## ኢየሱስ ስለ ሞቱ አስቀድሞ ተናገረ

8፥31-9፥1 ተን ምብ - ማቴ16፥21-28፤ ሉቃ9፥22-27

31ከዚያም የሰው ልጅ ብዙ መከራ እንደ
ሚቀበል፣ በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችና
በጸሐፍት እንደሚናቅ፣ እንደሚገደል፣ ከሦስት
ቀንም በኋላ እንደሚነሣ ያስተምራቸው ጀመር::
32እርሱም ይህን በግልጽ ነገራቸው:: በዚህ ጊዜ
ጴጥሮስ ኢየሱስን ለብቻው ወስዶ ይገሥጸው
ጀመር::
33ኢየሱስ ግን ዘወር ብሎ ደቀ መዛሙ
ርቱን እያየ ጴጥሮስን፣ "አንተ ሰይጣን፣
ወደ ኋላዬ ሂድ! አንተ የሰውን እንጂ የእግዚአ
ብሔርን ነገር አታስብምና" በማለት ገሠጸው::
34ከዚህ በኋላ፣ ሕዝቡን ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ "ሊከተለኝ

°26 አንዳንድ ቅጆች *በመንደሩም፤ ለማንም አትናገር!* የሚለው የላቸውም::
"29 በግሪኩ *ክርስቶስ*፣ በዕብራይስጡ *መሲሕ* የሚለው ቃል ትርጕም *የተቀባ* ማለት ነው

8፥22 *ቤተ ሳይዳ፤* የማቴ 11፥21 ማብ ይመ::

8፥24 *እንደ ዛፍ ሲንቀሳቀሱ፤* ሰውየው ስለ ዛፍ መናገሩ፣ ከጊዜ በኋላ የታወረ ወይም ስለ ዛፍ ቅርጽና እንቅስቃሴ በመዳሰስና በሰዎች ገለጻ ግንዛቤ ያገኘ ይመስላል::

8፥25 *ኢየሱስም እንደ ገና እጆቹን በሰውየው ዐይኖች ላይ ጫነ፤* ኢየሱስ የሰውየውን ዐይን ዳግመኛ መዳሰሱ ካደረጋቸውና የፈውስ ታምራት አሠራር ሁሉ የተለየ ነው:: *ሁሉንም ነገር አጥርቶ ማየት ቻለ፤* ኢየሱስ ዐይነ ስውራንን እንዲያዩ ማድረጉ እግዚአብሔር ድነትን ለመስጠት በሚመጣበት ጊዜ ሊያደርገው የገባውን የተስፋ ቃል (ኢሳ 35፥5) መፈጸሙን የሚያሳይ ሌላው ምልክት ነው::

8፥26 *ወደ መንደሩ አትግባ!* የተደረገው ታምር ይፋ ወጥቶ ኢየሱስ አገልግሎቱን ከመፈጸሙ በፊት ዕንቅፋት እንዳይፈጥርበት በማሰብ ነው፤ 1፥44 ይመ፤ እንዲሁም የ5፥19፡43፤ ማቴ 8፥4፤ 16፥20 ማብ ይመ::

8፥27 *የፊልጶስ ቂሣርያ፤* የ7፥24፤ ማቴ 16፥13 ማብ ይመ::

8፥29 *ክርስቶስ፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ፤ በዘመኑ የነበረው የአይሁድ አመለካከት "ክርስቶስ" የሚለውን መጠሪያ ከፖለቲካና ከብሔራዊ ስሜት ጋር የሚያገናኝ ስለ ነበር፣ ኢየሱስ ራሱን በዚህ ስም ከመጥራት ይቈጠብ ነበር:: ይህ ስም በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ሰባት ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ራሱ ኢየሱስ ይህን በመጠሪያነት የተጠቀመው ሦስት ጊዜ ብቻ ነው (9፥41፤ 12፥35፤ 13፥21)፤ በእነዚህም እንኳ በእጅ አዙር እንጂ በቀጥታ ለራሱ በመጠሪያነት አላዋለውም (በ9፥41 ላይ ግን ያዋለ ይመስላል):: ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ማርቆስ በ1፥1 ላይ ገልጾአል::

8፥30 *ስለ እርሱ ለማንም እንዳይናገሩ፤* 1፥44 ይመ፤ እንዲሁም የ5፥19፡43፤ ማቴ 8፥4፤ 16፥20 ማብ ይመ::

*8፥31-10፥52፤* የኢየሱስን ሞት አስመልክቶ በተነገረ ሦስት ትንቢያ ላይ የተመረኰዘ (8፥31፤ 9፥31፤ 10፥33-34) አዲስ ክፍል እዚህ (8፥31) ላይ ይጀምራል:: ኢየሱስ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የተገለጸውን አብዛኛውን አገልግሎቱን የፈጸመበትን ገሊላን ትቶ፣ ምድራዊ አገልግሎቱን ወደ ደመደመበት ወደ ኢየሩሳሌም መሄዱን ክፍሉ ያመለክታል:: ኢየሱስ፣ "ክርስቶስ" የሚለው ስም የእርሱ መጠሪያ ሆኖ ጥቅም ላይ ሲውል ትክክለኛ ትርጕሙ ምን እንደ ሆነ በዚህ ክፍል ውስጥ ይገልጻል::

8፥31 *የሰው ልጅ፤* ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ራሱን የሚጠራበት መጠሪያ ሲሆን፣ በወንጌላት ውስጥ 81 ጊዜ ተጽፎ ይገኛል፤ ከኢየሱስ በስተቀር በዚህ መጠሪያ የተጠቀመ ሌላ ሰው የለም:: በዳን 7፥13-14 ላይ የሰው ልጅ የተባለ ሰማያዊ "ሰው" በመጨረሻው ጊዜ ሥልጣን፣ ክብርና ልዑላዊ ኀይል ከእግዚአብሔር እንደ ተሰጠው ተገልጾአል:: ጴጥሮስ፣ "ክርስቶስ" ካለው ስያሜ አንጻር (ቍ 29)፤ ኢየሱስ "የሰው ልጅ" የሚለውን መጠሪያ መጠቀሙ (ቍ 31)፣ ይህ አጠራር ለመሲሑ የሚሰጥ መጠሪያ መሆኑን ያመለክታል፤ የዳን 7፥13 ማብ ይመ:: *መከራ እንደሚቀበል፤* በኢሳ 52፥13-53፥12 ባለው ክፍል መከራ ስለሚቀበለው አገልጋይ በተነገረው ትንቢት መሠረት ማለት ነው (ማር 9፥9፡12፡31፤ 10፥33-34፤ 14፥21፡41 ይመ):: *በሽማግሌዎች፤* ሰንሄድሪን በተባለው በአይሁድ ከፍተኛ ሸንጎ ውስጥ ተራ አባላት የነበሩ ናቸው:: *በካህናት አለቆች፤* የማቴ 2፥4 ማብ ይመ:: የካህናት አለቆች ሲባል፣ ሊቀ ካህናት ሆኖ በማገልገል ላይ የነበረውን ቀያፋ፣ የቀድሞውን ሊቀ ካህናት ሐናን እንዲሁም የሊቃነ ካህናቱን ቤተ ሰቦች ያካትታል:: የጸሐፍት የማቴ 2፥4 ማብ ይመ:: ሰንሄድሪን በተባለው የአይሁድ ከፍተኛ ሸንጎ ውስጥ የሽማግሌዎች፣ የካህናት አለቆችና የኦሪት ሕግ መምህራን ተወካዮች ይገኙበታል::

8፥32 *ጴጥሮስ … ይገሥጸው ጀመር፤* ጴጥሮስ፣ 'መሲሑ' መሠቃየትና መናቅ የሚደርስበት መስሎ አልታየውም፤ ኢየሱስ መከራና ሥቃይ ይቀበላል የሚለውም ትምህርት ከመሥመር የወጣ ስለ መሰለው ሊገሥጸው ቻለ::

8፥33 *ሰይጣን፤* ኢየሱስ ወደ መስቀል እንዳይሄድ ጴጥሮስ ያደረገው መከላከል፣ ኢየሱስ አገልግሎቱን እንደ ጀመረ ሰይጣን ካደረገው መፈታተን ጋር ተመሳሳይነት ስላለው (ማቴ 4፥8-10) ጌታ ጴጥሮስን ክፉኛ ገሠጸው::

8፥34 *ራሱን ይካድ፤* አንድ ሰው የራሱን ፍላጎት ብቻ የሕይወቱና የተግባሩ ማእከል ማድረግ የለበትም ማለት ነው:: *መስቀሉንም ተሸክሞ፤* የሞት ፍርድ የተፈረደበት ሰው ራሱ የሚሰቀልበትን ግንድ ተሸክሞ የሞትን ጽዋ ወደሚቀበልበት ቦታ ሲሄድ በዐይነ ልቡና የሚያሳይ ነው (ዮሐ 19፥17 ይመ):: መስቀልን መሸከም አንድ ሰው ለጌታ ሲል መከራንና ሞትን በፈቃደኝነት ለመቀበል ዝግጁ መሆኑን ያመለክታል:: *ይከተለኝ፤* የራሱ የጌታ ሞት በመስቀል ላይ እንደሚሆን ያመለክታል::

የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም
ተሸክሞ ይከተለኝ፤ 35ነፍሱን[ፐ] ለማዳን የሚወድ
ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን
የሚያጠፋት ሁሉ ግን ያድናታል። 36ሰው ዓለሙ
ሁሉ የእርሱ ቢሆንና ነፍሱን ቢያጣ ምን
ይጠቀመዋል? 37ለመሆኑ፣ ሰው ለነፍሱ ምን
መተኪያ አለው? 38በዚህ ዘማዊና ኀጢአተኛ
ትውልድ መካከል በእኔና በቃሌ የሚያፍር
ሁሉ፣ የሰው ልጅም በአባቱ ግርማ፣ ከቅዱሳን
መላእክት ጋር ሲመጣ ያፍርበታል!።”

9 ቀጥሎም፣ “እውነት እላችኋለሁ፤ እዚህ
ከቆሙት መካከል የእግዚአብሔር መን
ግሥት በኀይል ስትመጣ እስከሚያዩ ድረስ
ሞትን የማይቀምሱ አንዳንዶች አሉ”
አላቸው።

### የኢየሱስ መልክ አበራ

9፥2-8 ተጓ ምብ - ሉቃ 9፥28-36
9፥2-13 ተጓ ምብ - ማቴ 17፥1-13

2ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስን፣
ያዕቆብንና ዮሐንስን አስከትሎ ወደ አንድ
ረጅም ተራራ ይዞአቸው ወጣ፤ ብቻቸውንም
ነበሩ፤ በፊታቸውም ተለወጠ፤ 3ልብሱም በም
ድር ላይ ማንም አጣቢ አጥቦ ሊያነጣው በማ
ይችልበት ሁናቴ እጅግ ነጭ ሆነ። 4ኤልያስና
ሙሴም ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው።
5ጴጥሮስም ኢየሱስን፣ “መምህር ሆይ፣
እዚህ ብንኖር ለእኛ መልካም ነው፤ አንድ
ለአንተ፣ አንድ ለሙሴ፣ አንድ ለኤልያስ
የሚሆኑ ሦስት ዳሶች እንሥራ” አለው።
6እጅግ ስለ ፈሩ የሚናገረውን አያውቅም ነበር።
7ከዚያም ደመና መጥቶ ጋረዳቸው፤ ከደ
መናውም ውስጥ፣ “ይህ የምወደው ልጄ
ነው፤ እርሱን ስሙት!” የሚል ድምፅ መጣ።
8ወዲያውም ዙሪያቸውን ሲመለከቱ ከኢ
የሱስ በቀር ማንም አብሮአቸው አልነበረም።
9ከተራራው ላይ በሚወርዱበትም ጊዜ፣ የሰው
ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ያዩትን ለማንም
እንዳይናገሩ አዘዛቸው። 10እነርሱም የተናገ
ራቸውን ቃል በልባቸው አሳደሩት፤ ነገር ግን፣
‘ከሙታን መነሣት’ ምን ማለት እንደ ሆነ
እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር።
11ከዚያም፣ “ጸሐፍት አስቀድሞ መምጣት
ያለበት ኤልያስ ነው ለምን ይላሉ?” ሲሉ
ጠየቁት።
12ኢየሱስም፣ እንዲህ አላቸው፤ “ኤልያስ
በርግጥ አስቀድሞ መጥቶ ሁሉን ነገር እንደ
ነበረ ያደርጋል፤ ታዲያ፣ የሰው ልጅ ብዙ
መከራ መቀበልና መናቅ እንዳለበት የተጻፈው
ለምን ይመስላችኋል? 13ነገር ግን እላችኋለሁ፤
ኤልያስማ መጥቶ ነበር፤ እነርሱም ስለ እርሱ
በተጻፈው መሠረት ያሻቸውን ሁሉ አድርገ

8፥35 ዮሐ12፥25
8፥38 ማቴ8፥20፤ 10፥33፤ሉቃ12፥9፤1 ተሰ2፥19
9፥1 ማቴ24፥30፤25፥31፤ ማር13፥30፤ ሉቃ22፥18
9፥2 ማቴ4፥21
9፥3 ማቴ28፥3
9፥5 ማቴ23፥7
9፥7 ዘፀ24፥16፤ ማቴ3፥17
9፥9 ማቴ8፥20፡30
9፥12 ማቴ8፥20፤ 16፥21፤ሉቃ23፥11
9፥13 ማቴ11፥14

ፐ35 የግሪኩ ቃል ሕይወት ወይም ነፍስ ማለት ይሆናል።

8፥35 *ነፍሱን ለማዳን፤* አንድ ሰው የኢየሱስን ቤዛነት አልቀበልም ቢል፣ በሥጋዊ ሕይወት ሊኖር ይችላል፤ የዘላለምን ሕይወት ግን አያገኛትም። በአንጻሩም አንድ ሰው ክርስቶስን በመከተሉ ሥጋዊ ሕይወቱን ያጣ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ሥጋዊ ሕይወቱን ማጣቱ ለዘላለም ከሚያገኘው ሕይወት ጋር ሲነጻጸር ቊጥር ውስጥ የሚገባ አይደለም።

8፥36 *ዓለሙ ሁሉ፤* በዚህ ዓለም በጥረት ወይም እንዲሁ በተፈጥሮ ሊገኝ የሚችለውን ሁሉ የሚያካትት ነው። *ነፍሱን፤* የዘላለሙን ሕይወት ማለት ነው (ቊ 37 ላይም ይህንኑ ትርጒም ይይዛል)።

8፥38 *በእኔና በቃሌ የሚያፍር፤* ከሮሜ 1፥16 ጋር ያነጻጽሩ፤ ክርስቶስን ከመከተልና እርሱን ከማስደሰት ይልቅ፣ “ዘማዊውና ኀጢአተኛው ትውልድ” ጋር በመመሳሰልና ይህንኑ ትውልድ በማስደሰት የሚኖር ሰው፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ስፍራ የለውም። *የሰው ልጅም፤* የ8፥31 ማብ ይመ። *በአባቱ ግርማ … ሲመጣ፤* 2ተሰ 1፥6-10 ይመ። ኢየሱስ በሰው ሁሉ ላይ ሊፈርድ በክብር ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ፣ ቀድሞ በምድር ላይ የደረሰበት የመናቅ፣ የመዋረድና የመገደል ሁኔታ ይለወጣል።

9፥1 *እውነት እላችኋለሁ፤* የ3፥28 ማብ ይመ። *የእግዚአብሔር መንግሥት፤* የማቴ 3፥2 ማብ ይመ። *የእግዚአብሔር መንግሥት በኀይል ስትመጣ እስከሚያዩ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ፤* የማቴ 16፥28 ማብ ይመ።

9፥2 *ከስድስት ቀን በኋላ፤* የማቴ 17፥1 ማብ ይመ። *ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን፤* የ5፥37 ማብ ይመ። *አንድ ረጅም ተራራ፤* የሉቃ 9፥28 ማብ ይመ። *ተለወጠ፤* የማቴ 17፥2 ማብ ይመ።

9፥4 *ኤልያስና ሙሴ፤* የማቴ 17፥3፤ ሉቃ 9፥30 ማብ ይመ።

9፥5 *ሦስት ዳሶች፤* ጴጥሮስ፣ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር እንደ ገና የሚገናኝበት አዳዲስ የመገናኛ ድንኳኖችን ለመሥራት አስቦ ሊሆን ይችላል (ዘፀ 29፥42 ይመ)፤ ወይም በዳስ በዓል ጊዜ ይጣል የነበረው ዳስ ትዝ ብሎት ሊሆን ይችላል (ዘሌ 23፥42)። ያም ሆነ ይህ፣ ኢየሱስ የማይቀር ነው ብሎ የተናገረው መከራ ከመድረሱ በፊት ያ የክብር ተስፋ ቃል ከወዲሁ እዲፈጸም ጴጥሮስ ሳይጓጓ አልቀረም።

9፥7 *ከደመናውም ውስጥ … ድምፅ መጣ፤* ደመና ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ለጥበቃና ለምሪት በሰዎች መካከል መገኘቱን የሚያመለክት ነው (ለምሳሌ ዘፀ 16፥10፤ 19፥9፤ 24፥15-18፤ 33፥9-10)። *እርሱን ስሙት፤* ሰፋ አድርገን ካየን፣ “ታዘዙት” የሚል ትርጒም ይጨምራል። እውነተኛው መስማት እግዚአብሔር ሲናገር ትእዛዙን ሰምቶ መታዘዝ ነው (ያዕ 1፥22-25 ይመ)።

9፥9 *የሰው ልጅ፤* የ8፥31 ማብ ይመ። *ለማንም እንዳይናገሩ፤* የማቴ 8፥4፤ 16፥20 ማብ ይመ። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ መሲሕነቱንና ያደረገውን ታምራት ለተገኘው ሰው ሁሉ መንዛት ብዙ መዘዝ ነበረው፤ ተልእኮውን ፈጽሞ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ግን፣ የሠራው ሥራ እውነተኛ መሲሕነቱንና ባሕርይውን የሚገልጽ በመሆኑ ደቀ መዛሙርቱ ይህን የምሥራች ለሰው ሁሉ መናገር ነበረባቸው።

9፥10 *“ከሙታን መነሣት” ምን ማለት እንደ ሆነ፤* አይሁድ እንደ መሆናቸው መጠን የትንሣኤ ሙታን ትምህርት ለእነርሱ እንግዳ አልነበረም። የእነርሱ ትምህርተ መለኮት ዕውቀት ስለሚሠቃየውና ሞቶ ስለሚነሣው መሲሕ የሚገልጸው ነገር ባለመኖሩ፣ የሰው ልጅ ከሙታን ይነሣል የሚለው ሐሳብ ግራ አጋብቶአቸዋል።

9፥11 *አስቀድሞ መምጣት ያለበት ኤልያስ ነው፤* የማቴ 17፥10 ማብ ይመ።

9፥12 *ኤልያስ በእርግጥ አስቀድሞ መጥቶ ሁሉን ነገር እንደ ነበረ ያደርጋል፤* መሲሑ በሚመጣበት ጊዜ የመሲሑን መንገድ ስለሚያዘጋጀው ኤልያስ ወይም እንደ ኤልያስ ያለ ሌላ ሰው እንደሚመጣ መናገሩ ነው (የማቴ 17፥10 ማብ ይመ)። *የሰው ልጅ፤* የ8፥31 ማብ ይመ። *ብዙ መከራ መቀበልና መናቅ እንዳለበት፤* “ኤልያስ” የተባለው መጥምቁ ዮሐንስ (የቊ 13 ማብ ይመ) ተቀባይነት እንዳጣ ሁሉ፣ የሰው ልጅም እንዲሁ ይናቃል (የማቴ 17፥12 ማብ ይመ)።

9፥13 *ኤልያስማ መጥቶ ነበር፤* መጥምቁ ዮሐንስ ነው (ማቴ 17፥13 ይመ)። *እነርሱም፤* ሄሮድስንና ሄሮድያዳን ነው (6፥17-29 ይመ)። ዮሐንስም እንደ ኤልያስ ሁሉ ደካማ ከሆነ አገረ ገዥና ክፉ ከሆነችው ከገዥው ሚስት ተቃውሞ ገጥሞት ነበር። *ስለ እርሱ በተጻፈው መሠረት፤* መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያመለክተው ሁሉ አክዓብና ኤልዛቤል በኤልያስ ላይ ያደረሱበትን ስደት ለማለት ነው (1ነገ 19፥1-10)። በመጨረሻው ዘመን በኤልያስ አገልግሎት ላይ ስለሚደርስ መከራ የተነገረ ትንቢት የለም፤ ይሁን እንጂ ኤልዛቤል በኤልያስ ላይ ያደረሰችው ስደት በዮሐንስ ላይ የሚደርሰውን መከራ የሚያመለክት ነበር። በቊ 11-13 ላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች እንዲህ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ይቻላል፤ (1) ኤልያስ ክፉ በሆነችው በኤልዛቤል ዘመን አገለገለ፤ (2) በኤልያስ ምሳሌ የመጣው መጥምቁ ዮሐንስም በተመሳሳይ መንገድ በሄሮድያዳ እጅ መከራ ተቀበለ፤ (3) መጥምቁ ዮሐንስ ዐንገቱን እንደ ተቈረጠ፣ ወዲያው የሰው ልጅ መከራን መቀበል ጀመረ፤ ሰዎችም አልተቀበሉትም።

ውብታል::"

## ርኩስ መንፈስ ያለበት ልጅ ተፈወሰ

9፥14-28፤30፥32 ተጓ ምብ - ማቴ 17፥14-19፤ 22:23፤
ሉቃ9፥37-45

14ወደ ቀሩት ደቀ መዛሙርት ተመልሰው
ሲመጡ፣ ብዙ ሕዝብ ከበዋቸው፣ ጸሐፍት
ከእነርሱ ጋር ሲከራከሩ አዩ:: 15ሕዝቡ ሁሉ
ሲያዩት ወዲያው ተደንቀው እጅ ሊነሡት
ወደ እርሱ ሮጡ::
16እርሱም፣ "ከእነርሱ ጋር የምትከራከሩት
ስለምን ጕዳይ ነበር" ሲል ጠየቃቸው::
17ከሕዝቡ መካከል አንድ ሰው እንዲህ
አለው፤ "መምህር ሆይ፤ ርኩስ መንፈስ አድ
ሮበት ዲዳ የሆነውን ልጄን ወደ አንተ አምጥ
ቼዋለሁ፤ 18በተነሣበት ጊዜ ሁሉ ይጥለዋል፤
አረፋ ይደፍቃል፤ ጥርሱንም ያፋጫል፤ ሰውነ
ቱም ይደርቃል፤ ርኩስ መንፈሱን እንዲ
ያስወጡት ደቀ መዛሙርትህን ጠየቅኋቸው፤
እነርሱ ግን አልቻሉም::"
19ኢየሱስም መልሶ፣ "የማታምን ትውልድ
ሆይ፤ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ?
እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? ልጁን ወደ እኔ
አምጡት!" አላቸው::
20ሰዎቹም ወደ እርሱ አመጡት፤ ርኩስ
መንፈሱም ኢየሱስን ባየው ጊዜ ልጁን ወዲ
ያውኑ አንዘፈዘፈው፤ እርሱም መሬት ላይ
ወድቆ በመንፈራገጥም አረፋ ይደፍቅ ጀመር::
21ኢየሱስም የልጁን አባት፣ "ከያዘው ስንት
ጊዜው ነው?" ብሎ ጠየቀው::
እርሱም እንዲህ አለው፤ "ከሕፃንነቱ ጀምሮ
ነው፤ 22ሊገድለው ፈልጎ ብዙ ጊዜ እሳትም
ውስጥ ውሃም ውስጥ፣ ይጥለዋል፤ የሚቻልህ
ከሆነ ራራልን፤ ርዳንም::"
23ኢየሱስም፣ "የሚቻልህ ከሆነ አልህ?
ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ይቻላል" አለው::
24ወዲያውኑ የልጁ አባት፣ "አምናለሁ፤
አለማመኔን ርዳው!" በማለት ጮኸ:: 25ኢ
የሱስም ሕዝቡ ወደዚያ እየተንጋጋ በሩጫ
መምጣቱን ባየ ጊዜ፣ "አንተ ደንቈሮና ዲዳ
መንፈስ ከእርሱ ውጣ! ከእንግዲህም ተመ
ልሰህ እንዳትገባበት አዝሃለሁ!" ብሎ
ርኩሱን[r] መንፈስ ገሠጸው::
26ርኩሱም መንፈስ እየጮኸ ክፉኛ ካንፈ
ራገጠው በኋላ ከልጁ ወጣ፤ ብዙዎቹ! "ሞቶ
አል" እስኪሉ ድረስ ልጁ እንደ በድን ሆነ::
27ኢየሱስ ግን እጁን ይዞ አስነሣው፤ ልጁም
ተነሥቶ ቆመ::
28ኢየሱስ ወደ ቤት ከገባ በኋላ ደቀ መዛ
ሙርቱ ለብቻቸው፣ "እኛ ልናስወጣው ያልቻል
ነው ለምንድን ነው?" ብለው ጠየቁት::
29እርሱም፣ "የዚህ ዐይነቱ ሊወጣ የሚች
ለው በጸሎትና በጾም[x] ብቻ ነው" አላቸው::
30ከዚያም ተነሥተው በገሊላ በኩል አለፉ፤
ኢየሱስም ያሉበትን ስፍራ ማንም እንዲያውቅ
አልፈለገም፤ 31ለደቀ መዛሙርቱ፣ "የሰው
ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጣል፤ እነርሱም
ይገድሉታል፤ ከሦስት ቀንም በኋላ ይነሣል"
እያለ ያስተምራቸው ነበር:: 32እነርሱ ግን የሚላ
ቸው አልገባቸውም፤ እንዳይጠይቁትም ፈሩ::

## ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?

9፥33-37 ተጓ ምብ - ማቴ 18፥1-5፤
ሉቃ 9፥46-48

33ከዚህ በኋላ ወደ ቅፍርናሆም መጡ:: ቤት
ከገባ በኋላም፣ "በመንገድ ላይ የምትከራከሩት
ስለ ምን ነበር?" ብሎ ጠየቃቸው:: 34እነርሱ
ግን በመንገድ ላይ የተከራከሩት ከሁሉ የሚበልጥ
ማን ነው በሚል ስለ ነበር ዝም አሉ::
35ከተቀመጠ በኋላ ዐሥራ ሁለቱን ጠርቶ፣
"መጀመሪያ ለመሆን የሚፈልግ፣ ከሁሉ መጨ
ረሻና የሁሉም አገልጋይ ይሁን" አላቸው::
36ትንሽ ልጅ አምጥቶም በመካከላቸው
አቆመ፤ አቅፎትም፣ 37"ከእነዚህ ሕፃናት አንዱን
በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል፤ እኔ
ንም የሚቀበለኝ ሁሉ የሚቀበለው እኔን
ሳይሆን የላከኝን ነው" አላቸው::

## የማይቃወመን ሁሉ ከእኛ ጋር ነው

9፥38-40 ተጓ ምብ - ሉቃ 9፥49:50

38ዮሐንስም፣ "መምህር ሆይ፤ አንድ ሰው
በስምህ አጋንንት ሲያወጣ አየን፣ እኛን
ስለማይከተልም ከለከልነው" አለው::

[r]25 ወይም ክፉ
[x]29 አንዳንድ ቅጆች በጾም የሚለው የላቸውም

9፥20 ማር1፥26
9፥23 ማቴ21፥21፤ ማር11፥23፤ ዮሐ11፥40
9፥25 ቊ15
9፥28 ማር7፥17
9፥31 ቊ12፤ ማቴ8፥20፤16፥21፤ ሐሥ2፥23፤3፥13
9፥32 ሉቃ2፥50፤9፥45፤ 18፥34፤ዮሐ12፥16
9፥33 ማቴ4፥13፤ ማር1፥29
9፥34 ሉቃ22፥24
9፥35 ማቴ18፥4፤ ማር10፥43፤ሉቃ22፥26
9፥36 ማር10፥16
9፥37 ማቴ10፥40
9፥38 ዘኍ11፥27:29

9፥14 *ወደ ቀሩት ደቀ መዛሙርት፤* ከጴጥሮስ፣ ከያዕቆብና ከዮሐንስ ሌላ ዘጠኙን ደቀ መዛሙርት ማለት ነው (ቊ2 ይመ)::

*9፥18፤* ልጁ እንደዚያ ይሠቃይ የነበረው በርኩስ መንፈስ ምክንያት ነበር (ቊ 20:25-26 ይመ)::

9፥22 *ሊገድለው ፈልጎ፤* የ5፥5:13 ማብ ይመ::

9፥23 *የሚቻልህ ከሆነ አልህ? ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ይቻላል፤* ጥያቄው ኢየሱስ ልጁን የማዳን ኀይል አለው ወይም የለውም ሳይሆን፣ አባትየው ኢየሱስ ልጁን ሊያድነው የሚችል መሆኑን ማመኑ ላይ ነው:: እውነተኛ እምነት ያለው ሰው፣ የእግዚአብሔርን ችሎታ አይወስንም::

9፥24 *አምናለሁ፤ አለማመኔን ርዳው!* እምነት ፍጹም ሊሆን ስለማይችል፣ ከጥርጥር ነጻ የሆነ እምነት አይኖርም::

9፥25 *ሕዝቡ ወደዚያ እየተንጋጋ በሩጫ መምጣቱን ባየ ጊዜ ... ርኩሱን መንፈስ ገሠጸው፤* ኢየሱስ በተቻለው መጠን በዚህ ጊዜ ዝናው እንዲወጣ አልፈለገም::

9፥29 *የዚህ ዐይነቱ፤* የተለያዩ የአጋንንት ዐይነቶች መኖራቸውን የሚያመለክት ይመስላል:: *በጸሎት ... ብቻ፤* ደቀ መዛሙርት የተሰጣቸውን ኀይል ምን ጊዜም የሚያዙበትና ከእነርሱ እንደ ሆነ አድርገው ሳይቈጥሩ አልቀሩም፤ ጸሎት አለማድረጋቸውም በአጋንንት ላይ የተሰጣቸው ሥልጣን ከኢየሱስ የተገኘ መሆኑን የዘነጉ ያስመስላል (3፥15፤ 6፥7:13 ይመ)

9፥30 *በገሊላ በኩል አለፉ፤* ኢየሱስ በገሊላና በአካባቢዋ የነበረውን አገልግሎቱን በማጠናቀቁ (የ7፥24 ማብ ይመ)፣ በዚህ ጊዜ መከራን ለመቀበልና መሥዋዕት ለመሆን ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ (10፥32-34 ይመ):: ለብዙ ወራት ሲያደርግ እንደ ነበረው ሁሉ፣ ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ማስተማሩን ቀጠለ (ቊ 31)::

9፥31 *የሰው ልጅ፤* የ8፥31 ማብ ይመ::

9፥32 *አልገባቸውም፤* ቊ 10፤ 8፥32-33 ይመ::

9፥33 *ቅፍርናሆም፤* የ1፥21፤ ማቴ 4፥13 ማብ ይመ:: *ቤት፤* ምናልባት የጴጥሮስና የእንድርያስ መኖሪያ ቤት ሳይሆን አይቀርም (1፥29 ይመ)::

9፥34 *ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው፤* በዚያን ዘመን በነበረው የአይሁድ ኅብረተ ሰብ፣ ስለ ክብርና ማዕረግ ጕዳይ መነጋገር የተለመደ ነበር፤ በኢየሱስ አመለካከት ግን የዚህ ዐይነቱ ጕዳይ ስፍራ የለውም (ቊ 35፤ 10፥42- 45 ይመ):: *ዝም አሉ፤* ከማፈራቸው የተነሣ መሆኑ አያጠራጥርም::

9፥35 *ከተቀመጠ በኋላ፤* የ4፥1 ማብ ይመ::

9፥38 *ከእኛ ጋር ስለማይከተልህ፤* ሰውየው አማኝ መሆኑ ብዙ

39ኢየሱስ ግን እንዲህ አለ፤ "አትከልክ
ሉት፤ ማንም በስሜ ታምር ሠርቶ ወዲያውኑ
በእኔ ላይ ክፉ መናገር አይችልም፤ 40የማይ
ቃወመን ሁሉ ከእኛ ጋር ነውና፤ 41እውነት
እላችኋለሁ፣ የክርስቶስ በመሆናችሁ በስሜ
አንድ ኩባያ ውሃ የሚሰጣችሁ ሁሉ ዋጋውን
አያጣም::"

## ለሌላው መሰናክል መሆን

42"በእኔ ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናና
ሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ ከባድ የወፍጮ
ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል
ይሻለዋል:: 43ስለዚህ እጅህ ብታሰናክልህ ቍረ
ጣት፤ ሁለት እጅ ኖሮህ ወደ ገሃነም ከመሄድ፣
ጕንድሽ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል፤
44በገሃነም ትሉ አይሞትም፤ እሳቱ አይጠ
ፋምና[፳]:: 45እግርህ ብታሰናክልህ ቍረጣት፤
ሁለት እግር ኖሮህ ወደ ገሃነም ከመጣል፣
አንካሳ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል፤
46በገሃነም ትሉ አይሞትም እሳቱ አይጠ
ፋምና[፳]:: 47ዐይንህ ብታሰናክልህ ጐልጕለህ
አውጣት፤ ሁለት ዐይን ኖሮህ ወደ ገሃነም
ከመጣል፣ አንድ ዐይን ኖሮህ ወደ እግዚአብሔር
መንግሥት መግባት ይሻልሃል፤

48በገሃነም ትሉ አይሞትም፤
 እሳቱ አይጠፋምና፤
 49ሰው ሁሉ በእሳት ይቀመማልና::

9፥40 ማቴ12፥30፤ ሉቃ11፥23
9፥41 ማቴ10፥42
9፥42 ማቴ5፥29፤ 18፥6፤ሉቃ17፥2
9፥43 ማቴ5፥29፡ 30፤18፥8፤25፥41
9፥45 ማቴ5፥29፤ 18፥8
9፥47 ማቴ5፥29፤ 18፥9
9፥48 ኢሳ66፥24፤ ማቴ25፥41
9፥49 ዘሌ2፥13
9፥50 ማቴ5፥13፤ ሉቃ14፥34፡35፤ ሮሜ12፥18፤ 2ቆሮ13፥11፤ ቈላ4፥6፤1ተሰ5፥13
10፥1 ማቴ4፥23፤ ማር1፥15፤2፥13፤ 4፥2፤6፥6፡34፤ ዮሐ10፥40፤11፥7
10፥2 ማር2፥16
10፥4 ዘዳ24፥1-4፤ ማቴ5፥31
10፥5 መዝ95፥8፤ ዕብ3፥15
10፥6 ዘፍ1፥27፤ 5፥2

50"ጨው መልካም ነው፤ ነገር ግን ጨው
ጨውነቱን ቢያጣ እንዴት መልሳችሁ ጣዕም
እንዲኖረው ታደርጉታላችሁ? ጨው በውስጣችሁ
ይኑራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም ተስማሙ::"

## የባልና የሚስት ፍች

10፥1-12 ተጓ ምብ - ማቴ19፥1-9

10ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ ወደ ይሁዳ
አገርና በዮርዳኖስ ማዶ ወዳለው
አካባቢ ሄደ፤ ሕዝቡም እንደ ገና በዙሪያው
ተሰበሰበ፤ ከዚህ ቀደም ያደርገው እንደ ነበ
ረውም አስተማራቸው::
2አንዳንድ ፈሪሳውያንም መጥተው፣ "ሰው
ሚስቱን መፍታት ይገባዋልን?" ብለው ሊፈ
ትኑት ጠየቁት::
3እርሱም መልሶ፣ "ሙሴ ምን ብሎ አዘዛ
ችሁ?" አላቸው::
4እነርሱም፣ "ሙሴማ የፍች ወረቀት ጽፎ
እንዲፈታት ፈቅዶአል" አሉ::
5ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ "ሙሴ
ይህን ሕግ የጻፈላችሁ ልባችሁ ደንዳና በመ
ሆኑ ነው:: 6ነገር ግን በፍጥረት መጀመሪያ
እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራ
ቸው:: 7ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን
ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣመራል[ን]፤

[፳]44 እና 46 እነዚህ ጥቅሶች በአንዳንድ ቅጆች አይገኙም::
[ን]7 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ከሚስቱ ጋር ይጣመራል* የሚለው የላቸውም::

አያጠራጥርም፤ ይሁን እንጂ ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት አንዱ አል ነበረም:: ነገር ግን ደቀ መዛሙርቱ ቢያቅቱ በአንድ ወቅት ማድረግ የተሳ ናቸውን (ቍ 14-18፡28 ይመ) እርሱ በኢየሱስ ስም ማድረግ ችሎአል::

9፥39 *አትከልክሉት፤* ኢየሱስ ስለ ደቀ መዝሙርነት ያለው አመለካከት ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ጠባብ አመለካከት የላቀና የሰፋ ነበር::

9፥41 *እውነት እላችኋለሁ፤* የ3፥28 ማብ ይመ:: *አንድ ኩባያ ውሃ የሚሰጣችሁ፤* አማኞች በመሆናቸው ብቻ ለአማኞች የምናደርግላቸውን አነስተኛውን ነገር እንኳ እግዚአብሔር አይረሳውም:: *ዋጋውን፤* በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትንም ይጨምራል::

9፥42 *በእኔ ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱን፤* በቍ 36-37 የተጠቀሱትን ሕፃናት ወይም በቍ 38 ላይ የተጠቀሰውን ሰው ሊሆን ይችላል:: እዚህ ላይ ጌታ ለማስገንዘብ የፈለገው ጕዳይ ግልጽ ነው፤ በእኛ አመለካከት ቦታ የማይሰጣቸው አማኞች በእኛ ምክንያት ወደ ኀጢአት ቢገቡ፣ የከፋ ቅጣት ይጠብቀናል:: *የወፍጮ ድንጋይ፤* ጠፍጣፋና ከባድ የእህል መፍጫ ድንጋይ ሲሆን፣ በአንዳንድ አገሮች የሚንቀሳቀሰው በከብት ጕልበት ነው::

9፥43 *ቍረጣት፤* ነገሩን አጋኖ ለማቅረብ የገባ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው እንጂ በጥሬ ትርጕሙ የሚታይ አይደለም፤ እዚህ ላይ የገባውም ቍርጠኛ ውሳኔ ማድረግ የቱን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ ለማሳየት ነው:: *ገሃነም፤* የማቴ 5፥22 ማብ ይመ:: *ሕይወት፤* ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖሩት ዘላለማዊ ሕይወት ነው::

9፥47 *ወደ እግዚአብሔር መንግሥት፤* የማቴ 3፥2 ማብ ይመ::

*9፥48፤* ኢሳ 66፥24 በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ስለሚያስከትለው ቅጣት ይናገራል፤ ይህ የኢሳይያስ ትንቢት የመጨረሻው ቃል የዘላለም ቅጣት ምን እንደሚመስል የሚያመለክት ሆኖአል:: *ትሉ አይሞትም፤* የማቴ 5፥22 ማብ ይመ፤ በቈሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታ ትሎች ምንጊዜም አይጠፉም::

*9፥49፤* ይህ ሐሳብ በሁለት መልክ ሊታይ ይችላል፤ (1) በማቴ 3፥11 ላይ እንደተመለከተው በእሳት የተመሰለው መንፈስ ቅዱስ በምእመን ሕይወት ውስጥ የሚሠራውን ሊያመለክት ይችላል:: (2) ክርስቲያን ሁሉ በዚህ ዓለም በመከራ እሳት ውስጥ እያለፈ መንጻት እንዳለበት የሚያሞለክት ሊሆን ይችላል::

9፥50 *ጨው መልካም ነው፤* በጨው የተመሰለው የደቀ መዝሙርነት ዐይነተኛ መለያ ለኢየሱስና ለወንጌሉ ታማኝ ሆኖ መገኘትን ነው (8፥35፡38 ይመ፤ እንዲሁም የማቴ 5፥13 ማብ ይመ):: *እርስ በርሳችሁም ተስማሙ፤* ለኢየሱስና ለወንጌሉ ያለንን የጋራ ተልእኮ በምናስተውልበት ጊዜ፣ ግጭት ከመካከላችን ተወግዶ ሰላም ይሰፍናል::

10፥1 *ወደ ይሁዳ አገር፤* በብሉይ ኪዳን ዘመን የይሁዳ ምድር ይባል ለነበረው ግሪኮችና ሮማውያን የሰጡት ስም ነው:: ይህም በፓሌስቲና ምድር፣ በደቡቡ የእስራኤል መንግሥት ውስጥ ይገኝ የነበረ ነው:: ኢየሱስ በይሁዳ አውራጃ ስላደረገው አገልግሎት የሉቃ 9፥51 ማብ ይመ:: *በዮርዳኖስ፤* የ 1፥5 ማብ ይመ:: ኢየሱስ በዚህ ጊዜ የተጓዘው ከቅፍርናሆም በስተ ደቡብ አድርጎ፣ በሰማርያ ተራሮች አልፎ ወደ ይሁዳ አገር በመግባት ነው፤ ከዚያም ዮርዳኖስን ተሻግሮ ወደ ምሥራቅ በመሄድ የሄሮድስ አንቲጳስ ግዛት ወደ ሆነችው ወደ ፓርያ ዘለቀ (የማቴ 14፥1 ማብ ይመ):: ኢየሱስ በፓርያ ስላደረገው አገልግሎት የሉቃ 13፥22 ማብ ይመ::

10፥2 *ፈሪሳውያን፤* የ2፥16 ማብ ይመ:: *መጥተው ... ሊፈትኑት፤* የፈሪሳውያኑ ጥያቄ ተንኰል ያዘለ ነበር:: መጥምቁ ዮሐንስም ሄሮድስ አንቲጳስንና ሄሮድያዳን የገሠጻቸው በሕገ ወጥ ፍችና ሁለተኛ ጋብቻ ምክንያት ነበር (6፥17-18 ይመ)፤ በዚህ ተግሣጽ ምክንያት መጀመሪያ እስራት፣ ከዚያም ሕይወቱን አጥቶአል:: ኢየሱስም በዚህ ጊዜ ይገኝ የነበረው በሄሮድስ ግዛት ውስጥ ስለ ነበር ፈሪሳውያን ይህን ጥያቄ ያቀረቡለት፣ በሚሰጣቸው መልስ እንዲስትና ሄሮድስ መጥምቁ ዮሐንስን እንደ ያዘው እርሱንም ለማስያዝ አስበው ሳይሆን አይቀርም:: *ሰው ሚስቱን መፍታት ይገባዋልን?* በዚያን ዘመን የነበሩ አይሁድ፣ ፍች ሕጋዊ ነው ብለው ያምኑ ነበር፤ አከራካሪ የሚሆነው ግን ለፍች የሚያበቃው ምክንያት ምን መሆን አለበት የሚል ነበር (የማቴ 19፥3 ማብ ይመ)::

10፥5 *ልባችሁ ደንዳና በመሆኑ ነው፤* በቍ 6-9 ላይ ያለው ክፍል በግልጽ እንደሚያሳየው፣ ፍቺ በመሠረቱ የእግዚአብሔር ዕቅድ አልነበረም፤ ሆኖም የሰውን ድካም ለማገዝና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በማይመላለስ ኅብረተ ሰብ ውስጥ ሥርዐት ለማስፈን ሲባል ሕግ ወጥቶለት ነበር:: የዘዳ 24፥1 ዐላማ ፍች የሚያመጣውን መዘዝ ለማርገብ እንጂ ፍችን ሕጋዊ ለማድረግ አልነበረም::

10፥6 *በፍጥረት መጀመሪያ፤* ኢየሱስ የእግዚአብሔርን የመጀመሪያ ዕቅድ ለማሳየት ሲል፣ ሰው በኀጢአት ከመውደቁ በፊት ወደ ነበረው ሁኔታ አመለከተ:: እግዚአብሔር ወንድና ሴትን በፍጥረት ጊዜ በማስተሳሰር ጋብቻን ታላቅ የአንድነት በረከት አድርጎ መሠረተው::

8ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤ ከእንግዲህ አንድ
ሥጋ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም፤ 9ስለዚህ
እግዚአብሔር ያጣመረውን ማንም አይለየው።”
10እንደ ገና ወደ ቤት በገቡ ጊዜ፣ ደቀ መዛሙ
ርቱ ይህንኑ አንሥተው ጠየቁት። 11እርሱም፣
“ማንም ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ
በእርሷ ላይ ያመነዝራል፤ 12እርሷም ባሏን ፈትታ
ሌላ ብታገባ ታመነዝራለች” አላቸው።

## ኢየሱስ ሕፃናትን ባረከ

10፥13-16 ተጓ ምብ - ማቴ 19፥13-15፤ ሉቃ18፥15-17

13ኢየሱስ እንዲዳስሳቸው፣ ሰዎች ሕፃናትን
ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን
ገሠጿቸው። 14ኢየሱስም ይህን ሲያይ ተቈጥቶ
እንዲህ አላቸው፤ “ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ፤
አትከልክሏቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ
እነዚህ ላሉት ናትና። 15እውነት እላችኋለሁ፤
የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይ
ቀበል ሁሉ ከቶ አይገባባትም። 16ሕፃናቱንም
አቀፋቸው፤ እጁንም ጭኖ ባረካቸው።

## ሀብታሙ ወጣት

10፥17-31 ተጓ ምብ - ማቴ19፥16-30፤ ሉቃ18፥18-30

17ከዚያ ተነሥቶ መንገዱን ሲጀምር፣ አንድ
ሰው ወደ እርሱ እየሮጠ መጣ፤ በፊቱም
በጒልበቱ ተንበርክኮ፣ “ቸር መምህር ሆይ፤
የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ
ይገባኛል” አለው።
18ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ “ለምን
ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስ
ተቀር ቸር የለም፤ 19ትእዛዛትን ታውቃለህ፤
አትግደል፤ አታመንዝር፤ አትስረቅ፤ በሐሰት
አትመስክር፤ አታታልል፤ አባትህንና እናትህን
አክብር።”
20ሰውየውም፣ “መምህር ሆይ፤ እነዚህን
ሁሉ ከልጅነቴ ጀምሮ ጠብቄአለሁ” አለው።
21ኢየሱስም ተመለከተውና ወደደው፤ ‘እንግዲ
ያው አንድ ነገር ይጐድልሃል፤ ሂድና ያለህን
ሁሉ ሽጥ፤ ለድኾችም ስጥ፤ በሰማይ የተከ
ማቸ ሀብት ታገኛለህ፤ ከዚያ በኋላ ና፤ ተከተ
ለኝም” አለው።
22ሰውየው ይህን ሲሰማ ክፉኛ አዘነ፤ ብዙ
ሀብት ስለ ነበረውም እየተከዘ ሄደ።
23ኢየሱስ ዙሪያውን በመመልከት ደቀ
መዛሙርቱን፣ “ለሀብታሞች ወደ እግዚአብሔር
መንግሥት መግባት እንዴት ከባድ ነገር
ነው!” አላቸው።
24ደቀ መዛሙርቱም በንግግሩ ተገረሙ፤ ኢየ
ሱስ ግን እንደ ገና መልሶ እንዲህ አላቸው፤
“ልጆች ሆይ[m]፤ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት

10፥8 ዘፍ2፥24፤ 1ቆሮ6፥16
10፥11 ሉቃ16፥18
10፥12 ሮሜ 7፥3፤1ቆሮ7፥10:11
10፥14 ማቴ25፥34
10፥15 ማቴ18፥3
10፥16 ማር9፥36
10፥17 ማር1፥40፤ ሉቃ10፥25፤ ሐሥ20፥32
10፥19 ዘጸ20፥12-16፤ዘዳ5፥16-20
10፥21 ማቴ4፥19፤ 6፥20፤ሉቃ12፥33፤ ሐሥ2፥45
10፥23 መዝ52፥7፤ 62፥10፤ማር4፥19፤ 1ጢሞ6፥9:10:17
10፥24 ማቴ7፥13፤ ዮሐ3፥5

[m]24 አንዳንድ ቅጆች *በሀብት ለሚታመኑ* የሚል ሐረግ አላቸው።

10፥8 *ከእንግዲህ አንድ ... እንጂ ሁለት አይደሉም፤* ኢየሱስ ስለ ጋብቻ ከሥር መሠረቱ አንሥቶ በማስረዳት ባልና ሚስት አንድ ሥጋ ናቸው ወደሚለው መደምደሚያ መድረሱ፣ የጋብቻ ዐላማ በመሠረቱ በቋሚነት የሚያስተሳስር እንዲሆን የታቀደ መሆኑን ያረጋግጥልናል።

10፥9 *ስለዚህ እግዚአብሔር ያቀናጀውን፤* ኢየሱስ የጋብቻን ቅዱስነት ከእግዚአብሔር ሥልጣን ጋር ያያይዛል፤ ደግሞም ፍችን መከልከሉ ሰዎች ራስ ወዳዶች እንደ መሆናቸው፣ ጋብቻ በእነርሱ ምክንያት እንዳይጠፋ ለመጠበቅ ነው።

10፥11 *ማንም ሚስቱን ፈትቶ፤* በአይሁድ ልማድ ፍች ይፈጸም የነበረው በዳኛ ፊት ወይም በፍርድ ቤት ሥልጣን ሳይሆን፣ በራሱ በባልየው ፈቃድ ነበር። *በእርሷ ላይ ያመነዝራል፤* አንድ ሰው ሚስቱን ፈትቻለሁ ስላለ ከአምላካዊና ከግብረ ገባዊ የጋብቻ ሕግ ነጻ ይሆናል ማለት አይደለም፤ ይህ ጋብቻን ለዘለቄታው የሚያጸናው ኀይል በአይሁድ መምህራን ሸንጎ ዘንድ የሚታወቅ አልነበረም። ይሁን እንጂ የማቴ 19፥3 ማብ ይመ፤ በተጨማሪም በተለየ ምክንያት ፍች የተፈቀደበት የሚመስለውን ማቴ 19፥9 ይመ። በ1ቆሮ 7፥15 ላይ ያለውም ሐሳብ በልዩ ምክንያት ፍችን የሚደግፍ ይመስላል (የ1ቆሮ 7፥12:15 ማብ ይመ)።

10፥12 *ታመነዝራለች፤* ከዐውዱ ሁኔታ ጋር ሲገናዘብ፣ ኢየሱስ የተናገረው መጥመቁ ዮሐንስ ፊት ለፊት ለንጉሥ ሄሮድስ አንቲጳስና ለሄሮድያዳ የተናገረውን የሚደግፍ ነው።

10፥14 *የእግዚአብሔር መንግሥት፤* የማቴ 3፥2 ማብ ይመ። *እንደ እነዚህ ላሉት ናትና፤* የእግዚአብሔር መንግሥት ከእግዚአብሔር የተሰጠች ስጦታ ስለ ሆነች፣ እንደ ሕፃናት በየዋህነት ለሚቀበሏት የተገባች ናት።

10፥15 *እውነት እላችኋለሁ፤* የ3፥28 ማብ ይመ። *እንደ ሕፃን፤* እንደ ሕፃን የተባለበት ምክንያት፣ ሕፃናት ገሮችና የሚነገራቸውን ሁሉ የሚቀበሉ በመሆናቸው ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት በራስ ጥረት የምትገኝ ባለመሆኗ፣ እንደ ነጻ ስጦታ ልንቀበላት ይገባል። ወደ እርሷ የሚገቡትም ደካማ መሆናቸውን ያወቁና በበጎ ሥራቸው የማይመኩ ናቸው።

10፥16 *ባረካቸው፤* ኢየሱስ ልበ ንጹሓን ለሆኑ ሕጻናት ያለውን ፍቅር ገለጸ፤ እንደ እነርሱ ያሉትንም እንደዚሁ ይባርካል (ከማቴ 5፥3-10 ጋር ያነጻጽሩ)።

10፥17 *አንድ ሰው፤* ማርቆስ የሰውየውን ማንነት አይገልጽም፤ ሉቃስ (18፥18) ግን ‘ከአለቆች’ ይለዋል፤ በዚህም ከምክር ቤት ወይም ከሸንጎ አባላት አንዱ ነበር ማለት ይቻላል። ማቴዎስ ግን (19፥20) ‘ወጣት’ ብሎታል። *የዘላለምን ሕይወት፤* የማቴ 19፥16 ማብ ይመ። *ምን ማድረግ ይገባኛል?፤* ሀብታሙ ሰው የዘላለምን ሕይወት በጽድቅ ሥራው ለማግኘት አስቦ ነበር፤ ኢየሱስ ግን የዘላለም ሕይወት እንዲሁ በእምነት ሊቀበሉት የሚገባ ስጦታ መሆኑን አስተማረ (ቍ 15 ይመ)።

10፥18 *ለምን ቸር ትለኛለህ?* ኢየሱስ እንዲህ ያለው ቸር አይደለሁም ለማለት ሳይሆን፣ ሰውየው የዘላለምን ሕይወት እን ዲሁ በሚሰጠው በእግዚአብሔር ላይ ብቻ መታመን እንዳለበት ለማሳየት ነው። በሌላም በኩል ሰውየው የሚነጋገረው ከማን ጋር እንደ ሆነ እንዲያስተውል ሊሆን ይችላል።

10፥19 *አታታልል፤* ይህኛው ትእዛዝ ከዐሥርቱ ትእዛዛት መካከል፣ “አትመኝ” የሚለውን የመጨረሻውን ትእዛዝ ሳያመለክት አይቀርም። እንዲህ ከሆነም ኢየሱስ ከዐሥርቱ ትእዛዛት በባልንጀራ ላይ ክፉ ማድረግን፣ ወይም ክፉ ማሰብን የሚከለክሉትን ስድስቱን ይጠቅሳል (ዘፀ 20፥12-16፤ ዘዳ 5፥16-21፤ ይመ)።

10፥20 *እነዚህን ሁሉ ... ጠብቄአለሁ፤* ሰውየው፣ “ጠብቄ አለሁ” ሲል ከልቡ ነበር፤ ምክንያቱም ለእርሱ ሕግን መጠበቅ ማለት ውጫዊ ሥርዐትን ጠብቆ መገኘት ማለት ብቻ ነበር። ስለዚህ ሕግን መጠበቅ ሲባል፣ ማንም ሙሉ በሙሉ ሊፈጽመው የማይ ችለውን የልብ መታዘዝ የሚጠይቅ መሆኑን ጨርሶ ልብ አላለም። ጳውሎስም በክርስቶስ ከማመኑ በፊት የዚህ ዐይነት አመለካከት እንደ ነበረው ይናገራል (ፊል 3፥6)። *ከልጅነቴ ጀምሮ፤* አንድ አይሁዳዊ ሕጋትን ማክበር የሚጠበቅበት ከ13 ዓመቱ ጀምሮ ስለ ነበር ይህንኑ ለማመልከት ሳይናገር አልቀረም።

10፥21 *ኢየሱስም ተመለከተውና ወደደው፤* ኢየሱስ የሰውየው መልስ ከልብ የመነጨ መሆኑን ዐውቋል፤ ይሁን እንጂ በዚህ መልክ የመለሰለት፣ ሰውየው የሕጉን መንፈሳዊ ትርጒም ምን ያህል እንደሳተ ገልጾ ሊያሳፍረው ሳይሆን፣ እውነተኛ ፍቅር ለማሳየት ነው። *አንድ ነገር ይጐድልሃል፤ ሂድና ያለህን ሁሉ ሽጥ፤* የዚህ ወጣት መሠረታዊ ችግር ሀብቱ ስለ ነበር (ቍ 22 ይመ)፣ ኢየሱስ ይህን ያለው ከዚሁ ችግር ሊገላግለው ነው። ጌታ ይህን ትእዛዝ የሰጠው ለክርስቲያኖች ሁሉ ነው ለማለት አንዳች ፍንጭ የለም፤ ትእዛዙ ሀብታቸው ዕንቅፋት የሆነባቸውን ሰዎች ብቻ የሚመለከት ነው። *በሰማይ ... ሀብት፤* የዘላለም ሕይወት ወይም ድነት ስጦታ ነው። ይህ ሀብት የሚገኘው ኢየሱስን በመከተል ነው እንጂ፣ ራስን በመጨቈንና ሀብትን ለድኾች በመስጠት ብቻ አይደለም። ይህ ወጣት ሀብቱን ለድኾች ቢሰጥ ኖሮ፣ በኢየሱስ እንዳይታመን ዕን ቅፋት የሆነበትን ነገር ባስወገደ ነበር።

10፥22 *ብዙ ሀብት ስለ ነበረውም እየተከዘ ሄደ፤* ሰውየው ይህን አሳዛኝ ውሳኔ አድርጎ መሄዱ፣ ከዘላለም ሕይወት ይልቅ

መግባት እንዴት ከባድ ነገር ነው! 25ሀብታም
ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ይልቅ
ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀለዋል።"
26ደቀ መዛሙርቱም ይበልጥ በመገረም፣
"ታዲያ ማን ሊድን ይችላል?" ተባባሉ።
27ኢየሱስም አያቸውና፣ "ይህ በሰው ዘንድ
አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን እንዲህ
አይደለም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል"
አላቸው።
28ጴጥሮስም፣ "እነሆ እኛ
ሁሉን ትተን ተከተልንህ" አለው።
29ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፤ "እውነት
እላችኋለሁ፤ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ሲል
ቤቱን ወይም ወንድሞቹን ወይም እኅቶቹን
ወይም እናቱን ወይም አባቱን ወይም ልጆቹን
ወይም ዕርሻውን የተወ ሁሉ፣ 30አሁን በዚህ
ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን፣ ወንድሞችን፣
እኅቶችን፣ እናቶችን፣ ልጆችንና ዕርሻን መቶ
ዕጥፍ የማይቀበል፣ በሚመጣውም ዓለም የዘላ
ለም ሕይወት የማይወርስ የለም። 31ነገር ግን
ብዙ ፊተኞች የሆኑ ኋለኞች፣ ኋለኞች የሆኑም
ፊተኞች ይሆናሉ።

## ኢየሱስ ዳግም ስለ ሞቱ አስቀድሞ ተናገረ

10፥32-34 ተጓ ምብ - ማቴ 20፥17-19፤ ሉቃ 18፥31-33

32ወደ ኢየሩሳሌም ለመውጣት በመንገድ
ላይ ሳሉ፣ ኢየሱስ ፊት ፊታቸው ይሄድ ነበር፤
ደቀ መዛሙርቱ ተገረሙ፣ ሌሎች የተከተ
ሉት ደግሞ ፈርተው ነበር። ደግሞም ዐሥራ
ሁለቱን ከሕዝቡ ለይቶ ምን እንደሚደርስበት
ነገራቸው፤ 33እንዲህም አላቸው፤ "ወደ ኢየሩሳ
ሌም እንወጣለን፤ የሰው ልጅ ለካህናት አለቆ
ችና ለጸሐፍት አልፎ ይሰጣል፤ እነርሱም
የሞት ፍርድ ይፈርዱበታል፤ አሳልፈው ለአሕ
ዛብ ይሰጡታል፤ 34ያፌዙበታል፤ ይተፉበታል፣
ይገርፉታል፣ ከዚያም ይገድሉታል፤ እርሱ ግን
ከሦስት ቀን በኋላ ይነሣል።"

## የያዕቆብና የዮሐንስ ጥያቄ

10፥35-45 ተጓ ምብ - ማቴ 20፥20-28

35ከዚያም የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ
ወደ እርሱ ቀርበው፣ "መምህር ሆይ፤ የምን
ለምንህን ሁሉ እንድታደርግልን እንፈልጋለን"
አሉት።
36እርሱም፣ "ምን እንዳደርግላችሁ ትፈል
ጋላችሁ?" አላቸው።
37እነርሱም፣ "በክብርህ ጊዜ አንዳችን በቀ
ኝህ፣ አንዳችን በግራህ እንድንቀመጥ ፍቀድ
ልን" አሉት።
38ኢየሱስም፣ "የምትለምኑትን አታውቁም፤
እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ፣ የምጠመቀ
ውንስ ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን?"
አላቸው።
39እነርሱም፣ "አዎን እንችላለን" አሉት።
ኢየሱስም፣ "እኔ የምጠጣውን ጽዋ ትጠጣላ
ችሁ፤ እኔ የምጠመቀውንም ጥምቀት ትጠመቃ
ላችሁ፤ 40ነገር ግን በቀኜ ወይም በግራዬ
መቀመጥ ለተዘጋጀላቸው የሚሆን እንጂ እኔ

10፥25 ሉቃ12፥16-20፤16፥19-31
10፥27 ማቴ19፥26
10፥28 ማቴ4፥19
10፥30 ማቴ6፥33፤12፥32፤25፥46
10፥31 ማቴ19፥30
10፥32 ማር3፥16-19
10፥33 ማቴ8፥20፤27፥1፡2፤ሉቃ9፥51
10፥34 ማቴ16፥21፤ሐሥ2፥23፤3፥13
10፥37 ማቴ19፥28
10፥38 ኢዩ38፥2፤ማቴ20፥22፤ሉቃ12፥50
10፥39 ሐሥ12፥2፤ራእ1፥9

ኅብረቱን ምን ያህል እንደ ወደደ ያሳያል (ከ4፥19 ጋር ያነጻጽሩ)።

10፥25 *በመርፌ ቀዳዳ፤* ቀድሞ ፓሌስቲና ወይም ቅድስት ምድር ይባል በነበረው አገር ትልቅ እንስሳ ግመል ነበር፤ በትልቅ እንስሳና በትንሽ ቀዳዳ መካከል የተደረገው ንጽጽር፣ ከሰው አንጻር ሲታይ ሊደረግ የማይቻለውን ለመግለጽ ጥሩ መግለጫ ነው።

10፥27 *ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም፤* ድነት የሚገኘው ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር ነው። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት በግል የሚደረግ ማንኛውም በጎ ምግባር ከንቱ ነው፤ በእግዚአብሔር ጸጋ ካልሆነ በቀር ማንም ሊድን አይችልም።

10፥29 *እውነት እላችኋለሁ፤* የ3፥28 ማብ ይመ። *ወንጌል፤* የ1፥1 ማብ ይመ።

10፥30 *አሁን በዚህ ዘመን ... በሚመጣውም ዓለም፤* ይህ አባባል ከሰው ውድቀት ጀምሮ እስከ ዘላለም ያለውን ጊዜ ያካትታል። የአሁኑ ዘመን ክፉ ነው (ገላ 1፥4)፤ የሚመጣው የጽድቅ ዘመን ግን ከጌታ ዳግም ምጽአት ጀምሮ እስከ ዘላለሙ ይዘልቃል። *ከስደት ጋር ... መቶ ዕጥፍ፤* የደቀ መዝሙርነት ሕይወት ተስፋና ስደት፣ በረከትና መከራ በጥምር የሚገኙበት ሕይወት ነው፤ እግዚአብሔር ለአንድ ክርስቲያን አዲስና ክብር የተሞላበትን ነገር ሳይተካ አንዳች ነገር አይወስድበትም። የሚገርመው ነገር ክርስቲያኖች እርስ በርስ ያላቸው ኅብረት የሚጠናከረው በስደት ጊዜ ነው። *የዘላለም ሕይወት፤* የእግዚአብሔር ለሆኑት ከዚህ ዓለም የሕይወት ውጣ ውረድ ባሻገር ድል በርግጥ አለ።

10፥31 *ፊተኞች የሆኑ ኋለኞች ... ይሆናሉ፤* ለምሳሌ በጴጥሮስ ሕይወት እንደታየው (ቍ 28)፣ ብዙ መሥዋዕትነት ከፍለናል በማለት ለሚኮሩ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነው።

10፥32 *ወደ ኢየሩሳሌም ለመውጣት በመንገድ ላይ ሳሉ፤* ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዝ፣ መጀመሪያ የተነሣው ኤፍሬም ከምትባል ከተማ ሲሆን (ከዮሐ 11፥54 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ከዚያም ወደ ገሊላ (ሉቃ 17፥11)፣ ደግሞም በደቡብ በኩል በፔርያ አድርጎ ወደ ኢያሪኮ ሄደ (ሉቃ 18፥35)፤ በመጨረሻ ኢየሩሳሌም ደረሰ (ሉቃ 19፥41)። *የተከተሉት ደግሞ፤* ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም በጒዞ ላይ የነበሩት ሊሆኑ ይችላሉ። *ዐሥራ ሁለቱን፤* 3፥16-19 እና የሉቃ 6፥14-16 ማብ ይመ።

10፥33-34 *ለአሕዛብ ... ይገድሉታል፤* በማርቆስ ወንጌል ሕማማትን አስመልክቶ በተነገረው ትንቢት ውስጥ፣ ስለ ስቅላቱ በየትኛውም ክፍል በቀጥታ አልተነገረም፤ ይሁን እንጂ እንዲገድሉት ለአሕዛብ ስለ መስጠቱ የተነገረው ስቅላቱን ያመለክታል፤ ምክንያቱም በዚያን ዘመን ሮማውያን የሮም ዜጋ ባልሆኑት ሰዎች ላይ የሞት ቅጣት የሚፈጽሙት በመስቀል ላይ በመቸንከር ነበር።

10፥33 *የሰው ልጅ ለካህናት አለቆችና ለጸሐፍት፤* የ8፥31፤ ማቴ 2፥4 ማብ ይመ።

*10፥35-45፤* በ9፥33-37 ከተጠቀሰው ሐሳብ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፤ በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ስለ እውነተኛ ታላቅነት ተጠቅሶአል፤ ሁለቱም ክፍሎች የሰፈሩት መከራ እንደሚቀበልና እንደሚገደል በተናገረበት ክፍል ነው። ሁለቱም ክፍሎች ደቀ መዛሙርቱ በመንፈሳዊ ነገር ገና ያላደጉና የጌታን ዓላማ ለይተው ያላወቁ እንደ ሆኑ ያሳያሉ።

10፥35-36 *እንፈልጋለን ... ትፈልጋላችሁ?* የያዕቆብና የዮሐንስ የክብርና የሥልጣን ፍላጎት ሊሟላላቸው የሚችለው፣ ሁለቱም ዝቅ ብለው ለማገልገል ፈቃደኞች ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው ("የሚፈልግ ... የሚፈልግ" የሚለውን በቍ 43-44 ላይ ይመ)።

10፥35 *የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ፤* 1፥19፤ 3፥17 ይመ።

10፥37 *አንዳችን በቀኝህ፣ አንዳችን በግራህ እንድንቀመጥ፤* የክብርንና የሥልጣንን ቦታ የሚያመለክት ነው።

10፥38 *እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ፤* በዚያን ጊዜ በአይሁድ ኅብረተ ሰብ ዘንድ የተለመደ አባባል ሲሆን፣ የአንድን ሰው ዕጣ ፈንታ መካፈልን ያመለክታል። በብሉይ ኪዳን፣ የወይን ጠጅ ጽዋ እግዚአብሔር ከሰዎች ኀጢአትና ዐመፅ የተነሣ የሚያመጣው መዓት ምሳሌ ነው (መዝ 75፥8፤ ኢሳ 51፥17-23፤ ኤር 25፥15-28፤ 49፥12፤ 51፥7)። በዚህም መሠረት ኢየሱስ ሊጠጣ ያለው ጽዋ የሚያመለክተው በኀጢአተኞች የሰው ልጆች ምትክ የሚቀበለውን የአምላክ ቍጣ ነው (10፥45፤ 14፥36 ይመ)። *የምጠመቀውንስ ጥምቀት ልትጠመቁ፤* የጥምቀት ምሳሌ ከጽዋው ምሳሌ ጋር አንድ ሲሆን፣ የሚያመለክተውም የኢየሱስን መከራና ሞት ነው (ሉቃ 12፥50 ይመ፤ እንዴት እንደ ተመሰለ ለመረዳት ከሮሜ 6፥3-4 ጋር ያነጻጽሩ)።

10፥40 *እኔ የምሰጠው ነገር አይደለም፤* ኢየሱስ የአባቱን ሥልጣን ሊቀማ አልፈለገም።

የምሰጠው ነገር አይደለም” አላቸው::
41ዐሥሩ ይህን ሲሰሙ፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን
መቈጣት ጀመሩ:: 42ኢየሱስም በአንድነት
ሰብስቦ እንዲህ አላቸው፤ “የአሕዛብ አለቆች
ተብለው የሚታሰቡት እንደሚገዟቸው፣ ሹሞቻ
ቸውም በእነርሱ ላይ ሥልጣናቸውን እንደ
ሚያሳዩ ታውቃላችሁ፤ 43በእናንተ ዘንድ
ግን እንዲህ አይደለም፤ ከመካከላችሁ ታላቅ
መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ ይሁን፤
44ፊተኛ ለመሆን የሚፈልግ ሁሉ፣ የሁሉ
ባሪያ ይሁን፤ 45የሰው ልጅ ሊያገለግልና ሕይ
ወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ መጣ
እንጂ፣ ሊገለገል አልመጣምና::”

## ኢየሱስ ዐይነ ስውሩን በርጤሜዎስን ፈወሰ

10፥46-52 ተጓ ምብ - ማቴ 20፥29-34፤ ሉቃ18፥35-43

46ከዚህ በኋላ ወደ ኢያሪኮ መጡ:: ኢየሱስና
ደቀ መዛሙርቱ ከብዙ ሕዝብ ጋር ከኢያሪኮ
ሲወጡ ዐይነ ስውሩ የጤሜዎስ ልጅ በርጤሜ
ዎስ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ይለምን ነበር::
47እርሱም የናዝሬቱ ኢየሱስ መሆኑን በሰማ
ጊዜ፣ “የዳዊት ልጅ፣ ኢየሱስ ሆይ፤ ማረኝ!”
እያለ ይጮኽ ጀመር::
48ብዙዎችም ዝም እንዲል ገሠጹት፤ እርሱ
ግን፣ “የዳዊት ልጅ ሆይ፤ ማረኝ!” እያለ የባሰ
ጮኸ::
49ኢየሱስም ቆም ብሎ፣ “ጥሩት” አላቸው::
እነርሱም ዐይነ ስውሩን፣ “አይዞህ፤ ተነሥ፤
ይጠራሃል!” አሉት:: 50እርሱም ልብሱን ጥሎ
ብድግ በማለት፣ ተነሥቶ ወደ ኢየሱስ መጣ::
51ኢየሱስም፣ “ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋ
ለህ?” አለው::
ዐይነ ስውሩም፣ “መምህር ሆይ፤ እንዳይ
እፈልጋለሁ” አለው::
52ኢየሱስም፣ “ሂድ፣ እምነትህ አድኖሃል”
አለው፤ ወዲያውም ዐይኑ በራለት፤ በመንገድም
ኢየሱስን ተከትሎት ሄደ::

## ኢየሱስ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም ገባ

11፥1-10 ተጓ ምብ - ማቴ 21፥1-9፤
ሉቃ 19፥29-38
11፥7-10 ተጓ ምብ - ዮሐ 12፥12-15

11 ወደ ኢየሩሳሌም በደብረ ዘይት ተራራ
አጠገብ ወዳሉት ወደ ቤተ ፋጌና ወደ
ቢታንያ በቀረቡ ጊዜ፣ ኢየሱስ ከደቀ መዛ
ሙርቱ ሁለቱን እንዲህ በማለት ላካቸው፤
2“በፊታችሁ ወዳለው መንደር ሂዱ፣ ሰው
ተቀምጦበት የማያውቅ የአህያ ውርንጫ እዚያ
ታስሮ ታገኛላችሁ፤ ፈታችሁ አምጡት፤
3ማንም፣ ‘ምን ማድረጋችሁ ነው?’ ቢላችሁ፣
‘ለጌታ ያስፈልገዋል፤ በቶሎም መልሶ ይልከዋል’
ብላችሁ ንገሩት::”
4እነርሱም ሄዱ፤ በአንድ ቤት በራፍ እመ
ንገድ ላይ የአህያ ውርንጫ ታስሮ አገኙት፤
ፈቱትም:: 5በዚያ ከቆሙት አንዳንድ ሰዎች፣
“ውርንጫውን የምትፈቱት ለምንድን ነው?”
አሏቸው:: 6ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ ያላቸውን
ለሰዎቹ በነገሯቸው ጊዜ ፈቀዱላቸው:: 7ውርን
ጫውንም ወደ ኢየሱስ አምጥተው ልብሳቸውን
በጀርባው ላይ አደረጉ፤ እርሱም ተቀመጠ
በት:: 8ብዙ ሰዎች ልብሳቸውን በመንገድ
ላይ አነጠፉ፤ ሌሎች ደግሞ ለምለም የዛፍ
ቅርንጫፍ እየቈረጡ ያነጥፉ ነበር::

10፥43 ማር9፥35
10፥45 ማቴ20፥28
10፥47 ማቴ9፥27፤ ማር1፥24
10፥51 ማቴ23፥7
10፥52 ማቴ4፥19፤ 9፥22
11፥1 ማቴ21፥1፡ 17
11፥2 ዘኍ19፥2፤ ዘዳ21፥3፤1ሳሙ6፥7
11፥4 ማር14፥16
11፥9 መዝ118፥

10፥41 *ዐሥሩ፤* የተቀሩት ደቀ መዛሙርት ማለት ነው:: *መቈጣት፤* የተቀሩት ደቀ መዛሙርት የዮሐንስንና ያዕቆብን የተቈጡት እነርሱም ሥልጣንና ክብርን ለራሳቸው ስለ ፈለጉ ሳይሆን አይቀርም::

10፥43 *በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም፤* ዓለም ሥልጣንን ለማግኘት የሚከተለውን አመለካከት ኢየሱስ ገለባበጠው:: የደቀ መዝሙርነት ሕይወት የሚታወቀው በትሕትናና ፍቅር በተሞላበት አገልግሎት ነው::

*10፥45፤* ይህ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም አገልጋይ ሆኖ መምጣቱን የሚያመለክት የማርቆስ ወንጌል መሪ ጥቅስ ነው:: በርግጥም ኢሳ ይያስ አስቀድሞ እንደ ተነበየው፣ ኢየሱስ እኛን ለመቤዠት የተ ሠቃየና የሞተ አገልጋይ ነው (ኢሳ 52፥13-53፥12):: *የሰው ልጅ፤* የ8፥31 ማብ ይመ:: *ቤዛ፤* ከእስራት ነጻ ለመውጣት የሚከፈል ዋጋ ማለት ነው:: ኢየሱስ እኛን ከኀጢአትና ከሞት እስራት ነጻ ለማውጣት ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ:: *ለብዙዎች፤* ለእኛ ቤዛ ሆኖ ከተሰጠው ከአንዱ ሕይወት ጋር በማነጻጸር ነው:: *ለ (ብዙዎች)፤* በ(ብዙዎች) “ምትክ” ማለት ነው፤ ይኸውም ኢየሱስ በእኛ ፈንታ የእኛን ሞት መሞቱን ያመለክታል፤ የማቴ 20፥28 ማብ ይመ::

10፥46 *ኢያሪኮ፤* በጣም የቈየች የጥንት ከተማ ስትሆን፣ ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ 8 ኪ.ሜ ላይ፣ ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን ምሥራቅ 24 ኪ.ሜ ያህል ርቃ ትገኝ ነበር:: ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን፣ በብሉይ ኪዳን የምትታወቀው ኢያሪኮ ፈርሳ እንዳልነበረች ሆና ነበር፤ ይሁን እንጂ ከቀድሞዋ ኢያሪኮ ከተማ በስተ ደቡብ፣ ታላቁ ሄሮድስ ሌላ አዲስ ኢያሪኮ መሥርቶ ነበር *ከኢያሪኮ ሲወጡ፤* ሉቃስ “ወደ ኢያሪኮ በቀረበ ጊዜ” ይላል (ሉቃ 18፥35)፤ ይኸውም አዲሲቱን ኢያሪኮ ለማመልከት ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ማቴዎስና (20፥29) ማርቆስ የጥንቷን ከተማ ማለታቸው ሊሆን ይችላል:: *ዐይነ ስውሩ . . . ይለምን ነበር፤* በዚያን ዘመን ምእመናን ወደ ኢየሩሳሌም በሚጓዙበት የከተማ መውጫ መንገዶች ዳር፣ ዐይነ ስውር ተቀምጦ ሲለምን ማየት የተለመደ ነበር::

10፥47 *የናዝሬቱ፤* የማቴ 2፥23 ማብ ይመ:: *የዳዊት ልጅ፤* የመሲሑ ልዩ መጠሪያ ነው (ኢሳ 11፥1-3፤ ኤር 23፥5-6፤ ሕዝ 34፥23-24 ይመ፤ እንዲሁም የማቴ 1፥1፤ 9፥27 ማብ ይመ):: በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ በዚህ መጠሪያ የተጠራው እዚህ ቦታ ላይ ብቻ ነው::

10፥51 *መምህር፤* በዕብራይስጥ፣ “ረቢ” ይባላል::

*11፥1-11፤* የማርቆስ ወንጌል አዲስ ክፍል እዚህ ላይ ይጀመራል:: ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ደርሶአል፤ ቀሪ አገልግሎቱም እዚያው ቅድስቲቱ ከተማ ውስጥ ይሆናል:: በክብር የመግባቱ ሁኔታ የሕማማት ሳምንት መጀመሪያ ሲሆን፣ ይህም መሲሑ ሆን ብሎ ያደረገው ነው፤ የዚህ አገባብ ፍንጭ የሚገኘው በዘካ 9፥9 ላይ ሲሆን፣ በማቴ 21፥5፤ ዮሐ 12፥15 ላይም ተጠቅሶአል:: ኢየሱስ የአይሁድ አለቆች ጉዳት ሊያደርሱበት እንደሚፈልጉ እያወቀ፣ በመሲሕነቱ የሚመጣበትን ሁሉ ለመቀበል ዝግጁ በመሆኑ፣ በዚህ ጊዜ መሲሕነቱን ሊሰውር አልፈለገም::

11፥1 *በደብረ ዘይት ተራራ፤* ከኢየሩሳሌም ትይዩ በስተ ምሥራቅ የሚገኝ ተራራ ነው፤ ከፍታው 2700 ጫማ ሲሆን፣ ከጽዮን ተራራ በ200 ጫማ ይበልጣል:: ጫፉ ላይ ሆኖ ከተማዋ፣ በተለይ ደግሞ ቤተ መቅደሱ ወለል ብሎ ይታያል:: *ቢታንያ፤* የማቴ 21፥17 ማብ ይመ:: *ቤተ ፋጌ፤* የማቴ 21፥1 ማብ ይመ::

11፥2 *በፊታችሁ ወዳለው መንደር፤* ቤተ ፋጌ ሊሆን ይችላል:: *የአህያ ውርንጫ፤* ቃሉ በግሪክ ቋንቋ የምንም ዐይነት እንስሳ ግልገል ማለት ነው፤ እዚህ ላይ ግን የአህያ ውርንጫ ነው (ማቴ 21፥2፤ ዮሐ12፥15 ይመ):: *ሰው ተቀምጦበት የማያውቅ፤* አገልግሎት ላይ ውለው የማያውቁ እንስሳት ለሃይማኖት ነክ ጉዳይ ይፈለጉ ነበር (ዘኍ19፥2፤ ዘዳ21፥3፤ 1ሳሙ 6፥7 ይመ)::

11፥3 *ማንም፣ ‘ምንም ማድረጋችሁ ነው?’ ቢላችሁ፤* በባለቤቱ ብቻ ስለ ውርንጫው የሚቀርበው ጥያቄ ሳይሆን፣ ማንኛውም ሰው ለደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ ቢያቀርብ መልስ እንዲሰጡ ነው:: *ጌታ፤* የሉቃ 19፥31 ማብ ይመ::

11፥8 *የዛፍ ቅርንጫፍ፤* የዚህ ሐረግ ትርጕም በአቅራቢያው ካለው መስክ በቀላሉ የሚገኝ፣ “ቅጠል” ወይም “ቀንበጥ” ማለት ነው:: “የዘንባባ ዝንጣፊ” ያለው ዮሐንስ ብቻ ነው (ዮሐ 12፥13)፤ ዘንባባ በኢየሩሳሌም አካባቢ ስለማይገኝ ሰዎቹ ከኢያሪኮ ሳያመጡት አልቀረም::

9ከፊቱ የቀደሙትና ከኋላው የተከተሉትም
በታላቅ ድምፅ፣ እንዲህ ይሉ ነበር፤
"ሆሣዕና![ጨ]
*በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው!*
10የምትመጣው የአባታችን የዳዊት መንግሥት
የተባረከች ናት!
ሆሣዕና በአርአያም!"፡፡

11ኢየሱስም ኢየሩሳሌም ደረሰ፤ ከዚያም ወደ
ቤተ መቅደስ ገባ፤ በዙሪያው ያለውንም ሁሉ
ተመለከተ፤ ቀኑም ስለ መሸ ከዐሥራ ሁለቱ
ጋር ወደ ቢታንያ ወጣ፡፡

## ኢየሱስ ቤተ መቅደስን አጸዳ

11፥12-14 ተጓ ምብ- ማቴ21፥18-22
11፥15-18 ተጓ ምብ - ማቴ21፥12-16፤ ሉቃ19፥45-47፤ ዮሐ2፥13-16

12በማግሥቱ ከቢታንያ ሲወጡ ኢየሱስ
ተራበ፡፡
13እርሱም ቅጠል ያላት የበለስ ዛፍ ከሩቅ
አየ፤ ምናልባት ፍሬ ይገኝባት እንደ ሆነ
ብሎ ወደ እርሷ መጣ፤ ነገር ግን የበለስ ወራት
አልነበረምና ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘባ
ትም፡፡ 14ከዚያም ዛፏን፣ 'ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም
ማንም ፍሬ ከአንቺ አይብላ" አላት፡፡ ደቀ
መዛሙርቱም ይህን ሲናገር ሰሙ፡፡
15ወደ ኢየሩሳሌምም መጡ፤ ከዚያም ወደ
ቤተ መቅደስ ገብቶ፣ የሚሸጡትንና የሚገ
ዙትን ያስወጣ ጀመር፡፡ የገንዘብ መንዛሪዎችን
ጠረጴዛና የርግብ ሻጮችን መቀመጫ ገለባበጠ፤
16ማንም ዕቃ ተሸክሞ በቤተ መቅደሱ ቅጥር
ግቢ ውስጥ እንዳያልፍ ከለከለ፡፡ 17ሲያስተምራ
ቸውም፣
"'ቤቴ ለሕዝቦች ሁሉ የጸሎት ቤት ይባላል'
ተብሎ አልተጻፈምን?
እናንተ ግን የሌቦች ዋሻ አደረጋችሁት!"
አላቸው፡፡
18የካህናት አለቆችና ጸሐፍትም፣ ይህን ሲሰሙ
እንዴት እንደሚያጠፉት መንገድ ይፈልጉ
ጀመር፤ ሕዝቡ ሁሉ በትምህርቱ በመገረማቸው
ፈርተውታልና፡፡
19በመሸም ጊዜ ከከተማዪቱ ወጥተው
ሄዱ[ሀ]፡፡

## የበለሷ ዛፍ ደረቀች

11፥20-24 ተጓ ምብ - ማቴ 21፥19-22

20በማግሥቱ ጠዋት በመንገድ ሲያልፉ፣
በለሲቱ ከነሥሯ ደርቃ አዩ፡፡ 21ጴጥሮስ
ነገሩ ትዝ አለውና ኢየሱስን፣ "መምህር ሆይ፤
እነሆ፤ የረገምሃት በለስ ደርቃለች" አለው፡፡

25:26፤ማቴ23፥39
11፥10 ሉቃ2፥14
11፥11 ማቴ21፥12:17
11፥13 ሉቃ13፥6-9
11፥17 ኢሳ56፥7፤ ኤር7፥11
11፥18 ማቴ7፥28፤ 12፥12፤21፥46፤ ሉቃ20፥19
11፥19 ሉቃ21፥37
11፥21 ማቴ23፥7

[ጨ]9 በዕብራይስጡ "አድን!" ማለት ሲሆን ምስጋናን የሚገልጽ አባባል ነው፤ እንዲሁም ቍ 10 ይመ፡፡
[ሀ]19 አንዳንድ ቅጆች *ወጥቶ ሄደ* ይላሉ፡፡

11፥9 *ሆሣዕና!* የመዝ 118፥25 ማብ ይመ፤ *በ ... የሚመጣ የተባረከ ነው!* ከመዝ 118፥26 የተወሰደ ነው፡፡ በአይሁድ ፋሲካ ሰሞን የሚዘመርና ለወቅቱም ተስማሚ የሆነ መዝሙር ነበር፡፡

11፥10 *የምትመጣው የአባታችን የዳዊት መንግሥት!* ለዳዊት ልጅ ተስፋ የተገባለት የመሲሑ መንግሥት ማለት ነው (2ሳሙ 7፥11-14)፡፡

11፥11 *ቤተ መቅደስ!* የማቴ 4፥5 ማብ ይመ፡፡ *ዐሥራ ሁለቱ!* (3፥16-19 ይመ፤ እንዲሁም የሉቃ 6፥14-16 ማብ ይመ)፡፡ *ወደ ቢታንያ ወጣ!* ኢየሱስ በሕማማቱ ሰሞን እስከ ሐሙስ ዕለት ድረስ የቈየው በቅርብ ወዳጆቹ በማርያም፣ በማርታና በአልዓዛር ቤት ይመስላል (11፥19፤ 14፥13፤ ማቴ21፥17፤ ዮሐ 12፥1-3 ይመ)፡፡

11፥12 *በማግሥቱ!* በሕማማቱ ሰሞን፣ ሰኞ ዕለት ማለት ነው፡፡ *ቢታንያ!* የማቴ 21፥17 ማብ ይመ፡፡

11፥13 *የበለስ ወራት አልነበረም!* በእርግጥ በኢየሩሳሌም አካባቢ በለስ ቅጠል የሚያወጣው ብዙውን ጊዜ በመጋቢት ወይም በሚያዝያ ወር ነው፤ ይሁን እንጂ ቅጠሉ በሰኔ ወር እስካልረገፈ ድረስ ፍሬ አያፈራም፡፡ ይህቺኛዪቱ በለስ ግን በፋሲካ ወራት ሙሉ ሙሉ ቅጠል ማውጣቷ የተለየች ያደርጋታል፡፡

11፥14 *ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም ማንም ፍሬ ከአንቺ አይብላ!* በለስ እስራኤልን ስለሚወክል ሁኔታው የፍርድ ምሳሌ ሳይሆን አይቀርም (ሆሴ 9፥10፤ ናሆ 3፥12 ይመ)፡፡ ቅጠሉ እጅብ ያለ ዛፍ ብዙውን ጊዜ ፍሬ ይይዛል፤ ይህችኛዋ ግን ቅጠል ይዛ፣ ፍሬ ስላልተገኘበት ተረገመች፡፡ የቤተ መቅደሱ መንጻት (ቍ 15-19) በበለሷ ትረካ (ቍ 12-14 እና ቍ 20-25) መካከል መግባቱ፣ የፍርድ መሪ ሐሳብ መኖሩን የሚያጐላ ይመስላል (የ ቍ 21 ማብ ይመ)፡፡ ይሁን እንጂ ኢየሱስ እዚህ ላይ በበለሱ ምሳሌ ያስተማረው በእምነት ስለሚደረግ ጸሎት ነው (ቍ 21-25)፡፡

*11፥15-19!* ሦስቱ የወንጌል ጸሐፍት (ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ) የቤተ መቅደሱ መንጻት በኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን መጨረሻ እንደ ሆነ ጽፈዋል፡፡ ዮሐንስ ብቻ በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ እንደ ነበረ ይገልጻል፤ የማቴ 21፥12-17፤ ዮሐ 2፥14-17 ማብ ይመ፡፡

11፥15 *ቤተ መቅደስ!* እዚህ ላይ ራሱን ቤተ መቅደሱን ብቻ ሳይሆን፣ አሕዛብ ለጸሎት ይሰበሰቡበትና እግዚአብሔርን ያመልኩበት የነበረውን የቤተ መቅደሱን አደባባይ ጭምር ነው (ቍ 17 ይመ)፡፡ *የሚሸጡትንና የሚገዙትን!* ለፋሲካ በዓል የሚመጡ ምእመናን፣ ለመሥዋዕት የሚሆኑትን እንስሳት ማግኘት ነበረባቸው፡፡ ነጋዴዎችም የከብት ማጐሪያንና ገንዘብ የሚለዋወጡበትን ጠረጴዛ በአሕዛብ አደባባይ ላይ ሠርተው ነበር፡፡ *የገንዘብ መንዛሪዎችን ጠረጴዛ!* የዓመቱ ግብር በአገሬው ገንዘብ መከፈል ስለ ነበረበት፣ ምእመናኑ ይዘው የመጡትን ገንዘብ በውጭ ምንዛሪ ደንብ መሠረት መለወጥ ነበረባቸው፡፡ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የአገሩ ሕግም (የአበቶች ትውፊት በመባል የሚታወቀው የጥንት መጽሐፍ መሠረት) (የማቴ 15፥2 ማብ ይመ)፣ አንዳንድ የመሥዋዕት ዐይነቶች በጢሮስ ገንዘብ ተገዝተው እንዲቀርቡ ያዝ ነበር፡፡ *የርግብ ሻጮችን!* ሴቶች በሥርዐቱ መሠረት በሚነጹበት ጊዜ (ዘሌ 12፥6፤ ሉቃ 2፥22-24)፣ ሰዎች ከአንዳንድ የቆዳ በሽታ በሚነጹበት ጊዜ (ዘሌ 14፥22) እንዲሁም ለሌላ ጕዳይ (ዘሌ 15፥14:29) ርግቦች መሥዋዕት ሆነው ይቀርቡ ነበር፡፡ ድኾችም ለመሥዋዕት የሚያቀርቡት ርግቦችን ነበር (ዘሌ 5፥7)፡፡

11፥16 *ዕቃ ተሸክሞ በቤተ መቅደስ ቅጥር ግቢ ውስጥ!* ይህን የገለጸ ማርቆስ ብቻ ነው፡፡ ከከተማው ተነሥቶ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ለመሄድ አቋራጩ መንገድ በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ማለፍ ሳይሆን አልቀረም፡፡ የቍ 27 ማብ ይመ፡፡

11፥17 *ለሕዝቦች ሁሉ የጸሎት ቤት!* ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበራቸው አሕዛብ፣ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ገብተው ማምለክ እንደሚፈቀድላቸው ኢሳ 56፥7 ያረጋግጣል፡፡ የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች አሕዛብ የሚሰበሰቡበትን ቦታ የገበያ፣ ውካታ ያለበትና በሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ ልውውጥ አካባቢው የገማ እንዲሆን ማድረጋቸው፣ እግዚአብሔር በነቢዩ፣ "ቤቴ ለሕዝቦች ሁሉ የጸሎት ቤት ይባላል" ብሎ ለአሕዛብ ጭምር በበጎ ፈቃዱ የሰጠውን ዕድል እንደ ማበላሸት ነው፡፡ *የሌቦች ዋሻ!* ቤተ መቅደሱ ለዚህ የበቃው ሕዝቡ ገንዘቡን በመበዝበዙ ብቻ ሳይሆን፣ የቤተ መቅደሱንም ቅድስና በማጕደፋቸው ነው፡፡

11፥18 *የካህናት አለቆችና ጸሐፍትም!* የማቴ 2፥4 ማብ ይመ፡፡ *እንዴት እንደሚያጠፉት መንገድ ይፈልጉ ጀመር!* የ3፥6 ማብ ይመ፡፡ ኢየሱስ በማንኛውም ረገድ ለኑሮአቸው የሚያሠጋ ጠላት ሆኖ ታያቸው፡፡

11፥19 *ከከተማዪቱ ወጥተው ሄዱ!* ወደ ቢታንያ ነው (የቍ 11 ማብ ይመ)፡፡

11፥20 *በማግሥቱ ጠዋት!* የሕማማቱ ሰሞን፣ ማክሰኞ ዕለት ማለት ነው፡፡ *ከነሥሯ ደርቃ!* ይህ ዝርዝር አስረጅ የሚያመለክተው በለሲቱ ፈጽማ እንደ ደረቀች ነው (ኢዮ 18፥16 ይመ)፤ ይህም ወደፊት ማንም ከእርሷ ፍሬ እንደማያገኝባት ያሳያል፡፡ በ70 ዓ.ም ለሚመጣውም ፍርድ ጕልህ ማስጠንቀቂያ ነበር (13፥2 እና የማቴ 24፥2 ማብ ይመ)፡፡

11፥21 *መምህር!* በዕብራይስጥ "ረቢ" ይባላል፡፡ *የረገምሃት በለስ!* የቍ 14 ማብ ይመ፡፡ *ደርቃለች!* አባባሉ መሲሐቸውን እንቀበልም በማለት የተነሣሡት የአይሁድ ባለ ሥልጣናት ምን

²²ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ “በእግዚ
አብሔር እመኑ[a]፤ ²³እውነት እላችኋለሁ፤ ማንም
ይህን ተራራ፣ ‘ተንቀለህ ወደ ባሕር ተወርወር’
ቢለውና ይህንንም በልቡ ሳይጠራጠር ቢያምን
ይሆንለታል። ²⁴ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን
ሁሉ እንደ ተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ
ይሆንላችኋል። ²⁵እንዲሁም ለጸሎት በምትቆ
ሙበት ጊዜ፣ የሰማዩ አባታችሁ ኀጢአታችሁን
ይቅር እንዲልላችሁ፣ እናንተም በሰው ላይ
ያላችሁን ሁሉ ይቅር በሉ። ²⁶ይቅር ባትሉ
ግን የሰማዩ አባታችሁ ኀጢአታችሁን ይቅር
አይላችሁም[b]።”

## በኢየሱስ ሥልጣን ላይ ጥያቄ ተነሣ

11፥27-33 ተጓ ምብ - ማቴ 21፥23-27፤ ሉቃ20፥1-8

²⁷እንደ ገና ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፤ ኢየሱስ
በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚዘዋ
ወርበት ጊዜ፣ የካህናት አለቆች፣ ጸሐፍትና
የሕዝብ ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ቀርበው፣
²⁸“እነዚህን ነገሮች የምታደርገው በምን ሥልጣን
ነው? እነዚህን እንድታደርግስ ይህን ሥልጣን
የሰጠህ ማን ነው” አሉት።
²⁹ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ “እስቲ
እኔም አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፤ መልሱልኝ፤
እኔም እነዚህን ነገሮች በምን ሥልጣን እን
ደማደርግ እነግራችኋለሁ። ³⁰የዮሐንስ ጥምቀት
ከሰማይ ነበረችን ወይስ ከሰው? መልሱልኝ።”
³¹እነርሱም እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባባሉ፤
“ ‘ከሰማይ ነው’ ብንል፣ ‘ታዲያ ለምን አላመና
ችሁትም?’ ይለናል፤ ³²‘ታዲያ፣ ከሰው ነው’
እንበልን?” ሕዝቡ ሁሉ ዮሐንስ እውነተኛ ነቢይ
መሆኑን ያምኑ ስለ ነበር ፈሩ።
³³ስለዚህ ለኢየሱስ “አናውቅም” ብለው መለ
ሱለት።
ኢየሱስም፣ “እንግዲያው እኔም እነዚህን ነገሮች
በምን ሥልጣን እንደማደርግ አልነግራችሁም”
አላቸው።

11፥23 ማቴ21፥21
11፥24 ማቴ7፥7
11፥25 ማቴ6፥14
11፥32 ማቴ11፥9
12፥1 ኢሳ5፥1-7
12፥6 ዕብ1፥1-3
12፥10 ሐሥ4፥11
12፥11 መዝ118፥22:23
12፥12 ማቴ22፥22፤ ማር11፥18

## የወይን ስፍራ የተከራዩ ገበሬዎች ምሳሌ

12፥1-12 ተጓ ምብ - ማቴ 21፥33-46፤ ሉቃ20፥9-19

12 ከዚያም እንዲህ እያለ በምሳሌ
ይነግራቸው ጀመር፤ “አንድ ሰው
ወይን ተከለ፤ ዙሪያውን አጠረ፤ ለመጭመቂያው
ጕድጓድ ቈፈረ፤ የመጠበቂያም ማማ ሠራ
ለት፤ ከዚያም ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ
አገር ሄደ። ²በመከር ጊዜም ከወይኑ ፍሬ
እንዲያመጣለት ከአገልጋዮቹ አንዱን ወደ
ገበሬዎቹ ላከ። ³እነርሱ ግን ይዘው ደበደቡት፤
ባዶ እጁንም ሰደዱት። ⁴እንደ ገናም ሌላ
አገልጋይ ላከ፤ እነርሱም ራሱን ፈንክተውና
አዋርደው መለሱት”፤ ⁵አሁንም እንደ ገና
ሌላ ላከ፤ ይህኛውንም ገደሉት፤ ከሌሎች
ከብዙዎቹ መካከል አንዳንዶቹን ደበደቡ፤
አንዳንዶቹንም ገደሉ።
⁶“አሁንም የሚላክ ሌላ ነበረው፤ እርሱም
የሚወደው ልጁ ነበረ፤ “ልጄንስ ያከብሩታል”
በማለት ከሁሉ በኋላ ላከው።
⁷“ገበሬዎቹ ግን እርስ በርሳቸው፣ ‘ይህማ
ዋናው ወራሹ ነው፤ ኑ እንግደለው፤ ርስቱ
የእኛ ይሆናል’ ተባባሉ፤ ⁸ከዚያም ይዘው ገደሉት፤
ከወይኑ ስፍራም አውጥተው ጣሉት።
⁹“እንግዲህ የወይኑ አትክልት ባለቤት
ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል? ይመጣል፤
ገበሬዎቹን ይገድላል፤ የወይኑንም አትክልት
ለሌሎች ይሰጣል። ¹⁰እንዲህ የሚለውን የመ
ጽሐፍ ቃል አላነበባችሁምን፤

“ ‘ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
እርሱ የማእዘን ራስ[c] ሆነ፤
¹¹ጌታ ይህን አድርጎአል፣
ይህም ለዐይናችን ድንቅ ነው’?”

¹²ምሳሌውን የተናገረው ስለ እነርሱ መሆ
ኑን ስላወቁ፣ ሊይዙት ፈለጉ፤ ነገር ግን ሕዝቡን
ስለፈሩ ትተውት ሄዱ።

[a]22 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *በእግዚአብሔር ላይ እምነት ካላችሁ* ይላሉ።
[b]26 አንዳንድ ቅጆች ቍ 26 የላቸውም።
[c]10 ወይም *የማእዘን ድንጋይ*

ዐይነት ሶጣ እንደሚደርስባቸው የሚገልጽ ትንቢት ሳይሆን አይቀርም።

11፥23 *እውነት እላችኋለሁ፤* የ3፥28 ማብ ይመ። *ይህን ተራራ ... ባሕር፤* ከተራራው ባሻገር የሙት ባሕር የሚታይበትን የደብረ ዘይትን ተራራ ነው።

11፥27 *በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ፤* በዋናው የቤተ መቅደስ ሕንጻ ዙሪያ ብዙ አደባባዮች ነበሩ፤ ከእነዚህም፦ የሴቶች አደባባይ፣ የወንዶች (እስራኤላውያን) አደባባይ፣ የአሕዛብ አደባባይ የተባለው (ቍ 16 ይመ) ይገኙበታል። *የካህናት አለቆች፣ ጸሐፍት የሕዝብ ሽማግሌዎች፤* የ8፥31 ማብ ይመ።

11፥28 *ሥልጣን፤* የአይሁድ ሸንጎ፣ ኢየሱስ ሥልጣን ሳይኖረው ለምን እንደ ባለ ሥልጣን እንደሚሠራ ጥያቄ አቀረቡለት (የሉቃ 20፥2 ማብ ይመ)።

11፥30 *ከሰማይ ... ወይስ ከሰው፤* የአምላክን ስም በከንቱ ላለመጥራት ሲሉ፣ አይሁድ “ሰማይ” የሚለውን ቃል እግዚአብሔር ለማለት ይጠቀሙበት ነበር (ዘፀ 20፥7 ይመ)። ኢየሱስ ያቀረበው ጥያቄ የሚያሳየው፣ የእርሱም ሥልጣን እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ከእግዚአብሔር የመጣ መሆኑን ነው።

*12፥1-12፤* ብዙዎቹ የኢየሱስ ምሳሌዎች የሚያስተላልፉት አንድ ፍሬ ሐሳብ ነው። ይኸኛው ምሳሌ ግን ውስብስብ ነው፤ ዝርዝር ሐሳቡም በመጀመሪያው ምእተ ዓመት በገሊላ ከነበረው ማኅበራዊ ሁኔታ ጋር ይስማማል። ብዙ የገሊላ ምድር፣ በሌላ ስፍራ በሚኖሩ ሀብታም ባለ ርስቶች የተያዘ ስለሆነ፣ መሬታቸውን የሚያርሱላቸው ጭሰኞች ነበሩ። ይህ ምሳሌ በኢየሱስ ሕይወት ላይ የታለመውን ሤራና እግዚአብሔር በሤረኞች ላይ የሚያመጣውን ፍርድ በግልጽ ያሳያል፤ የማቴ 21፥35-37፡ 41 ማብ ይመ።

12፥1 *በምሳሌ፤* የ4፥2 ማብ ይመ። *አንድ ሰው ወይን ተከለ፤* አገላለጹ በኢሳ 5፥1-2 ላይ እስራኤል በወይን ተክል ምሳሌ የቀረበችበትን ዐይነት ነው። *የመጠበቂያም ማማ፤* የማቴ 21፥33 ማብ ይመ።

12፥7 *ርስቱ የእኛ ይሆናል፤* በአይሁድ ሕግ መሠረት ወራሽ የሌለው ንብረት፣ “ባለቤት እንደሌለው” ስለሚቈጠር ማንም ተነሥቶ ባለ መብት ነኝ ሊል ይችላል። ጭሰኞቹ ልጅየው መሬቱን ለመውረስ የመጣ ስለ መሰላቸው፣ እርሱን ከገደልን መሬቱን መውሰድ እንችላለን ብለው አሰቡ።

12፥9 *ለሌሎች፤* የማቴ 21፥41 ማብ ይመ።

12፥10 *የማእዘን ራስ፤* የመዝ 118፥22 ማብ ይመ።

12፥12 *ስለ እነርሱ፤* በ11፥27 ስለ ተጠቀሱት የአይሁድ ሸንጎ ተወካዮች ነው።

## ለቄሳር ግብር ስለ መክፈል
12፥13-17 ተጓ ምብ - ማቴ 22፥15-22፤ ሉቃ20፥20-26

13ከዚያም በነገር እንዲያጠምዱት ከፈሪሳ
ውያንና ከሄሮድስ ወገን ሰዎች ወደ እርሱ
ላኩ:: 14እነርሱም መጥተው እንዲህ አሉት፤
"መምህር ሆይ፤ አንተ ትክክለኛ ሰው መሆ
ንህን እናውቃለን፤ የሰዎች ማንነት ስለማ
ይገድህም አታዳላም፤ የእግዚአብሔርን መንገድ
ብቻ በእውነት ታስተምራለህ፤ ለመሆኑ ለቄ
ሳር ግብር መክፈል ይገባል ወይስ አይገባም?
15እኛስ እንክፈል ወይስ አንክፈል?"
ኢየሱስ ግን ግብዝነታቸውን ዐውቆ፣
"ለምን ልታጠምዱኝ ትፈልጋላችሁ? እስቲ
አንድ ዲናር አምጡልኝና ልየው" አላቸው::
16እነርሱም አመጡለት፣ "ይህ የማን መልክ
ነው? ጽሕፈቱስ የማን ነው?" አላቸው፤
እነርሱም፣ "የቄሳር ነው" አሉት::
17ኢየሱስም፣ "የቄሣርን ለቄሳር፣ የእግዚ
አብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ" አላቸው:: እነርሱም
በእርሱ ተደነቁ::

## ጋብቻና ትንሣኤ
12፥18-27 ተጓ ምብ - ማቴ 22፥23-33፤ሉቃ20፥27-38

18ከዚህ በኋላ የሙታን ትንሣኤ የለም
የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ እርሱ መጥተው እንዲህ
ሲሉ ጠየቁት፤ 19"መምህር ሆይ፤ የአንድ ሰው
ወንድም ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ
ቢሞት፣ ይህ ሰው ሴትየዋን አግብቶ ለወን
ድሙ ዘር እንዲተካ ሙሴ ጽፎልናል:: 20ታዲያ
ሰባት ወንድማማቾች ነበሩ፤ የመጀመሪያው
አግብቷት ዘር ሳይተካ ሞተ፤ 21ሁለተኛውም
ሴትየዋን አገባት፤ እርሱም ዘር ሳይተካ ሞተ፤
ሦስተኛውም እንዲሁ፤ 22ሰባቱም አገቧት፤
ዘር ግን አልተኩም፤ በመጨረሻም ሴትየዋ
ሞተች:: 23እንግዲህ፣ ሰባቱም አግብተዋታልና
በትንሣኤ[T] ለማናቸው ሚስት ልትሆን
ነው?" አሉት::
24ኢየሱስም፣ እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"የምትስቱት እኮ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የእግ
ዚአብሔርን ኀይል ስለማታውቁ ነው! 25ሙታን
በሚነሡበት ጊዜ እንደ ሰማይ መላእክት ይሆ
ናሉ እንጂ አያገቡም፤ አይጋቡም:: 26ስለ
ሙታን መነሣት ግን፣ በሙሴ መጽሐፍ ይኸ
ውም ስለ ቍጥቋጦው በተነገረው ክፍል፣
እግዚአብሔር 'እኔ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ
አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ ነኝ' ያለውን አላነ
በባችሁምን? 27እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ
እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም፤ ስለዚህ
እጅግ ተሳስታችኋል::"

## ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ
12፥28-34 ተጓ ምብ - ማቴ 22፥34-40

28ከጸሐፍትም አንዱ መጥቶ ሲከራከሩ ሰማ
ቸው፤ ኢየሱስ ለቀረበለት ጥያቄ ተገቢውን
መልስ መስጠቱን አስተውሎ፣ "ለመሆኑ ከትእ
ዛዛት ሁሉ የሚበልጠው የትኛው ነው?" ሲል
ጠየቀው::
29ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ "ከሁሉ
የሚበልጠው ይህ ነው፤ 'እስራኤል ሆይ ስማ፤
ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤ 30አንተም ጌታ
አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣
በፍጹም ሐሳብህና በፍጹም ኀይልህ ውደድ::'
31ሁለተኛውም ይህ ነው፤ 'ባልንጀራህን እንደ
ራስህ ውደድ::' ከእነዚህም የሚበልጥ ትእዛዝ
የለም::"
32ጸሐፊውም እንዲህ አለው፤ "መምህር ሆይ፤
መልካም ብለሃል፤ እርሱ አንድ መሆኑን፣ ከእር
ሱም ሌላ አለመኖሩን መናገርህ ትክክል

12፥13 ማቴ12፥10፤ 22፥16፤ማር3፥6
12፥17 ሮሜ13፥7
12፥18 ሐሥ4፥1፤ 23፥8፤1ቆሮ15፥12
12፥19 ዘዳ25፥5
12፥24 2ጢሞ3፥15-17
12፥25 1ቆሮ15፥42፡49:52
12፥26 ዘፀ3፥6
12፥28 ሉቃ10፥25-28፤20፥39
12፥30 ዘዳ6፥4:5
12፥31 ዘሌ19፥18፤ ማቴ5፥43
12፥32 ዘዳ4፥35፡39፤ኢሳ45፥6:14፤46፥9

T23 አንዳንድ ቅጆች *በትንሣኤ ሰዎች ከሙታን ሲነሡ* የሚል አላቸው

*12፥13-17፤* ይህ የተፈጸመው በሕማማቱ ሰሞን ማክሰኞ ዕለት ከቤተ መቅደሱ አደባባዮች በአንዱ ሊሆን ይችላል::

12፥13 ***ከፈሪሳውያንና፤*** የ2፥16 ማብ ይመ:: ***ከሄሮድስ ወገን፤*** የ3፥6 ማብ ይመ:: በገሊላ በሚያስተምርበት ጊዜ ኢየሱስን ለመግደል የተጠነሰሰው ሤራ እየከረረ መጥቶ፣ በዚህ ጊዜ የባሰ እየተጠናከረ ሄዶአል::

12፥14 ***ለቄሳር ግብር መክፈል፤*** በይሁዳ ምድር ይኖሩ የነበሩ አይሁድ ለሮማዊው ንጉሠ ነገሥት ግብር የመክፈል ግዴታ ነበረባቸው:: ግብሩም በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውምና አንዳንዶቹ ላለመክፈል በድፍረት ውሳኔ አድርገው ነበር፤ ለንጉሠ ነገሥቱ ግብር መክፈል ማለት የሮማውያንን ገዥነት አምኖ የመቀበል ያህል ነበርና፤ የማቴ 22፥15-17 ማብ ይመ::

12፥15 ***ዲናር፤*** የ6፥37፤ ማቴ 22፥19 ማብ ይመ::

12፥17 ***የቄሳርን ለቄሳር … ስጡ፤*** የማቴ 22፥21 ማብ ይመ:: ለእግዚአብሔር ያለብን ግዴታ ሳይጣስ በመንግሥትም በኩል የምንወጣው ግዴታ አለ (ሮሜ 13፥1-7፤ 1ጢሞ 2፥1-6፤ ቲቶ 3፥1-2፤ 1ጴጥ 2፥13-17 ይመ)::

12፥18 ***የሙታን ትንሣኤ የለም የሚሉ፤*** በትንሣኤ ሙታን አያምኑም፤ የሚቀበሉትም አምስቱን የሙሴ መጻሕፍት ብቻ ነበር፤ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውንም የአባቶች ወግና ልማድ ፈጽሞ አይቀበሉም ነበር (የማቴ 15፥2 ማብ ይመ):: እነዚህ አመለካከታቸው ከፈሪሳውያንና ከተራዎቹ አይሁድ ሃይማኖተኞች ጋር እንዳይጣጣሙ አድርጎአቸዋል:: ***ሰዱቃውያን፤*** ሀብታሞችና በቅንጦት የሚኖሩ የአይሁድ ክፍል ናቸው:: በአብዛኛው ይኖሩ የነበሩት በኢየሩሳሌም ሲሆን፣ ቤተ መቅደሱን መንከባከብና ማስተዳደር ቀዳሚ ተግባራቸው ነበር:: ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን ቍጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም እንኳ፣ በፖለቲካና በሃይማኖት ጉዳይ ተሰሚነታቸው ከፍተኛ ነበር፤ የማቴ 3፥7፤ ሉቃ 20፥27፤ ሐሥ 4፥1 ማብ ይመ::

*12፥19፤* የማቴ 22፥24 ማብ ይመ::

12፥26 ***በሙሴ መጽሐፍ፤*** የመጀመሪያዎቹ አምስቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት (ኦሪቶቹ) ናቸው:: ***ስለ ቍጥቋጦው ፤*** በዘፀ 3፥1-6 ያለውን ለመጥቀስ የተለመደ አባባል ነው (ስለ ኤልያስ በ1ነገ 19፥1-10 ላይ የተጻፈው በሮሜ 11፥2 እንዴት እንደ ተጠቀሰ ይመ)::

12፥28 ***ከ … ሁሉ የሚበልጠው የትኛው ነው?*** የአይሁድ መምህራን በሕጉ ውስጥ 613 አንቀጽ ያሏቸው መመሪያዎች አሉ ከማለታቸውም በላይ፣ እነዚሁኑ፣ "ከባድ" ("ትልቅ")፣ "ቀላል" ("ትንሽ") ትእዛዛት በማለት መድበዋቸው ነበር::

*12፥29፤* ጌታ የጠቀሰው የመጀመሪያው ጥቅስ በዕብራይስጥ "ሽማዕ" በመባል ይታወቃል፤ ይኸውም በዕብራይስጡ በዘዳ 6፥4 ጥቅሱ፣ "ሽማዕ" በሚል ቃል ስለሚጀምር ነው፤ "ሽማዕ" በአማርኛ "ስማ" ማለት ነው:: ጸሎተኞች የሆኑ አይሁድ ጧት ማታ ለጸሎት በሚቀርቡበት ጊዜ፣ "ሽማዕ"ን በመድገም ሃይማኖታቸውን ይገልጻሉ:: እስከ ዛሬ ድረስ በየትኛውም ምኵራብ አምልኮ የሚጀመረው በዚሁ፣ "በሽማዕ" ነው::

*12፥31፤* ባልንጀራን መውደድ እግዚአብሔርን እወዳለሁ ከሚል ሰው የሚጠበቅና የዚሁ ሰው የባሕርይ ገንዘቡ መሆኑን ለማሳየት፣ ኢየሱስ በዘሌ 19፥18 የተመለከተውን፣ በ"ሽማዕ" ላይ አከለበት:: ***ባልንጀራህን፤*** ሉቃ 10፥25-37 ይመ::

ነው፤ 33እርሱን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም
አእምሮህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኀይልህ
መውደድ፣ እንዲሁም ባልንጀራህን እንደ ራስህ
መውደድ ከሚቃጠል መሥዋዕት ሁሉና
ከሌሎችም መሥዋዕቶች ይበልጣል::"
34ኢየሱስም በማስተዋል እንደ መለሰለት
አይቶ፣ "አንተ ከእግዚአብሔር መንግሥት የራ
ቅህ አይደለህም" አለው:: ከዚህ በኋላ ሊጠ
ይቀው የደፈረ ማንም አልነበረም::

## ክርስቶስ የማን ልጅ ነው?

12፥35-37 ተጓ ምብ - ማቴ24፥41-46፤
ሉቃ 20፥41-44
12፥38-40 ተጓ ምብ - ማቴ23፥1-7፤
ሉቃ 20፥45-47

35ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ አደባባይ በሚ
ያስተምርበት ጊዜ እንዲህ ሲል ጥያቄ አቀረበ፤
"ጸሐፍት እንዴት ክርስቶስ የዳዊት ልጅ
ነው ይላሉ? 36ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ሲናገር፣
"ጌታ ጌታዬን፣ 'ጠላቶችህን ከእግርህ
በታች እስካደርጋቸው ድረስ በቀኜ ተቀመጥ'
አለው::" ይላል፤
37ታዲያ ዳዊት ራሱ 'ጌታ' ካለው፣ ዳዊት
እንዴት ተመልሶ ልጁ ይሆናል?"::
ብዙ ሕዝብም በደስታ ይሰማው ነበር::
38በሚያስተምርበትም ጊዜ እንዲህ አለ፤
"ከጸሐፍት ተጠንቀቁ፤ የተንዘረፈፈ ቀሚስ
ለብሰው መዞርን ይወዳሉ፤ በየአደባባዩም
የአክብሮት ሰላምታ ይሻሉ፤ 39በምኩራብ
ከፍተኛውን ወንበር፣ በግብዣም ቦታ የከበሬታን
ስፍራ ይፈልጋሉ፤ 40በረጅም ጸሎታቸው እያሳበቡ
የመበለቶችን ቤት ያራቍታሉ፤ እነዚህ የባሰ
ፍርድ ይቀበላሉ::"

12፥33 1ሳሙ15፥22፤ ሆሴ6፥6፤ሚክ6፥6-8፤ ዕብ10፥8
12፥34 ማቴ3፥2፤ 22፥46፤ሉቃ20፥24
12፥35 ማቴ9፥27፤ 26፥55
12፥36 2ሳሙ23፥2፤መዝ110፥1፤ ማቴ22፥44
12፥37 ዮሐ12፥9
12፥39 ሉቃ11፥43
12፥41 2ነገ12፥9፤ ዮሐ8፥20
12፥44 2ቆሮ8፥12
13፥2 ሉቃ19፥44
13፥3 ማቴ4፥21፤ 21፥1
13፥5 ቍ22፤ ኤር29፥8፤ኤፌ5፥6፤ 2ተሰ2፥3፡10-12፤ 1ጢሞ4፥1፤ 2ጢሞ3፥13፤ 1ዮሐ4፥6

## የመበለቲቱ ስጦታ

12፥41-44 ተጓ ምብ - ሉቃ21፥1-4

41ኢየሱስ በገንዘብ ማስቀመጫው አንጻር
ተቀምጦ ብዙ ሰዎች ስጦታቸውን ወደ ቤተ
መቅደሱ ገንዘብ ማስቀመጫ ሣጥን ሲያስገቡ
ይመለከት ነበር:: ብዙ ሀብታሞች ብዙ ገንዘብ
አስገቡ፤ 42አንዲት ምስኪን መበለት ግን ከአንድ
ሳንቲም የማይበልጡ ሁለት የናስ ቤሳዎች
አስገባች::
43ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ፣ እንዲህ
አላቸው፤ "እውነት እላችኋለሁ፤ ይህቺ ድኻ
መበለት ሣጥኑ ውስጥ ከጣሉት ከሌሎቹ የበ
ለጠ አስገባች:: 44እነዚህ ሁሉ ከተረፈው ሀብታ
ቸው ሰጡ፤ እርሷ ግን በድኽነት ዐቅሟ
ያላትን ሁሉ አውጥታ ለመኖሪያ የሚሆናትን
እንዳለ ሰጠች::"

## የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች

13፥1-37 ተጓ ምብ - ማቴ 24፥1-51፤ሉቃ21፥5-36

13 ከቤተ መቅደስ ሲወጣ ከደቀ መዛ
ሙርቱ አንዱ፣ "መምህር ሆይ፤
ድንጋዮቹ እንዴት እንደ ሆኑ፣ ሕንጻውም
እንዴት ውብ እንደ ሆነ እይ" አለው::
2ኢየሱስም መልሶ፣ "እነዚህን ታላላቅ ሕንጻ
ዎች ታያለህን? አንዱ ድንጋይ በሌላው ላይ
እንደ ሆነ አይቀርም፤ ሁሉም ፈራሽ ነው" አለው::
3ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ ትይዩ፣ በደብረ
ዘይት ተራራ ላይ ተቀምጦ ሳለ ጴጥሮስ፣
ያዕቆብ፣ ዮሐንስና እንድርያስ እንዲህ ሲሉ ጠየ
ቁት፤ 4"ይህ መቼ እንደሚሆን ንገረን፤ የዚ
ህስ ሁሉ ፍጻሜ ምልክቱ ምንድን ነው?"
5ኢየሱስም እንዲህ ይላቸው ጀመር፤
"ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤

12፥33 *ከሚቃጠል መሥዋዕት ሁሉና ከሌሎችም መሥዋዕቶች፤* ሰውየው ጥያቄውን ያቀረበውና ኢየሱስም የመለሰለት በቤተ መቅደስ ግቢ ውስጥ ለመሆኑ ይህ በቂ ማስረጃ ነው (11፥27 ይመ)::

12፥34 *ከእግዚአብሔር መንግሥት፤* የማቴ 3፥2 ማብ ይመ::

12፥35 *በቤተ መቅደሱ አደባባይ፤* የ 11፥27 ማብ ይመ:: *ክርስቶስ፤* የግሪክ ቃል ሲሆን፣ ትርጕሙ "የተቀባ" ማለት ነው:: *የዳዊት ልጅ፤* የ10፥47 ማብ ይመ:: መሲሑ ከዳዊት ዘር እንደሚመጣ ብዙዎቹ ያውቁ ነበር::

12፥36 *ጌታ ጌታዬን ... አለው፤* እግዚአብሔር የዳዊት ጌታ ለሆነው ለመሲሑ አለው ማለት ነው:: (የመዝ 110፥1 ማብ ይመ):: ጌታ ኢየሱስ ይህን የጠቀሰው መሲሑ የዳዊት ዘር ብቻ ሳይሆን፣ ከዳዊትም በላይ የዳዊት ጌታ መሆኑን ለማሳየት ነው::

12፥38 *የተንዘረፈፈ ቀሚስ፤* ጸሐፍት ጫፉ መሬት የሚነካ ባለ ዘርፍ የነጭ ሐር ቀሚስ ይለብሱ ነበር::

12፥39 *በምኩራብ ከፍተኛውን ወንበር፤* ቅዱሳት መጻሕፍት በውስጡ ከሚቀመጡበት ሣጥን ፊት ለፊት ያለው አግዳሚ ወንበር ሲሆን፣ በምኩራብ ውስጥ ለአምልኮ የተቀመጡ ሁሉ እዚያ የተቀመጡትን ሊያዩአቸው ይችሉ ነበር::

12፥40 *የመበለቶችን ቤት ያራቍታሉ፤* ጸሐፍቱ ቋሚ ደመወዝ ስላልነበራቸው ኑሮአቸውን የሚገፉት በበጎ አድራጊዎች ልግስና ነበር፤ የዚህ ዐይነት ሥርዐት ዐጕል በመሆኑ የግል ጥቅም ለማሳደድ ያመቻል፤ በተለይ መበለቶች ለዚህ ዐይነቱ ብዝበዛ የተጋለጡ ናቸው::

12፥41 *ወደ ቤተ መቅደሱ ገንዘብ ማስቀመጫ፤* በቤተ መቅደሱ ግቢ ውስጥ የሴቶች አደባባይ በሚባለው ስፍራ ይቀመጥ ነበር:: በዚህ ስፍራ ወንዶችም ሴቶችም መገኘት ይችላሉ፤ ሴቶች ግን ወደ ቤተ መቅደሱ ዋና ሕንጻ መጠጋት አይፈቀድላቸውም:: የምጽዋት ሣጥኑ የጥሩምባ ቅርጽ ያላቸው 13 አፎች አሉት፤ መባውም የሚሰበሰበው ከምእመኑ ነው::

12፥42 *ከአንድ ሳንቲም የማይበልጡ ... የናስ ቤሳዎች፤* በዚያን ዘመን በፓሌስቲና ምድር ይሠራባቸው የነበሩ አነስተኛ የገንዘብ ክፍልፋዮች ናቸው:: መበለቲቱ የሰጠችው መባ አነስተኛ ቢሆንም፣ ያመጣችው "ያላትን ሁሉ" ነው (ቍ 44፤ የ2ቆሮ 8፥12 ማብ ይመ)::

12፥43 *እውነት እላችኋለሁ፤* የ 3፥28 ማብ ይመ::

*13፥1-37፤* ማርቆስ በዚህ ምዕራፍ ላይ ያሰፈረው ገለጻ፣ 'የደብረ ዘይት ተራራ ምእላድ' ተብሎ ይታወቃል፤ ይህም በአምስት ክፍል ይመደባል፡- (1) ቤተ መቅደሱ እንደሚፈርስ ኢየሱስ የተናገረው ትንቢትና የደቀመዛሙርቱ ጥያቄ (ቍ 1-4)፤ (2) ከአታላዮችና በመጨረሻው ዘመን ከሚታዩ ሐሰተኛ ምልክቶች ስለ መጠንቀቅ (ቍ 5-23)፤ (3) ስለ ሰው ልጅ መምጣት (ቍ 24-27)፤ (4) የበለሷ ምሳሌ (ቍ 28-31)፤ (5) ንቁቶ ስለ መጠባበቅ የተሰጠ ምክር (ቍ 32-37)::

13፥1 *ድንጋዮቹ እንዴት እንደ ሆኑ፤* አይሁዳዊው ታሪክ ጸሓፊ ዮሴፍ ወልደ ክርዮን (ዮሲፉስ) እንደ ገለጸው፣ እነዚህ ድንጋዮች ነጫጭ ነበሩ፤ አንዳንዶቹ ርዝመታቸው 11 ሜትር ከፍታቸው 4 ሜትር፣ ስፋታቸውም 5 ሜትር ነበር::

*13፥2፤* የማቴ 24፥2 ማብ ይመ::

13፥3 *በደብረ ዘይት ተራራ፤* የ11፥1 ማብ ይመ:: *ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ ዮሐንስና እንድርያስ፤* 1፥16-20 ይመ::

*13፥4፤* ደቀ መዛሙርቱ የቤተ መቅደሱ መፍረስ የዓለምን ፍጻሜ የሚያስከትል መስሎአቸው ነበር (ማቴ 24፥3 ይመ):: *ምልክቱ፤* ደቀ መዛሙርቱ ቤተ መቅደሱ የሚፈርስበትና የዘመኑ ፍጻሜ መቃረቡን የሚያውቁበት መንገድ ነው::

13፥5 *ተጠንቀቁ፤* ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ በሰጠው ምእላድ በዚሁ ምዕራፍ በቍ 9፡23፡33፡35፡37 ላይ በተለያየ አባባል ማሳሰቢያ መስጠቱ፣ ከትምህርቱ ዐላማዎች አንዱ፣ ደቀ መዛሙርቱ በአንዳንድ ሁኔታ እንዳይታለሉ ለማስጠንቀቅ እንደ ሆነ ግልጽ ነው::

6“ብዙዎች፣ ‘እኔ እርሱ ነኝ’ እያሉ በስሜ
ይመጣሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ። 7ስለ
ጦርነትና ስለ ጦርነት ወሬ በምትሰሙበት
ጊዜ አትደንግጡ፤ ይህማ መሆን አለበት፤
ፍጻሜው ግን ገና ነው። 8ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣
መንግሥት በመንግሥት ላይ ይነሣል፤ በብዙ
ቦታም የመሬት መንቀጥቀጥና ራብ ይሆናል፤
እነዚህ ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው።
9“ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ ለአካባቢ ሸንጎ
አሳልፈው ይሰጧችኋል፤ በምኵራብ ይገርፏ
ችኋል፤ ምስክር ትሆኑም ዘንድ በእኔ ምክ
ንያት በገዦችና በነገሥታት ፊት ትቆማ
ላችሁ። 10አስቀድሞ ግን ወንጌል ለሕዝብ
ሁሉ መሰበክ አለበት። 11ተይዛችሁ ለፍርድ
በምትቀርቡበት ጊዜ፣ በዚያች ሰዓት የሚሰ
ጣችሁን ተናገሩ እንጂ ምን እንናገራለን በማ
ለት አስቀድማችሁ አትጨነቁ፤ የሚናገረው
መንፈስ ቅዱስ እንጂ እናንተ አይደላች
ሁምና።

12“ወንድም ወንድሙን፣ አባትም ልጁን ለሞት
አሳልፎ ይሰጣል፤ ልጆች በወላጆቻቸው ላይ
ያምፃሉ፤ ይገድሏቸዋልም። 13በእኔ ምክንያት
በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤
እስከ መጨረሻው የሚጸና ግን ይድናል።
14“‘የጥፋት ርኵሰት’ ስፍራው ባልሆነ ቦታ
ቆሞ በምታዩት ጊዜ አንባቢው ያስተውል፤
በይሁዳ ያሉ ወደ ተራሮች ይሽሹ፤ 15በቤቱ
ጣራ ላይ ያለ አይውረድ፤ ንብረቱንም ለማውጣት
ወደ ቤቱ አይግባ፤ 16በእርሻ ቦታ ያለ ልብሱን
ለመውሰድ አይመለስ። 17በእነዚያ ቀናት ለነፍሰ
ጡሮችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው! 18ይህም በክረ
ምት እንዳይሆን ጸልዩ፤ 19በመጀመሪያ እግዚ
አብሔር ፍጥረትን ከፈጠረበት ጊዜ አንሥቶ
እስከ አሁን ድረስ፣ እንዲሁ ደግሞም ወደ ፊት
አቻ የሌለው ታላቅ መከራ ይሆናልና። 20ጌታ
ቀኖቹን ባያሳጥራቸው ኖሮ ማንም ባልዳነ
ነበር፤ ስለ መረጣቸው ስለ ምርጦቹ ሲል
ግን ቀኖቹን አሳጥሮአል። 21በዚያን ጊዜ
ማንም፣ ‘እነሆ፤ ክርስቶስ[ሀ] እዚህ ነው?’ ቢላችሁ
ወይም፣ ‘እነሆ፤ እዚያ ነው’ ቢላችሁ አትመኑ።
22ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት ተነ
ሥተው፣ ምልክቶችንና ድንቆችን በማድረግ፣
ቢቻላቸው የተመረጡትን እንኳ ያስታሉ።
23ስለዚህ ተጠንቀቁ፤ ጊዜው ሳይደርስ ሁሉን
ነግሬአችኋለሁ።

24“በዚያን ጊዜ፣ ከመከራው በኋላ ‘ፀሓይ
ትጨልማለች፣
ጨረቃም ብርሃኗን አትሰጥም፤
25ከዋክብት ከሰማይ ይረግፋሉ፤
የሰማይ ኀይላትም ይናወጣሉ።’
26“በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በታላቅ ኀይልና
ግርማ በደመና ሲመጣ ያዩታል። 27እርሱም
መላእክቱን ልኮ ከአራቱ ነፋሳት፣ ከምድር ዳርቻ
እስከ ሰማያት ዳርቻ ምርጦቹን ይሰበስባል።
28“ምሳሌውን ከበለስ ተማሩ፤ ቅርንጫፏ
ሲለመልም፣ ቅጠሏ ሲያቈጠቍጥ በጋ እንደ
ተቃረበ ታውቃላችሁ፤ 29እንዲሁ ደግሞ እነዚህ
ነገሮች መፈጸማቸውን ስታዩ እንደ ቀረበ፣
በደጅም እንደ ሆነ ዕወቁ። 30እውነት እላችኋለሁ፣
እነዚህ ነገሮች እስከሚፈጸሙ ድረስ ይህ
ትውልድ[ለ] አያልፍም፤ 31ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤
ቃሌ ግን አያልፍም።

## ቀኑና ሰዓቱ አይታወቅም

32“ነገር ግን ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያችም
ሰዓት ከአብ በቀር፣ የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ፣

ሀ21 ወይም መሲሑ
ለ30 ወይም ዘር

13፥9 ማቴ10፥17
13፥11 ማቴ10፥19፡20፤ሉቃ12፥11፡12
13፥12 ሚክ7፥6፤ ማቴ10፥21፤ ሉቃ12፥51-53
13፥13 ማቴ10፥22፤ ዮሐ15፥21
13፥14 ዳን9፥27፤ 11፥31፤12፥11
13፥17 ሉቃ23፥29
13፥19 ማር10፥6፤ ዳን9፥26፤12፥1፤ ኢል2፥2
13፥21 ሉቃ17፥23፤21፥8
13፥22 ማቴ7፥15፤ ዮሐ4፥48፤ 2ተሰ2፥9፡10
13፥23 2ጴጥ3፥17
13፥25 ኢሳ13፥10፤ 34፥4፤ማቴ24፥29
13፥26 ራእ1፥7
13፥27 ዘካ2፥6
13፥30 ማር9፥1፤ ሉቃ17፥25
13፥31 ማቴ 5፥18
13፥32 ሐሥ1፥7፤ 1ተሰ5፥1፡2

13፥6 *‘እኔ እርሱ ነኝ’፤* መሲሑ ነኝ ማለት ነው።

13፥7 *ፍጻሜው፤* የሚያመለክተው የኢየሩሳሌምን መጥፋት ሳይሆን፣ የዘመኑን መጨረሻ ነው (ማቴ 24፥3 ይመ)።

13፥8 *የምጥ፤* የማቴ 24፥8 ማብ ይመ።

13፥9 *ለአካባቢ ሸንጎ፤* የምኵራብ አለቆችን ያቀፈ መንፈሳዊ ጉባኤ ነው። *ይገርፏችኋል፤* የአይሁድን ሕግ መተላለፍ በግርፋት የሚያስቀጣ ሲሆን፣ ከፍተኛው ቅጣት ሠላሳ ዘጠኝ ጅራፍ ነበር (2ቆሮ 11፥23-24 ይመ)።

13፥10 *አስቀድሞ፤* ከዘመን ፍጻሜ በፊት ማለት ነው (ማቴ 24፥14 ይመ)

13፥13 *እስከ መጨረሻው የሚጸና፤* እስከ መጨረሻው በእምነት መጽናት፣ ድነት ማግኘትን ያመለክታል (ከዕብ 3፥14፤ 6፥11-12፤ 10፥36 ጋር ያነጻጽሩ)።

13፥14 *የጥፋት ርኵሰት፤* የዳን 9፥25-27፤ ማቴ 24፥15 ማብ ይመ። *ስፍራው ባልሆነ ቦታ ቆሞ፤* 2ተሰ 2፥4 ይመ። *በይሁዳ ያሉ ወደ ተራሮች ይሽሹ፤* የማቴ 24፥16 ማብ ይመ።

13፥15 *በቤቱ ጣራ፤* የ2፥4፤ ሉቃ 17፥31 ማብ ይመ።

13፥16 *ልብሱን፤* የማቴ 5፥40 ማብ ይመ።

13፥17 *ለነፍሰ ጡሮችና ለሚያጠቡ፤* በአስጨናቂ ሁኔታ የሚሰደዱትን ሁሉ የሚወክሉ ናቸው።

13፥18 *በክረምት፤* ከባድ ዝናብ ዘንቦ፣ ወንዞች ሞልተው ከታሰበበት ቦታ ለመድረስ የሚያቅትበት ወቅት ነው።

13፥19 *አቻ የሌለው ታላቅ መከራ፤* የማቴ 24፥21 ማብ ይመ።

13፥20 *ምርጦቹ፤* የእግዚአብሔር ሰዎች የሆኑትን ነው።

13፥21 *ክርስቶስ፤* የማቴ1፥7 አማራጭ ትርጕም ይመ።

13፥24 *በዚያን ጊዜ፤* የዘመን ፍጻሜን ለመግለጽ የተለመደ የብሉይ ኪዳን አባባል ነው (ኤር 3፥16፡18፤ 31፥29፤ 33፥15-16፤ ኢል 3፥1፤ ዘካ 8፥23 ይመ)። *ከመከራው፤* ቍ 19 እና የማቴ 24፥21 ማብ ይመ።

*13፥25፤* በ ቍ 24-25 ላይ የተገለጸው ሐሳብ፣ የፍጥረተ ዓለም *መናጋትና ፈጽሞ መጥፋት የሚያመለክት አይደለም፤* በወደቀው ዓለም ላይ የሚመጣውን አስፈሪ ፍርድ የሚያመለክት የተለመደ አገላለጽ ነው (ኢሳ13፥10፤ 24፥21-23፤ 34፥4፤ ሕዝ 32፥7-8፤ ኢል 2፥10፡31፤ 3፥15፤ አሞ 8፥9 ይመ)።

13፥26 *የሰው ልጅ፤* የ8፥31 ማብ ይመ። *በታላቅ ኀይልና ግርማ በደመና ሲመጣ፤* የክርስቶስን ዳግም ምጽአት የሚያመለክት ነው (8፥38፤ 2ተሰ 1፥6-10፤ ራእ 19፥11-16 ይመ)።

13፥27 *መላእክቱን፤* የዘፍ 16፥7 ማብ ይመ፤ ከራእ 14፥14-16 ጋር ያነጻጽሩ። *ምርጦቹን ይሰበስባል፤* በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የተበተነውን ሕዝቡን እንደሚሰበስብ ተነግሮአል (ዘዳ 30፥3-4፤ ኢሳ 43፥6፤ ኤር 32፥37፤ ሕዝ 34፥13፤ 36፥24)።

13፥28 *ከበለስ፤* የ11፥13 ማብ ይመ።

13፥29 *እነዚህ ነገሮች፤* በቍ 5-23 ላይ የሰፈሩት ምልክቶች፣ ከኢየሩሳሌም መጥፋትና ከዘመን ፍጻሜ በፊት የሚደርሱ ናቸው። *እንደ ቀረበ ...፤ በደጅም እንደ ሆነ፤* ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የተነገረ ይሆናል (ሉቃ 21፥31፤ ማቴ 24፥33 ይመ)።

13፥30 *እውነት እላችኋለሁ፤* የ3፥28 ማብ ይመ። *ትውልድ፤* ቃሉ የተለመደውን የሰውን ዕድሜ የሚያመለክት ሆኖ ከታሰበ፣ ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ የነበረውን ትውልድ ወይም እነዚህ ምልክቶች መፈጸም በሚጀምሩበት ጊዜ የሚገኘውን ትውልድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል (የሉቃ 21፥32 ማብ ይመ)።

13፥32 *ስለዚያች ቀን፤* የጌታን መገለጥ አስመልክቶ የሚነገር የብሉይ ኪዳን አባባል ነው (አሞ 8፥3፡9፡13፤ 9፥11፤ ሚክ 4፥6፤ 5፥10፤ 7፥11)፤ ይኸውም የሰው ልጅ እንደሚመጣ የሚያመለክት ነው (ቍ26)። *መላእክት፤* የዘፍ16፥7 ማብ ይመ።

ወልድም ቢሆን፣ ማንም አያውቅም:: 33ስለዚህ
ጊዜው መቼ እንደሚሆን አታውቁምና ተጠ
ንቀቁ፤ ትጉ፣ ጸልዩም*:: 34ይህም ቤቱን
ለአገልጋዮቹ ትቶ፣ እያንዳንዱን አገልጋይ
በየሥራ ድርሻው ላይ አሰማርቶ፣ በረኛው ነቅቶ
እንዲጠብቅ አዝዞ የሄደውን ሰው ይመስላል::
35እንግዲህ የቤቱ ባለቤት በምሽት ወይም
በውድቅት፣ በዶሮ ጩኸት ወይም ጎሕ ሲቀድ
እንደሚመጣ አታውቁምና ተግታችሁ ጠብቁ፤
36ድንገት ሲመጣ ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ!
37ለእናንተ የምነግራችሁን ለሰው ሁሉ እናገ
ራለሁ፤ ተግታችሁ ጠብቁ!"

## ኢየሱስን ሽቶ የቀባችው ሴት

14፥1-11 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥2-16
14፥1፡2፡10፡11 ተጓ ምብ - ሉቃ22፥1-6
14፥3-8 ማመ - ዮሐ12፥1-8

14 ፋሲካና የቂጣ በዓል ሊከበር ሁለት
ቀን ሲቀረው፣ የካህናት አለቆችና
ጸሐፍት ኢየሱስን የሚይዙበትና የሚገድሉበትን
ዘዴ ይፈልጉ ነበር:: 2ሆኖም፣ "ሕዝቡ ዐመፅ
እንዳያነሣ በበዓሉ ሰሞን መሆን የለበትም"
ይባባሉ ነበር::

3እርሱም በቢታንያ በለምጻሙ ስምዖን ቤት
በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፣ አንዲት ሴት ዋጋው
እጅግ ውድ የሆነ ንጹሕ የናርዶስ ሽቱ የተሞ
ላበት የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ ይዛ መጣች፣
ቢልቃጡንም ሰብራ ሽቱውን በራሱ ላይ
አርከፈከፈችው::
4በዚያ ከነበሩት አንዳንዶቹ በድርጊቱ ተቈጥ
ተው እንዲህ ይባባሉ ነበር፤ "ሽቱው ለምን
በከንቱ ይባክናል? 5ከሦስት መቶ ዲናር በላይ
ተሽጦ፣ ገንዘቡን ለድኾች መስጠት ይቻል
ነበር::" ሴትየዋንም ነቀፏት::
6ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው፤ "ተዉአት፣
ለምን ታስቸግሯታላችሁ? መልካም ነገር
አድርጋልኛለች:: 7ድኾች ምን ጊዜም ከእና
ንተ ጋር ናቸው፤ በፈለጋችሁ ጊዜ ልትረዷቸው
ትችላላችሁ፤ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር
አልኖርም፤ 8እርሷ ማድረግ የምትችለውን
ያህል አድርጋለች፤ ለመቃብሬ እንዲሆን ሰውነቴን
አስቀድማ ቀብታለች:: 9እውነት እላችኋለሁ፤
ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በሚሰበክበት
በማንኛውም ስፍራ እርሷ ያደረገችው መታሰቢያ
ሆኖ ይነገርላታል::"
10ከዚህ በኋላ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ የሆነው
የአስቆሮቱ ይሁዳ አሳልፎ ሊሰጠው ወደ
ካህናት አለቆች ሄደ:: 11እነርሱም ይህን ሲሰሙ
ደስ አላቸው፤ ገንዘብ ሊሰጡትም ቃል ገቡለት፤
ስለዚህ እርሱን አሳልፎ የሚሰጥበትን ምቹ
ጊዜ ይጠባበቅ ነበር::

## የጌታ እራት

14፥12-26 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥17-30፤ ሉቃ22፥7-23
14፥22-25 ተጓ ምብ - 1ቆሮ11፥23-25

12የፋሲካ በግ በሚታረድበት በቂጣ በዓል
የመጀመሪያው ቀን፣ ደቀ መዛሙርቱ ወደ

13፥33 1ተሰ5፥6
13፥34 ማቴ25፥14
13፥37 ሉቃ12፥35-40
14፥1 ማቴ12፥14፤ ዮሐ11፥55
14፥3 ማቴ21፥17፤ ሉቃ7፥37-39
14፥7 ዘዳ15፥11
14፥8 ዮሐ19፥40
14፥9 ማቴ24፥14፤ ማር16፥15
14፥10 ማቴ10፥4፤ ማር3፥16-19
14፥12 ዘፀ12፥1-11፤ ዘዳ16፥1-4፤1ቆሮ5፥7

*33 ጸልዩ የሚለው ቃል በአንዳንድ ትጆች አይገኝም::

*ወልድም ቢሆን፤* በመሠረቱ የእግዚአብሔር አብ ዕቅድ ከእግዚአብሔር ወልድ የተሰወረ ሊሆን አይችልም:: ጌታ ሥጋ ሆኖ ፍጹም ሰው በመሆን ከአብ ጋር መስተካከልን ለጊዜው በገዛ ፈቃዱ ትቶአል (ፊል 2፥6-8 ይመ)፤ በምድራዊ ሕይወቱም ብዙ ነገር ማድረግ ሲችል ለዐላማው ሲል ራሱን ወስኖአል (ማቴ 26፥53-54፤ ሉቃ9፥29-36 ይመ):: ስለዚህ ያን ቀን በተመለከተ፣ "ወልድም ቢሆን እንኳ አያውቀውም" ሲል ዕውቀቱን እስከ ጊዜው በገዛ ፈቃዱ እንደ ተወ እናያለን እንጂ፣ በሥላሴ አካላት ዘንድ መበላለጥን አያመለክትም (ዮሐ 10፥30 ይመ):: *ማንም አያውቅም፤* የዘመኑ ፍጻሜ መቼ እንደሚሆን ቍልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነገር ካለ፣ የእምነት ዕንቅፋት ይሆናል እንጂ አንጻች አያግዝም:: አንዳንድ ምልክቶች ተሰጥተዋል፤ ይሁን እንጂ የወደፊቱን ሁኔታ በዝርዝርና በቅደም ተከተል እንዲያመለክቱ ተብሎ አይደለም::

13፥35 *በምሽት ወይም በውድቅት፣ በዶሮ ጩኸት ወይም ጎሕ ሲቀድ፤* ሮማውያን ሌሊቱን ከፍለው ጊዜን የሚለዩበት አራቱ የሌሊት ጊዜያት መለኪያ ናቸው (የማቴ 14፥25 ማብ ይመ)::

14፥1 *ፋሲካ፤* የጌታ መልአክ የግብፃውያንን የበኵር ልጅ ገድሎ የዕብራውያኑ ቤት ግን ሳይነካ ማለፉን የሚያስታውሱበት የአይሁድ በዓል ነው (ዘፀ 12፥13፡23፡27 ይመ):: የበግ ጠቦት ወይም የፍየል ግልገል የሚያርዱት በ"ኒሳን" (ከመጋቢት እስከ ሚያዝያ) ወር በዐሥራ አራተኛው ቀን ሲሆን፣ የሚበሉትም በፀሐይ መግቢያና በእኩለ ሌሊት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር:: የአይሁድ የቀን አቈጣጠር የሚጀምረው ፀሐይ መጥለቂያ ላይ ስለ ሆነ፣ የፋሲካ በዓል የሚደረገው በኒሳን ወር በዐሥራ አምስተኛው ቀን ነው:: *የቂጣ በዓል፤* ይህ በዓል ከፋሲካ ዕለት ጀምሮ እርሾ ያልገባበት ቂጣ በተከታታይ ለሰባት ቀን የሚበላበት በዓል ነው (ዘፀ 12፥15-20፤ 23፥15፤ 34፥18፤ ዘዳ 16፥1-8 ይመ):: *የካህናት አለቆች፤* የ8፥31 ማብ ይመ:: *ጸሐፍት፤* የማቴ 2፥4 ማብ ይመ::

14፥2 *በበዓሉ ሰሞን መሆን የለበትም፤* በፋሲካ በዓልና ለአንድ ሳምንት በሚቈየው የቂጣ በዓል ሰሞን፣ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ቍጥር ከአምሳ ሺህ እስከ ብዙ መቶ ሺህ ይደርስ ነበር፤ ይህን ያህል ብዛት ባለውና በቀላሉ ሊነሣሣ በሚችል ሕዝብ መካከል ኢየሱስን መንካት ሁከት ሊያስከትል ይችላል::

*14፥3-9፤* ይህ ሁኔታ በዮሐንስ ወንጌል የተፈጸመው የሕማማት ሰሞን ከመግባቱ በፊት ነው (ዮሐ 12፥1 ይመ):: ማቴዎስና ማርቆስ ግን የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎችን ጥላቻና የይሁዳን ክሕደት፣ ኢየሱስን ሽቶ ከቀባችው ሴት ፍቅርና ቅን አገልግሎት ጋር ለማነጻጸር ሲሉ ታሪኩን ወደ ፋሲካው ሰሞን ያቀረቡት ይመስላል::

14፥3 *ቢታንያ፤* የማቴ 21፥17 ማብ ይመ:: *ለምጻሙ ስምዖን፤* የማቴ 26፥6 ማብ ይመ:: *በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፤* እየተመገበ ሳለ ማለት ነው:: *አንዲት ሴት፤* ከዮሐንስ ወንጌል (12፥3) እንደምንረዳው ይህች ሴት የማርታና የአልአዛር እኅት የነበረችው ማርያም ናት:: *ናርዶስ፤* በአብዛኛው በሕንድ አገር ከሚበቅል የተክል ዐይነት የሚገኝ ሽቱ ሲሆን፣ ሽቱው የሚሠራው ከዚሁ ተክል ሥሮች ከሚወጣ ጥሩ መዐዛ ካለው ዘይት ነው:: *የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ፤* የታሸገ ባለ ረጅም አንገት የሽቱ መያዣ ሲሆን፣ ሽቱው ሲፈለግ ዐንገቱ ላይ ይሰበራል፤ ቢልቃጡም የሚይዘው ሽቱ አንድ ጊዜ ለመቀባት በቂ ነበር:: *በራሱ ላይ አርከፈከፈችው፤* በበዓላት ሽቱ መቀባባት የተለመደ ነበር (መዝ 23፥5፤ ሉቃ 7፥46 ይመ):: የሴትየዋ አድራጎት ምን ያህል ለጌታ የተሰጠ ሕይወት እንዳላት ያሳያል::

14፥4 *በዚያ ከነበሩት አንዳንዶቹ፤* ማቴዎስ (26፥8) ደቀ መዛሙርት እንደ ሆኑ ሲናገር፣ ዮሐንስ (12፥4-5) ደግሞ ለይቶ የአስቆሮቱ ይሁዳ ነው ይላል::

14፥5 *ለድኾች ማስጠት፤* በፋሲካ ዋዜማ ለድኾች ምጽዋት መስጠት በአይሁድ ዘንድ የተለመደ ነበር (ዮሐ 13፥29 ይመ)::

14፥7 *ድኾች ምን ጊዜም ከእናንተ ጋር ናቸው፤* እንዲህ በማለቱ ኢየሱስ ለድኾች አይጨነቅም ማለት አይደለም፤ እርሱ ራሱ ለችግረኞች የሚራራ ነውና (ማቴ 6፥2-4፤ ሉቃ 4፥18፤ 6፥20፤ 14፥13፡21፤ 18፥22፤ ዮሐ 13፥29 ይመ)::

14፥8 *ለመቃብሬ እንዲሆን፤* የቀብር ሥርዐት ከመፈጸሙ በፊት፣ አስከሬንን መዐዛ ባለው ዘይት መቀባት በአይሁድ ዘንድ የተለመደ ነበር (16፥1 ይመ):: ለወንጀለኛ ግን እንደዚህ ያለ ሥርዐት ስለማይፈጸምለት፣ ኢየሱስ እንደ ወንጀለኛ ተቈጥሮ እንደሚገደል ከወዲሁ የሚያመለክት ይመስላል::

14፥9 *እውነት እላችኋለሁ፤* የ3፥28 ማብ ይመ:: *ወንጌል፤* የ1፥1 ማብ ይመ::

14፥10 *የአስቆሮቱ ይሁዳ፤* የ3፥19 ማብ ይመ:: *ካህናት አለቆች፤* የ8፥31 ማብ ይመ:: በፋሲካ በዓል ኢየሱስን ለመያዝ


# የሕማማት ሳምንት

ቢታንያ፣ ደብረ ዘይትና
ኢየሩሳሌም

**4.** ቤተ መቅደሱን ማንጻት ሰኞ

ማቴ 21:10—17
ማር 11:15—18
ሉቃ 19:45—48

በሚቀጥለው ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ፤ በዚያም በአሕዛብ አደባባይ በነጋዴዎችና የአሕዛብ ገንዘብን በአይሁድ ገንዘብ በመለወጥ ብዙ ትርፍ በሚያገኙ ገንዘብ ለዋጮች ተሞልቶ አገኘ:: ኢየሱስም እነዚህን ሰዎች አባረረ፤ ጠረጴዛዎቻቸውንም ገለባበጠ::




**7.** ፋሲካ
የመጨረሻ እራት
ሐሙስ

ማቴ 26:17-30፤ ማር 14:12-26፤
ሉቃ 22:7-23፤ ዮሐ 13:1-30

በላይኛው ክፍል ኢየሱስ ራሱንና ደቀ መዛሙርቱን ለሞቱ አዘጋጀ:: የፋሲካ መብል የተለየ ትርጉም እንዲኖረው አደረገ:: የቆረሰው እንጀራና በጽዋ ያለው ወይን በቅርብ የሚሠዋውን ሥጋውንና የሚፈሰውን ደሙን እንደሚወክሉ አሳየ:: በዚህም «የጌታ እራትን» ሥርዓት መሠረተ:: ከዘመሩ በኋላ ከፊቱ ያለውን በማወቅ በጣም ወደ ጸለየበት ስፍራ ወደ ጌቴሰማኒ ሄዱ::

**8.** ስቅለት- ዐርብ ማቴ 27:1-66፤ ማር 15:1-47፤ ሉቃ 22:66-23:56፤ ዮሐ 18:28-19:37


አልፎ ከተሰጠ፣ ከታሰረ፣ ደቀ መዛሙርቱ ከተለዩት፣ በሐሰት ከተከሰሰ፣ ከተካደ፣ ወታደሮች ከመቱትና ካፌዙበት በኋላ «የራስ ቅል» ወደ ተባለ ስፍራ መስቀል ተሸክሞ እንዲሄድ ተደረገ፤ በዚያም ከሌሎች ሁለት እስረኞች ጋር ሰቀሉት::

**9.** መቃብሩ

የኢየሱስ ሥጋ ከምሽቱ 12:00 በፊት በመቃብሩ ውስጥ ዋለ:: ዐርብ ማታ፣ ሰንበት ጀምሮ እስኪያልቅ በመቃብር ውስጥ ነበረ::

**10.** ትንሣኤ- እሁድ ማቴ 28:1-13፤ ማር 16:1-20፤ ሉቃ 24:1-49፤ ዮሐ 20:1-31

ጠዋት በማለዳ ወደ መቃብሩ የሄዱት ሴቶች የመቃብሩ መዝጊያ ድንጋይ ተንከባሎ አገኙት:: አንድ መልአክም ኢየሱስ ሕያው እንደሆነ ነግሮአቸው መልእክት ላካቸው:: ኢየሱስ በአትክልት ስፍራ ለመግደላዊት ማርያም፣ ከዚያም ለጴጥሮስ፣ በኤማሁስ መንገድ ይጓዙ ለነበሩ ሁለት ደቀ መዛሙትና በኋላም ከቶማስ በስተቀር ለሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ታየ:: የትንሣኤው እውነተኝነት የተረጋገጠ ነው::




**5. የክርክርና የምሳሌዎች ቀን**
**ማክሰኞ**

ማቴ 21:23-24:51፤ ማር 11:27-13:37፤
ሉቃ 20:1-21:36

በኢየሩሳሌም
በካህናት የተዘጋጀበትን ወጥመድ አመለጠ::

ከደብረ ዘይት ላይ ሆኖ
ኢየሩሳሌምን ተመለከተ::
(ማክሰኞ ከሰዓት በኋላ፣
ትክክለኛ ቦታው አይታወቅም)
በምሳሌ አስተማራቸው፤ ሕዝቡንም ከፈሪሳውያን እንዲጠበቁ አስጠነቀቃቸው:: የሄሮድስ ቤተ መቅደስ እንደሚፈርስ አስቀድሞ ተናገረ፤ ለደቀ መዛሙርቱም ወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮችና ስለ ዳግም ምጻቱ ነገራቸው::

**6. የዕረፍት ቀን**
**ረቡዕ**
በወንጌላት ውስጥ አልተጠቀሰም

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለዚህ ቀን ምንም አል ጠቀሱም፤ ሆኖም የቀናት መቀጠል (ማር 14:1፤ ዮሐ 12:1) በወንጌላት ውስጥ ሌላ ቀን እንዳለ የሚያመለክት ይመስላል::

የሮማውያን መንገድ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ቀጥ ያለ ዳገት ሆኖ የተሠራ ሲሆን፣ በምሥራቅ የይሁዳ ምድረ በዳ በምዕራብ ደግሞ የቄድሮን ሸለቆ በአስገራሚ እይታ ይገኛሉ::

**1. ቢታንያ መድረሱ**
**ዐርብ ዮሐ 12:1**

ኢየሱስ ከወዳጆቹ ከማርያም፣ ማርታና አልዓዛር ጋር ለመሆን ከፋሲካ ስድስት ቀን ቀደም ብሎ ቢታንያ ደረሰ:: በሚቀጥለው ማክሰኞ ምሽት ኢየሱስ እዚያው ቢታንያ እያለ ማርያም ትሕትናን ለማሳየት እጅግ ውድ በሆነ ሽቱ የኢየሱስን እግር ቀባች:: ይህ ድርጊት ማርያም ለኢየሱስ ራሷን መስጠቷንና ልታገለግለውም ሙሉ ፈቃደኛነቷን ያመለክታል::

**2. ሰንበት- የዕረፍት ቀን**
**ቅዳሜ**
በወንጌላት ውስጥ አልተጠቀሰም

የሚቀጥለው ቀን ሰንበት ስለሆነ በባሕሉ እንደ ተለመደው ጌታ ከወዳጆቹ ጋር ቀኑን አሳለፈ::

**3. በክብር መግባት**
**እሁድ**
ማቴ 21:1-11፤ ማር 11:1-11፤
ሉቃ 19:28-44፤ ዮሐ 12:12-19

ሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ኢየሱስ የተነገረለትን ትንቢት ለመፈጸም በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ (ዘካ 9:9):: ሕዝቡ «ሆሳዕና» በማለት መዝ 118:25-26 ባለው ቃል ተቀበለው:: ይህም መሲሑ እንደ ሆነና የሚመጣው የእስራኤል ንጉሥ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው::

ኢየሱስ ቀርበው፣ “የፋሲካ እራት የት እንድ
ናዘጋጅልህ ትፈልጋለህ?” አሉት።
13 እርሱም ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን እን
ዲህ ሲል ላካቸው፤ “ወደ ከተማ ሂዱ፤ እንስራ
ውሃ የተሸከመ ሰው ይገናኛችኋል፤ 14 ወደሚገ
ባበት ቤትም ተከተሉት፤ የቤቱንም ጌታ፣
“ ‘መምህሩ፣ ከደቀ መዛሙርቴ ጋር የፋሲካን
ራት የምበላበት የእንግዳ ማረፊያ የትኛው
ነው?’ ” ብሎአል በሉት፤ 15 እርሱም በሰገነቱ
ላይ የተሰናዳና የተነጠፈ ሰፊ አዳራሽ ያሳያ
ችኋል፤ እዚያ አዘጋጁልን።”
16 ደቀ መዛሙርቱም ወጥተው ወደ ከተ
ማዪቱም ሄዱ፤ ማንኛውም ነገር ኢየሱስ
እንዳላቸው ሆኖ አገኙት፤ ፋሲካውንም አሰ
ናዱ።
17 በመሸም ጊዜ ኢየሱስ ከዐሥራ ሁለቱ ጋር
መጣ። 18 በማዕድ ላይ ሳሉም፣ “እውነት እላች
ኋለሁ፣ ከመካከላችሁ አንዱ፣ አብሮኝ የሚበ
ላው እርሱ አሳልፎ ይሰጠኛል” አላቸው።
19 እነርሱም አዘኑ፤ እያንዳንዳቸውም፣ “እኔ
እሆንን?” ይሉት ጀመር።
20 እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “ከዐሥራ ሁለቱ
አንዱ፣ ከእኔ ጋር እጁን በወጭቱ ውስጥ
የሚያጠልቀው ነው። 21 የሰው ልጅስ ስለ
እርሱ እንደ ተጻፈው ይሄዳል፤ የሰውን ልጅ
አሳልፎ ለሚሰጥ ለዚያ ሰው ግን ወዮለት፤
ያ ሰው ባይወለድ ይሻለው ነበር።”
22 ሲበሉም እንጀራ አንሥቶ ባረከ፤ ቈርሶም
ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸውና፣ “እንኩ፤ ይህ
ሥጋዬ ነው” አላቸው፣
23 ጽዋውንም አንሥቶ፤ አመስግኖም ሰጣቸው፤
ሁሉም ከዚያ ጠጡ።
24 ደግሞም እንዲህ አላቸው፤ “ይህ ስለ
ብዙዎች የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው፤
25 “እውነት እላችኋለሁ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት
አዲሱን የወይን ፍሬ እስከምጠጣበት እስከዚ
ያች ቀን ድረስ ዳግም ይህን አልጠጣም።”
26 ከዚህ በኋላ መዝሙር ዘምረው ወደ ደብረ
ዘይት ተራራ ወጡ።

## ጴጥሮስ እንደሚክደው ኢየሱስ አስቀድሞ ተናገረ

14፥27-31 ተጓ ምብ - ማቴ26፥31-35

27 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እንዲህ ተብሎ
እንደተጻፈ፣ ሁላችሁ ትክዱኛላችሁ፤
‘እረኛውን እመታለሁ
በጎቹም ይበተናሉ’ ”
28 ከተነሣሁ በኋላ ግን፣ ቀድሜአችሁ ወደ
ገሊላ እሄዳለሁ።”
29 ጴጥሮስም፣ “ሁሉም ቢሰናከሉ እንኳ እኔ
አላደርገውም” አለ።
30 ኢየሱስም፣ “እውነት እልሃለሁ፤ በዚህች
ሌሊት ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮኽ፣ ሦስት
ጊዜ ትክደኛለህ” አለው።
31 ጴጥሮስም፣ “ከአንተ ጋር ብሞት እንኳ ከቶ
አልክድህም” በማለት ይበልጥ አጽንቶ ተናገረ።
ሁሉም ደግሞ እንደዚሁ አሉ።

## ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ጸለየ

14፥32-42 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥36-46፤ ሉቃ22፥40-46

32 ከዚህ በኋላ ጌቴሴማኒ ወደሚባል ስፍራ
ሄዱ፤ ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን፣ “እኔ ስጸልይ

14፥15 ሐሥ1፥13
14፥20 ዮሐ13፥18-27
14፥21 ማቴ8፥20
14፥22 ማቴ14፥19
14፥23 1ቆሮ10፥16
14፥24 ማቴ26፥28
14፥25 ማቴ3፥2
14፥26 ማቴ21፥1
14፥27 ዘካ13፥7
14፥28 ማር16፥7
14፥30 ቍ66-72፤ ሉቃ22፥34፤ ዮሐ13፥38
14፥31 ሉቃ22፥33፤ ዮሐ13፥37

24 አንዳንድ ቅጆች ሐዲስ የሚለው ቃል የላቸውም።
30 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ሁለት ጊዜ የሚለው ሐረግ የላቸውም።

ዕቅድ ባይኖራቸውም፣ ይኸኛው ያላሰቡት መልካም አጋጣሚ ሆነላቸው (ቍ 2 ይመ)።

14፥11 *ገንዘብ፤* ሠላሳ ጥሬ ብር ነው (ማቴ 26፥15)።

14፥12 *በቂጣ በዓል የመጀመሪያው ቀን፤* በመሠረቱ የኒሳን ወር ዐሥራ አምስተኛው ቀን የፋሲካ ማግሥት ማለት ነው (የቍ 1 ማብ ይመ)፤ ይሁን እንጂ፣ “የፋሲካ በግ በሚታረድበት” የሚለው ሐረግ ቀኑን የኒሳን ወር ዐሥራ አራተኛው ቀን ያደርገዋል፤ የፋሲካ በግ የሚታረደው በዚህ ቀን ነበርና (ዘፀ 12፥6)። አንዳንድ ጊዜ ስምንቱ ቀን በሙሉ የቂጣ በዓል በመባል ስለሚታወቅ፣ “በቂጣ በዓል የመጀመሪያው ቀን” የተባለው የኒሳን ወር ዐሥራ አራተኛውን ቀን ሊሆን ይችላል።

14፥13 *ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን፤* ጴጥሮስንና ዮሐንስን ነው (ሉቃ 22፥8)። *እንስራ ውሃ የተሸከመ ሰው፤* በዚያ ጊዜ በነበረው ልማድ እንስራ የሚሸከሙት ሴቶች ብቻ ስለ ነበሩ፣ ሰውየውን ለይቶ ማወቅ አስቸጋሪ አልነበረም።

14፥14 *የእንግዳ ማረፊያ የትኛው ነው?* በአይሁድ ልማድ መሠረት ማንኛውም የኢየሩሳሌም ነዋሪ የፋሲካን በዓል ለማክበር ከሩቅ የመጣ ምእመን ማረፊያ ሲጠይቀው የመስጠት ባህል ነበረው። ጌታም እንደዚህ ዐይነት ልብ ያለውን ባለ ማረፊያ ቤት ከሩቁ ዐውቆአል።

14፥15 *አዘጋጁልን፤* ዝግጅቱ ለፋሲካ በዓል የሚያስፈልገውን ምግብና መጠጥ ሁሉ ይጨምራል፤ ይኸውም ቂጣ፣ የወይን ጭማቂ፣ መራራ ቅጠል፣ ወጥና የበግ ጠቦት ነበር።

14፥17 *በመሸም ጊዜ፤* በሕማማት ሰሞን ሐሙስ ዕለት ማለት ነው።

14፥18 *በማዕድ ላይ ሳሉም፤* በመሠረቱ የፋሲካ እራት የሚበላው ተቁሞ ሲሆን (ዘፀ 12፥11)፣ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን ግን ጋደም ብሎ ግራ እጅን በመደገፍ ነበር። *እውነት እላችኋለሁ፤* የ3፥28 ማብ ይመ።

14፥20 *ከእኔ ጋር እጁን በወጭቱ ውስጥ የሚያጠልቀው፤* የማቴ 26፥23 ማብ ይመ።

14፥21 *የሰው ልጅ፤* የ8፥31 ማብ ይመ። *ስለ እርሱ እንደ ተጻፈው፤* ኢየሱስ ይህን ሲናገር በኢሳ 53 ላይ፣ “ስለሚሠቃየው አገልጋይ” የተጻፈው ክፍል በልቡ እንዳለ አያጠራጥርም።

*14፥22፤* የጌታን እራት በተመለከተ በአዲስ ኪዳን አራት ትረካዎች አሉ (ማቴ 26፥26-28፤ ማር 14፥22-24፤ ሉቃ 22፥19-20፤ 1ቆሮ 11፥23-25)። የማቴዎስና የማርቆስ ትረካ በጣም ይመሳሰላሉ፤ የሉቃስና የጳውሎስም ተመሳሳይነት አላቸው። በሁሉም ትረካ የሚከተሉት ነጥቦች ይገኛሉ፦ እንጀራን ማንሣት፣ ማመስገን ወይም መባረክ፣ እንጀራውን መቍረስ፣ “ይህ፣ ሥጋዬ ነው” ማለት፣ ጽዋውን ማንሣት፣ ደሙ ከኪዳኑ ጋር ግንኙነት እንዳለው ገለጻ ማድረግ። የጌታ እራት ሥርዐት ወደ ፊት መከበር እንዳለበት ኢየሱስ ማዘዙን የገለጹት ጳውሎስና ሉቃስ ብቻ ናቸው። *ይህ ሥጋዬ ነው፤* ኅብስቱ ስለ እነርሱ የተሰጠውን ሥጋውን ይወክላል ማለት ነው (ሉቃ 22፥19፤ 1ቆሮ 11፥24 ይመ)።

14፥24 *ስለ ብዙዎች፤* የሮሜ 5፥15 ማብ ይመ። *የአዲስ ኪዳን ደሜ፤* ጽዋው የኢየሱስን ደም ይወክላል፤ ደሙም ሞቱን ያመለክታል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው አዲሱ ኪዳን ሊጸና የሚችለው ስርየት በሚያስገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ብቻ ነው (ኤር 31፥31-34፤ ዕብ 8፥8-12 ይመ፤ እንዲሁም የሉቃ 22፥20 ማብ ይመ)፤ የዘፀ 24፥6-8 ማብ ይመ።

14፥25 *እውነት እላችኋለሁ፤* የ3፥28 ማብ ይመ። *በእግዚአብሔር መንግሥት፤* የማቴ 3፥2 ማብ ይመ።

14፥26 *መዝሙር፤* የማቴ 26፥30 ማብ ይመ። *ደብረ ዘይት ተራራ፤* የ11፥1 ማብ ይመ።

14፥30 *እውነት እልሃለሁ፤* የ3፥28 ማብ ይመ። *ሁለት ጊዜ ሳይጮኽ፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ፤ ቍ 72 ይመ።

14፥32 *ጌቴሴማኒ፤* በደብረ ዘይት ተራራ ተዳፋት ላይ የነበረ የአትክልት ቦታ ሲሆን፣ ኢየሱስ ከሚያዘወትራቸው ቦታዎች አንዱ ነበር (ሉቃ 22፥39፤ ዮሐ 18፥2 ይመ)። የቦታው ስያሜ በዕብራይስጥ፣ “የዘይት መጭመቂያ” ማለት ነው፤ ይኸውም ዘይት ከወይራ ፍሬ እንደሚጨመቅበት ያሳያል።

እናንተ እዚህ ቈዩ" አላቸው:: [33]ጴጥሮስን፣
ያዕቆብንና ዮሐንስንም ይዞ ሄደ፤ እጅግ ያዝን
ይጨነቅ ጀመር:: [34]ደግሞም፣ "ነፍሴ እስከ
ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ እዚሁ ሁኑና ነቅታችሁ
ጠብቁ" አላቸው::
[35]ጥቂት እልፍ ብሎም በምድር ላይ በመ
ውደቅ ቢቻል ሰዓቱ ከእርሱ እንዲያልፍ
ጸለየና፣ [36]"አባ[ሩ]፤ አባት ሆይ፤ ሁሉ ነገር
ይቻልሃልና ይህን ጽዋ ከእኔ አርቀው፤ ነገር
ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን"
አለ::
[37]ተመልሶም ሲመጣ ደቀ መዛሙርቱን
ተኝተው አገኛቸው፤ ጴጥሮስንም እንዲህ
አለው፣ "ስምዖን ሆይ፣ ተኝተሃልን? አንድ
ሰዓት እንኳ ነቅተህ መጠበቅ አቃተህ? [38]ወደ
ፈተና እንዳትገቡ ትጉ፤ ጸልዩም፤ መንፈስ
ዝግጁ ነው፣ ሥጋ ግን ደካማ ነው::"
[39]እንደ ገናም ሄዶ መጀመሪያ የጸለየውን
ደግሞ ጸለየው:: [40]ዳግመኛም ሲመለስ ዐይና
ቸውን እንቅልፍ ከብዶት ተኝተው አገኛቸው፤
የሚመልሱለትንም አያውቁም ነበር::
[41]ሦስተኛ ጊዜም መጥቶ እንዲህ አላቸው፤
"አሁንም እንደተኛችሁና እንዳረፋችሁ ናችሁ?
ይበቃል! ሰዓቲቱ ደርሳለች፤ እነሆ፤ የሰው ልጅ
ለኀጢአተኞች እጅ አልፎ ይሰጣል:: [42]ተነሡ፤
እንሂድ፤ አሳልፎ የሚሰጠኝ መጥቶአል::"

### ኢየሱስ ተያዘ

14፥43-50 ተጓ ምብ - ማቴ26፥47-56፤ ሉቃ22፥47-50፤ ዮሐ18፥3-11

[43]ወዲያው እየተናገረ ሳለ ከዐሥራ ሁለቱ
አንዱ ይሁዳ መጣ፤ አብረውትም ሰይፍና
ዱላ የያዙ፣ ከካህናት አለቆች፣ ከጸሓፍትና
ከሽማግሌዎች የተላኩ ብዙ ሰዎች ነበሩ::
[44]አሳልፎ የሚሰጠውም፣ "እኔ የምስመው
እርሱ ነውና ያዙት፤ ተጠንቅቃችሁም ወሰዱት"
በማለት አስቀድሞ ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር::
[45]እንደ ደረሰም ወዲያው ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣
"መምህር ሆይ!" ብሎ ሳመው፤ [46]ሰዎቹም
ኢየሱስን ያዙት አሰሩትም:: [47]በአቅራቢያው
ቆመው ከነበሩት አንዱ ሰይፉን መዞ የሊቀ
ካህናቱን አገልጋይ ጆሮ ቈረጠ::
[48]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እንደ ወን
በዴ በሰይፍና በቈመጥ ልትይዙኝ መጣች
ሁን? [49]በየዕለቱም በቤተ መቅደስ እያስተ
ማርሁ ከእንናተ ጋር ስኖር አልያዛችሁኝም፤
መጻሕፍት ይፈጸሙ ዘንድ ይህ ሆነ::" [50]በዚህ
ጊዜ ሁሉም ትተውት ሸሹ::
[51]ዕርቃኑን ለመሸፈን በፍታ ያገለደመ አንድ
ወጣት ኢየሱስን ይከተል ነበር:: ሰዎቹም ይህን
ወጣት በያዙት ጊዜ፣ [52]ግልድሙን ጥሎ ዕራ
ቍቱን ሸሸ::

### ኢየሱስ በሸንጎ ፊት

14፥53-65 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥57-68፤ ዮሐ18፥12:13:19-24
14፥61-63 ተጓ ምብ - ሉቃ 22፥67-71

[53]ኢየሱስንም ወደ ሊቀ ካህናቱ ወሰዱት፤
በዚያም የካህናት አለቆች፣ ሽማግሌዎችና
ጸሓፍት ሁሉ ተሰበሰቡ:: [54]ጴጥሮስም ከሩቅ
እየተከተለው፣ እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ዘለቀ፤
በዚያም ተቀምጦ ከሎሌዎቹ ጋር እሳት ይሞቅ

14፥33 ማቴ4፥21
14፥34 ዮሐ12፥27
14፥35 ቍ41፤ ማቴ26፥18
14፥36 ማቴ20፥22፤ 26፥39፤ሮሜ8፥15፤ ገላ4፥6
14፥38 ማቴ6፥13፤ ሮሜ7፥22:23
14፥41 ቍ35፤ ማቴ26፥18
14፥43 ማቴ10፥4
14፥45 ማቴ23፥7
14፥49 ኢሳ53፥7-12፥ ማቴ1፥22፤ 26፥55
14፥50 ቍ27
14፥54 ማቴ26፥31 ዮሐ18፥18

[ሩ]36 በአራማይክ ቋንቋ አባት የሚጠራበት ነው::

14፥33 *ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን፤* የ5፥37 ማብ ይመ::

14፥36 *አባ አባት ሆይ፤* ከአብ ጋር ልዩ ቅርበት እንዳለው የሚያሳይ ነው:: *ይህን ጽዋ፤* ተልእኮው ይፈጸም ዘንድ ኢየሱስ ከአብ እጅ የተቀበለውን የሞት ጽዋና በላዩ የመጣውን የእግዚአብሔር ቍጣ ነው:: ኢየሱስ እንዲህ ያለው፣ ይህን ያህል ሞትን ስለ ፈራ አይደለም፤ እርሱ የፈራው ሞቱ የዓለምን ኀጢአት በራሱ ላይ እንዲ ሸከም ስለሚያደርገው ነው፤ የ10፥38 ማብ ይመ::

14፥37 *ስምዖን፤* የ1፥16 ማብ ይመ:: ለጴጥሮስ በግል የተነገረው፣ ምናልባት ከቶ ኢየሱስን አልክድም ብሎ ስለ ነበር ሊሆን ይችላል (ቍ 29-31 ይመ)::

14፥38 *ወደ ፈተና እንዳትገቡ፤* በፈተና እንዳትወድቁ ማለት ነው:: እዚህ ላይ ፈተናው አስጨናቂና አሥጊ ሁኔታ ቢደርስባቸውም ጸንቶ በእምነት አለመገኘት ነው:: *መንፈስ ዝግጁ ነው፤* የሰው መንፈስ በእግዚአብሔር ቍጥጥር ሥር ከሆነ፣ የሥጋን ድካም ይቋቋ ማል፤ አባባሉ ከመዝ 51፥12 የተወሰደ ነው::

14፥41 *የሰው ልጅ፤* የ8፥31 ማብ ይመ::

14፥43 *ይሁዳ፤* የ3፥19 ማብ ይመ:: *ሰይፍና ዱላ የያዙ... ብዙ ሰዎች፤* ከቤተ መቅደሱ አካባቢ ራቅ ባለው ቦታ፣ ሥነ ሥርዐት እንዲያስከብሩ የተመደቡ ረዳት ፖሊሶች ወይም የአገሪ ገዥው ግቢ ጠባቂዎች ናቸው:: ጌታን በመያዙ ግርግር ውስጥ ከቤተ መቅደስ ጠባቂዎች በተጨማሪ ቢያንስ የተወሰነ የሮማ ወታደር ቡድን እንደ ነበረ ዮሐንስ ይጠቍማል (18፥3):: አንዳንዶቹ ዱላ ይዘው መገኘታቸው፣ የቅርብ ጊዜ ምልምል እንደ ነበሩ ያሳያል:: *ከካህናት አለቆች፣ ከጸሓፍትና ከሽማግሌዎች፤* የ8፥31፤ ማቴ2፥4 ማብ ይመ:: ኢየሱስ እንዲያዝ የትእዛዝ ወረቀት የወጣው ከአይሁድ ሸንጎ ነበር::

14፥45 *መምህር ሆይ፤* በዕብራይስጥ፣ "ረቢ" ይባላል:: *ሳመው፤* ደቀ መዛሙርት ለመምህራቸው የአክብሮት ሰላምታ የሚያቀርቡት በመሳሳም ነበር፤ የሉቃ 22፥47 ማብ ይመ::

14፥47 *በአቅራቢያው ቆመው ከነበሩት፤* ይህ ሰው ጴጥሮስ እንደ ነበርና ጆሮውን የተቈረጠው ሎሌ ማልኮስ ይባል እንደ ነበር ከዮሐንስ ወንጌል እንረዳለን (ዮሐ 18፥10)::

14፥49 *በቤተ መቅደስ፤* የ11፥27 ማብ ይመ:: *መጻሕፍት ይፈጸሙ ዘንድ፤* በኢሳ 53፣ በተለይም በዘካ 13፥7 ላይ የተጻፈውን የሚመለከት ሊሆን ይችላል:: በዘካርያስ የተመለከተውን ኢየሱስ በቍ 27 ላይ ጠቅሶታል፤ ይህም በከፊል ይሁን እንጂ በዚህ ጊዜ ትንቢቱ ተፈጽሞአል::

14፥50 *ትተውት ሸሹ፤* በቍ 27-31 ላይ የተጻፈው እንዲፈጸም ነው::

14፥51 *አንድ ወጣት፤* ስሙ ሳይጠቀስ እንዲሁ መገለጹ፣ ይህ ሰው ይህንኑ ወንጌል የጻፈው ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ሳይሆን አይቀርም:: *በፍታ፤* በመሠረቱ አብዛኛው ሕዝብ በዚያን ዘመን ከላይ የሚደርበው ከበግ ጠጕር የተሠራ ልብስ ነበር፤ ይህ ወጣት ግን በዘብ ጠባቂው እጅ ጥሎት የሸሸው ጥሩ በፍታ በመሆኑ ከሀብታም ቤተ ሰብ እንደ ሆነ ያመለክታል::

14፥52 *ዕራቍቱን ሸሸ፤* ወጣቱ የውስጥ ልብስ አለመልበሱ ኢየሱስን ለመከተል በጥድፊያ እንደ ተነሣ ያመለክታል::

*14፥53-15፥15፤* በኢየሱስ ላይ የቀረበው ክስ የተካሄደው በሁለት ደረጃ ነው፤ የመጀመሪያው በአይሁድ ሸንጎ ፊት የቀረ በበት ሲሆን፣ ሁለተኛው በሮማውያን ባለ ሥልጣናት ፊት የቀረበበት ክስ ነው:: በእያንዳንዱም ደረጃ ሦስት ጊዜ ችሎት ፊት ቀርቦአል፤ በአይሁድ ሸንጎ ፊት የቀረበው:- (1) ከሁሉ በፊት ከቀድሞው ሊቀ ካህናት ከሐና ፊት ቀረበ (በዮሐ 18፥12-14:19-23 ላይ ብቻ የተጻፈው) (2) በሊቀ ካህናቱ በቀያፋና በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቀረበ (14፥53-65)፤ (3) ሌሊቱን ሙሉ ያደሩበትን ችሎት በውሳኔ በዘጋው በአይሁድ ሸንጎ ፊት ለመጨረሻ ጊዜ ቀረበ (15፥1):: በሮማውያን ችሎት ፊት የቀረበው:- (1) ጲላጦስ ፊት ቀረበ (15፥2-5)፤ (2) በሄሮድስ አንቲጳስ ፊት ቀረበ (በሉቃ 23፥6-12 ላይ ብቻ የተጻፈው)፤ (3) በጲላጦስ ፊት የተጀመረው ቀጥሎ በዚሁ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጠበት (15፥6-15):: ማርቆስ በሄሮድስ አንቲጳስ ፊት ስለ ነበረው ክስ ምንም ባለመጻፉ፣ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ በጲላጦስ ፊት የነበረው ክስ ሌላ ነገር ጣልቃ ሳይገባበት ተተርኮ ይገኛል (15፥2-15)::

14፥53 *ሊቀ ካህናቱ፤* የቀድሞውን ሊቀ ካህናት የሐና አማች (የልጁ ባል) ቀያፋ ነው:: *የካህናት አለቆች፣ ሽማግሌዎችና ጸሓፍት ሁሉ፤* ጠቅላላው የአይሁድ ሸንጎ ማለት ነው::

14፥54 *እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ፤* ጕዳዩ በምሥጢር እንዲ

ነበር::
55የካህናት አለቆችና ሸንጎው በሙሉ ኢየ
ሱስን ለመግደል ምስክር ፈለጉ፤ ነገር ግን ማግ
ኘት አልቻሉም:: 56ብዙዎች በሐሰት ቢመስክሩ
በትም፣ ቃላቸው አንድ ሊሆን አልቻለም::
57አንዳንዶቹም ተነሥተው እንዲህ ሲሉ
በሐሰት መሰከሩበት፤ 58"ይህ፣ 'የሰው እጅ
የሠራውን ቤተ መቅደስ አፍርሼ፣ በሦስት ቀን
ሌላ የሰው እጅ ያልሠራውን እሠራለሁ' ሲል
ሰምተነዋል::" 59ይህም ሆኖ፣ እንኳ ምስክ
ርነታቸው አንድ አልሆነም::
60ሊቀ ካህናቱም ተነሥቶ በፊታቸው በመ
ቆም፣ "እነዚህ በአንተ ላይ የሚመሰክሩት ምን
ድን ነው? ለምን አትመልስም?" በማለት ኢየ
ሱስን ጠየቀው:: 61ኢየሱስ ግን ዝም አለ፤
ምንም መልስ አልሰጠም::
ሊቀ ካህናቱም እንደ ገና፣ የቡሩኩ ልጅ፣
ክርስቶስ[ሀ] አንተ ነህን? ሲል ጠየቀው::
62ኢየሱስም፣ "አዎን ነኝ፤ የሰው ልጅ በኀ
ያሉ ቀኝ ሲቀመጥ፣ በሰማይ ደመናም ሲመጣ
ታዩታላችሁ" አለ::
63ሊቀ ካህናቱም ልብሱን ቀደደና፣ እንዲህ
አለ፤ "ሌላ ምን ምስክር ያስፈልገናል? 64ስድቡን
ሰምታችኋል፤ ታዲያ፣ ምን ይመስላችኋል?"፤
እነርሱም ሞት ይገባዋል በማለት በአንድ
ቃል ፈረዱበት:: 65በዚህ ጊዜ አንዳንዶቹ ይተፉ
በት ጀመር፤ ዐይኑንም ሸፍነው በጡጫ እየ
መቱት፣ "እስቲ ትንቢት ተናገር!" ይሉት
ነበር:: ሎሌዎችም በጥፊ እየመቱ ወሰዱት::

14፥55 ማቴ5፥22
14፥58 ዮሐ2፥19
14፥61 ኢሳ53፥7፤ ማቴ16፥16፤27፥12፡14፤ማር15፥5፤ ሉቃ23፥9፤ዮሐ4፥25፡26፤19፥9
14፥62 ራእ1፥7
14፥63 ዘሌ10፥6፤ 21፥10፤ዘኍ14፥6፤ ሐሥ14፥14
14፥64 ዘሌ24፥16
14፥65 ማቴ16፥21
14፥66 ቍ54
14፥67 ቍ54፤ ማር1፥24
14፥68 ቍ30:72
14፥70 ቍ30: 68:72፤ሐሥ2፥7
14፥71 ቍ30:72
14፥72 ቍ30:68

## ጴጥሮስ ኢየሱስን አላውቀውም አለ

14፥66-72 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥69-75፤ ሉቃ22፥56-62፤ ዮሐ18፥16-18:25-27

66ጴጥሮስ በግቢው ውስጥ በታችኛው በኩል
ሳለ፣ ከሊቀ ካህናቱ ገረዶች አንዲቱ መጣች፤
67ጴጥሮስ እሳት ሲሞቅ አይታ ትኵር ብላ
ተመለከተችውና፣
"አንተም ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር ነበርህ"
አለችው::
68እርሱ ግን፣ "የምትዪውን አላውቅም፤
አይገባኝምም" በማለት ካደ:: ከዚያም ወደ
መግቢያው በር ወጣ አለ፤ በዚህ ጊዜ ዶሮ
ጮኸ[ለ]::
69ገረዲቱም ባየችው ጊዜ እዚያ ለቆሙት፣
"ይህ ሰው ከእነርሱ አንዱ ነው" ብላ እንደ ገና
ተናገረች:: 70እርሱ ግን አሁንም ካደ::
ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ በዚያ የቆሙት ሰዎች
ጴጥሮስን፣ "የገሊላ ሰው እንደ መሆንህ መጠን፣
በእርግጥ አንተ ከእነርሱ አንዱ ነህ" አሉት::
71እርሱ ግን፣ "እናንተ የምትሉትን ሰው
እኔ አላውቀውም" እያለ ይምል ይገዘት ጀመር::
72ወዲያውም ዶሮ ሁለተኛ[ሐ] ጮኸ:: ጴጥ
ሮስም፣ "ዶሮ ሁለት ጊዜ[መ] ከመጮኹ በፊት
ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ" ያለው የኢየሱስ ቃል
ትዝ አለው:: ከዚያም ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ::

[ሀ]61 ወይም *መሲሑ*
[ለ]68 አንዳድ ቅጆች *ዶሮ ጮኸ* የሚለው የላቸውም::
[ሐ]72 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ሁለተኛ* የሚለው ቃል የላቸውም::
[መ]72 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ሁለት ጊዜ* የሚለው ሐረግ የላቸውም

ያዝ ሲሉ የአይሁድ ሸንጎ አባላት በቀያፋ ቤት ሳይሰበሰቡ አልቀሩም::

14፥55 *ሸንጎው፤* ከፍተኛው የአይሁድ ፍርድ ሰጪ አካል ሲሆን፣ አይሁድ "ሰንሄድሪን" ይሉታል:: በአዲስ ኪዳን ዘመን የሸንጎ ስብጥር ከሦስት ዐይነት ክፍሎች ነበር፤ ይኸውም ከካህናት አለቆች፣ ከሽማግሌዎችና ከጸሐፍት የተውጣጣ ነበር፤ ቍጥራቸውም ሰብሳቢ ከሆነው ከሊቀ ካህናቱ ጋር 71 ነበር:: አይሁድ በሮም ግዛት ሥር በነበሩበት ዘመን፣ የአይሁድ ሸንጎ የሞት ፍርድ መበየን ካለመቻሉ በስተቀር፣ ከፍተኛ ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር (ዮሐ 18፥31 እና የማቴ 27፥2 ማብ ይመ)::

14፥56 *ብዙዎች በሐሰት ቢመሰክሩበትም፤* በአይሁድ የሕግ ሥነ ሥርዐት፣ ምስክሮችም እንደ ከሳሽ ይቈጠሩ ነበር:: *ቃላቸው አንድ ሊሆን አልቻለም፤* በዘዳ 19፥15 መሠረት አንድ ተከሳሽ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ምስክሮች በአንድ ቃል ካልመሰከሩበት ወንጀለኛ አይባልም::

*14፥58፤* ኢየሱስ በየትኛውም ወንጌል በቀጥታ እንዲህ ብሎ አልተናገረም፤ ምናልባት ይህን ያሉት በዮሐ 2፥19 ላይ የተናገረውን በማጣመም በስያፍ መጥቀሳቸው ነው::

14፥61 *የቡሩኩ ልጅ፤* "ቡሩክ" የሚለው፣ የእግዚአብሔር ስም በቀጥታ ሳይጠራ በአክብሮት የሚጠራበት መንገድ ነበር (የ11፥30 ማብ ይመ):: "የቡሩኩ ልጅ" የሚለው፣ "የእግዚአብሔር ልጅ" ከሚለው ጋር አቻነት አለው፤ በዚህ አገባቡ ግን መለኮትነቱን ለመግለጽ ሳይሆን መሲሕነቱን ለማመልከት ነው፤ በአይሁድ ሕዝብ እምነት መሠረት ሕዝቡን ለመታደግ ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው መሲሕ፣ ሰው እንጂ አምላክ አልነበረም:: *ክርስቶስ፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ::

14፥62 *የሰው ልጅ፤* የ8፥31 ማብ ይመ:: ይህ፣ "የሰው ልጅ" የሚለው አባባል በዳን 7፥13 እና በመዝ 110፥1 ላይ የሰፈረውን ሐሳብ አንድ ላይ ያገናኛል::

14፥63 *ልብሱን ቀደደና፤* የጥልቅ ኀዘን ወይም የድንጋጤ ምልክት ነው (ዘፍ 37፥29፤ 2ነገ 18፥37፤ 19፥1 ይመ):: ሊቀ ካህናቱ ግን ልብሱን የቀደደው፣ የኢየሱስን መልስ በእግዚአብሔር ላይ የተሰነዘረ የስድብ ቃል አድርጎ በመቍጠሩና የፍርድ ውሳኔ የማሳለፉ ምልክት አድርጎ ነው (የማቴ 26፥65 ማብ ይመ)::

14፥64 *ስድቡን፤* እግዚአብሔርን መሳደብ የሚባለው ኀጢአት የእግዚአብሔርን ስም መስደብ ብቻ ሳይሆን (ዘሌ 24፥10-16 ይመ)፣ ሥልጣኑን ወይም ክብሩን መጋፋትንም ይጨምራል (2፥7፤ 3፥28-29፤ ዮሐ 5፥18፤ 10፥33 ይመ):: ኢየሱስ፣ "መሲሑ እኔ ነኝ" ማለቱንና፣ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን ክብርና ሥልጣን የእርሱም እንደ ሆነ አድርጎ መናገሩ እግዚአብሔርን እንደ ተሳደበ አድርጎ ቀያፋ ቈጠረበት፣ የሙሴ ሕግም በዚህ ዐይነት መንገድ የበደለ ሰው በድንጋይ ተወግሮ እንዲሞት ያዛል (ዘሌ 24፥16)::

14፥65 *ይተፉበት ... በጡጫ እየመቱት፤* ይህ ድርጊት በነበረው ልማድ መሠረት የውግዘትና የጥላቻ መግለጫ ነው (ዘኍ 12፥14፤ ዘዳ 25፥9፤ ኢዮ 30፥10፤ ኢሳ 50፥6):: *ዐይኑንም ሸፍነው፤* ጥንት ኢሳ 11፥2-4 ላይ የሚገኘውን ሐሳብ፣ "መሲሑ ማየት ሳያስፈልገው እንዲሁ በማሽተት ይፈርዳል" በማለት የሚተረጕሙ ሰዎች ነበሩ:: ይህንኑ መሠረት በማድረግም እንደ ሸፈኑት ይገመታል:: *እስቲ ትንቢት ተናገር!* የመታህ ማን እንደ ሆነ ዕወቅ ማለታቸው ነው::

14፥66 *በታችኛው፤* ኢየሱስ በቀያፋ ቤት በላይኛው ደርብ ሲገረፍ ሳለ፣ ጴጥሮስ ታች ግቢ ውስጥ ነበረ:: *ከ ... ገረዶች አንዲቱ፤* በር ጠባቂዋ ናት (ዮሐ 18፥16)::

14፥67 *ከናዝሬቱ፤* የማቴ 2፥23 ማብ ይመ::

14፥68 *የምትዪውን አላውቅም፤ አይገባኝም፤* አይሁድ ሕግ ፊት ቀርበው ስለ አንድ ነገር አለማወቃቸውን በሥርዐቱ መሠረት የሚገልጹት ይህን በመሰለ ዐይነተኛ አባባል ነበር::

14፥70 *የገሊላ ሰው፤* የገሊላ ሰዎች በአነጋገራቸው በቀላሉ ይታወቁ ነበር:: ጴጥሮስም በአነጋገሩ የገሊላ ሰው መሆኑ ታውቆበታል፤ በሊቀ ካህናቱ ግቢ በይሁዳ ሰዎች መካከል መገኘቱም፣ የኢየሱስ ተከታይ መሆኑን መስክሮበታል::

### ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት
15፥2-15 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥11-26፤ ሉቃ23፥2፡3፡18-25፤
ዮሐ18፥29-19፥16

15 ጠዋት በማለዳ የካህናት አለቆች
ከሽማግሌዎች፣ ከጸሐፍትና ከመላው
የሸንጎ አባላት ጋር ወዲያው ከተማከሩ በኋላ
ኢየሱስን አስረው ወሰዱት፤ ለጲላጦስም አሳ
ልፈው ሰጡት።
2ጲላጦስም፣ "አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን?"
ሲል ጠየቀው፤
ኢየሱስም፣ "አንተው አልኸው፣" በማለት
መለሰለት።
3የካህናት አለቆችም በብዙ ነገር ከሰሱት።
4ጲላጦስም፣ "ለምን መልስ አትሰጥም? እነሆ
በብዙ ነገር ከሰውሃል" ሲል እንደ ገና ጠየ
ቀው።
5ኢየሱስ ግን ምንም አልመለሰም፤ ጲላ
ጦስ ተገረመ።
6በበዓል ሕዝቡ እንዲፈታላቸው የሚጠ
ይቁትን እስረኛ የመልቀቅ ልማድ ነበር።
7በዐመፃ ተነሣሥተው ነፍስ ከገደሉ ዐመፀ
ኞች ጋር የታሰረ በርባን የሚባል አንድ ሰው
ነበረ። 8ሕዝቡም መጥተው እንደ ተለመደው
እንዲያደርግላቸው ጲላጦስን ለመኑት።
9ጲላጦስም፣ "የአይሁድን ንጉሥ እንድፈታ
ላችሁ ትፈልጋላችሁን?" ሲል ጠየቃቸው፤
10ምክንያቱም የካህናት አለቆች ኢየሱስን አሳ
ልፈው የሰጡት በቅናት መሆኑን ያውቅ ነበር።
11የካህናት አለቆች ግን በርባንን በእርሱ ምትክ
እንዲፈታላቸው እንዲጠይቁ ሕዝቡን አነሣሡ።
12ጲላጦስም እንደ ገና፣ "እንግዲያው የአይ
ሁድ ንጉሥ የምትሉትን ምን እንዳደርገው
ትፈልጋላችሁ?" አላቸው።
13እነርሱም እንደ ገና፣ "ስቀለው!" እያሉ
ጮኹ።
14ጲላጦስም፣ "ለምን? ምን የፈጸመው ወንጀል
አለ" አላቸው።
እነርሱ ግን፣ "ስቀለው!" እያሉ የባሰ ጮኹ።
15ጲላጦስም ሕዝቡን ደስ ለማሰኘት ሲል በር
ባንን ፈታላቸው፤ ኢየሱስን ግን ገርፎ እንዲሰቀል
አሳልፎ ሰጠው።

### ወታደሮች በኢየሱስ ላይ አፌዙ
15፥16-20 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥27-31

16ወታደሮቹ ፕራይቶሪዮን ወደ ተባለ ወደ
ገዡ ግቢ ወሰዱት፤ ሰራዊቱንም ሁሉ በአንድነት
ሰበሰቡ። 17ቀይ ልብስም አለበሱት፤ የእሾኽ
አክሊል ጐንጕነው በራሱ ላይ ደፉበት። 18ከዚ
ያም፣ "የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፤ ሰላም ለአንተ
ይሁን!" እያሉ እጅ ነሡት፤ 19ራሱንም በበትር
መቱት፤ ተፉበትም፤ ተንበርክከውም ሰገዱለት።
20ካፌዘቡትም በኋላም ቀዩን ልብስ ገፈፉት፤ የገዛ
ልብሱን አለበሱት፤ ሊሰቅሉትም ወሰዱት።

### የኢየሱስ ስቅለት
15፥22-32 ተጓ ምብ - ማቴ27፥33-44፤ ሉቃ23፥33-43፤
ዮሐ19፥17-24

21የአሌክሳንድሮስና የሩፎስ አባት ስምዖን
የተባለ አንድ የቀሬና ሰው ከገጠር ሲመጣ
መስቀሉን እንዲሸከም አስገደዱት።

15፥1 ማቴ5፥22፤ 27፥1፡2፤ሉቃ22፥66
15፥2 ቍ9፡12፡ 18፡26፤ማቴ2፥2
15፥5 ማር14፥61
15፥9 ቍ2
15፥11 ሐሥ3፥14
15፥15 ኢሳ53፥6
15፥16 ዮሐ18፥28፡ 33፤19፥9
15፥18 ቍ2
15፥20 ዕብ13፥12
15፥21ማቴ27፥32፤ ሉቃ23፥26፤ ሮሜ16፥13

15፥1 *ጠዋት በማለዳ፤* አንድ የሮማ ባለ ሥልጣን የዕለት ሥራውን የሚጀምረው ጎሕ ሲቀድ ነበር። *ጠዋት፤* የሕማማቱ ሰሞን ዓርብ ዕለት ነው። *ሸንጎ፤* የ14፥55 ማብ ይመ። *ከተማከሩ በኋላ፤* በዚህ ጊዜ የተማከሩት ኢየሱስ እግዚአብሔርን ተሳድቦአል ለማለት ሳይሆን፣ በመንግሥት ላይ ዐመፅ አነሣስቷል ለማለትና ሕግ ፊት ለማቅረብ ነበር (ሉቃ 23፥1-14 እና የሉቃ 23፥2 ማብ ይመ)። *ለጲላጦስ፤* ከ26-36 ዓ.ም. የይሁዳ ገዥ የነበረ የሮማ ባለ ሥልጣን ሲሆን፣ መቀመጫው በሜድትራኒያን ባሕር ጠረፍ ላይ የምትገኘው ቂሣርያ ከተማ ነበረች። (እ.ኤ.አ. በ1961 ዓ.ም. በቂሣርያ በምርምር ሥራ ላይ የነበሩ የሥነ ቅርስ ሊቃውንት፣ በጲላጦስ ዘመን የነበረና የጲላጦስ ስም የተቀረጸበት ድንጋይ በቍፋሮ አግኝተዋል።) ጲላጦስ ወደ ኢየሩሳሌም በሚመጣበት ጊዜ ታላቁ ሄሮድስ ባሠራው ግዙፍና ውብ በሆነው ቤተ መንግሥት ይቀመጥ ነበር፤ ቤተ መንግሥቱም የሚገኘው ከቤተ መቅደሱ በስተ ምዕራብ ሲሆን፣ ትንሽ ወደ ደቡብ ወረድ ብሎ ነበር። ማርቆስም በቍ16 ላይ፣ "ፕራይቶሪዮን" የሚለው ይህንኑ ቤተ መንግሥት ለማመልከት ነው፤ ኢየሱስም ተከሶ በሮማውያን ሸንጎ ፊት የቀረበው በዚሁ ቦታ ነበር።

15፥2 *ጲላጦስም ... ጠየቀው፤* በሮማውያን ፍርድ ቤት የፍርድ ውሳኔ የሚሰጠው በንጉሠ ነገሥቱ በተሾመ ብቸኛ ባለ ሥልጣን ነበር።

15፥3 *በብዙ ነገር፤* የሉቃ 23፥2 ማብ ይመ። ክሱ የወንጀል ከሆነ፣ ተጨማሪ ክሶችን አክሎ ማቅረብ የተለመደ ነበር።

15፥4 *ለምን መልስ አትሰጥም?* ኢየሱስ የመከላከያ መልስ ካልሰጠ ጲላጦስ በእርሱ ላይ እንዲፈርድበት የሮማ ሕግ ይፈቅድለታል።

15፥6 *ልማድ፤* የዮሐ 18፥39 ማብ ይመ።

15፥7 *በዐመፃ፤* ማርቆስ ይህን ዐመፃ እንደ ታወቀ ቈጥሮ ያቅርብ እንጂ፣ ከሌሎች ምንጮች ስለዚህ ዐመፅ የሚናገር አናገኝም። የሮማ መንግሥት በየቦታው በሾማቸው አስተዳዳሪዎች ሥር ይህ ዐይነት ዐመፅ በየጊዜው ይነሣ ነበር (ሉቃ 13፥1 ይመ)። *በርባን፤* "ተቀናቃኞች" የተባሉት፣ የአይሁድ የዐመፀኞች ቡድን አባል ሊሆን ይችላል።

15፥13 *ስቀለው!* የቍ 24 ማብ ይመ።

15፥15 *ገርፎ፤* ሮማውያን በጫፎቹ ላይ ዐጥንትና እርሳስ የተቋጠረባቸው ባለ ብዙ ጠፍር ዐለንጋ ይጠቀሙ ነበር። በአይሁድ ደንብ አንድ ሰው ሊገረፍ የሚገባው ግፋ ቢል አርባ ጅራፍ ነበር (በቋሚነት የተደነገገው 39 ጅራፍ ሲቈጠር ስሕተት ቢኖር 40ኛው ማስተካከያ ነበር)፤ በሮማውያን ዘንድ ግን የግርፋቱ መጠን ወሰን ስላልነበረው፣ ብዙውን ጊዜ ተገራፊዎቹ በዚያው ሕይወታቸው ያልፋል።

15፥16 *ፕራይቶሪዮን፤* ቃሉ በመጀመሪያ አንድ ጀኔራል ድንኳኑን የተከለበትን ቦታ ወይም የአንድ ጦር ሰፈር ዋና መሥሪያ ቤት ያለበትን የሚያመለክት ነበር (የቍ1 ማብ ይመ)። *ሰራዊቱንም ሁሉ፤* በፕራይቶሪዮን ይገኙ የነበሩት ወታደሮች፣ ከአይሁድ ውጭ ከፓሌስቲና ምድር ነዋሪዎች መካከል የተመለመሉ ነበሩ፤ የበላይ አለቃቸውም ወታደራዊው ገዥ ነበር።

15፥17 *ቀይ ልብስ፤* ጥንት ወታደር የሚለብሰው ካባ ሳይሆን አይቀርም፤ የቀለሙም ዐይነት ከቤተ መንግሥት ወገን መሆንን ያመለክታል (ማቴ 27፥28 ይመ)። *የእሾኽ አክሊል፤* በፓሌስቲና ምድር በብዛት ከሚገኝ እሾኻማ ተክል የተጐነጐነ ነበር። ልብሱም ሆነ አክሊሉ በኢየሱስ ላይ የተሰነዘሩ ማፌዣዎች ነበሩ።

15፥18 *የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን!* "ቄሳር ሆይ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን!" ከሚለው ለሮማ ንጉሠ ነገሥት ከሚሰጠው የአክብሮት አባባል ጋር የሚመሳሰል የፌዝ ሰላምታ ነው።

15፥19 *ተፉበት፤* በመካከለኛው ምሥራቅ ለንጉሣውያን ቤተ ሰቦች አክብሮት የሚገለጸው በመሳም ነበር፤ ወታደሮቹም በአንድ በኩል ንጉሥ ነህ እያሉት በሌላ በኩል የመሳም ተቃራኒ ተግባር በመፈጸም መቀለጃ ማድረጋቸው ይሆናል።

15፥21 *የአሌክሳንድሮስና የሩፎስ፤* የተጠቀሱት በማርቆስ ወንጌል ብቻ ነው፤ የማርቆስ አጻጻፍ በተደራስያኑ ዘንድ እንደሚታወቁ አድርጎ ነበር። በሮሜ 16፥13 የተጠቀሰውም ሰው ይኸው ሩፎስ ሊሆን ይችላል። *ስምዖን፤* የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም የመጣ አይሁዳዊ ሊሆን ይችላል ("ከቀሬና ከመጡት አይሁድ" ከሚለው ከሐሥ 6፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

22ከዚያም ኢየሱስን፣ ትርጒሙ "የራስ ቅል
ስፍራ" ወደ ተባለ ወደ ጎልጎታ ወሰዱት። 23ከከ
ርቤ ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅም ሰጡት፤
እርሱ ግን አልተቀበለም። 24ከዚያም ሰቀሉት፤
እያንዳንዱም ምን እንደሚደርሰው ለማወቅ
ዕጣ ተጣጥለው ልብሱን ተከፋፈሉ።
25ሲሰቅሉትም ጊዜው ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት
ነበረ። 26የክሱ ጽሑፍም፣ "የአይሁድ ንጉሥ"
የሚል ነበር። 27ከእርሱም ጋር ሁለት ወንበዴ
ዎችን አንዱን በቀኙ አንዱን በግራው ሰቀሉ።
28መጽሐፍ፣ "ከዐመፀኞች ጋር ተቈጠረ" ያለውም
በዚሁ ተፈጸመ[+]። 29በመንገድ የሚያልፉትም
ራሳቸውን እየነቀነቁ የስድብ ናዳ በማውረድ
እንዲህ ይሉት ነበር፤ "አዬ! ቤተ መቅደስን
አፍርሰህ በሦስት ቀን የምትሠራ አንተ ነህ፤
30እስቲ አሁን ከመስቀል ውረድና ራስህን
አድን።"
31እንዲሁም የካህናት አለቆችና ጸሐፍት በማ
ሾፍ እርስ በርሳቸው እንዲህ አሉ፤ "ሌሎችን
አዳነ፤ ራሱን ግን ማዳን አልቻለም፤ 32አይተን
እናምን ዘንድ ይህ ክርስቶስ[‡]፣ ይህ የእስራኤል
ንጉሥ እስቲ ከመስቀል ይውረድ።" ከእርሱ
ጋር የተሰቀሉትም እንደዚሁ የስድብ ናዳ ያወር
ዱበት ነበር።

15፥23 ቍ36፤ መዝ69፥21፤ ምሳ31፥6
15፥24 ምሳ22፥18
15፥26 ቍ2
15፥29 መዝ22፥7፤ 109፥25፤ዮሐ2፥19
15፥31 መዝ22፥7
15፥32 ቍ2፤ ማር1፥61
15፥33 አሞ8፥9
15፥34 መዝ22፥1
15፥36 ቍ23፤ መዝ69፥21
15፥37 ዮሐ19፥30
15፥38 ዕብ10፥19፡20
15፥39 ቍ45፤ ማቴ4፥3፤ ማር1፥1፡11፤9፥7

## የኢየሱስ መሞት

15፥33-41 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥45-56፤ ሉቃ23፥44-49

33ከስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት
ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ።
34በዘጠኝም ሰዓት ኢየሱስ፣ "ኤሎሄ፣ ኤሎሄ
ላማ ሰበቅታኒ?" ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤
ትርጓሜውም "አምላኪ፣ አምላኪ ለምን ተው
ኸኝ?" ማለት ነው።
35በዚያ ቆመው ከነበሩት አንዳንዶቹ ይህን
ሲሰሙ፣ "ኤልያስን ይጣራል" አሉ።
36ከዚያም አንድ ሰው ፈጥኖ ሄዶ የሆመጠጠ
የወይን ጠጅ በሰፍነግ ነከረ፤ በዘንግም ሰክቶ
እንዲጠጣው ለኢየሱስ አቀረበለት፤ ከዚያም፣
"ተዉት፤ እስቲ ኤልያስ መጥቶ ሲያወርደው
እናያለን" አለ።
37ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ነፍሱንም
ሰጠ።
38የቤተ መቅደሱም መጋረጃ ከላይ እስከ
ታች ከሁለት ተቀደደ። 39በኢየሱስ ትይዩ ቆሞ
የነበረውም የመቶ አለቃ እንደዚህ ጮኾ[ኀ]
ነፍሱን ሲሰጥ ባየ ጊዜ፣ "ይህ ሰው በእውነት
የእግዚአብሔር ልጅ ነበር" አለ።

[+]28 አንዳድ ቅጆች ቍ 28 የላቸውም (ኢሳ 53፥12)።
[‡]32 ወይም መሲሕ
[ኀ]39 አንዳንድ ቅጆች *እንደዚህ ጮኾ* የሚለው ሐረግ የላቸውም።

*የቀሬና፤* በሰሜን አፍሪካ ብዙ የአይሁድ ሕዝብ የሚኖሩባት የሊቢያ ዋና ከተማ ነበረች። *መስቀሉን እንዲሸከም፤* የሞት ፍርድ የተፈረደበት ሰው ክብደቱ 14-18 ኪሎ ግራም ያህል የሆነ የሚሰቀልበትን ግንድ ራሱ እስከ መሰቀያ ቦታ ድረስ ተሸክሞ እንዲሄድ ይገደድ ነበር። ኢየሱስም የራሱን መስቀል ተሸክሞ መሄድ ጀመረ (ዮሐ 19፥17 ይመ)፤ ነገር ግን ከግርፋቱ የተነሣ ደክሞት ስለ ነበር፣ ስምዖን መስቀሉን እንዲሸከምለት አስገደዱት።

15፥22 *የራስ ቅል ስፍራ፤* ወንጌላቱ ስለ ኩረብታ ያነሡት ነገር ባይኖርም፣ ቦታው የራስ ቅል የሚመስል መለስተኛ ኩረብታ ሳይሆን አይቀርም፤ ወይም በዚያ ስፍራ ብዙ ሰው በፍርድ ስለ ተገደለበት የተሰጠ ስያሜ ሊሆን ይችላል።

15፥23 *ከከርቤ ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ፤* አንድ ሰው ሥቃይ እንዳይሰማው ሰውነቱን ለማደንዘዝ ሲባል፣ ዕጣን ከወይን ጠጅ ጋር ተቀላቅሎ ይሰጥ እንደ ነበር፣ 'ታልሙድ' የተባለው የአይሁድ መጽሐፍ ማስረጃ ይሰጣል (ምሳ 31፥6 ይመ)። ከርቤ በዓረብ ምድረ በዳና በአንዳንድ የአፍሪካ ምድር ከሚገኙ ዕፀዋት የሚገኝ የዕጣን ዐይነት ነው።

15፥24 *ሰቀሉት፤* ስቅሎ መግደል የሮማውያን የሞት ቅጣት አፈጻጸም ሲሆን፣ ወንጀለኛው በመስቀል ላይ በምስማር ይቸነከር ነበር። ወፈር ያለ የብረት ምስማር በእጅ አንጓና በእግር ቍርጭምጭሚት ላይ ይመታል፤ የተሰቀለውም ሰው ቶሎ ካልሞተ ጭኖቹን በመስበር ቶሎ እንዲሞት ይደረጋል (ዮሐ 19፥33 ይመ)። የሥነ ቅርስ ተመራማሪዎች በኢየሩሳሌም አቅራቢያ በስቅላት የሞተ ሰው ሰውነቱ በመስቀል ላይ እንዴት እንደ ተመታ የሚጠቍም ማስረጃ አግኝተዋል፤ የቅሪተ አካሉ ዘመንም ከ7 ዓ.ም እስከ 66 ዓ.ም. መሆኑ ታውቋአል። በስቅላት የሚቀጡትም ባሪያዎች፣ ወራዳ ተግባር የፈጸሙና የሮማ ዜግነት የሌላቸው ወንጀለኞች ነበሩ። በመስቀል ላይ መሞት የቱን ያህል አሠቃቂና ውርደት የተሞላ እንደ ነበር በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት የነበሩ ጸሓፊዎች በግልጽ ያስረዳሉ። *ልብሱን ተከፋፍለው፤* የስቅላት ሞት የተፈረደበትን ሰው እንደ ልብሶቹ ያሉትን ጥቃቅን ነገሮች ገዳዩ ቡድን እንዲወስድ ተፈቅዶለት ነበር። የኢየሱስ ልብስ ሲባል የለበሰውና በላዩ የደረበው ልብስ፣ መታጠቂያው፣ ሰንደል ጫማውና ምናልባትም የራስ ጥምጥሙን ጭምር ሊሆን ይችላል።

15፥26 *የክሱ፤* እንዲሰቀል የተፈረደበት ሰው ወደሚሰቀልበት ቦታ ሲሄድ፣ የተከሰሰበት ወንጀል በዕንጨት ሰሌዳ ላይ ከተጻፈ በኋላ ተይዞ ወንጀለኛው ፊት ይኼዳል፤ ከዚያም ከተሰቀለው ሰው ራስ በላይ ይንጠለጠላል። *"የአይሁድ ንጉሥ"፤* የክሱ አገላለጽ በአራቱ ወንጌላት ውስጥ መጠነኛ ልዩነት ይታይበታል፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ "የአይሁድ ንጉሥ ነኝ" አለ በማለት ስቀላት እንደ ተፈረደበት አራቱም ወንጌላት ይስማማሉ።

15፥27 *ሁለት ወንበዴዎች፤* በሮማውያን ሕግ መሠረት ዝርፊያ መፈጸም በሞት አያስቀጣም፤ ስለዚህ ማርቆስ የተጠቀመበት ቃል በመንግሥት ላይ የተነሡትን ዐመፀኞች የሚያመለክት መሆን አለበት።

*15፥28፤* ጥንታዊና ተአማኒ የሆኑ የግሪክ ቅጆች በዚህ ቍጥር ላይ የተጻፈው ሐሳብ የላቸውም፤ የቍ 27 አማራጭ ትርጒም ይመ። ምናልባት ከሉቃ 22፥37 የተጠቀሰ ሊሆን ይችላል (ሉቃስ ለራሱ የወሰደው ከኢሳ 53፥12 ነው) ማርቆስ ከብሉይ ኪዳን እምብዛም አይጠቅስም።

15፥29 የ14፥58 ማብ ይመ።

15፥32 *ክርስቶስ፤* የማቴ 1፥17 አማራጭ ትርጒም ይመ። *ከእርሱ ጋር የተሰቀሉትም፤* ከሁለቱ ወንበዴዎች አንዱ ወደ መጨረሻው ሰዓት አካባቢ ንስሓ ገብቶ ኢየሱስ በመንግሥቱ እንዲያስበው ለመነው (ሉቃ 23፥39-43)።

*15፥34፤* ጌታ የተናገረው በአራማይክ ቋንቋ ቢሆንም፣ አባባሉ የዕብራይስጥ ባሕርይ አለው፤ አራማይክ ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን በፓሌስቲና ምድር በስፋት ከሚነገሩት ቋንቋዎች አንዱ ነበር። ቃላቱ ኢየሱስ የሰውን ልጆች ኀጢአት በመስቀል ላይ በተሸከመበት ጊዜ አብ ከእርሱ ዘወር በማለቱ ምን ያህል እንደ ተሰማው ያመለክታል (የመዝ 22 መግቢያውንና የመዝ 22፥1 ማብ ይመ)።

15፥35 *ኤልያስን፤* በአቅራቢያው ቆመው የነበሩት ሰዎች ኢየሱስ፣ "ኤሎሄ፣ ኤሎሄ" ብሎ ሲጮኽ ኤልያስን የሚጠራ መሰላቸው። በዚያን ዘመን ኤልያስ በጭንቅ ሰዓት ደጋጎችን ለመ ጠበቅና ጻድቃንን ለመታደግ ይመጣል የሚል እምነት ነበር (ቍ 36)።

15፥36 *የሆመጠጠ የወይን ጠጅ፤* የቀን ሠራተኞችና ወታደሮች የሚጠጡት ጒምዛዛና መናኛ የወይን ጠጅ ነው።

15፥37 *በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤* ኢየሱስ በኀይል መጮኹ ሌሎች ሰዎች በመስቀል ላይ ተሰቅለው እንደሚሞቱት ዐይነት ተራ ሞት እንዳልሞተ ያሳያል፤ እነዚያ ነፍሳቸው የምታልፈው ለረጅም ሰዓት ከመሠቃየታቸው የተነሣ ዝለውና ኀሊናቸውን ከሳቱ በኋላ ነበር።

15፥38 *የቤተ መቅደሱም መጋረጃ፤* በቅድስትና በቅድስተ ቅዱሳን መካከል የነበረው መጋረጃ ነው (ዘፀ 26፥31-33)። የመጋረጃው መቀደድ እኛ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ለመቅረብ እንድንችል፣ ክርስቶስ ስለ እኛ ወደ ሰማያዊት መቅደስ መግባቱን ያሳያል (ዕብ 9፥8-10፡12፤ 10፥19-20)።

15፥39 *የመቶ አለቃ፤* በሮማውያን ሰራዊት ውስጥ የመቶ

40በዚህ ጊዜ ሴቶች ከሩቅ ሆነው ይመለ
ከቱ ነበር፤ ከእነርሱም መካከል መግደላዊት
ማርያም፣ የታናሹ ያዕቆብና የዮሳ እናት
ማርያም፣ እንዲሁም ሰሎሜ ነበሩ፤ 41እነዚህ
ሴቶች በገሊላ ሲከተሉትና ሲያገለግሉት
የነበሩ ናቸው፤ ደግሞም አብረውት ወደ ኢየሩ
ሳሌም የመጡ ሌሎች ብዙ ሴቶች ነበሩ።

## የኢየሱስ መቀበር

15፥42-47 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥57-61፤ ሉቃ23፥50-56፤ ዮሐ19፥38-42

42ጊዜው እየመሸ መጥቶ የሰንበት ዋዜማ
ይኸውም የመዘጋጀት ቀን ሆነ፤ 43የተከበረ
የሸንጎ አባልና የእግዚአብሔርን መንግሥት
ይጠባበቅ የነበረው የአርማትያሱ ዮሴፍ በድፍ
ረት ወደ ጲላጦስ ሄዶ የኢየሱስን ሥጋ ለመ
ነው። 44ጲላጦስም እንዲህ በቶሎ መሞቱን ሲሰማ
ተደነቀ፤ የመቶ አለቃውንም ጠርቶ ከሞተ ምን
ያህል ጊዜ እንደ ሆነ ጠየቀው፤ 45መሞቱንም
ከመቶ አለቃው ካረጋገጠ በኋላ ሥጋውን ለዮሴፍ
ሰጠው። 46ዮሴፍም በፍታ ገዛ፤ ሥጋውንም
አውርዶ በበፍታው ከከፈነው በኋላ፣ ከዐለት
በተወቀረ መቃብር አኖረው፤ የመቃብሩንም
ደጃፍ በድንጋይ ገጠመው። 47ማርያም መግደላ
ዊትና የዮሳ እናት ማርያም የት እንዳኖሩት
ይመለከቱ ነበር።

## ትንሣኤው

16፥1-8 ተጓ ምብ -ማቴ 28፥1-8፤ ሉቃ24፥1-10

**16** ሰንበት ካለፈ በኋላ መግደላዊት
ማርያም፣ የያዕቆብ እናት ማርያምና
ሰሎሜ ሄደው የኢየሱስን ሥጋ ለመቀባት ሽቱ
ገዙ። 2በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ጠዋት በማ
ለዳ፣ ገና ፀሐይ እንደ ወጣች፣ ወደ መቃብሩ
በመሄድ ላይ ሳሉ፣ 3"ድንጋዩን ከመቃብሩ ደጃፍ
ላይ ማን ያንከባልልልናል?" በማለት እርስ
በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር።
4ቀና ብለው ሲመለከቱ፣ በጣም ትልቅ
የነበረው ድንጋይ ከደጃፉ ላይ ተንከባሎ አዩ።
5ወደ መቃብሩ እንደ ገቡም፣ ነጭ ልብስ
የለበሰ ጐልማሳ በቀኝ በኩል ተቀምጦ አዩና
ደነገጡ።
6እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤ "አትደንግጡ፤
የምትፈልጉት የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱ
ስን ነው፤ እርሱ ተነሥቶአል፤ እዚህ የለም፤ እርሱን
ያኖሩበት ስፍራ ይኸውላችሁ። 7ነገር ግን
ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱና ለጴጥሮስ፣
'ቀድሞአችሁ ወደ ገሊላ ይሄዳል፤ እንደ ነገ
ራችሁ እዚያ ታገኙታላችሁ' ብላችሁ ንገሯ
ቸው።"
8ሴቶቹም እየተንቀጠቀጡና እየተደነቁ ከመ
ቃብሩ ሸሽተው ወጡ፤ ፈርተው ስለ ነበር
ለማንም አንዳች አልተናገሩም።
9በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ማለዳ ከሙታን
ከተነሣ በኋላ፣ ሰባት አጋንንት ላወጣላት ለማ
ርያም መግደላዊት በመጀመሪያ ታየ። 10እር
ሷም ሄዳ፣ ከእርሱ ጋር የነበሩት እያዘኑ ሲያ
ለቅሱ አግኝታ እርሱ ሕያው መሆኑንና ለእርሷም
መታየቱን ነገረቻቸው፤ 11እነርሱ ግን አላመኗ
ትም።
12ከዚህ በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱ
ወደ ገጠር ሲሄዱ በሌላ መልክ ታያቸው።
13እነርሱም ተመልሰው ይህንኑ ለቀሩት ነገ
ሯቸው፤ ይሁን እንጂ እነርሱንም አላመኗ

15፥40 መዝ38፥11፤ ማር16፥1፤ሉቃ24፥10፤ ዮሐ19፥25
15፥41 ማቴ27፥55፡56፤ ሉቃ8፥2፡3
15፥42 ማቴ27፥62፤ ዮሐ19፥31
15፥43 ማቴ3፥2፤ 5፥22፤ሉቃ2፥25፡38
15፥45 ቍ39
15፥46 ማር16፥3
15፥47 ቍ40
16፥1 ሉቃ23፥56፤ ዮሐ19፥39፡40
16፥3 ማር15፥46
16፥5 ዮሐ20፥12
16፥6 ማር1፥24
16፥7 ማር14፥28፤ ዮሐ21፥1-23
16፥9 ማር15፥47፤ ዮሐ20፥11-18
16፥11 ቍ13፡14፤ ሉቃ24፥11
16፥12 ሉቃ24፥13-32

ወታደሮች አዛዥ ነበር። *ነፍሱን እንደ ሰጠ ባየ ጊዜ!* የቍ37 ማብ ይመ። *የእግዚአብሔር ልጅ!* የማቴ 27፥54፤ ሉቃ 23፥47 ማብ ይመ።

15፥40 *መግደላዊት ማርያም!* ከ16፥9 እና ከሉቃ 8፥2 እንደምንረዳው ኢየሱስ ከዚህች ሴት ሰባት አጋንንት አስወጥቶአል። *የታናሹ ያዕቆብና የዮሳ እናት ማሪያም!* ቍ47፤ 16፥1 ይመ። *ሰሎሜ!* የዘብዴዎስ ሚስት፣ የያዕቆብና የዮሐንስ እናት ሳትሆን አትቀርም (ማቴ 27፥56 ይመ)።

15፥42 *የመዘጋጀት ቀን!* ዓርብ ዕለት ማለት ነው። ምሽት ተቃርቦ ስለ ነበር፣ ፀሐይ ጠልቃ ሰንበት ከመግባቱ በፊት የኢየሱስን ሥጋ ከመስቀል ለማውረድ ጥድፊያ ነበር።

15፥43 *የሸንጎ!* የአይሁድ ሸንጎ ወይም "ሰንሄድሪን" ማለት ነው (የ14፥55 ማብ ይመ)። *የእግዚአብሔርን መንግሥት!* የማቴ 3፥2 ማብ ይመ። *የአርማትያሱ!* የማቴ 27፥57 ማብ ይመ። *ጲላጦስ!* የቍ1 ማብ ይመ። *የኢየሱስን ሥጋ ለመነው!* የሉቃ 23፥52 ማብ ይመ።

15፥44 *ተደነቀ!* በመስቀል ላይ የተሰቀሉ ሰዎች፣ ሁለት ሦስት ቀን ድረስ ሳይሞቱ ይቆዩ ነበር፤ ኢየሱስ ቶሎ መሞቱ ግን እጅግ የሚያስደንቅ ነበር።

15፥45 *ሥጋውን ለዮሴፍ ሰጠው!* በከፍተኛ ወንጀል ሞት ተፈርዶበት የሞተን ሰው ሬሳ፣ በተለይ ደግሞ ቤተ ዘመዶቹ ላልሆኑት ሰዎች መስጠት አልተለመደም ነበር።

15፥46 *ከዐለት በተወቀረ መቃብር!* መቃብሩ ማንም ያልተቀበረበት አዲስ እንደ ነበረና ባለቤቱም የአርማትያሱ ዮሴፍ መሆኑን ማቴዎስ ይነግረናል (ማቴ 27፥60)። ይኸው መቃብር በስቅላቱ ቦታ አጠገብ ባለው የአትክልት ስፍራ ውስጥ ነበረ (ዮሐ 19፥41 ይመ)። ኢየሱስ የተቀበረበት ቦታ መሆኑ የሚነገርለት በኢየሩሳሌም የሚገኘው የቅዱስ ስፑልቸር ቤተ ክርስቲያን፣ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት የመቃብር ቦታ እንደ ነበር ሥነ ቅርሳዊ ማረጋገጫ አለ። *በድንጋይ!* ክብና ጠፍጣፋ ድንጋይ ሲሆን፣ እያዘቀዘቀ በሚሄድ ቦታ ቍልቍል የሚንከባለል ነው።

16፥1 *ሰንበት ካለፈ በኋላ!* ቅዳሜ ምሽት በ12፡00 ሰዓት ማለት ነው። በሰንበት ዕለት መገበያየት አይቻልም ነበር። *መግደላዊት ማርያም፣ የያዕቆብ እናት ማርያምና ሰሎሜ!* የ15፥40 ማብ ይመ። *የኢየሱስን ሥጋ ለመቀባት!* ሴቶቹ ኢየሱስ ከሙታን ይነሣል የሚል ግምት አልነበራቸውም። *ሽቱ!* ሬሳ እንዳይበሰብስ በልዩ ቅባት ማሸት የአይሁድ ልማድ አልነበረም፤ እነዚህ ሴቶች ግን ሽቱ ይዘው ወደ መቃብር የሄዱት ፍቅራቸውን ለመግለጽ ያህል ነው።

16፥3 *ድንጋዩን... ማን ያንከባልልልናል?* ድንጋዩን በመቃብሩ ደጃፍ ላይ መግጠም ቀላል ነው፤ ነገር ግን አንድ ጊዜ የተዘጋጀለትን ፈር ተከትሎ ከደጃፉ ጋር ከገጠመ፣ መልሶ ማንቀሳቀስ በጣም ይከብዳል።

16፥5 *ወደ መቃብሩ እንደ ገቡም!* በሰፊው የመቃብሩ የፊት ለፊት መግቢያ፣ ወደ ውስጥ ሲዘለቅ ከፊት ለፊት የሚታይ አንድ ክፍል አለ፤ በዚህ ክፍል ወደ ውስጥ ሲገባም አራት ማእዘን የሆነ ክፍተት ይገኛል፤ ይህም ክፍተት ወደ አስከሬኑ ማስቀመጫ (ዋናው መቃብር) ይመራል። *ነጭ ልብስ የለበሰ ጐልማሳ!* ማቴዎስ (28፥2) አንድ መልአክ ይለዋል፤ የሉቃ 24፥4 ማብ ይመ።

16፥6 *የተሰቀለውን!* የ15፥ 24 ማብ ይመ። *ተነሥቶአል!* ትንሣኤ የማርቆስ ወንጌል ትረካ ከፍተኛው ደረጃ ነው። የጌታ አሟሟት የተለየና የከበረ ቢሆንም፣ ከሙታን ባይነሣ ኖሮ ፍጻሜው እጅግ አሳዛኝ በሆነ ነበር፤ ነገር ግን ሞትን አሸንፎ በመነሣቱ ኀያልነቱንና የእግዚአብሔር ልጅነቱን አስመስክሮአል (ሮሜ 1፥4)።

16፥7 *ለጴጥሮስ!* ጴጥሮስ በራሱ በመተማመኑና ከዚያም ኢየሱስን በመካዱ ጌታ ልዩ ትኩረት ሰጥቶታል (14፥29-31፡66-72)። *እንደ ነገራችሁ!* 14፥28 ይመ።

*16፥9-20!* ይህ ክፍል የማርቆስ ወንጌል አካል አይደለም የሚል ከፍተኛ ጥርጥር አለ። ዐበይት በሆኑት የጥንት ቅጂችም አይገኝም። በቃላት አመራረጥ፣ በአጻጻፍ ስልትና በትምህርተ መለኮት ይዘቱ ከቀረበው የማርቆስ ወንጌል ጋር አይጣጣምም። ወንጌሉ 16፥8 ላይ ሲያበቃ አይቀርም፤ አለዚያም የመጨረሻው ክፍል ጠፍቶ ሊሆን ይችላል።

16፥9 *ለማርያም መግደላዊት!* የ15፥40 ማብ ይመ።

*16፥12-13!* ወደ ኤማሁስ ይጓዙ ስለ ነበሩት ሁለት ሰዎች

ቸውም።
14ከዚያም ዐሥራ አንዱ በማዕድ ላይ
ሳሉ ተገለጠላቸው፤ ከተነሣ በኋላ ያዩት
ሰዎች የነገሯቸውን ስላላመኗቸው፣ አለ
ማመናቸው ንና የልባቸውን ድንዳኔ ነቀፈ።
15እንዲህም አላቸው፤ “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤
ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፤ 16 ያመነ
የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።
17የሚያምኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤
በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ልሳንም
ይናገራሉ፤ 18እባቦችን በእጃቸው ይይዛሉ፤
የሚገድል መርዝ ቢጠጡ እንኳ አይጐዳቸውም፤
እጃቸውንም በሕመምተኞች ላይ ይጭናሉ፤
እነርሱም ይፈወሳሉ።”
19ጌታ ኢየሱስ ይህን ከተናገራቸው በኋላ
ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በእግዚአብሔርም ቀኝ
ተቀመጠ። 20ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ወጥተው፣
በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ፤ ጌታም ከእነርሱ ጋር
ይሠራ ነበር፤ ትምህርታቸውንም ተከትለው
በሚፈጸሙ ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር[†]።

16፥14 ሉቃ24፥36-43
16፥15 ማቴ28፥18-20፤ ሉቃ24፥47፡48፤ ሐሥ1፥8
16፥16 ዮሐ3፥16፡ 18፡36፤ሐሥ16፥31
16፥17 ማር9፥38፤ ሉቃ10፥17፤ ዮሐ4፥48፤ሐሥ2፥4፤ 5፥16፤8፥7፤10፥46፤ 16፥18፤19፥6፡ 13-16፤1ቆሮ2፥10፡ 28፡30፤13፥1፤ 14፥2-39
16፥18 ሉቃ10፥19፤ሐሥ6፥6፤28፥3-5

[†]20 አንዳንድ የጥንት ቅጆች በቍ9-20 ላይ ያለው ክፍል የላቸውም።

የቀረበ አጭር ትረካ ነው (ሉቃ 24፥13-35 ይመ)።
16፥14 *ዐሥራ አንዱ፤* የአስቆሮቱ ይሁዳ ራሱን ስለ ገደለ፣ በዚህ ወቅት የሐዋርያት ቍጥር ዐሥራ አንድ ነበር (ማቴ 27፥5 ይመ)።
16፥16 *የተጠመቀ፤* የ1፥4፤ ሮሜ 6፥3-4 ማብ ይመ።
16፥18 *የሚገድል መርዝ ቢጠጡ እንኳ፤* ይህ ሐረግ በቀሙ ኪታዮ፣ በአዲስ ኪዳን በተግባር ስለ መፈጸሙ አልተጻፈም፤ (ከሐሥ 28፥3-6 ጋር ያነጻጽሩ)።
16፥19 *በእግዚአብሔርም ቀኝ፤* በመለኮታዊ ሥልጣኑ ቦታ መቀመጡን ያሳያል (14፥62፤ መዝ 110፥1 ይመ)።